አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ-ግብር

# ራጋ ማጋ- ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማረቆ ብሄረሰብ

በ

ተመስገን ታደሰ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ታህሳስ/2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ራጋ ማጋ- ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማረቆ ብሄረሰብ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚይኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ተመስገን ታደሰ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ታህሳስ/ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚይኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

# ራያ ማያ-ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማረቆ ብሄረሰብ

በ

ተመስገን ታደሰ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ ስም | ፊርማ |
| ፈታኝ ስም | ፊርማ |

ታህሳስ/2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ምስጋና

በዚህ ጥናት የሚካተቱ ዋና ዋና ነጥቦችን በቢጋር መልክ በማዘጋጀትና ቃላዊ ማብራሪያ በመስጠት፣ የጥናቱ ረቂቅ ከተዘጋጀ በኋላም ጥቃቅን የሆኑ የፊደል ግድፈቶችን ሳይቀር በማረም ምሁራዊ ድጋፉ ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶክተር ፈቃደ አዘዘን አመሰግናለሁ፡፡

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ እውን መሆን የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

ለጥናቱ በቂና ዝርዝር መረጃዎችን በማቀበል ለተባበራችሁኝ መረጃ ሰጭዎች በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይም የብሄረሰቡ ራጋ፣ ማጋዎችና ግለሰቦች፣ የማረቆ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ፍርድ ቤት፣ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ሀላፊዎችና ሰራተኞች በሙሉ ልባዊ ምስጋና ይድረሳችሁ ስል ለቀናነታችሁ ከፍ ያለ ዋጋ በመስጠት ነው፡፡

ጥናትህ ምን ላይ ደረሰ? በማለት የሰውን ስራ እንደራሳችሁ ስራ በመጨነቅ ስታበረታቱኝ ለነበራችሁት የልብ ጓደኞቼና የስራ ባልደረቦቼ ሙሉቀን ንጋቱና ከድር ጋሻው ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡ ሙሉቀን ምስጋና ሲያንስህ ነው፡፡ ለጥናቱ የሚያግዙ መጽሀፍትን አፈላልገህ በማምጣት፤ ኮምፒተርህን የራሴ እስኪመስለኝ ድረስ እንድጠቀምበት በመስጠት፤ በጥናቱ ላይ የነበሩትን የፊደላትና የሰዋስው ግድፈቶች በማደት ባለውለታዮ መሆንህን ሳስብ በእውነት ምስጋና ያንስህል እላለሁ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## አጠቃሎ

*ይህ ጥናት "ራጋ ማጋ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርአት በማረቆ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የብሔረሰቡን የግጭት አፈታት አጠቃላይ ገፅታና የብሔረሰቡ አባላት እርስ በርስና ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚያጋጥሟቸውን ግጭቶች ወደ ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም እንዲያመጡ ያደረጓቸውን ምክንያቶች ለማወቅ ተቋሙን ከሚመሩት ማጋዎችና ራጋ፣ በተቋሙ ከተዳኙ የብሄረሰቡ ተወላጆች፣ ከፍርድ ቤት ዳኞች፣ ከአቃቤ ህጎች፣ ከፖሊስ፣ ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ሃላፊዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በቃለ-መጠይቅ፣ በቡድን ውይይትና በምልከታ ሲሆን በቪዲዮ፣ በፎቶ፣ በፅሁፍና በመቅረፀ-ድምጽ ተይዘዋል።*

*በተለያዩ ዘዴዎች ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ ተንታኝ (Descriptive analysis) ስልት በአብነት (real case stories) እየተደገፉ ተተንትነዋል። በብሄረሰቡ ከቀላል እስከ ግድያ ድረስ ያሉ ግጭቶች በራጋ ማጋ ታይተው መፍትሄ እንደሚሰጣቸውም የጥናቱ ውጤት ያሳያል።*

*በብሔረሰቡ በተደጋጋሚ የሚከሰቱት የግጭት አይነቶች ቤተሰባዊ ግጭቶች (የባልና ሚስት፣ የውርስ ይገባኛል፣ የልጅና የአባት፣ የእናትና ልጅ)፣ ከጥሬ ሀብት ውስንነት ጋር የተያያዙ ግጭቶች (የእርሻ መሬትና የመጠጥ ውሃ ችግሮች)፣ ወንጀሎች (በተለይ ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ድብደባ፣ ግድያ) እንዲሁም የጎሳና የብሔረሰብ ግጭቶች ናቸው።*

*ራጋ ማጋ በብሔረሰቡ ትልቅ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል። ብሄረሰቡ የተቋሙን አሰራር ከሀገረሰባዊ እምነቶችና ልማዶች (ከበርቼ፣ ከቁምጥና በሽታ፣ ከሙት መንስና ከእናት አባት ውቃቢ) ጋር ስለሚያገናኘው ከእርቅ በፊትም ሆነ በኋላ ብቀላ አይፈፀምም።*


*ራጋ ማጋ ተዋረዳዊ ስልጣን ባላቸው ሶስት ተቋማት የተደራጀ ነው። እነዚህም የቤተ-ዘመድ ጉባኤ፣ማጋና ራጋ ሲሆኑ ተቋማቱ የሚፈቷቸው ግጭቶችም ተለይተው ይታወቃሉ። እነዚህ ተቋማት የየራሳቸውን ተቋማዊ ስልጣን አክብረው የሚሰሩ ሲሆን ተጠሪነታቸውም ለራጋ ነው።*

*በብሄረሰቡ የራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ስርዓት ውስጥ ሴቶች ሚና እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። የሴቶቹ ሚና ከእርቅ ጀምሮ እስከ ፍፃሜ የሚዘልቅ ሲሆን የእርቅ ስርዓቱም የሴቶችን፣ የህፃናትንና የአረጋዊያንን መብቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው።*

*ራጋ ማጋ ከመደበኛው የፍትህ ተቋም ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ሲሆን ሁለቱ የፍትህ ተቋማት በብሄረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ የእርስ በርስና ድንበር ተሻጋሪ ግጭቶች በጋራ እንደሚፈቱ ጥናቱ ያሳያል። የሁለቱ የፍትህ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር የየራሳቸውን አላማና ግብ ከማሳካት አንፃር ሲሆን በተናጠል የሚፈቷቸው ግጭቶችም እንዳሉ ጥናቱ ያሳያል።*

*በማረቆ ብሄረሰብ የራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ሂደት እርድና ጉማ (የደም ካሳ) በእርቅ መቋጫነትና ማፅኛነት የሚያገለግሉ ሲሆን እርዱም ሆነ ጉማው ከሀገረሰባዊ እምነቶች ጋር የተቆራኙና ባህላዊ ትዕምርቶችን እንደያዙ በጥናቱ ተረጋግጧል።*

# የማረቆ ወረዳ አስተዳደር ካርታ




በማረቆ ወረዳ ባህልና ኮሚኒኬሽን ቢሮ የተዘጋጀ

## ሙዳዬ ቃላት

ጎንቱ ጎንቱ   በእድሜ ጠና ያሉ ትልልቅ ሽማግሌዎች።

ኢዶት   የእናት ውቃቢ።

አልዎቾ   የአባት ውቃቢ።

ጌጊዎ   የከብት መዋጮ።

ውጆ   የወተት እቀብ።

ዳንግ   ድንበር።

ጣውንት   ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴቶችን ማግባት።

ፊርኦ   ቂም።

አያንቶ   ትልቅ የሀገር ሽማግሌ።

# ማውጫ

ገፅ

ምስጋና.....I

አጠቃሎ.....II

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ .....1

1.1. የጥናቱ አደረጃጀት.....3

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት .....4

1.3. የጥናቱ ዓላማ .....5

1.4. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች .....5

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ.....6

1.6. የጥናቱ ወሰን.....6

1.7. የጥናቱ ዘዴ.....7

1.8. መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች .....7

1.8.1. ቃለ-መጠይቅ .....7

1.8.2. የቡድን ውይይት .....8

1.8.3. ምልከታ .....8

1.9. በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች .....8

ምዕራፍ ሁለት

የማረቆ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ.....10

2.1. የማረቆ ብሄረሰብ የትመጣነትና ስያሜ.....10

2.2. የማረቆ ወረዳ የመሬት አቀማመጥና የአየር ፀባይ .....12

2.3. የማረቆ ብሄረሰብ ኢኮኖሚያዊ መሰረት .....13

2.4. የማረቆ ብሔረሰብ ቋንቋና ሀይማኖት .....14

2.5. የማረቆ ብሄረሰብ ማህበራዊ ተቋማት .....15

ምዕራፍ ሶስት


የንድፈ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....18
3.1. የግጭት ምንነትና ትውራዊ ቅኝት ....18
3.2. የግጭት አይነቶችና. አነሳሽ ምክንያቶች....23
3.2.1. የግጭት አይነቶች....23
3.2.2. የግጭት መነሻ ምክንያቶች ....24
3.3. የግጭት አፈታት ዘዴዎች ....26
3.3.1. የግጭት አፈታት ዘዴ ከመስኩ ምሁራን አንጻር ....26
3.3.2. የግጭት አፈታት ከህግ ሰነዶች አንጻር ....28
3.3.2.1. የግጭት አፈታት ከኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች አንፃር ....28
3.3.2.2. የግጭት አፈታት ዘዴ ከአለም አቀፍ ህጎች አንጻር ....30
3.4. አውድ በፎክሎር ጥናት....32
3.4.1.ባህላዊ አውድ....32
3.4.2. ማህበራዊ አውድ....34
3.5. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ....35


ምዕራፍ አራት


ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማረቆ ብሄረሰብ ....41
4.1.ግጭት ፅንሰ ሀሳብ በማረቆ ብሄረሰብ እይታ ....41
4.2. የግጭት መፍቻ ተቋማት በማረቆ ብሄረሰብ ....42
4.3. የግጭት አይነቶችና መንስኤዎቻቸው በማረቆ ብሄረሰብ ....47
4.3.1. ቤተሰባዊ ግጭቶች....47
4.3.2. ከጥሬ ሀብት ውሱንነት ጋር የተያያዙ ግጭቶች ....48
4.3.3. ወንጀል ....49
4.3.4 የጎሳና የብሄረሰብ ግጭቶች ....51
4.4. የግጭት አፈታት ሂደት በማረቆ ብሄረሰብ ....52
4.4.1. በቤተ-ዘመድ ጉባኤ የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው ....53
4.4.2. በማጋዎች የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው ....57
4.4.2.1. የቀላል ግጭቶች አፈታት ሂደት ....57

4.4.2.2. የአካል ማጉደልና የግድያ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ለእርቅ ማዘጋጀት..........63
4.4.3. የራጋ የእርቅ አፈፃፀም ሂደት ..........68
4.4.3.1. በራጋ የሚከናወን ምርመራና ውሳኔ ..........69
4.4.3.2. በገዳይ የሚዘጋጅ የእርቅ ማስፈፀሚያ ድግስ ..........70
4.4.3.3. የእርድ ዝግጅት እርድና የእርቅ ፍፃሜ ..........75
4.5. ሴቶችና ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም በማረቆ ብሄረሰብ ..........82
4.6. በራጋ ማጋ ላይ የሚታዩ ሀገረሰባዊ እምነቶችና ተግባሮቻቸው ..........84
4.6.1. ሀገረሰባዊ የእርቅ መለመኛ ስልትነት ..........86
4.6.2. ሀገረሰባዊ እምነቶች በወንጀል መመርመሪያ ስልትነት በማረቆ ብሄረሰብ..........88
4.6.3. ሀገረሰባዊ እምነቶች የእርቅ ቦታና ቀንን ለመምረጥ..........92

ምዕራፍ አምስት

የሀገረሰባዊውና መደበኛው የፍትህ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር በማረቆ ብሄረሰብ..........95
5.1. ራጋ ማጋ ከፍርድ ቤትና ከአቃቢ ከህግ ጋር ያለው ግንኙነት..........95
5.2. ራጋ ማጋ ከፖሊስ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር..........100
5.3. ራጋ ማጋ ከሴቶች ጉዳይ ቢሮ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር..........101
5.4. በመደበኛው የፍትህ ተቋም መፍትሔ የሚሰጣቸው ጉዳዮች..........102
5.5. ለራጋ ማጋ መሪዎች የሚደረጉ እገዛዎች..........103
5.6. የራጋ ማጋ ጥንካሬና ድክመት በብሄረሰቡ አተያይ ..........105

ምዕራፍ ስድስት

ማጠቃለያና ይሁንታ..........107
6.1. ማጠቃለያ..........107
6.2. ይሁንታ..........110

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ፎክሎር የሰው ልጆች እየኖሩ የሚማሩት አለምን፣ ማህበረሰባቸውንና ራሳቸውን፣ እምነታቸውን፣ ባህልና ትውፊታቸውን የሚገልፁበት እውቀት ነው። ይህንም Sims *and* Stephen (2005፡8) "*Folklore is informally learned, unofficial knowledge about the world, ourselves, our communities, our beliefs, our cultures and our traditions, that is expressed creatively through words, music, customs, actions, behaviors and materials*" በማለት ይገልፁታል።

ፎክሎር ከሌሎች ሰብዓዊ ሳይንሶች ጋር የሚጋራቸው ጉዳዮች ቢኖሩትም የራሱን የጥናት ትኩረትና አቅጣጫ የሚከተል መስክም ነው። ፎክሎር የማይዳስሰው ሰዋዊና ጥበባዊ ጉዳይ የለም። የጥናት ዘርፉ ጉዳዩ የሰው ልጅ ነው፤ ጥበብ ነው። የሰው ልጆች ደግሞ ትናንት የኖሩበትን አለም ለመገምገም፣ ዛሬና ነገ የሚኖሩበትን አለም ለመግራትና ለመቆጣጠር ፎክሎርን በመሳሪያነት ይጠቀማሉ። ይህ የፎክሎር ከሰው ልጆች የህይወት ዑደት ጋር አይነጣሌነት ለዘርፉ ፈርጀ ብዙነት መነሻ ሆኗል። ለዚህም ነው Dorson (1972) ብዙዎቹ የፎክሎር ተመራማሪዎች ፎክሎርን በአንድ ብያኔ ከመግለፅ ይልቅ የሚያጠናቸውን ጉዳዮች መዘርዘር ላይ እንደሚያተኩሩ የሚገልፀው።

እንደ Dorson (1972፡3) ፎክሎር አራት የጥናት ዘርፎችን በስሩ የያዘ የጥናት መስክ ነው። እነርሱም፡- ቃላዊ ፎክሎር(Oral Folklore)፣ ሀገረሰባዊ ልማድ (Social folk custom)፣ ቁሳዊ ባህል (material culture) እና ሀገረሰባዊ ጥበብ (folk arts) ናቸው። እነዚህ የፎክሎር ዘርፎች የየራሳቸው መለያ ባህርያትና የአጠናን ስልት ግንኙነት ያላቸው ሲሆን አንዱ ከአንዱ ጋር የሚገናኝበትም ሁኔታ አለ። የጥናት መስኮቹ አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ ይዞታ አላቸው።ይህ ደግሞ አንዱ የአንዱ መገለጫ በመሆን እንዲያገለግሉ አድርጓቸዋል።ቃላዊ ፎክሎር በሶስቱ የፎክሎር ዘርፎች የሚደገፍ ሲሆን ሀገረሰባዊ ልማድም እንዲሁ የሌሎችን ድጋፍ ይፈልጋል። ይህ የባህርይ ተሻጋሪነት አንዳንዴ በጉልህ አንዳንዴ ደግሞ በስሱ ይታያል።

እንደ Dorson (1972፡3-4) ገለጻ ሀገረሰባዊ ልማድ(Social folk custom) አራት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮችን በስሩ የያዘ የፎክሎር ዘርፍ ነው።እነሱም ፌስቲቫሎችና ክብረበዓላት

(festivals and celebration)፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች(recreations and games)፣ ሀገረሰባዊ መድሀኒት(folk medicine) እና ሀገረሰባዊ ሀይማኖት(folk religion) ናቸው፡፡ እነዚህ የሀገረሰባዊ ልማድ ክፍሎች የሰው ልጆች በቡድን ወይም በጥንድ የሚውኗቸው፣ ደስታና ሀዘናቸውን የሚጋሩባቸው በሀገረሰባዊ እውቀት ህግና ስርዓት የተበጀላቸው ልማዶች ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ራጋ ማጋ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በሚል ርዕስ መቅረቡ በአንባቢዎች ላይ ግርታን ሊፈጥር ይችላል፡፡ በተለይ ግጭት በፎክሎር የጥናት መስክ ውስጥ እንዴት ሊጠና ይችላል የሚል ጥያቄ ቢነሳ ተገቢነት አለው፡፡ ጥያቄው ምልሽ ካላገኘ ደግሞ ፎክሎር ጉዳዩ ያልሆነን የጥናት መስክ ያጠናል የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደረስ ይገፋፋል፡፡በመሆኑም ግርታውን ከጅምሩ ማጥናት ተገቢ ይመስለኛል፡፡

በግርድፉ ግጭት የፎክሎር ጥናት ዋና ጉዳይ አይደለም፤ ፎክሎር ከሌሎች የጥናት መስኮች ነጥቆ ወደ ራሱ ያመጣው የጥናት ትኩረትም አይደለም፡፡ የፎክሎር ጥናት ዋና ጉዳዩ ግጭቶች ሲፈቱ በሚከናወኑ ሀገረሰባዊ ስርዓቶች ላይ ነው፡፡ በሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም የአንድ ብሄረሰብ አባላት ያጋጠማቸውን ግጭት ለማብረድ፣ ለማርገብና በዘለቄታዊነት ለመፍታት የሚያከናውኗቸው ሀገረሰባዊ ልማዶች በሙሉ በፎክሎር የጥናት መስክ የሚታዩ ጽንሰ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ግጭት ሀገረሰባዊ በሆነ መንገድ ሲፈታ ግጭት ውስጥ በገቡት ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ብሄረሰቦች የሚፈፀሙ የተለያዩ ልማዶች አሉ፡፡ ግጭቱ ከተፈጠረበትና ጥፋት ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ሌሎች ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ ተበዳዩን ለማረጋጋትና ተጎጂን ለእርቅ ለመለመን ብሄረሰቡ ያመነባቸው ሀገረሰባዊ ተቋማት ልዩ ልዩ ልማዳዊ ስርዓቶችን ይፈፅማሉ፡፡

በእርቅ ስርዓቱ ላይ የሚከናወኑ የወንጀል መመርመሪያ ስልቶች፣ መሃላዎችና እርግማኖች፣ የእርቅ ማስፈፀሚያ ድግስና በድግሱ ላይ የሚከናወኑ የፀሎትና የቃል ኪዳን ስርአቶች በሙሉ ሀገረሰባዊ ልማዶችን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ግጭቶች በእርቅ ከተደመደሙ በኋላም በእርቅ ማፅኛነት የሚከናወኑ የአዳር ድግስና የእርድ ስርዓት መሰረታቸው ሀገረሰባዊ ልማድ ሲሆን አፈፃፀማቸውም ከልማዱና ከእምነቱ ጋር ይገናኛል፡፡ ይህ ጥናት በማረቆ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ላይ ያተኮረውም እነዚህ ሀገረሰባዊ ልማዶችና ስርዓቶች ስለሚመለከቱት ነው፡፡

## 1.1. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት "ራጋ ማጋ- ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርአት በማረቆ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ በስድስት ዋና ዋና ምዕራፎች የቀረበ ሲሆን በእያንዳንዱ ምዕራፍ ስር ደግሞ ልዩ ልዩ ንዑሳን ርዕሶች ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አንድ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ አላማ፣ በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎችን፣ የጥናቱን ጠቀሜታና የጥናቱን ወሰን የጥናቱን ዘዴና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንዲሁም በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይዟል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ስለ ማረቆ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ መረጃ የተሰጠበት ሲሆን የብሔረሰቡን የትመጣነትና ስያሜ፣ የወረዳውን የአየር ፀባይ፣ የመሬት አቀማመጥ፣ የብሔረሰቡን መተዳደሪያ፣ ቋንቋና ሃይማኖት እንዲሁም ስለብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋማት ያትታል፡፡

ምዕራፍ ሶስት የንድፈ ሃሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የቀረቡበት ሲሆን ስለ ግጭት ምንነት፣ አይነቶችና አነሳሽ ምክንያቶች ፣ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ከመስኩ ምሁራን እና ከህግ ሰነዶች አንፃር ተቃኝቶበታል፡፡ በዚህ ክፍል በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በቀደምት ስሙ እንዲሁም በኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰሩ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ምን አይነት ናቸው የሚለውን ለማሳየት በአጭር ባጭሩ ተቃኝተዋል፡፡

በምዕራፍ አራት ደግሞ የግጭት ፅንሰ ሃሳብ በማረቆ ብሔረሰብ፣ የግጭት መፍቻ ተቋማት፣ የግጭት አይነቶችና መንስኤዎቻቸው፣የግጭት አፈታት ሂደት፣ሴቶችና ሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋም እንዲሁም በራጋ ማጋ[1] ላይ የሚታዩ ሀገረሰባዊ አምነቶችና መርሆች በስፋት ቀርበዋል፡፡

---

[1] ራጋ ማጋ የሚለው ጥምር ቃል ራጋና ማጋ ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገኘ የሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ጥቅል መጠሪያ ነው፡፡ ራጋ በብሄረሰቡ ከባድ ግጭቶችን የሚፈታ ተቋም ሲሆን ማጋ መካከለኛ የሆኑ ግጭቶችን ይፈታል፡፡ የቤተ- ዘመድ ጉባኤ ደግሞ ቤተሰባዊ ግጭቶችን የሚፈታ ሀገረሰባዊ ተቋም ነው፡፡ ራጋ "ራጋ ማጋ" ከሚለው ቃል ላይ ቀድሞ የመጣበት የራሱ ምክንያት አለው፡፡ ሶስቱ ተቋማት የየራሳቸው የስልጣን ልክና አሰራር ቢኖራቸውም በብሄረሰቡ ለራጋ የተለየ ክብር ይሰጠዋል፡፡ በብሄረሰቡ ከራጋው በላይ ወሳኝ የለም፤ ይከበራልም፤ይፈራልም፡፡ በዚህም የተነሳ በሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ስያሜ ላይ ራጋ ቅድሚያ ተሰጥቶት ራጋ ማጋ እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህ ሲባል ግን ማጋና የቤተ-ዘመድ ጉባኤ በብሄረሰቡ አይፈሩም፤ አይከበሩም ማለት አይደለም፡፡

ምዕራፍ አምስት የራጋ ማጋና የመደበኛው የፍትህ ተቋማት እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነትና የጋርዮሽ አሰራር እንዲሁም የሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋማት ላይ የሚታዩ ጥንካሬዎችና ደካማ ጎኖች በሰፊው ተዳሰበታል፡፡

ምዕራፍ ስድስት የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ የቀረቡበት ሲሆን በጥናቱ የተደረሰባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ተጨምቀው ቀርበውበታል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አሁን አሁን በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ አንዳንዴም ሙሉ ወጪ ለህትመት የሚበቁ ጋዜጦች፣ መፅሄቶች፣ መጣጥፎችና ጥናቶች እየተበራከቱ ነው፡፡ የሽፋን መጠናቸው ቢለያይም የህትመት ሚዲያዎች ስለብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ ልማድና አኗኗር በሰፊው ማስተዋወቅ እየተለመደ ነው፡፡ እኔም እንደ ፎክሎር ተማሪነቴ እነዚህን ጽሁፎች ማንበብ አዘወትራለሁ፡፡ ለዚህም ጥናት ርዕስ ፍንጭ የሆነኝን መረጃ ማግኘት የቻልኩት በተደጋጋሚ ከማነባቸው ከነዚህ ምንጮች ነው፡፡

ስለብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ ልማድና አኗኗር ጽሁፎችን ለህትመት ከሚያበቁ የህትመት ሚዲያዎች ውስጥ "የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ተጠቃሽ ነው፡፡ ጋዜጣው "ልዩ ቅኝት" በሚለው አምዱ የካቲት 19-2003 ዓ.ም ላይ ስለ ኮንቶማዎች[2] (ማረቆ በሚለው የብሄረሰቡ መጠሪያ ውስጥ የሚገባ የአንድ ጎሳ ስም ነው) ያቀረበው ጽሁፍ የዚህ ጥናት ዋና አነሳሽ ነው፡፡

በጋዜጣው ላይ የሰፈረው ፅሁፍ የሰጠኝን ፍንጭ መረጃ ይገኛ ስለብሄረሰቡ ያውቃሉ የተባሉ ግለሰቦችን በማፈላለግ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሞከርኩ፡፡ የአገኘሁት መረጃም የማረቆዎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት ለየት ያለ በመሆኑ ትኩረቴን ሳበው፡፡ ማረቆዎች በመካከላቸው የሚከሰቱ የተለያዩ ግጭቶችን የሚፈቱት ባህል፣ወግና ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ በመሆኑ የግጭት አፈታታቸው ቢጠና ወደ ፊት ብሄረሰቡን ከማስተዋወቅ በላይ በጥናትና ምርምር መስክ አንዳች ፋይዳ ይኖረዋል በሚል ለማጥናት ተነሳስቻለሁ፡፡

---

[2] በጋዜጣው ላይ የተፃፈው የኮንቶማ ብሄረሰብ ተብሎ ሲሆን በዚህ ጥናት የምጠቀመው ማረቆ ብዮ ነው፡፡ በመስክ ቆይታዮ ላይ እንዳገኘሁት መረጃ ብሄረሰቡ ኮንቶማ የሚለዉን ቃል ለአንድ ጎሳ መጠሪያነት እንጅ ለብሄረሰቡ ጥቅል መጠሪያነት አይጠቀመውም፡፡ ህጋዊ የሆነው የብሄረሰቡ መጠሪያ ማረቆ የሚለው ቃል በመሆኑ በጥናቱ ማረቆ እያልኩ እጠቀማለሁ፡፡ ይህን ጉዳይ በመስክ ዘገባዬ ላይ በስፋት የዳሰስኩት ስለሆነ እዚህ ላይ በድጋሚ አላነሳውም፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አላማ የማረቆ ብሄረሰብ የግጭት አፈታት ስርዓት ምን እንደሚመስል መመርመር ሲሆን ጥናቱ የሚከተሉትን ንዑሳን ዓላማዎች ይዟል፡፡ እነሱም፡-

1. የማረቆ ብሄረሰብ ለግጭት የሚሰጠውን አካባቢያዊ ብያኔ ማሳየት፡-
2. የብሄረሰቡ የራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ሂደት ምን እንደሚመስል መግለጽ፡-
3. የራጋ ማጋን የግጭት አፈታት ሥርዓትና አፈጻጸም ማሳየት፡-
4. በራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ የሚታዩ ትዕምርቶች ፍቺና ፋይዳ መመርመር፡-
5. ለራጋ ማጋ የሚቀርቡ የግጭት አይነቶችንና የሚሰጡ ውሳኔዎችን መግለጽ፡-
6. ብሄረሰቡ ለራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ሥርዓት ያለውን አመለካከት ማሳየት፡-
7. በማረቆ ብሄረሰብ ራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ሥርዓትና በመደበኛው የፍትህ ተቋም መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡-

1. የማረቆ ብሄረሰብ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀማቸው ተቋማት ምን ምን ናቸው?
2. በማረቆ ብሄረሰብ ግጭቶች እንዴት ይፈታሉ?
3. በብሄረሰቡ የእርቅ ማዕኛ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?
4. የብሄረሰቡ ተወላጆች የሚያጋጥሟቸውን ግጭቶች በራጋ ማጋ እንዲፈቱ የሚያደርጋቸው ጉዳይ ምንድን ነው?
5. መደበኛው የፍትህ ተቋም ለራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ስርዓት ምን አይነት ይሁንታ አለው? የሚሉ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡

### 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ፡-

1. የማረቆዎች ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት አወቃቀርና ክዋኔ ምን እንደሚመስል ያስተዋውቃል፡፡
2. የማረቆዎች ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ከዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት ጋር ግጭቶችን በጋራ በመፍታት ለብሄረሰቡ ላቅ ያለ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡
3. ጥናቱ ብሄረሰቡን ያስተዋዉቃል ተብሎ ይታመናል፡፡

### 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በጉራጌ ዞን ማረቆ ወረዳ ውስጥ በሚገኙት የማረቆ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ያተኩራል፡፡ የጥናቱ አብይ ጉዳይ በተለያዩ የሽምግልና እርከኖች የሚፈቱት የግጭት አይነቶች ላይ የሚደረገውን የግጭት አፈታት ሥርዓት መርምሮ ማሳየት ነው፡፡

የማረቆ ወረዳ በሀያ ስድስት ቀበሌዎች የተከፈለ ሲሆን የጥናቱ መረጃ ሰጭዎች ከተወሰኑ ቀበሌዎች ብቻ የተመረጡ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የጥናቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሀያ ስድስቱንም ቀበሌዎች የሚወክሉና እየተዘዋወሩ የሚያስታርቁ በመሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የብሄረሰቡ ማጋ በመሆን የሚያገለግሉ አምስት ሽማግሌዎችና ራጋው በቁልፍ መረጃ አቀባይነት አገልግለዋል፡፡ አጋጣሚያዊ ቢሆንም ሽማግሌዎቹና ማጋው ከተለያዩ ቀበሌዎች የተገኙ ናቸው፡፡

እነዚህም ቁልፍ መረጃ አቀባዮዎች ሁለቱ አበጋዞች፣ አንዱ ሃጅ ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ በማዕረግ የማይጠሩ ማጋዎች ናቸው፡፡ ሽማግሌዎቹ ባላቸው ማህበራዊ ደረጃና ምግባር በሁሉም የብሄረሰቡ አባላት ዘንድ የተከበሩ ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት ከስድስቱ ሽማግሌዎች በተጨማሪ አስራ ሁለት አጋዥ መረጃ አቀባዮች ተካተዋል፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች የብሄረሰቡ ተወላጆችና ያጋጠማቸውን ወደ ፊትም የሚያጋጥማቸውን ግጭት በራጋ ማጋ የፈቱና የሚፈቱ ግለሰቦች እንዲሁም የመደበኛው የፍትህ ተቋማት ሰራተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች ነሲባዊ በሆነ መንገድ ገበያ ውስጥ መርጬ ቃለ መጠይቅ ያደረኩላቸው ሲሆን ከመደበኛው የፍትህ ተቋማት ላይ

የተመረጡት መረጃ አቀባዮች የየቢሮዎቹ ሀላፊዎች ሲሆኑ ስልታዊ በሆነ መንገድ የተመረጡ ናቸው።

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በገላጭ-ተንታኝ (descriptive analysis) ስልት የቀረበ ነው። እንደ Bauman (1983:363-367) እና Ben-Amos(1993:215-216) የፎክሎር አጥኚ መስክ ላይ ያገኛቸውን ፎክሎራዊ ጉዳዩች ሊያደራጅባቸው የሚችሉ ባህላዊ(cultural context) እና ማህበራዊ (social context) የሚባሉ አውዶች እንዳሉ ይገልጻሉ። በነዚህ ሁለት ዋና ዋና አውዶች ውስጥም ስድስት ንዑሳን አውዶች ይካተታሉ። እነርሱም ፍቻዊ አውድ(context of meaning)፣ ተቋማዊ አውድ(Institutional context)፣ ተግባቦታዊ አውድ(Context of communicative system)፣ የማህበራዊ መሰረት አውድ(Social base)፤ ግለሰባዊ አውድ (Individual context) እና ሁነታዊ አውድ(context of situation) ናቸው። እነዚህ ሁለት ሰፋፊና ስድስት ንዑሳን አውዶች በዚህ ጥናት ለተገኙ መረጃዎች መተንተኛ መንገድ በመሆን አገልግለዋል።

## 1.8. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

አንድን ጥናት ስናስብ ትኩርት ልናደርግባቸው ከሚገቡን ጉዳዮች ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ መረጃዎች እንዴትና በምን መልኩ ይሰብሰቡ የሚለው ነው። በተለይ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች መስክ ላይ የሚሰበሰቡ ከሆነ አጥኚው የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀመ መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት ይኖርበታል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ጥሬ መረጃዎች በሶስት ዘዴዎች ተሰብስበዋል። እነዚህም፡-

### 1.8.1. ቃለ-መጠይቅ

ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ያለውን መዋቅር፣ የእርቅ አፈጻጸሙን ደንብ፣ አውድ እና ፋይዳ ለማወቅ በብሄረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን የሀገር ሽማግሌዎችንና በራጋ ማጋ እርቅ የሚዳኙ ግለሰቦችን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል። ለቃለ-መጠይቅ የዋሉት ክፍትና(open ended) ሁነት የሚጠራቸው እግረ መንገዳዊ ጥያቄዎች ናቸው።

### 1.8.2. የቡድን ውይይት

በተለያዩ መንገዶች የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነትና አሳማኝነት ለማረጋገጥ የቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡ የብሄረሰቡን ባህል፣ወግና ልማድ ያውቃሉ የሚባሉና በሀገረሰባዊው የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ከሆኑት የአገር ሽማግሌዎች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በተለይ በእርቅ ስርዓቱ ላይ ስለሚፈጸሙ ክዋኔያዊ ስርዓቶችና ስለ ብሄረሰብ አመጣጥ መረጃዎችን ያጠናከርኩት ሽማግሌዎችን በቡድን በማወያየት ነው፡፡

### 1.8.3. ምልከታ

በራጋ ማጋ መፍትሄ የሚሰጣቸውን የግጭት አይነቶች ለማጥናት ግጭቶቹ ሲፈቱ የሚከናወኑ ስርአቶችን መመልከትና ትዕምርቶችን መተርጎም ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በብሄረሰቡ አባላት የተፈጠሩ ቀላል ግጭቶችን ሲፈቱ በመመልከት መረጃዮን ለማጠናከር ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

ከላይ የቀረቡትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም የተገኙትን መረጃዎች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ማለትም በማስታወሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ ግራፍ ተይዘዋል፡፡

## 1.9. በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

ይህን ጥናት ለመስራት ያጋጠመኝ የመጀመሪያው ችግር የቪዲዮ ካሜራ እጥረት ነው፡፡ ጥናቱን ለመስራት የተፈቀደልኝ በጀት ቪዲዮ ካሜራና ሌሎች ቁሳቁሶች ሊያሟላ ባለመቻሉ ብዙ መጉላላቶች አጋጥሞኝ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ችግሩን ከጓደኛዬ በመዋስ ልፈታው ችያለሁ፡፡

ሌላውና ሁለተኛው ችግር ወደ መስክ ከሄድኩ በኋላ የወረዳው ባለስልጣናት የጥናቱን ርዕስ[3] የተለየ ፖለቲካዊ ትርጉም በመቀባት መጉላላቶችን አድርሰውብኛል፡፡ ችግሩ የተፈጠረው በጥናቱ ርዕስ ላይ ኮንቶማ የሚል ቃል በመኖሩ ሲሆን መጀመሪያ ላይ የእናስርሀለን ማስፈራሪያም ሰንዝረውብኛል፡፡ ይህንንም ችግር ከወረዳው አስተዳዳሪ ጋር እንዲሁም ከአማካሪዬና ከትምህርት ክፍሉ ሀላፊ ጋር በመወያየት ርዕሱ መስተካከሉን የሚገልፅ ደብዳቤ በመውሰድ ችግሩ በዘላቂነት ሊፈታ ችሏል፡፡

---

[3] *የዚህ ጥናት የመጀመሪያ ርዕስ ራጋ ማጋ- ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርአት በኮንቶማ ብሄረሰብ ነበር፡፡*

ሶስተኛው በመስክ ቆይታዬ በዋናነት ያጋጠመኝ ችግር ሽማግሌዎች መረጃ ከሰጡ በኋላ የሚጠይቁት ብር ነበር። በተለይ በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት አንዳንድ ሽማግሌዎች መረጃ ከመስጠታቸውም በፊት ይህን ያህል ትከፍላለህ እያሉ አስቸግረውኝ ነበር። ምንም እንኳ መረጃ ሰጭዎች ብዙ ብር እየጠየቁ ቢያስቸግሩኝም በጊዜ ሂደት የጥናት አጋዤ የሆነው ወልዩ ዲተሞ ከሽማግሌዎቹ ጋር እያግባባኝና መልካም ግንኙነት በመፍጠር ችግሩን ለመቅረፍ ችያለሁ።

## ምዕራፍ ሁለት

## የማረቆ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ

በዚህ ምዕራፍ ስለብሄረሰቡ አመጣጥ፣ስለወረዳው መልክዓምድራዊ ገፅታና ስለብሄረሰቡ መተዳደሪያ፣ ስለብሔረሰቡ ቋንቋ፣ ሀይማኖትና በብሄረሰቡ ውስጥ ስለሚገኙት ማህበራዊ ተቋማት አደረጃጀት ያትታል።

### 2.1. የማረቆ ብሄረሰብ የትመጣነትና ስያሜ

የሠው ልጆች በህይወት ዑደታቸው ለሚፈጠሩባቸው በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡት ከራሳቸው ልምድና የቃል ታሪክ በመነሳት ነው። በተለይ በየጊዜው ለሚነሱና የፅሁፍ ማስረጃ ለማይቀርብባቸው ጥያቄዎች ብቸኛው የመልስ ማጣቀሻ አፈ-ታሪክ ነው።

የሰው ልጆች የትመጣን? እንዴት መጣን? ማን አመጣን? አይነት ጥያቄ ከሀይማኖታዊ አስተምህሮ ባሻገር ምላሽ ለመስጠት የሚሞከሩት አፈ-ታሪክን መነሻ በማድረግ ነው። በመስክ ቆይታዬ ያነጋገርኳቸው የብሄረሰቡ የሀገር ሽማግሌዎች ሀጂ ጃተኖ[4] (ስክርብ[5]፣54)፤ኢማም (ስክርብ፣82) እንደሚናገሩት ማረቆዎች ትውልድ ሀገራቸው አረብ[6] ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በሱማሊያ ጠረፍ በኩል ነው። ይህንን ሃሳብ ኢማም፡-

> *ማረቆ መጀመሪያ አመጣጡ ከአረብ ነው። የመጣነው በመሽኛ ነው፤እንዲሁ ዘለን አይደለም። እኛ ከመጣን ጀምሮ አሁን አንድ ሺ ሶስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ (1389) አመት ሆነን ማለት ነው። እኛ ከመጣን ወዲህ። የሊቢዶ ማረቆ የፊቱ የአያት የአያት አያቱ ነው የመጣው እኛ። ከዚያ እኛ በ615 ዓ.ም ከዛ በመሽኛ መጣን። ከአረብ 651 ዓ.ም ሀይማኖት ለማስፋፋት መጣን (ስክርብ፣82)።*

በማለት ይገልፃሉ።

---

[4]*ስሜ ሃጂ ጃተኖ መኪ ይባላል። እድሜዬ 85 ነው። የምተዳደረው በግብርና ሙያ ነው በማሳረስ። ኡዳሳ ዋሼ ቬራ ቀበሌ ነው የምኖረው። ከጫቦ ጎሳ ነው የተወለድኩት(ስክርብ፤2004፣40)።*

[5]*በዚህ ጥናት ውስጥ "ስክርብ" የሚል ቃል በተደጋጋሚ ተጠቅሜያለሁ። ይህ ቃል "transcribe" ከሚለው የእንግሊዘኛ ቃል የተወሰደ ሲሆን ቃሉን የምጠቀመው ከመስክ ሰብስቤ ያመጣሁትን ጥሬ መረጃ ወደ ወረቀት መመለሴንና ለጥናቱ በሚመች መልኩ መጠቀሜን ለማሳየት ነው። ይህን ወደ ወረቀት የተመለሰ መረጃ በጥናቱ ላይ በምጠቀምበት ጊዜ መረጃ የሰጠኝን አካል ማንነት ለማሳወቅ ስሙን፣ መረጃው ወደ ወረቀት የተመለሰ መሆኑን ለማሳወቅ ሲባል ስክርብ፣ እንዲሁም ወደ ወረቀት የተመለሰው መረጃ የሚገኝበትን ገፅ ለመጠቆም ገፁን በአንድ ላይ አቀናጅቼ አቅረቤዋለሁ። ለምሳሌ፡-ሀጂ ጃተኖ(ስክርብ፣30) ማለት ሀጅ ጃተኖ ወደ ወረቀት በተመለሰው መረጃ ገጽ 30 ላይ እንደገለፁት ለማለት ነው።*

[6]*የማረቆ ብሄረሰብ የሀገር ሽማግሌዎች የሆኑት ሀጂ ጃተኖ መኪ እና ኢማም ቱኬ የመጣነው ከአረብ ሀገር ነው የሚል ጥቅል መልስ ሰጥተውኛል። የብሄርሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ በጥልቀት ለማወቅና ከታሪክ እውነታዎች ጋር ለማገናኘት ስል ብሄረሰቡ ከየትኛው የአረብ ሀገር እንደመጣ ለማወቅ ያደኩት ሙከራ ሊሳካ አልቻለም። የብሄረሰቡ ሽማግሌዎችም በብሄረሰቡ ጥንተ አመጣጥ ላይ የተለያየ አመለካከት ነው ያላቸው። ይሁን እንጅ ሌሎቹ የሀገር ሽማግሌዎች በሀሳቡ ላይ ባለመስማማታቸው እርግጠኛ ሆኘ ለጥናቱ በመረጃ ግብዓትነት ልጠቀመው አልቻልኩም።*

ሀይሉ ጓጎሮ የማረቆ ብሄረሰብን ጥንተ አመጣጥ በተመለከተ በመስክ ቆይታየ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ማረቆ እና ሀድያ ከአንድ ነገድ እንደተገኙ ነግረውኛል፡፡ በሀድያ ብሄረሰብ ላይ ጥናት የሰሩ ምሁራን እንደሚያብራሩት ሀድያና ማረቆ በቋንቋ ግንኙነት አላቸው፡፡ በሀድያ ብሄረሰብ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን የሰሩ ምሁራን ከሀይሉ ሀሳብ ጋር የሚቀራረብ አመለካከት መያዛቸው የብሄረሰቡን ትክክለኛ የትመጣነት ለማወቅ ሰፊ ጥናት ማካሄድ ተገቢ እንደሆነ የሚጠቁም መረጃ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ አለባቸውና ሳሙኤል(2002፣ 8) ተስፋዬ (2009፣455)ን በመጥቀስ "የሀድያ ህዝብ የሀድይሳን ዘዬ በሚመለከት የዳበረ ስነ-ልሳናዊ ጥናት ባይደረግም አንዳንድ አጥኚዎች ወይም ጸሀፊዎች ወደ አምስት የሚደርሱ ዘዬዎች እንዳሉ ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህም የሶሮ፣ የሌሞ፣ የሻሸጎ፣የባዳዋቾ እና የሲቢዶ ወይም የማረቆ በመባል የተከፈሉ ናቸው" በማለት የብሄረሰቦቹን ግንኙነት ይገልፁታል፡፡

በሀይማኖት ማስፋፋትን በአላማነት ይዘው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ማረቆዎች መጀመሪያ የሰፈሩት በሀረር ነበር፡፡ ይሁን እንጅ የተነሱበት አላማ በሀረር ብዙ እንዲቆዩ አላደረጋቸውም፡፡ ብሄረሰቦቹ ሀይማኖት እየሰበኩ ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ በርካታ ቦታዎችን አካለው፣ ወልደውና ተዋልደው አሁን ላይ ደርሰዋል፡፡

እንደ ኢማም[7] (ስክርብ፣82) ገለፃ ማረቆዎች አሁን ላይ እስከሰፈሩበት ቦታ ድረስ ያካተቷቸውና ሀይማኖት እየሰበኩ የኖሩባቸውን ቦታዎች ሀረር፣ ዱከም፣ አሰላ፣ ዶፋ፣ መቻራ፣ ሻሸመኔ፣ ቆሸሜ፣ ሻንቃ፣ አልካሶ፣ ሙሳ፣ ግራሬ እና ማረቆ ወረዳ ናቸው፡፡ ብሄረሰቡ በሰፈረባቸው ቦታዎች ሁሉ የራሱን መሪዎችም እየመረጠ ሲተዳደር ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ በተለያየ ወቅት የተነሱ ነገስታት በነዚሁ መሪዎቻቸው ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎች ያሳርፉባቸው ነበር፡፡

የማረቆ ብሄረሰብ "ማረቆ" የሚለውን ስያሜ እንዴት አገኘ? ስያሜውን ማን ሰጠው? እና መሰል ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጣቸው የብሄረሰቡ ዋና ዋና የሀገር ሽማግሌዎች መረጃዎችን የጥንት አባቶቻቸው በቃል የነገሯቸውን በማጣቀስ ነው፡፡ የብሄረሰቡን ስያሜ በተመለከተ

---

*[7] ስሜ ኢማም ቱኬ ይባላል፡፡ እድሜዬ 67 ነው፡፡ የጎሳ ተወላጅነቴ በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ አዣኔ ጎሳ ነኝ፡፡ ኡዳሳ ረጼ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው የምኖረው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የባህል፣የቋንቋ፣ የቃል ታሪክ አዋቂና የሀገር ሽማግሌዎች ተወካይ ነኝ መረጃም አለኝ (ስክርብ፣2004፣75)፡፡*

ሀይሉ፡-

> *በጥንት ጊዜ የማህበረሰቡ መጠሪያ ሊቢዶ ይባል ነበር። አሁንም ቢሆንም አንዳንዶች ሊቢዶ የሚለውን መጠሪያ ይጠቀሙበታል። ማረቆ የሚለው ስም ግን የመጣው ቀደም ሲል የማር ግብር ከመስጠትና ከአንዳንድ ሁኔታዎቸች የተነሳ የአማራው የገዢ ስርዓት የሠጠው እንደሆነ ይታመናል (ስክርብ፣9) በማለት ያብራሩታል።*

ማረቆ ከሚለው ስያሜ ጋር በተያዘ ሁለት የተለያዩ አፈ-ታሪካዊ መረጃዎች አሉ። አንደኛው በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት የሊቢዶ ብሄረሰብ ለመንግስት ይገብር የነበረው የዝሆን ጥርስ በቤተመንግስቱ እልፍኝ ለማር ማስቀመጫ የሚሆን እቃ ይሰራበት ነበር። በዚህ የተነሳ አፄው ለብሄረሰቡ ልዩ ፍቅር ስለነበራቸው ያንን የተከበረ የማር እቃ የሚያመጣልኝን ህዝብ እንዳትነኩት እያሉ ለወታደሮቻቸው ማሳሰቢያ ይሰጡ እንደነበርና ማረቆ የሚለው ቃልም የማር እቃ ከሚለው የአፄው ንግግር ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይነገራል። ሁለተኛው አፈ-ታሪክ ደግሞ በ1970 ዓ.ም ገደማ አቡነ ዜና ማርቆስ በአካባቢው ቤተክርስቲያን በስማቸው በማሰራታቸው የብሄረሰቡ ስያሜም ከዚሁ የማርቆስ ቤተ-ክርስቲያን ስያሜ ጋር እንደሚገናኝ ይነገራል።

ማረቆዎች በበርበሬ አምራችነታቸው ይታወቃሉ። በርበሬውም "የማረቆ በርበሬ" በሚል የሚታወቅ ሲሆን ብሄረሰቡን እስከ ውጭ ሀገር ድረስ እንድንታወቅ አድርጎናል በሚል ማረቆ በሚለው መጠሪያቸው ይኮሩበታል። ብሄረሰቡ ሊቢዶና ማረቆ የሚሉትን ቃላት በአንድ አጣምሮ ሊቢዶ ማረቆ እያለ የሚጠቀምበት ጊዜም አለ።[8]

## 2.2. የማረቆ ወረዳ የመሬት አቀማመጥና የአየር ፀባይ

የማረቆ ወረዳ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ(47(1)[9]መሰረት ከተቋቋሙት ዘጠኝ ክልሎች ውስጥ አንዱ በሆነው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጉራጌ ዞን ከተዋቀሩት አስራ ሶስት ወረዳዎች መካከል 1994 ዓ.ም እንደተቋቋመ የወረዳው የመረጃና የህዝብ ግንኙነት ቢሮ 2002 ዓ.ም ያዘጋጀው ትራዝ ይገልጻል።

---

[8] *ሀይሉ(ስክርብ፣9)።*

[9] *አንቀጽ (47(1)"Member states of the federal democratic republic of Ethiopia are the following: The state of Tigray, The state of Afar, The state of Amhara, The state of Oromia, The state of Somalia, The state of Benshangul/Gumuz, The state of the Southern Nation, Nationalities and Peoples, The state of Gambela Peoples, The state of Harari People" ይላል።*

የማረቆ ወረዳ ጠቅላላ ስፋቱ 327.5 ስ.ኪ.ሜ ነው። ወረዳው በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ከስልጤ ዞን በምስራቅ ከመስቃን ወረዳና ከኦሮሚያ ክልል በሰሜን ከሶዶ ወረዳ እንዲሁም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ከኦሮሚያ ክልል ጋር ይጎራበታል። ወረዳው በሃያ አምስት (25) የገጠር ቀበሌዎችና በአንድ የከተማ አስተዳደር የተከፈለ ነው። የወረዳው ዋና ከተማ ከአዲስ አበባ ቡታጅራ ዝዋይ መስመር በ159 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የቆሼ ከተማ ነው።

የማረቆ ወረዳ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው መልከዓምድር ሜዳማ ነው። ቀሪው ሀያ በመቶ የሚሸፍነው የወረዳው መሬት ደግሞ ኮረብታማና ዳገታማ ነው። የወረዳው አማካኝ የሙቀት መጠን 160 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሲሆን 1200 ሚ.ሜ አመታዊ የዝናብ መጠን አለው።

## 2.3. የማረቆ ብሄረሰብ ኢኮኖሚያዊ መሰረት

የሰው ልጆች ኢኮኖሚያዊ መሰረታቸውን እንደሚኖሩበት አካባቢ መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የአየር ፀባይ ይመርጣሉ። ይህ አይነቱ የአኗኗር ዘይቤና የመኖሪያ አካባቢ መረጣ በአገራችን የታሪክ ጉዞ የነበረና አሁንም ያለ ነው።

የማረቆ ብሄረሰብ አሰፋፈሩም ሆነ የኢኮኖሚ መሰረቱ የአካባቢዉን መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የአየር ፀባይ መሰረት ያደረገ ነው። ብሄረሰቡ ቀደም ባሉት ዘመናት አርብቶ አደር እንደነበር ሀይሉ እና ዲንቀላ[10](ስክርብ፣30) ይገልጻሉ። እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገለፃ ብሄረሰቡ ወደ ማረቆ መጥቶ ሲሰፍር በአርብቶ አደርነት ህይወቱን ይመራ ነበር።

የብሄረሰቡ ከአርብቶ አደርነት በተጨማሪ እርሻን እንደ አንድ መተዳደሪያ አድርጓል። ማህበረሰቡ በአሁኑ ወቅት ከከብት እርባታ በተጨማሪ ኑሮውን በእርሻ ይደጉማል። ይህም ሲባል በአሁኑ ጊዜ የማረቆ ብሄረሰብ መተዳደሪያ ጥምር ግብርና ነው ማለት ይቻላል። አሁን አሁን በብሄረሰቡ በተለይ ወጣቱ ትውልድ በንግድ ስራ እየተሰማራ ነው። እንደ ሀይሉና ዲንቀላ (ስክርብ፣30-31) ገለጻ ከሆነ ቀደም ሲል በተለያየ ቦታ በሰው ቤት ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩ ወጣቶች በተለያዩ አካባቢዎች የቀሰሙትን ልምድ በመጠቀም ጥሩ የንግድ ስራ እየሰሩ ነው።

---

*[10]ዲንቀላ ቧን እባላለሁ። የምኖረው በማረቆ ወረዳ በቆሼ ከተማ ነው። እድሜዬ ሃምሳ ሁለት ነው። ከበቹ ጎሳ ነው የምወለደው። በግብርናና ንግድም በመነገድ ነው የምተዳደረው(ስክርብ፤2004፣29)።*

ማረቆዎች በግብርና ሙያ (እርሻና ከብት እርባታ) የሚታወቁ ቢሆንም በተለያዩ በእደ-ጥበብ ሙያዎችም ይታወቃሉ። በተለይ ማህበረሰቡ የቆዳና የሸክላ ስራ በመስራት፣ የእርሻ መሳሪያዎችን ሀገረሰባዊ እውቀትንና ጥበብን በመጠቀም ያዘጋጃል፤ይጠቀማልም::

## 2.4. የማረቆ ብሔረሰብ ቋንቋና ሀይማኖት

በወረዳው የህዝብ ግንኙነት ቢሮ የተዘጋጀው ጥራዝ እንደሚያሳየው በ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት የማረቆ ወረዳ ሕዝብ ብዛት 78,084 እንደሚሆን ይገመታል። ከዚህ ውስጥ 38,259 የሚሆኑት ወንዶች ሲሆኑ 39,825 ሴቶች ናቸው። ይህ ህዝብ የተለያዩ ቋንቋዎችን እየተጠቀመ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወቱን ይመራል።

የብሄረሰቡ ቋንቋ ማርቅኛ[11] ሲሆን ከኩሽቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ እንደሚመደብ Bender (1976፣36) ይገልፃል። በማረቆ ወረዳ ከማርቅኛ ቋንቋ በተጨማሪ አማርኛ፣ ኦሮሞኛና ጉራጊኛ ቋንቋ ይነገራል።

ሰማኒያ በመቶ (80%) የሚሆነዉ የማረቆ ብሄረሰብ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ እንደሆነ ይገመታል። ከእስልምና ሃይማኖት በተጨማሪ የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮችም በብሄረሰቡ ውስጥ ይገኛሉ። እንደመረጃ አቀባዮቹ ሀይሉ[12](ስክርብ፣29)፣ ሙርኪ (ስክርብ፣ 82) እና ኢማም (ስክርብ፣82) ገለፃ የማረቆ ብሄረሰብ አሁን ላይ የሁለቱ ሀይማኖቶች ተከታይ ቢሆንም አያቶቻቸውና ቅድመ አያቶቻቸው የአንድ እምነት ተከታይ እንደነበሩ ይናገራሉ።

ምንም እንኳ ብሄረሰቡ ከአረብ አገራት ሀይማኖት ለማስፋፋት ሲመጡ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ቢሆኑም በጊዜ ብዛት የተወሰኑት ሃያ በመቶ ያህሉ የክርስትና ሀይማኖትን ተቀብለዋል። ይህንን ሀሳብ ኢማም (ስክርብ፣82) "መጀመሪያ እኮ ሙስሊም ነበርን ሁላችንም" በማለት በቡድን ውይይት ላይ ቀድሞ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ እንደነበሩ ይገልፃሉ።

---

*[11] የብሄረሰቡ አባላት አንዳንድ ጊዜ ማርቅኛ የሚለውን ቃል ሊቢጥሶ ወይም ሊቢዶኛ በማለት ይጠቀማሉ።*
*[12] ሀይሉ ጋጉሮ እባላለሁ። እድሜዬ 52 ነው። የማረቆ ልማት ማህበር ግዥና ክፍያ ክፍል ሃላፊ ነኝ። የመኖሪያ ቀበሌዬ ቆሼ ዙሪያ ነው። ከአሁን በፊት የወረዳው አስተዳዳሪና፣ የወረዳው ፍርድ ቤት ፕሬዜዳንትና ዋና ዳኛ ሆኜም ሰርቻለሁ። ከዚህ በተጨማሪ አሁን ላይ እንደ ሀገር ሽማግሌም ሆኜ እሰራለሁ። የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጅ ነኝ (ስክርብ፤2004፣9)።*

ምንም እንኳ አሁን አሁን በተለያዩ ምክንያቶች እየቀነሰ ቢመጣም የማረቆ ብሄረሰብ በርካታ ባህላዊ እምነቶች ነበሩት፡፡ ይህንን ሀሳብ ሀይሉ ሲገልፁ፡-

> *የኛ ብሄረሰብ ሊቢዶ ማረቆ ሽማግሌዎች እንደባህል በወንዝ እግዜኦ የማለት ልማድም አለ፡፡ ወንዝ ላይ ይሄዱና አም ጭዳ ምናምን ያዘጋጁና ዳልቻ ይታረድ ይባልና በመዋጮ ወይም በግለሰብ ይሰጥና ጎንቱ ጎንቱ[13] የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ሴቶችን ጨምረው ይሄዱና እግዜኦ ማረን ስጠን ተለመነን ብለው ድርቁን አንቻለውም እንቦሳውም ሊሞት ነው ሳሩም እየጠወለገ ነው ብለው ይለምኑታል እሱም ይለመነናል ማለት ነው (ስክርብ፣ 30) በማለት ይናገራሉ፡፡*

ማረቆዎች ባህላዊ እምነቶች የሚከውኑት በማህበረሰባቸው ችግሮች ሲከሰቱ ነው፡፡ በተለይ ድርቅና በሽታ በሚከሰትበት ወቅት ፀሎታቸውን ይሰማናል በሚሉት ወንዝ አካባቢ እየተሰባሰቡ ስርአቱን ይከውናሉ፡፡ በዚህ ስርአት ላይ ፋጣ የሚባል ከጠጅ የተዘጋጀ መጠጥ ወደ ሰማይና ወደ ተዳሚዎቹ ሰዎቹም እየተረጨ ልመናና ፀሎት ይካሄዳል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ባህላዊ እምነቶች እየተዳከሙ ነው፡፡ ድሮ በርካታ ባህላዊ እምነቶች በተለይ በፀሀይ ማምለክ፣ በእናት አባት ውቃቢ-ኢዶት አልዎቾ[14] ያምኑ ነበር፡፡ የማረቆ ብሔረሰብ በጨሌና በዛር ያምናሉ፡፡ ይሁን እንጂ የእስልምናም ሆነ የክርስትና ሀያማኖት እስተምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረ በመምጣቱ ባህላዊ እምነቶችን ቀስ በቀስ እንዲከስሙ እያደረጋቸው ነው፡፡[15]

## 2.5. የማረቆ ብሄረሰብ ማህበራዊ ተቋማት

የማረቆ ብሄረሰብ የእርስ በርስ ማህበራዊ ግንኙነቱንና ኢኮኖሚያዊ አቅሙን የሚያጎለብትባቸው የተለያዩ ተቋማት አሉት፡፡ ማህበረሰቡ በባህላዊ ደንብና ስርአት የሚመራቸውን ተቋማት በተለያየ መልክ ከማደራጀቱም በላይ ተቋማቱን ከዕለት ተዕለት ህይወቱ ጋር በእጅጉ አቆራኝቷቸዋል፡፡ ማረቆዎች በነዚህ ተቋማት እየተጠቀሙ የመረዳዳት፣ የመከባበርና አብሮ የመኖር ባህልን አዳብረው ለዘመናት ወግና ልማዳቸውን ይዘው የኖሩ ህዝቦች ናቸው፡፡

የማረቆ ብሄረሰብ ማህበራዊ ግንኙነቱን ከሚያጠናክርባቸው ተቋማት ውስጥ ማህበር አንድ ነው፡፡ ማረቆዎች ለማህበር የተለየ ክብር አላቸው፡፡ በብሄረሰቡ ስለማህበር ሲነሳ የወጣት ማህበርና የፈረስ ማህበር ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እንደ ዲንቁላ(ስክርብ፣31) ገለፃ በማረቆ

---

*[13] ጎንቱ ጎንቱ የሆኑ ሲባል በእድሜ ጠና ያሉ በማህበራዊ ደረጃቸውም በማህበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚያነሷቸው ሀሳቦች ተቀባይነት ያላቸው ትልልቅ አባቶች ለማለት ነው፡፡*
*[14] በማርቅኛ ኢዶት አልዎቾ የሚለው ቃል ኢዶት እና አልዎች ከተሰኙ ሁለት ቃላት የተገኘ ሲሆን ኢዶት ማለት የእናት ውቃቢ ማለት ነው፡፡ አልዎቾ ማለት ደግሞ የአባት ውቃቢ ማለት ነው፡፡*
*[15] ሀይሉ (ስክርብ፣32)፡፡*

ብሄረሰብ የወጣት ማህበራት ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ ወጣቶች እየተደራጁ የማቋቋሚያ ገንዘብ በማዋጣት የወደፊት ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ያጎለብታሉ። በወጣቶች ማህበር አንድ ሰው ልጅ ሲድር ለተጋቢዎች መቋቋሚያ የሚሆን ከብቶችን በማውጣት ይሰጣል። ማረቆዎች ይህን ማህበር ጌጊዎ[16] ሲሉ ይጠሩታል። ይህ የከብት መዋጮ ሁለቱ ተጋቢዎች የወደፊት ሕይወታቸው ችግር ላይ እንዳይወድቅ ከማድረግ አንፃር ሚናው የጎላ ነው።

በሌላ መልኩ የማረቆ ብሄረሰብ የእርስ በርስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እሴቱን የሚያጎለብተው በፈረስ ማህበር ነው። እንደ ሀይሉ (ስክርብ፣31) ገለፃ የፈረስ ማህበር በማረቆ ብሄረሰብ ዘንድ ትልቅ ከበሬታ የሚሰጠው ሲሆን በማህበሩ አንድ ታዋቂ ሰው ሲሞት ለቅሶው ላይ ፈረሰኞች ፈረሳቸውን ይዘው ያጅባሉ። ሟቹ በፈረሰኞች የሚታጀበው ባለው ማህበራዊ ደርጃ[17] መነሻነት ነው። ሀይሉ እንደሚገልፀው የፈረስ ማህበር ከአሁን በፊት ከለቅሶ ውጭ ባሉ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በተለይ በሰርግ ላይ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። አሁን አሁን ማህበረሰቡ በተለይም በከተማ ውስጥ ሙሽሮች ከፈረስ ይልቅ በመኪና መታጀብን ይመርጣሉ። ይሁን እንጅ በገጠር አካባቢ አሁንም ሙሽሮች በፈረስ ይታጀባሉ።

ሌላውና የማረቆ ብሄረሰብ እርስ በርስ ተረዳድቶ የሚኖርበት ተቋም እቁብ ነው። እንደ ሀይሉ (ስክርብ፣31) ገለፃ በማረቆ ብሄረሰብ ሴቶች የራሳቸው እቁብ አላቸው። ሴቶቹ የሚጥሉት እቁብ ውጆ[18] (የወተት እቁብ) ሲባል የአንድ ሰፈር ሴቶች ወተት እየተለካኩ በማውጣት በተራ ይደርሳቸዋል። ወተቱ የደረሳት ሴት ወተቱን በመናጥ ቅቤውንና ለማህበርና ለሰርግ አሬራውንና እርጎውን ደግሞ ለቤት ፍጆታ ታውላለች።

---

*[16]ጌጊዎ ቃሉ ማርቅኛ ሲሆን ትርጉም የከብት መዋጮ ማለት ነው። ለመዋጮ የሚውሉት ከብቶች ከመሆናቸው ውጭ በብር ከሚጣል እቁብ ጋር ልዩነት የለውም። እንደ እቁብ እየተዋጣ የሚሰጥ በመሆኑ ከባድ አይደለም።*

*[17]በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ አንድ ሟች በፈረስ ማህበር የሚታጀበው ለማህበረሰቡ ባበረከተው አስተዋፆ ወይም የነበረውን የጀግንነት ውሎ፣ የሀብቱን ብዛትና ባለፀጋነቱን በማየት፣አራሽነቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የብሉልኝ ጠጡልኝ ባህሪውን መነሻ በማድረግ በፈረሰኞች ታጅቦ ሲፎከርለት ሲነገርለት ይውላል። የፈረስ ማህበር በሌሎች የሃገራች ብሄረሰቦችም የተለመደ ነው። ይህ ማህበር በአዊ ብሄርሰብ ዘንድ የተለየ ክብር ይሰጠዋል።*

*[18]በማረቆ ብሄረሰብ ውጆ የወተት እቀብ ነው። የወንድወሰን አውላቸው(1998፣22) በስፋት እንዳብራራው በሰባት ቤት ጉራጌ ሴቶች ከሚጥሏቸው የእቁብ አይነቶች ውስጥ የቅቤ እቁብ ተጠቃሽ ነው። በብሄረሰቡ ይህ እቁብ ውጆ ተብሎ ይጠራል። ማረቆዎችና ሰባት ቤት ጉራጌዎች ውጆ የሚለውን ቃል በመጠቀም ደረጃ ቢመሳሰሉም ወተትንና ቅቤን መጠቀማቸው ግን ሁለቱ ብሄረሰቦች የሚጋሯቸው ባህሎች ይኖራሉ የሚል ጥርጣሬን ያሰፋል። በአሁኑ ሰዓት ሰፊ ጥናት ቢካሄድ ተጎራባች ብሄረሰቦች አንድም የዘር ግንዳቸው ተመሳሳይ ነው፤አሊያም በተለያዩ ምክንያቶች የባህል ውርርስ ተካሂዷል።*

የማገረቆ ብሄረሰብ ከወተት እቁብ በተጨማሪ የብር እቁብ ይጥላል፡፡ ማገረቆዎች የተሻለ ቤት ለመስራት ለህያ ወይም ለሰላሳ እየሆኑ እቁብ በመግባት ቤታቸውን ከሳር ወደ ቆርቆሮ ቤት እየቀየሩ እንደሆኑ ሀይሉ (ስክርብ፣31) ይገልጻል፡፡

ብሄረሰቡ የተለያዩ ስራዎችን ተባብሮ መስራት ይወዳሉ፡፡ ይህ የስራ መረዳዳት(ደቦ) ለማህበረሰቡ የጠበቀ ማህበራዊ ግንኙነት መለኪያም ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ሀዘን ላይ የተቀመጠ የብሄረሰቡ አባል እርሻው የሚታረስለት፣ አዝመራው የሚሰበሰብለት በደቦ ነው፡፡

እድር ለማገረቆዎች ሌላው መደጋገፍያቸው ነው፡፡ ማገረቆዎች በእድር እርስ በርስ ብቻ ሳይሆን ከአጎራባች ብሄረሰቦችም ጋር ግንኙነት ይፈጥሩበታል፡፡ ብሄረሰቡ ከራሱና ከአጎራባች ማህበረሰቦች ጋር በተለየዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት አማካኝነት ጠንካራ ግንኙነቶችን በመፍጠር ችግሮችን በጋራ እየፈታና እየተረዳዳ ይኖራል፡፡[19]

---

[19] *ሀይሉ(ስክርብ፣29)፤ዲንቁላ(ስክርብ፣29)፡፡*

## ምዕራፍ ሶስት

## የንድፈ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የመስኩ ምሁራንን በማጣቀስ ከግጭት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጉዳዮች ይዳሰሱበታል፡፡ በተለይም ምሁራኑ የግጭትን ምንነት በተመለከተ የሚያነሷቸውን ነጥቦች፣ የግጭት አይነቶችና አነሳሽ ምክንያቶች፣ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ከምሁራንና ከህግ ሰነዶች አንፃር ምን እንደሚመስሉ የሚዳሰሱ ሲሆን የቀደምት ጥናቶች ቅኝትም በዚሁ ምዕራፍ ተካቶ ቀርቧል፡፡

### 3.1. የግጭት ምንነትና ትውራዊ ቅኝት

ግጭት ምንድን ነው? መነሻውስ? ግጭት እንዴት ይረግባል? እና መሰል ጥያቄዎችን ቀጥተኛና ወጥ መልስ ለመስጠት ቢያዳግትም በተለያዩ የጥናት መስኮች ጥናት የሰሩ ምሁራንን አጣቅሶ ምላሽ መስጠት ይቻላል፡፡

የግጭትን ምንነት በቀጥታ ወደ ባለሙያዎች በመውሰድ ሙያዊ ብያኔ ከማስቀመጥ በፊት መዝገበ ቃላዊ ብያኔውን ማየቱ የተሻለ ነው፡፡ የLeslu አማርኛ እንግሊዘኛ አውዳዊ መዝገብ ቃል ግጭትን "ትግል፣ ልዩነት፣ አለመስማማት፣ ጠብ፣ ውጊያ፣ ግጭት፣ አለመግባባት" Leslu (1973፡226) በማለት ይበይነዋል፡፡ ደስታ(1962፣249) ደግሞ"መግጨት፣መጋጨት፣ ድንገተኛ ጥል፣ እለተ ጠብ፣ ያልታሰበ አደጋ፣ የጊዜ ጦርነት፣ መታ፣ ተመተመ፣ ከረከመ" የሚል መዝገበ ቃላዊ ብያኔ ሰጥተውታል፡፡

በሌላ መልኩ በተለያዩ የጥናት መስኮች ምርምር ያካሄዱ የመስኩ ምሁራን ካላቸው ልምድና የምርምር ውጤት በመነሳት የተለያዩ ብያኔዎችን ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ አንዳንድ ምሁራን(Fisher,2000; Levinson,1996; Fisher,1982, Cohen,1960) ግጭትን ከፍላጎት አለመሳካትና ከአቅርቦት እጥረት ጋር የሚያያዙት ሲሆን ብዙዎች ደግሞ ከተቃራኒ አላማና ግብ ጋር እንደሚገናኝን ይገልፃሉ፡፡ በተለይ Fisher (2000:1) "ግጭት ግንኙነት ባላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች መካከል በሚኖር የግብ ልዩነት መነሻነት አንዱ ሌላውን ለመቆጣጠር ሲባል የሚፈጠር ተቃርኗዊ ስሜት ነው" በማለት ይበይኑታል፡፡

የሰው ልጆች ዕርስ በርሳቸው በማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ግንኙነት እስካላቸው ድረስ በፍላጎትና በሀሳብ ሁል ጊዜ ተጣጥመው ይኖራሉ ለማለት ያስቸግራል፡፡

ምክንያቱም የአንዱን ወገን ስሜትና ፍላጎት ሌላው ወገን ሊጋራ የሚችልበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለዚህም Fisher (2000፡1) "የግጭት አለመፈጠር በሰዎች መካከል ያለው የእርስ በርስ ተራክቦ ዝቅተኛ መሆኑን ማሳያ ምልክት ነው" ሲሉ ይገልጻሉ።

እንደምሁሩ ገለፃ የዕርስ በርስ ተራክቦ በሌለበት ሁኔታ ሰዎች ሊጋጩ አይችሉም። በመሆኑም የርስ በርስ ተራክቦ ያላቸው ቡድኖች ስሜትና ፍላጎት አንድ አይነት አቋም መያዝ ከተሳናቸው መጨረሻቸው ግጭትና መለያየት ይሆናል። Fisher ይህንን ተቃርኖ ትኩረት ሰጥተው ግጭትን ከሰው ልጆች ስሜትና ፍላጎት አለመጣጣም ጋር ያገናኙትም ለዚህ ነው።

ግጭት ከሰው ልጆች አዕምሮታዊ ብስለት ጋር መገናኘቱ ጽንሰ ሀሳቡ ውስብስብ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ምሁራን የሰው ልጆች በሚኖራቸው የእርስ በርስ ማህበራዊ ግንኙነት የተለያዩ ባህሎችን፣ ልማዶችን በመልመድ እንደሚያገኟቸው ሁሉ ግጭትን እንደ አንድ የእውቀት አሀድ በመልመድ ያዳብሯቸዋል።

ግጭት የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ ሰፋ አድርጎ ማየት አልተለመደም። በዚህም የተነሳ ቃሉን የጥፋት መገለጫ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህን ሀሳብ (ደስታ፣1962)፤ የአማርኛ መዝገብ ቃላት፣1993) ለግጭት ከጥፋት ጋር የተዛመደ ፍቺ ሰጥተውታል።

ይሁን እንጅ በመስኩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን (Coser, 1956; Lambert & Myers, 1999; Fisher, 2000; Klyukanov, 2005) ገለፃ ግጭት በሰው ልጆች የዕርስ በርስ ግንኙነት ላይ የራሱ አወንታዊ ሚና እንዳለው ይገልፃሉ። በተለይ Coser (1956) ግጭት በሰው ልጆች ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ዘርፈ ብዙ አዎንታዊ ጎን እንዳለው በመግለፅ የሚከተሉትን ጥቅሞች በዝርዝር ገልጧል፦

- ❖ ግጭት ማንነትን ለመገንባትና ራስን ሆኖ ለመገኘት አስተዋፃው የጎላ ነው። ግጭት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ማንነታቸውን በዙሪያቸው ካሉ ሌሎች ነገሮች ለይተው እንዲመለከቱ ያደርጋል።
- ❖ ግጭት ሰዎች ህብረትን እንዲፈጥሩ ያደርጋል። ግጭቶች ግንኙነትን እንደሚያጠነክሩ ሁሉ በጠላትነት የሚተያዩ ቡድኖችን ወይም ግለሰቦችን ወደ አንድ የጋራ ግብ

እንዲመጡና የጋራ ግባቸውን እንዲያሳኩ በማድረግ በመካከላቸው የተፈጠረውን የጋራ ስጋት ለመፍታት ያስችላቸዋል፡፡

ግጭት በራሱ ጠቃሚም ጎጂም አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ በቡድኖች ወይም በግለሰቦች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን የምንፈታበትና የምንቆጣጠርበት ዘዴ የግጭትን ጠቃሚነትና ጎጂነት ይወስናል፡፡ ግጭትን በሀይል ሚዛን በልጦ ለመፍታት መሞከር ጥፋት ማስከተሉ አይቀርም፡፡ ቡድኖች ርስ በርስ ተደጋግፈው የጋራ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ከተደረገ ደግሞ ግጭት ከጉዳቱ ይልቅ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡[20]

በብዙዎቹ የመስኩ ምሁራን (Lambert & Myers,1999; Fisher,2000; Klyukanov,2005) አተያይ ግጭት በሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ህይወት ላይ ከሚያደርሰው ተፅዕኖ አንፃር ገንቢ (Constructive) እና አፍራሽ (destructive) ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነዚህ ምሁራን የሰው ልጆች በሚኖራቸው ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ሳቢያ የሚፈጠሩ ግጭቶች ገንቢነታቸውንና አፍራሽነታቸውን ለመፈረጅ የሚያስችሉ የተለያዩ መለኪያ መስፈርቶችን ያስቀምጣሉ፡፡ Lambert እና Myers የተባሉት ምሁራን ግጭቶችን ገንቢና አፍራሽ የሚያስብሉ[21] ነጥቦችን ሲገልጹ፡-

> *Conflict is destructive when: The conflict prevents or stops people from working, the dispute hurts a relationship and there are uncontrolled emotions. And Conflict is constructive when: opens people up to new ideas, develops common goals and builds a strong relationship (Lambert & Myers, 1999:44). {ግጭት ሰዎች ስራቸውን እንዲያቆሙ የሚያስገድድ ከሆነ፣ የሰዎች የርስ በርስ ግንኙነት እንዲቀንስ ካደረገና ሰዎች ስሜታቸውን እንዳይቆጣጠሩ የሚገፋፋ ከሆነ አሉታዊ ገጽታ የሚኖረው ሲሆን ግጭቱ ሰዎችን ወደ አዲስ ሀሳብ የሚመራ፣ሰዎች የጋራ ግብና አላማቸውን ለማሳደግ ከጠቅማቸውና የርስ በርስ ግንኙነታቸውን የሚያጠነክረላቸው ከሆነ ደግሞ አዎንታዊ ገጽታ ይኖረዋል Lambert እና Myers (1999:4)} በማለት ይገልጻሉ::*

በሌላ በኩል Klyukanov (2005፡190-191) የግጭትን ገንቢነትና አፍራሽነት በተመለከተ የተለያዩ መለኪያዎች አስቀምጧል፡፡ እንደ ምሁሩ ገለፃ ግጭት ገንቢ የሚሆነው የሚፈጠረው ግጭት የራስንና የሌሎችን ባህል ለማወቅ አጋዥ ከሆነ ነው፡፡ በግጭት መነሻነት ቡድኖች ለሌሎች ቡድኖች ባህልና ማንነት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ያግዛቸዋል፡፡

---

[20] Fisher (2000፡1).

[21] *Klyukanov (2005፡190-191) የግጭትን ገንቢነትና አፍራሽነት ለመለካት የሚያስችሉ ነጥቦችን በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡*

በሌላ መልኩ ምሁሩ ግጭት አፍራሽ የሚሆነው ራሱን ለሌሎች ቡድኖች ባህል፣ ወግና ልማድ ዝግ ያደረገ ቡድን ከሌሎች ቡድኖች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሻከረ እስከ እልቂት የሚያደርሱ ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በነዚህ ቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመቆጣጠር ጊዜ ስለሚወስድ የንብረትና የሰው ህይወት ሊጠፋበት ይችላል። በዚህ ጥፋት መነሻነት ግጭቱ በአፍራሽነት እንደሚፈረጅ ምሁሩ ሀሳባቸውን ያቀርባሉ።

በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በዘመናዊ ወይም በባህላዊ የፍትህ መስጫ ተቋማት እልባት ያገኛሉ። ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ግጭታቸውን በእርቅ ከጨረሱ ግን የቀድሞ ሰላማዊ ግንኙነታቸው ይታደሳል። ለዚህም ብዙዎች (Webel and Galtung, 2007; Bendeman, 2007) ባህላዊ የፍትህ ተቋም ከመደበኛው የፍትህ ተቋም የተሻለ እንደሆነ ይናገራሉ። በተለይም፦

> *Alternative dispute resolution is often regarded as better option than the courentional mechanicsms, because of lower cost, greater spead involved and as a potential of presenting a more successful and sustainable solution (Bendeman,2007:137).{አማራጭ የሙግት መፍቻ ስልት ከዘመናዊ የግጭት መፍቻ ስልት የተሻለ አማራጭ ነው። ምክንያቱም በዝቅተኛ ወጪና ፍጥነት የተሞላበት መፍትሔ ከማስገኘቱም በላይ ዘለቄታዊነቱና ውጤታማነቱ አስተማማኝ ነው (Bendeman,200፡137)}።*

በማለት ባለሙያው የሁለቱን የፍትህ መስጫ ተቋም ጎን ለጎን በመውሰድ ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር ሀሳቡን አብራርቷል።

ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ከዘመናዊው ይልቅ ተመራጭ የሚሆነው በዚህ ብቻ አይደለም። በባህላዊ የፍትህ መስጫ ተቋማት ግጭቶችን መፍታት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የወደፊት ሰላማዊ ህይወት ላይ የራሱ አወንታዊ ሚና ስላለው ተመራጭነቱ ይጎላል።

እርቅ ውጤታማ የሚሆነው ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን በዘላቂነት ለማስማማት የሚከናወነው የእርቅ ሂደት በአግባቡ ሲከናወን ነው። በተለይ ለእርቅ አስፈላጊ የሆኑ ማህበራዊ እሴቶች ሳይሸራረፉ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ Bar-Tal የተባሉ ባለሙያ የእርቅንና የህገረሰባዊ እምነቶችን ተጣጥሞሻዊ አካሄድ አስረድተዋል።

በቡድኖች መካከል የሚከናወን እርቅ የተለያዩ ነጥቦች መያዝ ይኖርበታል። አንደኛው ወደ እርቅ የሚመጡ አካላት ለግጭት ባበቃቸው ጉዳይ ላይ በግልጽ መወያየት ይኖርባቸዋል።

ቡድኖችን ለዘላቂታዊና ሰላማዊ ህይወት የሚጋብዝ እርቅ ባለጉዳዮች በግልፅነት እንዲወያዩ በር መክፈት ይኖርበታል፡፡[22]

ሁለተኛው ደግሞ የሚከናወነው እርቅ ፍትህ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡ ግጭት ውስጥ የገቡት ቡድኖች ከእርቅ በኂላ ቀድሞ የነበራቸውን ሰላማዊ ግንኙነት መመለስ መቻል አለበት፡፡ የእርቅ የመጨረሻ ግብ ግንኙነታቸው የተቋረጡባቸውንና ለብቀላ የተዘጋጁ ቡድኖችን ወደ ሰላማዊና ቤተሰባዊ ግንኙነት መመለስ ነው፡፡ በመሆኑም እርቁ ባላንጣዎችን በመልካም ግንኙነት እንዲቀራረቡ ማገዝ መቻል አለበት፡፡

ሌላውና ሶስተኛው ደግሞ እርቅ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ወደ ፊት በሚኖራቸው የርስ በርስ ግንኙነት የራሳቸውንና የጋራ ደህንነታቸውን በጋራ የመጠበቅ ሚና እንዳለባቸው የሚያሳምንና ተመሳሳይ አቋም እንዲኖራቸው የሚያግዝ መሆን አለበት፡፡ እነዚህ ነጥቦች ለእርቅ ውጤታማነት እጅግ አስፈላጊና ከግንዛቤ መግባት እንዳለባቸው ምሁሩ አፅንኦት ሰጥተው ያብራሩታል፡፡

ግጭትን ከስነ-ልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች አንጻር የሚያጠኑት Bar-Tal በባህላዊ የፍትህ ተቋማት መፍትሔ የሚሰጣቸው አለመግባባቶች ዘለቂታዊነት እንዲኖራቸው ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት የተለያዩ ሀሳፊነቶችን መወጣት አለባቸው፡፡ እንደ ምሁሩ ማብራሪያ አጠቃላይ የእርቅ ሂደት የተሳካ ይሆን ዘንድ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የያዟቸውንና የሚያምኑባቸውን ማህበረሰባዊ እምነቶች [23](societal beliefs) መቀየር ይኖርባቸዋል፡፡ ቡድኖቹ የያዟቸውን ማህበረሰባዊ እምነቶች መቀየር ካልቻሉ እርቅ ሊኖር አይችልም፡፡ Bar-Tal እነዚህን ማህበረሰባዊ እምነቶች የእርቅ ሂደት ተግዳሮቶች ሲል ይገልፃቸዋል፡፡[24]

---

[22] Bar-Tal (2007፡356).

[23]*Bar-Tal (2000,353) ማህበረሰባዊ እምነትን ሲበይን፡- Societal beliefs are defined as society member's shared cognitions on topics and issues that are of special concern for society and contribute to their sense of uniqueness.*

[24]*Bar-Tal(2000፡357-359) በዝርዝር እንደሚያስረዳው የእርቅ ሂደት ተግዳሮቶች የሚባሉት ሀገረሰባዊ እምነቶች አራት ናቸው፡፡ አንደኛው ቡድኖች በማህበረሰባዊ ግባቸው ላይ ያላቸው እምነት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ቡድኖች ሌሎችን የተናቁና ዝቅተኛ ናችው የሚል ማህበረሰባዊ እምነት ያላቸው ከሆነ ነው፡፡ ሌላውና ሦስተኛው ቡድኖች ሌሎችን ቡድኖች ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች እንዳልተመረጡና ብቁ እንዳልሆኑ አድርጎ ማህበረሰባዊ እምነት ማዳበር ነው፡፡ አራተኛው ቡድኖች ለሰላም[24] (peace) ያላቸው አተያይ ነው፡፡*

### 3.2. የግጭት አይነቶችና አነሳሽ ምክንያቶች

ምንም እንኳ ግጭቶችን በአይነት ከፋፍሎ ማጥናት የራሱ ችግር ቢኖረውም ምሁራን ግጭቶችን በተለያዩ ክፍሎች እየመደቡ ያጠኗቸዋል፡፡ በዚህ ክፍል የመስኩ ምሁራን በአንድ መድበው ያጠኗቸውን የግጭት አይነቶችና አነሳሽ ምክንያታቸው ቀርቧል፡፡

#### 3.2.1. የግጭት አይነቶች

ግጭት መልኩ ብዙ ነው፡፡ ይህን መልከ ብዙነት Fisher (2003:3) ሲያብራሩት የሰው ልጆች በሚያሳልፏቸው የህይወት ውጣ ውረዶች የተለያዩ ግጭቶች ያጋጥሟቸዋል፡፡ ምሁሩም በሰው ልጆች የእለት ተዕለት ሕይወት የሚያጋጥሙ ግጭቶችን በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍሏቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

ግለሰባዊ ግጭት (Interpersonal Conflict):- ይህ የግጭት አይነት የሚፈጠረው ሁለት ሰዎች የተጋጩ ፈላጎት፣ ግብ ወይም አቀራረብ ሲያዳብሩ ነው፡፡ ለግለሰባዊ ግጭቶች እንደ መነሻ ተደርጎ የሚቆጠረው የተግባቦት ችግር ነው፡፡ ይህ ግጭት ግለሰቦች የተግባቦት ክኂላቸውን በትምህርት ማበልፀግ ሲችሉ የግጭቱ መንስኤም አብሮ ይደርቃል ሲሉ ባለሙያው ይናገራሉ፡፡ በማረቅ ብሄረሰብ ይህ የግጭት አይነት በተደጋጋሚ የሚከሰት ሲሆን ግጭቱ በሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም መፍትሄ ይፈለግለታል፡፡

ሚናዊ ግጭቶች (Role Conflict):-የሰው ልጆች በአንድ ማህበራዊ ስርአት ላይ ያላቸው ሀላፊነት፣ ግምትና ሚና በሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ግርታን ሲፈጥር ግጭቱ ይከሰታል፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ያላቸው መብትና ግዴታ በውል ተለይቶ የማይታወቅ ከሆነ በሰራተኞቹ መካከል ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ አለቃ የአለቅነቱን ስራተኛ ደግሞ የሰራተኝነቱን ሚና በአግባቡ የማይወጣ ከሆነ ግጭቱ የሚና ግጭት ይባላል፡፡ የሚና ግጭቱ በተቋሙ ውስጥ በሚሰሩት ግለሰቦች ሁሉ የሚደርስ ከሆነ ከግለሰባዊ ግጭት ጋር የሚገናኝበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ቡድናዊ ግጭት (Inter-group Conflict):- ሰዎች ቡድን ለይተው ወደ ግጭት ሲገቡ ቡድናዊ ግጭት እንለዋለን፡፡ ቡድኑ በጎሳ ወይም በዘር የተደራጀ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳች ጉዳይ የተጋሩና ለአንድ ግብ የተደራጁ ቡድኖች ለሌሎች ቡድኖች አሉታዊ የሆነ አመለካከት በማዳበር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያገኟቸዋል፡፡ይህ የመገለልና የንቀት ስሜት ቡድኖችን ግጭት ውስጥ እንዲገቡ ይገፋፋቸዋል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች ቡድኖች ወይም ጎሳዎች ለማስታረቅ የሚበቁና የማይበቁ ተብሎ የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት የሚፈጠርበት አጋጣሚ

ብዙ ነው። ይህን መሰሉ ንቀታዊ የጎሳ ወይም የቡድን መገለል (መከፋፈል ልንለው እንችላለን) አንዳንዴ ለግጭት ያበቃል። እንደ Bar-Tal አይነት ምሁራን ይህን ማህበረሰባዊ እምነት *"societal beliefs of delegitimizing the opponent concern denial of the adversary's humanity through dehumanization, extreme negative trait characterization, out casting, use of political negative labels, and negative group comparison (Bar-Tal,2000:354)"* በማለት ማህበረሰባዊ እምነቱ ቡድኖችን ወደ ግጭት በመገፋፋቱ በኩል ያለውን ተፅዕኖ ይገልፁታል።

**የብዙሀ ቡድን ግጭት** (Multi-party Conflict) ፡- እነዚህ ግጭቶች ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ናቸው። የብዙሀ ቡድን ግጭቶች ማህበረሰቦች ወይም ተቋማት በጥሬ ሀብት ቁጥጥር ወይም በፖሊሲ አተገባበር ላይ የተለያየ አቋም ሲኖራቸው የሚፈጠሩ ናቸው። እነዚህ የልዩነት ግጭቶች ውስብስብ ሲሆኑ አይነተኛ መነሻቸውም ኢኮኖሚ፣ እሴትና የስልጣን ጉዳይ ነው። በማረቆ ብሄረሰብ የመጠጥ ውሀንና የእርሻ መሬትን ለመቆጣጠር ሲል ጎሳ ከጎሳ ጋር እንዲሁም ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር የሚያጋጥሙት ግጭቶች በዚህ የግጭት አይነት ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው።

**አለማቀፋዊ ግጭቶች** (International Conflict) ፡- እነዚህ ግጭቶች በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታዩ ሲሆን በሀገሮች መካከል የሚከሰቱ ናቸው። የግጭቶቹ መነሻ ሀገራትን የጥሬ ሀብት ፍላጎት መሰረት የሚያደርግ ሲሆን ውስን ጥሬ ሀብቶችን ለመጠቀም ከሚደረግ ውድድር ጋር ግንኙነት አላቸው። ውስን ጥሬ ሀብት የግጭቶቹ መነሻ ይሁኑ እንጅ የእሴትና የስልጣን ጉዳይም አይነተኛ መነሻዎች ናቸው።

### 3.2.2. የግጭት መነሻ ምክንያቶች

የብዙ ግጭቶች መነሻ ምክንያት በውል እነዚህ ነገሮች ናቸው ብሎ በእርግጠኛነት መናገር ይከብዳል። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ግጭቶች በአንድ ጊዜ ፈንድተው የሚወጡ ሳይሆን የበርካታ ችግሮች ድምር ውጤቶች ናቸው። በአንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ውስጥ ፈንድቶ ለመውጣት ምክንያት የሚፈልግ የስሜት፣ የሀሳብ ወይም የፍላጎት ተቃርኖ በአንድ አጋጣሚ ወደ ለየለት ግጭት ይለወጣል። ይህን በተመለከተ Fisher የተባሉት ምሁር *"conflicts are not of a pure type, but invove a mixture of sources"* Fisher

*(2000:2)* በማለት ግጭቶች የተለያዩ ምንጮች ድምር ውጤት እንደሆነ ይገልፃሉ። ምሁሩ እንደገለፁት ግጭት በዋናነት አራት መነሻ ምክንያቶች አሉት። እነርሱም:-

**ኢኮኖሚያዊ ግጭቶች** (Economic conflict) ፡- የመጀመሪያው የግጭት መነሻ የኢኮኖሚ ጉዳይ ነው። ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በሚያጋጥማቸው የጥሬ ሀብት ውስኑነት ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ቡድኖቹ ወይም ግለሰቦቹ እነዚህን ውስን የሆኑ ጥሬ ሀብቶች ለማግኘት ያላቸው ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ሁለቱ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች እነዚህን ውስን ጥሬ ሀብቶች የግል ለማድረግ ውድድርና ፉክክር ስለሚገቡ መጨረሻቸው ግጭት ይሆናል።

**የእሴት ግጭት** (value conflict) ፡- እነዚህ የግጭት መነሻ ምክንያቶች በሰው ልጆች የአኗኗር ዘይቤ፣የርዕዮተ አለም ምርጫና ፍላጎት መቃረን ማለትም የአኗኗር መርህ፣ ስርአቶችና እምነቶች ላይ የሚፈጠሩ ሳንካዎች ናቸው።ቡድኖች እነዚህ እሴቶች ሲሸረሸሩባቸው ወይም የማይቀበሏቸውን እሴቶች በሌሎች አካላት ጫና እንዲቀበሉ ግፊቱ ሲበረታባቸው ግጭቶች ይከሰታሉ።

**የስልጣን ግጭት** (power conflict) ፡- ይህ የግጭት መነሻ የሚፈጠረው አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ በሌላኛው ቡድን ወይም ግለሰብ ላይ የስልጣን ተፅዕኖ ሲያሳርፍ ነው። ቡድኖች በሌሎች ቡድኖች ላይ የሀይል ሚዛናቸውን በማሳደግ ማህበራዊ ድባቡን የእንቆጣጠር ስሜትን ሲያዳብሩ ግጭቱ ይፈጠራል። ተፅዕኖ የደረሰባቸው ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች የሀይል ሚዛኑን ወደ ራሳቸው ለመመለስ የስልጣን ሽኩቻቸው በአሸናፊነትና በተሸናፊነት ይጠናቀቃል። ይህ የግጭት መንስኤ በግለሰቦች፣ በቡድኖች ወይም በሀገር ደረጃ ሊፈጠር ይችላል።

**የተግባቦት ችግር** (Ineffective Communication):- የተግባቦች ችግር ሌላኛው የግጭት ምንጭ ነው። ምንም እንኳ በቡድኖች ወይም በግለሰቦች መካከል መሰረታዊ የሚባል ተቃርኗዊ ፍላጎትና ስሜት ባይኖራቸውም በሚኖራቸው ግንኙነት ወቅት ዕርስ በርስ ሳይግባቡ ወይም ሳይረዳዱ ሲቀር ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። Notter(1995:9) ይህንኑ ሀሳብ *"conflict situations are often based on Imperfect Communication and perception"* በማለት የግጭትን መነሻ ምክንያት ይናገራሉ።

### 3.3. የግጭት አፈታት ዘዴዎች

በዚህ ርዕስ ስር ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች የሚነሱ ሲሆን የመጀመሪያው የሰው ልጆች የሚያጥሟቸውን ልዩ ልዩ ግጭቶች ለመፍታት ያግዛሉ ተብለው በመስኩ ምሁራን የቀረቡ የግጭት መፍጫ ዘዴዎች በዝርዝር የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የግጭት አፈታት በህግ ሰነዶች ላይ ምን እንደሚመስል በዝርዝር የተቃኘበት ክፍል ነው፡፡

#### 3.3.1. የግጭት አፈታት ዘዴ ከመስኩ ምሁራን አንጻር

ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና ለመቆጣጠር ተቀናጅቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ግጭት በአንድ አካል ወይም በድን ፍላጎት ብቻ ሊፈታ አይችልም፡፡ ምሁራንም (Bar-Tal, 2000; William, 2004; Notter, 1995) ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖችን ወይም ግለሰቦች በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት የጋራ ችግራቸው በማድረግ በሶስተኛ ወገን አደራዳሪነትና ሽምጋይነት ግጭታቸውን መፍታት እንዳለባቸው ይገልፃሉ፡፡

በቡድኖችም ሆነ በግለሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ወደ ከፋ ጥፋት ከማምራታቸው በፊት እልባት የሚሰጥባቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነዚህ የግጭት ማብረጃና መፍቻ ስልቶች በተለያየ ክፍል እንደሚከፈሉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ *Imobighe (2003፡5)"conflict management approaches can be classified in a number of ways. They can, for instance, be classified in to tow broad categories"* በማለት የግጭት ቁጥጥር ዘዴዎች በተለያዩ መንገዶች ሊከፍሉ እንደሚችሉ በመጠቆም ዘዴዎቹን በሁለት ሰፋፊ ክፍሎች ይከፍሏቸዋል፡፡

የመጀመሪያው የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የመክፈያ መንገድ የሚከሰቱት ግጭቶች ከሚፈቱበት መንገድ አንጻር ሲሆን በዚህም ሰላማዊ (peaceful) እና ወታደራዊ ሀይል (military) ተብለው ይከፈላሉ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ግጭቱን ለመፍታት ከሚሳተፉት አካላትና ከድርድሩ ወይም ከክርክሩ ሂደት አንጻር የሚታይ ነው፡፡ እንደ Imobighe (2003፡5) ገለፃ በዚህ ምድብ ስር ምሁራን ትኩረት ሰጥተው የሚያቀርቧቸው ሶስት ዋና ዋና የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነዚህም ድርድር (Negotiation)፣ሽምግልና(mediation) እና ዳኝነት(Arbitration) ናቸው፡፡

ድርድር (Negotiation) ፡- ድርድር በግለሰቦች፣ በቡድኖች፣ በብሄረሰቦች ሰፋ ሲልም በሀገሮች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍተታት ከሚያገለግሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ነው። ድርድር ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በራሳቸው ፈቃድና ውሳኔ ላይ የሚደርሱበት ዘዴ ነው። ይህንንም Weble እና Galtung (2007፡84) የተባሉ ምሁራን "Negotiation is a conflict resolution method in which the couflicting parties reach agreement through muctual consensus" ሲሉ አብራርተው ገልፀውታል።

ግጭት ውስጥ ያሉ አካላት በድርድር ችግሮቻቸውን ለመፍታት አቀራራቢ ወገን ያስፈልጋቸዋል። ይህም ማለት በመካከላቸው ያለው የተቃርኖ ሀሳብ እንዲረግብና የሁለቱ ወገኖች ድርድር ፍሬያማ እንዲሆን በሶስተኛ ወገን እገዛ ይደረግላቸዋል።

ሽምግልና (Mediation) ፡- ሽምግልና ሌላኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ ሲሆን ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በመካከላቸው የተፈጠሩ ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ የሚደረግበት አጠቃላይ ሂደት ነው። በዚህ የግጭት መፍቻ ስልት ሁለቱን ወገኖች የሚያሸማግል ሶስተኛ ወገን ቢኖርም የመጨረሻው የእርቅ ሂደት ላይ ውሳኔ የሚተላለፈው በሁለቱ ወገኖች የጋራ ስምምነት ነው።

በሽምግልና ሂደት ውስጥ የሽምጋዩ አካል ሁለንተናዊ ሰብዕና ከግምት ውስጥ የሚገባ ሲሆን በተሽማጋዮችም ይሁንታን ማግኘት ይኖርበታል። ይህን ሀሳብ Webel እና Galtung የተባሉ ምሁራን በሽምግልናው ላይ የሚሳተፍ ሶስተኛ ወገን በማህበረሰቡና ግግት ውስጥ በገቡት ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ሀገሮች ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት። ምሁራኑ ይህንን *ሀሳብ ጠቅለል አድርገው ሲያብራሩ፡-*

> *"The mediators, particularly respected elders of the village community assistes in organizing or moderating dialogue, in socially valuable places such as the yards of mosques and churches or shades of old tree" (Webel and Galtung, 2007:85). {አሸማጋዩ በእድሜ ጠና ያለ በማህበረሰቡ ዘንድ በተከበሩ ቦታዎች ላይ ማለትም በመስጊዶች፣በቤተ-ክርስቲያን ወይም በእድሜ ጠገብ ዛፎች ጥላ ስር ውይይቶችን መምራትና ማደራጀት የሚችል መሆን አለበት (Webel እና Galtung, 2007:85) በማለት ይገልፃሉ}።*

በሽምግልና የሚከናወን እርቅ ውጤታማ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች ለሽማግሌዎች የሚሰጡት ክብር ነው። ሽማግሌዎችን ማክበርና ቃላቸውን መጠበቅ እንደ አንድ ማህበራዊ እሴት በሚቆጠርበት ማህበረሰብ ውስጥ ሽማግሌዎች

ቀጥተኛ የሆነ ውሳኔ ማሳለፍ ባይችሉ እንኳ ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች የማህበረሰቡን ማህበራዊ እሴቶች እንዲጠብቁ በመገፋፋት እርቁ ይከናወናል፡፡

ዳኝነት (Arbitration) ፡- ሌላውና ሶስተኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ ዳኝነት ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከሚያስችሉት ስልቶች ውስጥ ሽምግልና አንዱ ነው፡፡ ይህ የግጭት መፍቻ ስልት ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖችን ወይም ግለሰቦችን ለማስማማት ሶስተኛ ወገኖች ጣልቃ የሚገቡበትና ውሳኔ የሚያስተላልፉበት ስልት ነው፡፡

### 3.3.2 የግጭት አፈታት ከህግ ሰነዶች አንጻር

የሰዎችን ባህልና ልማድ አደርጎ ግጭቶችን መፍታት የተለመደ ቢሆንም ዘመናዊ በሚባለው እውቀትና ጥበብ የሚረቀቁና ስራ ላይ የሚውሉ ዘመናዊ ህጎች፣ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና መመሪያዎችም የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለማርገብና ለመፍታት ያገለግላሉ፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የማነሳውም በኢትየጵያና በአለም አቀፍ ደረጃ የተረቀቁ ህጎች ግጭቶችን ከመፍታት አንፃር ያላቸውን አስተዋፅዖ ነው፡፡

#### 3.3.2.1 የግጭት አፈታት ከኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች አንፃር

የሰው ልጆች በሚኖራቸው የዕርስ በርስ ማህበራዊ ግንኙነት ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ግጭቶች መፍትሄ የሚያገኙት ከዘመናዊ ትምህርት በተገኘ እውቀት ተረቆና ዳብሮ በፀደቀ ህግ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆችን ወግ ልማድ መሰረት ባደረጉ ባህላዊ ህገ ደንቦችና ስርዓቶችም ጭምር ነው፡፡

ኢትዮጵያዊያ በዘመናዊ ህግ መተዳደር ከመጀመራቸው በፊት ችግሮቻቸውን በፍትሀ ነገስት[25] አማካኝነት ሲፈቱና ሲመሩበትም ኖረዋል፡፡ በዘመኑ ፍትሀ ነገስት የህግ መፅሀፍ ብቻ ሳይሆን በመፅሀፉ እውቀት ለተካኑ ሰዎች የተለየ ድጋፍና ከበሬታ ትሰጥ እንደነበርም ዳኛ እየሆኑ የሰሩ ሰዎች በቂ መረጃ ይሆናሉ፡፡ በአብዛኛው በፍትሀ ነገስት የተደነገጉት ህጎች

*[25] ፍትሀ ነገስት የሚለው ቃል ፍትሀና ነገስት በሚሉት ሁለት ቃላት የተሰናሰለ ወይም የተያያዘ ቃል ነው፡፡ ትርጓሜውም ውሳኔ መስጠት፣ ህግና ስርአትን ማስፈን ማለት ሲሆን ነገስታቱ ክርስቲያኖች ከመሆናቸው ጋር ስጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ፍትህ ይመለከቱ ስለነበር በነገስታቱ ስም ፍትሃ ነገስት ተብሎ ተሰይሟል፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን በጽሁፍ ከአሉዋት ጥንታውያን የህግ መጽሀፍት መካከል ታላቁና የታወቀው ፍትሀ ነገስት የተባለው መጽሀፍ ነው፡፡ ፍትሀ ነገስት ከአረበኛ ወደ ግዕዝ የተተረጎመውና በስራ ላይ የዋለው በንጉሰ ነገስቱ አጼ ዘርዐያቆብ (ከ 1444-1468) ዓ.ም እንደሆነ (ዲበኩሉ፤1993፣38-44) አብራርቶታል፡፡*

"አይን ያጠፋ አይን ያጥፋ" ከሚለው የኦሪት ህግ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። በተለይ ፍትሀ ነገስት(1958፣548) "አንዱ አንዱን በሰይፍ ቢገድል መትቶ በገደለው በሰይፍ ይሙት" የሚለውን ህግ መጥቀስ ይቻላል።

ፍትሀ ነገስት የኦሪታዊነት አሻራ ባረፈባቸው ህጎች የተቀናጁ አንቀፆችን ቢይዝም በዳይ ተገቢውን ቅጣት ከተቀበለ በኋላ ከተበዳይ ጋር መታረቅ እንዳለበት ይገልጻል። ይህን ሀሳብ በፍትሀ ነገስት (1958፣552) "ዳኞች በገዳዮቹና በባላጋሮች መካከል ታረቁ ብለው ፈርደዉ ከባለደሞቹ ያስታርቁት፤ ቢወዱም ባይወዱም ያስታርቋቸው" በማለት ቀሪው የሚችና የገዳይ ቤተሰብ ወደ ፊት በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው ተጠቅሷል።

በ1923 ዓ.ም የተረቀቀውና ስራ ላይ የዋለው የመጀመሪያው ህገ መንግስት ሌላው ነው። ህገ-መንግስቱ ስድስት አንቀፆች ያሉት ሲሆን ሁለቱ ምዕራፎች ስለ ንጉሰ ነገስቱ ስልጣን የሚያትቱ ናቸው። በህገ መንግስት ምዕራፍ አራት ስለ ንጉሱ አማካሪዎች እንዲሁም ምዕራፍ አምስትና ስድስት ስለ ሚኒስትሮችና ስለ ዳኝነት ያትታል። ይሁን እንጅ ህገ-መንግስቱ ስለ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ምንም ሀሳብ አልተካተተ። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ህጎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን የዘነጉት ከጅምሩ ነው ለማለት ያስደፍራል።

በ1948 ተሻሽሎ የወጣው ህግ መንግስት በአንቀፅ 108 ላይ የዳኝነት ስልጣን በህግ ለተቋቋመ ፍርድ ቤት የተሰጠ መሆኑን በማስረገጥ ዳግም ኢትዮጵያዊያን በልማድ ወጋቸው ችግሮቻቸውን የሚፈቱባቸው ባህላዊ ተቋሞቻቸው እውቅና ተነፍገዋቸዋል። ይህ የሚያሳየን ከፍትሀ ነገስት በኋላ ስራ ላይ የዋሉት ዘመናዊ ህጎች አንዳንዶቹ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን ሙሉ በሙሉ የዘነጉ አንዳንዶቹ ደግሞ ጥልቀትና ዘለቄታዊ ዋስትና የሌለው የህግ ዋስትና የሰጡ መሆናቸውን እንታዘባለን።

ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለው የ"ኢ.ፌ.ዲ.ሪ" ህገ መንግስት አስራ አንድ ምዕራፎችና አንድ መቶ ስድስት አንቀፆችን የያዘ ሲሆን ህገ-መንግስቱ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ስፋትና ጥልቀት ባኖረውም እውቅና ሰጥቷል። በህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 78(5) "የተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች በአንቀጽ 34(5) መሰረት የሀይማኖትና የባህል ፍርድ

ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጡ ይችላሉ" በማለት ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት እውቅና የሚሰጥ ሀሳብ አስፍሯል፡፡

በሌላ በኩልም በተለያየ ጊዜ ስራ ላይ የዋሉ የፍትሀብሔር ህጎች ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት በተለያየ ደረጃ እውቅና የሰጡበት አጋጣሚ አለ፡፡ *በ1952 ዓ.ም የወጣው የፍትሀ* ብሄር ህግ ከአንቀጽ 676-682 የባልና ሚስት ግጭትን በተመለከተ ሁለቱ ተጋቢዎች በቤተ-ዘመድ ሽምግልና መፍታት እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡ ከባልና ሚስት ግጭት ጋር በተያያዘ በ1992 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የቤተሰብ ህግ ደግሞ በአንቀጽ 121(3) ላይ "አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ከፍቺ በመልስ ለማግባባት ከመጣር አልፌው ባልና ሚስቱን የሚመለከት ማንኛውንም ትዕዛዝም ሆነ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የላቸውም" በማለት በ1952 ዓ.ም ከወጣው የፍትሐብሄር ህግ ብዙም የተለየ እውቅና ያልሰጠ ህግ ነበር፡፡ የቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 20 ግልግልና እርቅ ከዘመናዊ ህግ ጋር ባልተቃረነ መልኩ ሊሰራባቸው እንደሚችል ይገልፃል፡፡

በአጠቃላይ በተለያየ ጊዜ ስራ ላይ የዋሉት የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች ደረጃው ቢለያይም ለባህላዊ ሽምግልና ስርዓቶች እውቅና ሰጥተዋል፡፡ ከሁሉም የህግ ሰነዶች በተሸለ ፍትሀ ነገስት ለባህላዊ ሽምግልና ሙሉ ትኩረት ከመስጠቱም በላይ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የግዴታ መታረቅ እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ ከፍትሀ ነገስት በኂላ ያሉት የህግ ሰነዶች ግን ለባህላዊ ተቋማትም ሆነ ግጭት ውስጥ ለሚገቡት አካላት ነፃነት የሚሰጡ ናቸው፡፡

#### 3.3.2.2 የግጭት አፈታት ዘዴ ከአለም አቀፍ ህጎች አንጻር

በተለያዩ አህጉሮች ያሉ ሀገራት ዳር ደንበራቸውን ጠብቀው በመከባበርና በጋራ ጥቅሞቻቸው ላይ በመተጋገዝ ይኖራሉ፡፡ ሀገራት በሚኖራቸው ግንኙነት አንዳንዴ በሀሳብና በፍላጎት ዕርስ በርስ አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ በመካከላቸው የነበረው ትብብርም ተረስቶ ሀገራቱ ግጭት ውስጥ የሚገቡበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ሀገራቱ እነዚህን ግጭቶች በማርገብና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በመፍታት ቀደምሲል የነበራቸውን ሰላማዊ ግንኙነት ለመመለስ የተለያዩ ድርጅቶችን ደንቦችንና ህጎችን ያወጣሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የአፍሪካ ህብረትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የአፍሪካን ህብረት በአፍሪካ ሀገራት መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ለመፍታት የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡ የድርጅቱ አላማ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 2(1) በአፍሪካ

ሀገሮች መካከል አንድነትን፣ ወዳጅነትና ትብብርን ማጠናከር፣የህዝቡን ኑሮ ማሻሻል፣የአባል ሀገራቱን ሉአላዊ የግዛት አንድነትና ነጻነታቸውን ማጠናከር፣ የአፍሪካ ሀገሮችን ከቀኝ ግዛት ማላቀቅ፣አለም አቀፍ ትብብሮችን ማጠናከር፣ የተባበሩትን መንግስታትን ቻርተርና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን ማክበር የሚሉ ናቸው፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እነዚህን አላማዎች በመያዝ በአባል ሀገራቱ መካከልና ዕርስ በርስ የሚከሰትን ግጭት ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፈታት እንዳለበት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 3(3) ላይ ተገልጿል፡፡ እንደ ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱባቸው ዘዴዎች ሽምግልና(mediation)፣ እርቅ(concililation)፣ ዳኝነት (Arbitation) እና ድርድር (negotiation ) ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የግጭት አፈታት ዘዴ ሌላኛው ነው፡፡ ድርጅቱ የተመሰረተው እ.ኤ.አ በ1945 ሲሆን የተቋቋመበት ዋና አላማ በአባል ሀገራት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ማድረግ፣ አባል ሀገራቱም ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህን ለማስፋት በመቻቻልና በሰላም ለመኖር መስማማታቸውን በአንቀጽ አንድ (1) ላይ በሰፊው ተገልጿል፡፡

ድርጅቱ በአገሮች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችና አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እንዲያግዘውም በስሩ የፀጥታው ምክር ቤትንና አለም አቀፍ ፍርድ ቤትን አቋቁሟል፡፡ በአንቀጽ 30፣40 እና 41 መሰረት የጸጥታው ምክር ቤት በአገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን፣ የግዛት ሉአላዊነትን በመጣስ የሚደረጉ ወረራዎችን፣ የአለምን ሰላምና ደህንነት የሚያደፈርሱና ማንኛውንም ፀብ አጫሪነት ተግባራት እየተከታተለ አፋጣኝ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብ ወይም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የመፍትሔ አቅጣጫዎች የመወሰን ሙሉ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

ይህ አለም አቀፍ ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 33(1)[26] መሰረት በአገሮች መካከል የሚከሰቱ ማንኛውም አይነት ግጭቶች መጀመሪያ መፍትሔ ሊፈልግላቸው የሚገባው

---

[26]*Stefan Wolff and Christalla Yakinthou(2011,3) እንደሚገልፁት የተባበሩት መንግስታት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ33(1) እንዲህ ይላል "first of all, seek a solution by negotiation, enquiry, mediation, conciliation, arbitration, judicial settlement, resort to regional agencies or arrangements, or other peaceful means of their own choice"*

በቅድሚያ ድርድር(negotiation)፣ሽምግልና (mediation)፣ በእርቅ(conciliation)፣ዳኝነት (arbitration)፣በህጋዊ ስምምነት(Judical settlement)፣በአካባቢያዊ ድርጅቶች እገዛ (resolt to regional agencies) ወይም ወደ ግጭት የገቡት አካላት ራሳቸው በመረጡት ሰላማዊ መንገድ መፍትሔ ማፈላለግ እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡

## 3.4. አውድ በፎክሎር ጥናት

አንድን ተከዋኝ የፎክሎር አይነት በክዋኔ-ተኮር አቀራረብ ለማጥናት እና ለመረዳት የተለያዩ ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም የፎክሎር አይነቱ ከዋኝ፣ አድማጭ ወይም ተደራሲ፣ ለክዋኔ የሚቀርበው ጉዳይ፣ መቼት፣ መልዕክት፣ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ ህገ-ደንብ እና የአድማጩ ምላሽ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

እንደ Bauman (1983፣362) በክዋኔ ተኮር አቀራረብ የትኛውንም ፎክሎር አይነት መረዳትና መተርጎም የሚቻለው በዚያው በማህበረሰቡ ወይም በቡድኑ ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ በዚህ መነሻነት አንድ የፎክሎር ተመራማሪ ከመስክ ያገኘውን መረጃ በእነዚህ ሁለት የአውድ አይነቶች መድቦና አደራጅቶ መተንተን አለበት፡፡ እነዚህም አውዶች፡-

### 3.4.1. ባህላዊ አውድ

እንደ Bauman (1983፡362) ገለፃ ባህላዊ አውድ የአንድ ማህበራዊ ቡድን ብቻ የሆነ የግንኙነትና የመግባቢያ ደንብ ነው፡፡ ይህ የአውድ አይነት አንድ የፎክሎር አይነት (fokloric gener) በየባህሉ የሚሰጠውን ትርጉም (meaning) እና ትዕምርታዊ ግንኙነቶችን ይመለከታል፡፡ በውስጡም ሶስት ንዑሳን አውዶችን ያቅፋል፡፡ እነርሱም፡-

የትርጉም አውድ (context of meaning)፡- እንደ Bauman (1983፡363) ገለጻ የትርጉም አውድ አንድን የፎክሎር አህድ ለመረዳት ከሚያስችሉ ባህላዊ አውዶች ውስጥ ዋናው ነው፡፡ ይህ አውድ አንድን ቡድን ወይም ባህል ለማወቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የሚሰጥ ሲሆን የባህሉን መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳብ፣ ትርጉምና የባህሉን ባለቤቶች የበለጠ ለመረዳት ያስችላል፡፡ በዚህ አውድ የአንድ ቡድን የአኗኗር ዘይቤና ፎክሎራዊነት የእምነት ስርዓቶችና

እሴቶች ያላቸው የዕርስ በርስ ተመጋጋቢነት፣ መንስኤና ውጤት፣ ክዋኔዎች፣ የትዕምርቶችና የዘይቤያዊነት ግንኙነቶች መልስ ያገኛሉ።

ይህ አውድ አንድ የፎክሎር አይነት ከይዘት፣ ከትርጉም እና ከምንነት አንጻር ያለው አንድምታ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል። የአንድን ፎክሎራዊ አሀድ ባህላዊ ትርጉም ለማወቅ በራሱ በባህሉ ውስጥ ባሉ የአተረጓጎም እይታዎች ላይ መመርኮዝ ያስፈልጋል። የባህሉ ባለቤቶች በፎክሎራቸው ውስጥ የሕይወት መስመራቸው በምን መልኩ እንደተወከለና እንዴት እንደተላለፈ ይመረምራል።

**ተቋማዊ አውድ** (Instititutional context)፡- እንደ Bauman (1983፡364) ማብራሪያ ተቋማዊ አውድ አንድ የፎክሎር አይነት በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ያለውን ትርጉምና ሚና ይመለከታል። የፎክሎር ፅንሰ ሀሳብ ከቡድን ከፍ ሲልም ከተቋም ጋር ይገናኛል። በመሆኑም በቡድኑ ጠቅለል ባለ አገላለጽ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ፎክሎራዊ አሀድ የሚተገበርበትና ጥቅም ላይ የሚውልበት የራሱ ተቋምና ተቋማዊ አደረጃጀት ይኖረዋል። ተቋማቱ ለተለያዩ አላማዎችና ግቦች የሚመሰረቱ ሲሆን ፖለቲካን፣ ሃይማኖትን፣ ኢኮኖሚን፣ ቡድንን፣ ጎረቤትን መሰረት ሊያደርጉ ይችላሉ። እነዚህን በመሰሉ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ አሀዶች በምንና እንዴት ይገናኛሉ? በየትኛው ባህል ውስጥ ይገኛሉ? እንዴትስ ያገለግላሉ? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ፎክሎራዊ አሀዶቹ በሚገኙበት ተቋምና በተቋሙ ውስጥ በሚኖራቸው ጠቀሜታ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል።

**ተግባቦታዊ አውድ** (Context of communicative system)፡- Bauman (1983፡364) እንደሚያብራራው ተግባቦታዊ አውድ አንድ የፎክሎር አይነት ከሌላው የፎክሎር አይነት ጋር ያለውን ዝምድና ይመለከታል። አብዛኞቹ የፎክሎር አይነቶች ግንኙነት ይኖራቸዋል። ግንኙነቱ በአንዳንዶቹ የፎክሎር አይነቶች ጥብቅ ሲሆን በአንዳንዶቹ ደግሞ ለላ ያለ ነው። ለምሳሌ ስነ ቃል፣ ቁሳዊ ባህልና ትውን ጥበባት ዕርስ በርስ የሚኖራቸውን ግንኙነት መመርመር ላይ ትኩረት የሚያደርግ አውድ ነው። አብዛኞዎቹ የፎክሎር አይነቶች ግንኙነት አንዱ በአንዱ ላይ ያለውን ጥገኝነት ከማሳየቱም በላይ የአንዱ ህልውና በአንዱ መኖር እንደሚመሰረት በግልፅ የሚያሳይ ነው። ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሀገረሰባዊ ልማድ፣ በቁሳዊ ባህልና በስነ-ቃል አማካኝነት ህልውናው ሲጠበቅ ስነ ቃል በቁሳዊ ባህል፣

ሀገረሰባዊ ልማድና በሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ህልውናው ተጠብቆ ይኖራል፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድ በበኩሉ በሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ በቁሳዊ ባህልና በስነ-ቃል እየተገለፀ ኖሯል፤ ወደ ፊትም ይኖራል፡፡ ይህ ማለት አንዱ የፎክሎር አይነት በአንዱ እየተገለፀ ይኖራል፤ ግንኙነቱም አያቆምም፡፡ ለዚህም ነው ተግባቦታዊ አውድ ይህን የማይቆም የፎክሎር አይነቶች ግንኙነት ለመመርመር አስፈላጊ የሚሆነው፡፡

### 3.4.2. ማህበራዊ አውድ

ማህበራዊ አውድ ደግሞ ከአንድ ቡድን አልፎ ብዙዎችን ሊያሳትፍ የሚችል አውድ ነው፡፡ ይህን አውድ ለመረዳት የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ኢኮኖሚያዊ መሰረት፣ ፖለቲካዊ መዋቅሮችና ማህበራዊ ባህሪያትን ማጤን ይገባል፡፡ ማህበራዊ አውድ በስሩ ሶስት ንዑሳን አውዶችን ይይዛል፡፡ እነርሱም፡-

**ማህበራዊ መሰረት** (Social base)፡- እንደ Bauman (364-365) ማብራሪያ የማህበራዊ መሰረት አውድ ከፎክሎሩ ባለቤቶች ማንነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን አውድ ይመለከታል፡፡ ፎክሎራዊ አሀዱን በዚህ አውድ ውስጥ አስገብቶ ለማጥናት ማህበረሰቡን ወይም ቡድኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የፎክሎር ተመራማሪዎች ስለ ቡድን የተለያዩ አመለካከቶች ያሏቸው ቢሆንም አብዛኞቹ ቡድን አንድን ነገር የጋራ አድርገው የሚጠቀሙ ማንኛውንም አይነት የሰዎች ስብስብ ይመለከታል፡፡ እንደ Bauman ገለፃ አሁን ላይ የፎክሎር ትምህርት እየተስፋፋ በመምጣቱ አንድን ቡድን በጎሳ፣ በዘር፣ በስራ እና በእድሜ ለይቶ ከመከፋፈል በላይ በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃም ፎክ ይኖራል፡፡ በዚህም የተነሳ የአንድን ፎክሎራዊ አሀድ  በማህበራዊ አውድ መነሻነት ለመረዳት የፎክሎሩን ባለቤቶች ማንነት ማወቅ ግድ ይሆናል፡፡

**ግለሰባዊ አውድ** (Individual context)፡-  Bauman (1983፡365) እንደሚያብራራው ፎክሎር በቡድን እንደሚገለጸው ሁሉ በግለሰብ ደረጃም ይገለጻል፡፡ እንድ የፎክሎር አይነት ወይም ፎክሎራዊ አሀድ  በግለሰብ የሕይወት ፍልስፍና ውስጥ የሚይዘው ቦታ፣ ለግለሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ፣ ግለሰቡ ለፎክሎራዊ አሀዱ የሚሰጠው ትርጉም እና ከሌሎች ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የህይወት ፍልስፍናና አመለካከት ጋር የተዋቀረበት ሁኔታ በዚህ አውድ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይመረመራል፤ ይተረጎማል፤ ድምዳሜም ይሰጣል፡፡

ሁኔታዊ አውድ (Situational context)፡- እንደ Bauman (1983፡365-366) አገላለፅ ሁኔታዊ አውድ የአንድን ፎክሎራዊ አሀድ በተገኘበት፣ በተፈጠረበትና በተከወነበት ሁነት ውስጥ የነበረውን ትርጉም ለማወቅ የሚያግዝና በአሁኑ ጊዜ የፎክሎር ተመራማሪዎች በስፋት የሚጠቀሙበት አውድ ነው፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ የሚጠናው የፎክሎር አሀድ አከዋወኑና አወቃቀሩ ወቅታዊ ወይም ሁኔታዊ ነው፡፡ ይህ አውድ የፎክሎሩን ግላዊያዊ መቼት(physical setting)፣ የተሳታፊዎችን ማንነትና ሚና፣ ባህላዊ የክዋኔ ህጎችን፣ የተግባቦትንና የአተረጓጎም ደንቦችን፣ የተግባራትን ቅደም ተከተልና የሁኔታውን ፍሰት ለመረዳት ያስችላል፡፡ ሁኔታዊ አውድ የቅርብ ጊዜ ሲሆን የፎክሎር ተመራማሪዎችንም ትኩረት እየሳበ ነው፡፡

እንደ Bauman (1983፡365-366) አገላለፅ በአንድ የፎክሎር አይነት ውስጥ የተደራጀ፣ ፍሰታዊ እና የተለመደ አከዋወን ወይም አውድ ሊኖር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ድንገቴ የሆነ ለውጥን የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ድንገቴ ሁኔታዎች የሚከሰቱትም ለክዋኔ ከሚመረጠው የፎክሎር አሀድ (fokloric item)፣ ለመከወን ከምንጠቀመው ስልት፣ ከተፈጠረው አጋጣሚያዊ ጉዳይ እና ከሁኔታው ጊዜያዊ መዋቅር አንጻር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ጥቅል ባህላዊ ትርጉም በተጨማሪ ሌላ የአተረጓጎም አቅጣጫን አጥኚው እንዲመራመር ያስችለዋል፡፡ አጥኚው ሁኔታዊ አውድን ለማግኘት ራሱንም ሆነ ቡድኑን መጠየቅ ያለበት እየተከናወነ ያለው የፎክሎር ቅንጣት አሁን ባለው ሁኔታ ውስጥ ምን ማለት ነው? በዚህ በአስቸኳይ ዓላማ ውስጥ ምን ይፈይዳል? ለማህበረሰቡ/ለቡድኑ ተግባቦት እንዴት ያገለግላል? የሚሉትን ጉዳዮች ነው ፡፡

## 3.5. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ቀደም ሲል በነበረው የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ እንዲሁም በአሁኑ የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከሀያ የማያንሱ ጥናታዊ ጽሁፎች ያገኘሁ ሲሆን ሁሉም ጥናቶች በአጭር በአጭሩ ተቃኝተዋል፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ሁሉም ተካተው አልቀረቡም፡፡ በዋናነት ጥናቶቹ ብዙ መሆናቸው በዚህ ክፍል እንዳላካትታቸው ያስገደደኝ ቢሆንም ከተሰሩበት አካባቢ ወይም ብሄረሰብ ውጭ አብዛኛዎቹ ተመሳሳይ ዘዴና አካሄድ ያላቸው በመሆኑ ከፊሎቹን በምሳሌነት ማሳየቱ በቂ ይሆናል በሚል ነው፡፡ በመሆኑም ለኔ

የጥናት አካባቢ ቀረብ ይላሉ ያልኳቸውንና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር በሚገኙ ብሄረሰቦች ላይ የተሰሩ አምስት ጥናታዊ ፅሁፎችን ብቻ ተመርጠው ተቃኝተዋል፡፡

ቅኝቱ ባህላዊ የግጭት አፈታት ላይ የተሰሩ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች ብቻ የተካሄደ ሲሆን በጥናቶቹ መረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት፣ በጥናቶቹ አቀራረብ፣ ግኝቶች፣ ጥንካሬዎችና ድክመቶች እንዲሁም ከኔ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነቶች በአጭሩ ቀርቧል፡፡

በዚህ ቅኝት የመጀመሪያው የወንድወሰን አውላቸው በ1998 ዓ.ም "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ የግጭት አፈታትና የአስተዳደር ስርዓት" በሚል ርዕስ ያቀርበው ጥናት ሌላው ነው፡፡ የሰባት ቤት ጉራጌዎችን ባህላዊ አስተዳደርና ግጭት አፈታት ማሳየት የጥናቱ አላማ ነው፡፡

አጥኚው በጥናቱ እንዳመለከተው በሰባት ቤት ጉራጌ በተደጋጋሚነት የሚከሰቱ የግጭት አይነቶች የጎሳ ግጭት፣ የቤተሰብ ግጭትና የግለሰቦች ግጭት ቀዳሚውን ስፍራ የሚይይዙ ሲሆን ግጭቶቹ በባህላዊ መንገድ መፍትሔ ይሰጣቸዋል፡፡

በሰባት ቤት ጉራጌ ለግጭት መነሻነት ከሚታወቁት ጉዳዮች ውስጥ መንፈስ አንዱ ሲሆን የሰዎች የተለያየ ፍላጎትም ሌላኛው እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በሰባት ቤት ጉራጌ አንድ ሰው ግጭት ውስጥ የሚገባው ለግጭት የሚያበቃ ርኩስ መንፈስ ሲሰፍርበት ነው ተብሎ እንደሚታመንም አጥኚው በጥናቱ ላይ አሳይቷል፡፡

በሰባት ቤት ጉራጌዎች ግጭቶች መፍትሄ የሚሰጥባቸው ሁለት ባህላዊ ተቋማት አሉ፡፡ አንደኛው ዝምድናን መሰረት ያደረገ ተቋም ሲሆን በውስጡም አበራስ (ቤተሰብ) እና ጥብ (ጎሳ) የሚባሉ ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡ ሁለተኛው መኖሪያ አካባቢን መሰረት ያደረገ ተቋም ሲሆን ቃያ፣ ጀፎረ፣ አሚያና እና ገን የሚባሉ ንዑሳን ክፍሎችን የያዘ የግጭት መፍቻ ተቋም ነው፡፡ ሰባት ቤት ጉራጌዎች እነዚህ ተቋማት በመጠቀም ግጭቶቻችውን እንደሚፈቱ ጥናቱ ያሳያል፡፡

በጥናቱ ላይ እንደሚታየው መግቢያ ማጠቃለያና አጠቃሎ የሚባሉት ክፍሎች ተለይተው አይታወቁም፡፡ ጥናቱ አጠቃሎ የሌለው ከሆኑም በላይ የአጠቃሎ ባህርያት ያላቸው ገለፃዎች በመግቢያው ላይ ሰፍረዋል፡፡ አጥኚው የጥናቱን ግኝቶች በመግቢያው ላይ በተደጋጋሚ

ገልጿቸዋል፡፡ ይህ የአጥኚው አካሄድ መግቢያውን ውስብስብ ከማድረጉም በላይ አንባቢ ተገቢውን መረጃ በቀላሉና በተገቢው የጥናት ክፍል እንዳያገኝ አድርጎታል፡፡

በሌላ በኩል በጥናቱ ላይ የሚታየው ቀርነት የአላማ ተፈፃሚነት ከጥያቄ የማያመልጥ መሆኑ ነው፡፡ አጥኚው "የሰባት ቤት ጉራጌን ባህላዊ የአስተዳደርና የግጭት አፈታት ገላጭ ዶክመንተሪ ፊልም መስራት" የሚል ዝርዝር አላማ አስቀምጧል፡፡ የአንድ ጥናት አላማ የሚለካ መሆን አለበት፣ የሚታይና ተጨባጭነት ሊኖረው ይገባል፡፡ በጥናቱ ተቋቁሞ ጊዜ ይዞት የተነሳው አላማ ከግብ ደርሷል ወይ ተብሎ መለካት አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አይነቱ አላማ የተፈፃሚነቱ ጉዳይ ከጥያቄ የማያመልጥና ለክትትልም የማያመች በመሆኑ የአላማ ቀርነት አለበት ለማለት ደፍሬያለሁ፡፡

ሁለተኛው ይልማ ተፈሪ በ 1998 ዓ.ም "የሽምግልናና እርቅ ሥርዓት በወላይታ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማም የወላይታ ባህላዊ የሽምግልና ስርዓት ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡

ብሄረሰቡ በእርሻና ግጦሽ መሬት፣ በከብት ዝርፊያ፣ በውርስና በጋብቻ መነሻነት ግጭቶች እንደሚፈጠሩ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በነዚህ ምክንያቶች ግድያ፣ ድብደባ፣ ስርቆት፣ እንዲሁም የቡድን ጠቦች በብሄረሰቡ ብዙ ጊዜ ይፈጠራሉ፡፡

አጥኚው የወላይታ ብሔረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ጭሜሳ፣ ጨቆ፣ ጨጫ፣ ጫታ የሚባሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን እንደሚጠቀም በጥናቱ አሳይቷል፡፡

በነፍስ ግድያ የግጭት አፈታት መሰረት ሰው የገደለ ለሽማግሌዎች በሚስጥር በመናገር ለሟች የእርቅ ጥያቄ እንደሚያቀርብ በጥናቱ አሳይቷል፡፡ ከዚያም የሟች ቤተሰብ ለእርቁ ፈቃደኛ ሲሆኑ ገዳይ ፊቱን ጥላሸት በመቀባትና በደረቀ የኮባ ቅጠል ሰውነቱን ሸፍኖ ወልደው የጨረሱ ላምና በግ ጎትቶና አንገቱን በማቀርቀር ምህረት እንደሚጠይቅ በጥናቱ ገልጿል፡፡

በሁለቱ የደም ሰዎች መካከል እርቁ ከወረደ በኋላ ገዳይ ያመጣቸውን ላምና በግ በመባረክ በሽማግሎዎች አማካኝነት ደማቸው ገዳይንና የሟችን የቅርብ ቤተሰብ በመቀጠልም የሁለቱም ወገኖች መሀል ግንባር በመቀባት እርቁ እንደሚቋጭ በጥናቱ አሳይቷል፡፡

በጥናቱ ላይ በዋናነት የሚታየው ድክመት በእርቅ ሥርዓቱ ላይ ያለውን ሂደት ከመግለጽ ባለፈ በእያንዳንዱ የእርቅ ሂደት ላይ ስለሚፈፀሙት ስርዓቶችና ተግባራት አንዳች ባህላዊ ፋይዳና ተምሳሌቶችን አለማብራራቱ ነው፡፡

ሶስተኛው ደግሞ "ህገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርአት በደኮ ጋሞ" በሚል ርእስ በ1998 ዓ.ም በተመስገን ምንዋጋው የቀረበው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ነው፡፡ ጥናቱ በደኮ ጋሞ ያለውን አገር በቀል እውቀት ማስተዋወቅና ቅርፃ ማቆየትን አላማ አድርጎ ተነስቷል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን አቀራረቡም ገላጫዊ ነው፡፡

አጥኚው ሱትሳ፣ ጨሚሶ፣ ቦንቃና ፆታዊ ግንኙነት የፈፀሙ ዘመዳሞች ግጭት እና ቃዞ መርሼ የሚባሉ የግጭት አይነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ እንደሚከሰቱ በጥናቱ አሳይቷል፡፡ እነዚህ ግጭቶች ባህላዊ በሆነ መልኩ መፍትሔ የሚሰጥባቸው ስምንት ባህላዊ ተቋማት እንዳሉም አጥኚው በጥናቱ አሳይቷል፡፡

በደኮ ጋሞ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ የየራሳቸው የስራ ሀላፊነት ያላቸው መሆኑንና አንዱ ተቋም በሌላው ላይ ጣልቃ እንደማይገባ አጥኚው ይገልፃል፡፡ ማህበረሰቡ ኮረፌኔ፣ ቦላናዶና፣ የነፍስ ግድያ ግጭትን ይፈታል፡፡ ጊቃኤቃ- የድንበር ግጭትን ይፈታል፣ ካሬ- እርስ በርስና ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር ጦርነት ሲነሳ ያበርዳል፣ማካ- ዘመዳሞች የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈፅሙ የማንፃት ስራ ያከናውናል፣ ማሮ- በመተት እና በወሳጅ ግጭት ውስጥ የሚገቡ ሰዎችን የሚያስማማ ሲሆን አንጀት አንባቢዎችን፣ ጠንቋዮችንና ጠጠር ጣዮችን የሚያጠቃልል ተቋም ነው፡፡ ዎጋ ኤራስ ደግሞ በሌሎች ተቋማት የተሰጡ ውሳኔዎችን በይግባኝ የሚያይ ተቋም በማለት የተቋማቱን ተግባር አጥኚው በሰፊው አሳይቷል፡፡

አጥኚው የማህበረሰቡ የግጭት እሳቤና የመፍትሔ መስጫ አቅጣጫ በተረኩና በምሳሌያዊ ንግግሩ ውስጥ እንደሚገኝ አስረጅ ምሳሌዎችን በማቅረብ አሳይቷል፡፡ ይህ አካሄዱ ዋነኛው የጥናቱ ጥንካሬ ሲሆን በአስረጅነት ያቀረባቸው አስረጀዎች በአንባቢ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የግልፅነትና የአመክንዮ ጥያቄዎች መልስ የሚሠጡ ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ተጨባጭ የሆኑ ጥካሬዎች ቢኖሩትም ሊተነተኑና ሊተረጎሙ የሚችሉ በርካታ ተምሳሌቶችን እንደ ቀላልና ተራ ጉዳይ ሲያልፋቸው ይስተዋላል፡፡

በአራተኛነት የተቃኘው አብረሃም ታደሰ በ1999 ዓ.ም "ህገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ ያቀረበው የሁለተኛ ዲግሪ የመመረቂ ጽሁፍ ነው፡፡ ጥናቱ በሲዳማ ብሄረሰብ ውስጥ የሚከናወኑትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ስርዓቶችና ደንቦችን ማጥናት፣ የተለያዩ የግጭት አይነቶችን መጠቆምና እነዚህን ግጭቶች በባህላዊ መንገድ የሚፈቱባቸው ተቋማት ምን ምን እንደሆኑ መጠቆም፣ ባህላዊ ተቋማቱ ከዘመናዊ ህጎች ጋር ተቀናጅተው ተግባር ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ መጠቆም የሚሉ አላማዎችን የያዘ ነው፡፡

የሲዳማ ብሄረሰብ ዕርስ በርስና ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚጋጭ አጥኚው ጠቁሟል፡፡ ብሄረሰቡን ለግጭት ከሚያበቁ ምክንያቶች ውስጥ የግጦሽ እና የእርሻ መሬት ይገባኛል ውርስና የውሃ እጥረት፣ የማህበረሰቡን ሰላም በሚያውኩ ነገሮች፣ ጠለፋ፣ ስርቆት፣ የመቃብር ቦታዎችን መዳፈር እንደሆኑ ይገልፃል፡፡

ማህበረሰቡ ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር የሚጋጨው በየስምንት አመቱ በሚከበረው የጉልበት መፈተሻ ክብረበዓል ምክንያት ነው፡፡ ክብረበዓሉ የበላይነትና የጀግንነት ማሳያ በመሆኑ በአጎራባች ብሄረሰቦች ላይ የከብት ዝርፊያ ይከናወናል፡፡ ይህ ደግሞ ለከፍተኛ ጥፋት የሚያደርስ ግጭት እየፈጠረ መሆኑን አጥኚው በጥናቱ ገልጿል፡፡

የሲዳማ ብሄረሰብ እርስ በርስና ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር የሚከሰቱ ግጭቶችን በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ይፈታል፡፡ ከነዚህ ባህላዊ ተቋማት ውስጥ የመንደር ሽንጎ፣ የቤተሰብ ጉባኤ እና የቤተ-ዘመድ ጉባኤ ተጠቃሾች መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡

አጥኚው በመደበኛው የፍትህ ስርአትና በባህላዊው የፍትህ ተቋም መካከል ያለውን የእርስ በርስ ግንኙነት ለማሳየት ያደረገው ጥረት በጠንካራ ጎን የሚነሳለት ነጥብ ነው፡፡ በሌላ በኩል በጥናቱ ትንታኔ የሚያነሳቸውን ሀሳቦች ለማስረገጥና ለማብብራራት የተጠቀማቸው አብነቶች ጥናቱን የተሟላ ከማድረጋቸውም በላይ ለአንባቢ ተጨማሪ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡

በሌላ በኩል ጥናቱ የእርቁን ስርዓት መግለፅ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል። ይህ ደግሞ በእርቅ ስርአቱ ላይ የሚከናወኑ ስርዓቶች በብሄረሰቡ ዘንድ የሚሰጣቸውን ባህላዊ ፍቺና ያላቸውን ሚና አጉልቶ አለማሳየቱ እንደ ድክመት የሚታይ ነው።

አምስተኛውና የመጨረሻው ስለሺ አባተ "የሽክቾ ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት" በሚል ርዕስ በ2002 ዓ.ም የተሰራው ጥናት ነው። የጥናቱ አላማ የግጭት መፍቻዎችና ያላቸውን ፋይዳ፣ግጭት በመከላከል፣ በማብረድና በመፍታት ረገድ የስኑ-ቃሎችን ፋይዳ ማመልከት ነው።

በብሄረሰቡ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ግጭቶች ከማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ችግሮች ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ጥናቱ ያመለክታል። እነዚህን ግጭቶች በዘላቂነት ለመፍታትና ወደግጭት የገቡ ግለሰቦችን ወይም በድኖችን ለማስታረቅ ሾቾ እና ሽቦ የተባሉ ተቋማት እንዳሉ ጥናቱ ያሳያል።

በማህበረሰቡ ውስጥ ተጨባጭ መረጃ ያልተገኘላቸውን ችግሮች ለመፍታትና ውሳኔ ለመስጠት ኮዎ፣ ፌቾ፣ ማሪዮማጮ፣ በገደብ ማስታረቅ ወዘተ የሚባሉ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉም ጥናቱ ያሳያል። ይህ ጥናት ከዚህ በፊት ከቀረቡት ጥናቶች ለየት የሚያደርገው በግጭት አፈታቱ ጊዜ የሚከወኑ ድርጊቶችን ትዕምርታዊ ፍቺ በንዑስ ርዕስ ስር መተንተኑ ነው። ይህ ደግሞ ዋናው የጥናቱ ጥንካሬ ነው።

በአጠቃላይ ከለይ የተቃኙት ጥናቶች በየጥናት አካባቢው ያሉትን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አሰራር፣ አወቃቀር፣ ለማህበረሰቡም የሚሰጡት ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማብራራት፣ በተቋማቱ ላይ የሚተገበሩ የግጭት አፈታት ሂደቶችን በመግለፅ፣ ግጭቶቹ በሚፈቱበት ጊዜ የሚጠቀሟቸውን ስልቶች እንዲሁም የግጭት አይነቶችንና መነሻ ምክንያቶችን በማሳየት ከኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ አካሄድ አላቸው።

ይሁን እንጅ ጥናቶቹ ከኔ ጥናት ጋር የሚለያዩባቸው ጉዳዮች አሉ። በመጀመሪያ ጥናቱ በተከናወነበት ብሄረሰብ ጥናቶቹ ይለያያሉ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በጥናቶቹ ላይ የሚታዩና ተጨማሪ ማብራሪያና ፍቺ የሚፈልጉ ትዕምርቶችን በእያንዳንዱ የግጭት አፈታት ሂደት ላይ ትኩረት መስጠቱ የኔን ጥናት የተለየ ያደርገዋል። ጥናቱ የሚከተለው የመተንተኛ ዘዴም እስካሁን ከቀረቡት ጥናቶች ሁሉ የተለየ ነው።

# ምዕራፍ አራት

## ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማረቆ ብሄረሰብ

በዚህ ምዕራፍ የማረቆ ብሄረሰብ ስለግጭት ያለውን አመለካከትና ግንዛቤ፣ ብሄረሰቡ ስለሚጠቀማቸው የግጭት መፍቻ ተቋማት፣ የግጭት አይነቶችና መነሻ ምክንያታቸው፣ የብሄረሰቡ የግጭት አፈታት ሂደት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ይብራራሉ። ሴቶች በብሄረሰቡ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ላይ ያላቸውን ሚና እንዲሁም በራጋ ማጋ ላይ ጎልተው የሚታዩ ሀገረሰባዊ እምነቶችና መርሆች በትኩረት የተዳሰሱ ጉዳዮች ናቸው።

### 4.1.የግጭት ፅንሰ ሀሳብ በማረቆ ብሄረሰብ

የተለያዩ ትምህርት መስኮች በጋራ ጉዳይነት የሚያተኩሩባቸው ፅንሰ ሀሳቦች በበዙበት ጊዜ የየመስኩ ምሁራን የግጭትን ምንነት እንዲሁም ከግጭት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ከየራሳቸው የጥናት መስክና ይዘውት ከተነሱት አላማና ግብ አንጻር የተለያዩ ድምዳሜዎችን እንዳስቀመጡ በምዕራፍ ሶስት ላይ በሰፊው ለማየት ተችሏል።

ግጭት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሳይንሳዊ እውቀትን ብቻ ማጣቀስ በቂ አይደለም። ግጭት አይነቱና መነሻ ምክንያቱ ውስብስብ በመሆኑ ለመበየን የቡድኖችን ወይም የብሄረሰብን ባህል ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል። ሳይንሳዊ እውቀትን[27] ብቻ መሰረት አድርጎ ግጭትን መበየንም ሆነ መተንተን በድምዳሜያችን ላይ የምልዑነት ጥያቄ ያስነሳል። በመሆኑም ግጭት በማረቆ ብሄረሰብ ዘንድ እንዴት ይገለጻል? ለብሄረሰቡ ግጭት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር መልስ ያገኛል።

የብሄረሰቡ ማጋዎች እንደሚገልጹት ግጭት የብሄረሰቡ የጥቃት መመከቻናና የጥቅም ማስከበሪያ መንገድ ነው። በብሄረሰቡ ውስጥ በደል የደረሰበት አካል በደሉን ለማስቆም ሲል ወደ ግጭት ይገባል። ይህ ሁኔታ ብሄረሰቡ ግጭትን እንደ አንድ የበደል ማካካሻ እንዲቆጠር አድርጎታል። ይህን የግጭትን እሳቤ ሀጂ ጃተኖ(ስክርብ፣54) "ማረቆ የሰው ሀቅ አይፈልግም፤ የሰው ሀቅ። መጀመሪያም በራሱ ድንበር ሰው መጥቶ ሲሰፍር ነው ጥል

---

*[27]እንደ አሉላና ገብሬ(2004፣79) ገለፃ "ሀገረሰባዊ እና ሳይንሳዊ እውቀት የየራሳቸው መገለጫዎች ያላቸው እውቀቶች ቢሆኑም በመካከላቸው ልዩነቶች አሏቸው። ሳይንሳዊ እውቀት በመደበኛ ቋንቋ፣ በሂሳብ ቀመርና በጽሁፍ የሚገለፅ አለማዊ እውቀት ሲሆን ሀገራዊ እውቀት ግን በፅሁፍና በቀመር የማየተነተንና በአብዛኛው አለማዊና መንፈሳዊ አስተሳሰቦችን አታምሮ የያዘ እውቀት መሆኑ ነው" በማለት ሁለቱ የእውቀት አይነቶች መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዳሉ።*

የሚነሳው። የኔን አትንካ በሚል ነው ጥል የሚመጣው፤ የሚጋደለውም በራሱ እውነት ነው" በማለት የግጭት እሳቤ ከአትንኩብኝ ባይነት ጋር አገናኝተዉ ይገልጹታል።

ማረቆዎች ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ግጭቶች ይከሰታሉ። በተለይ አሁን ላይ የሰፈሩበትን ቦታ ያለማነው እኛ ነን በማለት የሌሎች ብሄረሰብ አባላት ድንበር ተሻግረው እንዲሰፍሩም ሆነ ከብቶቻቸውን እንዲያሰማሩ አይፈቅዱም። ይህን ሀሳብ ሀጂ ጃተኖ (ስክርብ፣54) "ይህን ሁሉ አገር ማረቆ ነው ያሳደረው" በማለት ብሄረሰቡ አሁን የሰፈረበትን ቦታ ቀደም ሲል በአካባቢው ይኖር የነበረውን የኦሮሞ ማህበረሰብ በጦርነት አስለቅቆ እንደያዘው ይገልፃሉ።

እንደ ሀጂ ጃተኖ ገለጻ የማረቆ ብሄረሰብ ዳንግ[28] በተለይ ድንበርና ውሀ ተጋፍቶ አይነካም። ይህን የብሄረሰቡን ባህላዊ እሴት ጥሶ የሰውን ሀቅ የተዳፈረ የብሄረሰቡ ተወላጅ በሚጋዎች ተገቢ የሆነ የማካካሻ ቅጣት ይጠብቀዋል። ለዚህም ሲል አንድ የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጅ የሌሎችን ብሄረሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ጎሳዎች ጥቅም በማክበር የራሱን ብቻ የመጠቀም ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ ይኖራል።

በአጠቃላይ ብሄረሰቡ የኔ የሚላቸውን መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብቶች ለማስከበር ከሌሎች ቡድኖች፣ ጎሳዎች ወይም ሰፋ ሲል ብሄረሰቦች ጋር ግጭት ውስጥ ይገባል። ይህ የብሄረሰቡ አካሄድ ግጭትን የጥቅም ማስከበሪያ እንዲሁም የጥቃት መመለሻና መመከቻ አድርገው እንዲመለከቱት አድርጓል።

## 4.2 የግጭት መፍቻ ተቋማት በማረቆ ብሄረሰብ

> *The chief value of the notion of of institution is as analaytical integrating concept, focusing at tention on how aspects of culture fit together, and how does a particular item or gener relate to other aspects of cultural life to make up larger interrelated configurations?Where does it fit into the culture, and how dose it function? (Bauman,1983:364).*

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ባህላዊ እሳቤዎች በተለያዩ ተቋማት ውስጥም ሊገኙ ይችላሉ። በማረቆ ብሄረሰብ የራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ጎልተው የሚታዩት ሀገረሰባዊ እምነቶች፣ልማዶችና ስርዓቶች ራሳቸውን ችለው ሊጠኑ የሚችሉ የፎክሎር

[28] ዳንግ ቃሉ ማርቅኛ ሲሆን የአማርኛ አቻ ፍቺው ድንበር ማለት ነው።

ዘርፎች ቢሆኑም በብሄረሰቡ ልዩ ልዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተቋማት ላይ ሲንፀባረቁ ይስተዋላል። እነዚህ ሀገረሰባዊ እምነቶች፣ልማዶችና ስርዓቶች በራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ የራሳቸው ሚና ሲኖራቸው ፍቺና ትርጓሜያቸውም በተቋሙ የአሰራር ደንብና መዋቅራዊ አደረጃጀት አውድ ውስጥ የሚታኝ ነው።

የሰው ልጆች በሚኖራቸው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተራክቦ በቡድን፣ በግለሰብ ወይም በብሄረሰብ ደረጃ ግጭቶች ሊያጋጥሟቸው ይችላል። ግጭቶቹን ለማርገብና በዘለቄታነት ለመፍታት ሲታሰብ ቅድሚያ ትኩረት ከሚሰጣቸው ቁም ነገሮች መካከል ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ወደ እርቅ የሚመልስ አንድ ተቋም ወይም አካል ማዘጋጀት ነው። በአብዛኛው በኢትዮጵያዊያን ባህል ይህን የማስማማትና እርቀ ሰላም የመፍጠር ሀላፊነትን የሚወጡት ሽማግሌዎች ናቸው። ሽምጋይነት በችሮታ የሚገኝ አይደለም፤ በርካታ መስፈርቶች ያሉት የአንድ ብሄረሰብ አባላትን ሙሉ አመኔታ በማረጋገጫነት የሚፈልግ ማህበረ ባህላዊ ይዘት የተላበሰ ሹመት ነው።

በየትኛውም ብሄረሰብ ባህል ውስጥ ሽማግሌዎች ለሽምግልና የሚመረጡባቸው ልዩ ልዩ መስፈርቶች ይኖራሉ። መስፈርቶቹ ከብሄረሰቡ ባህል ወግና ልማድ የሚቀዱ ማህበራዊ ደንቦችን በመንተራስ የሚቀረፁ ናቸው። በብዙዎቹ የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ባህል ለሽምግልና የሚታጩ ግለሰቦች (አንዳንዴም ቡድኖችና ጎሳዎች ሊሆኑ ይችላሉ) እድሜና መንፈሳዊነት ተጠቃሾች ናቸው።

የማረቆ ብሄረሰብም በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶችን የሚያበርድበትና ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥባቸው ሶስት ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አሉት። እነርሱም የቤተ ዘመድ ጉባኤ፣ ማጋና ራጋ ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ተቋማት ቀላል ከሚባሉ አለመግባባቶች ከፍተኛ እስከሆነው የግድያ ግጭት ደረስ መፍትሔ የሚሰጡባቸው የአሰራር ሂደቶች አሏቸው።

የመጀመሪያው ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም የቤተ-ዘመድ ጉባኤ ነው። የቤተ-ዘመድ ጉባኤ የአንድን ቤተሰብ አባላት ማለትም አባትንና እናትን፣ ልጅን፣ እክስትንና አጎትን፣የጎሳ አባላትንና ዋርሳዎችን፣ሚዜዎችንና የቅርብ ጓደኞችን የሚያጠቃልል ነው። በነዚህ የቤተሰብ አባላት መካከል የሚፈጠሩ ቀላል ግጭቶች በተቋሙ መፍትሔ ይፈለግላቸዋል።

የቤተ-ዘመድ ጉባኤ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ስር የሚገኝ በመሆኑ ከኩርፊያ ጀምሮ ያሉ የቤተሰብ አለመግባባቶችን ማርገቡ በብሄረሰቡ ማጋዎች ላይ ያለውን የስራ ጫና ከማቃለሉም በላይ የቤተሰብን አንድነት ያጠናክራል።

በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ ግጭትን የሚያረግበውና የመፍትሔ ሀሳብ የሚያቀርበው ሁለተኛው የፍትህ ተቋም ማጋ ነው። ማጋ በብሄረሰቡ ዘንድ የተለየ ማህበራዊ ደረጃ የሚሰጣቸውን ማጋዎች (ሽማግሌዎች) የሚይዝ ተቋም ነው። ይህ ተቋም በየጎሳውና በየቀበሌው በእድሜ ጠና ጠና ያሉ፣ በማስታረቅም ከአሁን በፊት ከበሬታን ያተረፉ ሽማግሌዎች በጥቅሉ የሚጠሩበት ቃልም ነው። ማጋዎች[29]በቁጥር ብዙ ሲሆኑ ከቤተዘመድ ጉባኤ አቅም በላይ የሆኑ አለመግባባቶችን የሚፈቱ የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው። በብሄረሰቡ ውስጥ የማጋዎች ቁጥር የተወሰነ አይደለም።

ማጋ እንደተቋም ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት እንደየፍላጎቶቻቸው ያስማሙናል ያሏቸውን ማጋዎች እየመረጡ ጉዳያቸውን የሚያስጨርሱበት ተቋም ነው። ማጋዎች ቋሚነት የሌላቸው ሲሆን ግጭት ውስጥ ለገቡት ወገኖች በገለልተኛነት ውሳኔ ይሰጣሉ። ለማስታረቅ የሚመረጡት ማጋዎች ከሁለቱም ባለጉዳዮች ጋር የስጋ ዝምድና እንዲኖራቸው አይፈለግም። ይህ የሚሆነው አንዳንድ ጊዜ ከውሳኔ በኋላ ሊመጣ ከሚችል ሀሜት ለመዳን ሲባል እንጅ ሁሉም የብሄረሰቡ አባላት ማጋዎች ላይ ሙሉ እምነት አላቸው።[30]

ማጋ በብሄረሰቡ ውስጥ በድብቅም ሆነ በይፋ የተፈጠሩ ግጭቶች በማጋዎች አማካኝነት መፍትሔ የሚፈለግበት ተቋም ነው። ይህ ሀገረሰባዊ ተቋም እንደ አንድ ተቋም የራሱ የግጭት አፈታት ሂደቶች፣ የወንጀል ምርመራና የወንጀል መከላከል ስልቶችን የያዘ ነው።

በማጋዎች የሚመራው ይህ ተቋም በዳይንና ተበዳይን መልሶ በማገናኘት በብሄረሰቡ ውስጥ ብቀላ እንዳይኖር የራሱን ጥረት ያደርጋል። ተቋሙ ጥረቱን የሚጀምረው አንድ ግጭት ከተፈጠረበት እለት እስከ መጨረሻው የእርቅ ስርዓት ድረስ ነው። ማጋ ግጭት ውስጥ የገቡ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ተቀራርበው እንዲወያዩ ሁኔታዎች የሚመቻችባቸው፣ ተበዳይ ለህክምናና ለክስ ያወጣው ወጭ እንዲመለስ የሚደረግበት ተቋም ሲሆን ወደ

---

*[29]በዚህ ጥናት ውስጥ ማጋዎች ስል በብሄረሰቡ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ከቤተ-ዘመድ ጉባኤ በመቀጠል የሚፈቱ ሽማግሌዎችን ሲሆን ማጋ ስል ደግሞ ማጋዎቹ የሚመሩትን ሀገረሰባዊ ተቋም ነው።*
*[30]ሀይሉ(ስክርብ፣17)።*

ሶስተኛው የብሄረሰቡ የግጭት መፍቻ ተቋም የማይደርሱ ግጭቶች መፍትሄ የሚያገኙበት ነው።

ሶስተኛው የማረቆ ብሄረሰብ ማህበረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ራጋ[31] ነው። ይህ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም በብሄረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ከባባድ ግጭቶች የመጨረሻ መፍትሔ የሚያገኙበት ነው። ከብሄረሰቡ ማጋዎች አቅም በላይ የሆኑ የአካል ማጉደልና የግድያ ግጭቶች እርቅ የሚጸድቅበትና በዳይ ላይ የሚጣለው የካሳ ክፍያ የሚወሰንበት ተቋም ነው። ይህን ሀሳብ የብሄረሰቡ ማጋ የሆኑት ሀይሉ (ስክርብ፣16) "በኛ ባህል ራጋ ማለት ይህንን የእርቅ አጨራረስ ሊወስን የሚችል…ነው" በማለት በማጋዎች የተጀመረው የእርቅ ሂደት የመጨረሻ ፍፃሜ በራጋው ውሳኔ እንደሚቋጭ ይገልፃሉ።[32]

በብሄረሰቡ ውስጥ የተከሰቱ ከባባድ ግጭቶች የእርቅ ሂደታቸው በማጋዎች ቢጀመርም የሚያልቀው በራጋ ብቻ ነው። ማጋዎች ከፍተኛ የሆነ ጥፋት ያስከተለን ግጭት ወይም ግድያ ወደ ባሰ እልቂት እንዳያመራ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ለእርቅ በማሳመንና የተለያዩ ወጭዎችን በማስመለስ ፍጻሜውን ራጋው እንዲነግር ያደርጋሉ። ራጋውም በማጋዎች ታይቶ የቀረበለትን ውሳኔ በማየትና በዳይን የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ የመጨረሻውን ውሳኔ ያስተላልፋል።

ራጋን የሚመራው አንድ ሰው ብቻ ነው። ይህንንም ሀይሉ (ስክርብ፣17) "የማጠቃለያውን የሚናገረው ብቸኛው ሽማግሌ ነው። ራጋ አንድ ሰው ነው" በማለት ይገልጻሉ። ራጋ የማጋዎችን ውሳኔ የማፈረስ ሙሉ ስልጣን አለው። ራጋው ባለጉዳዮችን አቅርቦ በማነጋገር በማጋዎች በኩል ያላለቀ ነገር አለ በማለት ማጋዎች እንደገና እንዲጨርሱት ያዛል። ይህን ሀሳብ ሀይሉ (ስክርብ፣18) "…በማጋዎች ያላለቀ ነገር አለ ብሎ ካመነበት ራጋው እንደገና ይመልሳቸዋል" በማለት የራጋውን ስልጣን ይገልጻሉ።

በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ ራጋ ሆኖ ለመመረጥ እውቀት ብቻ በቂ ነው። ይህም ሲባል የብሄረሰቡን ባህልና ወግ ጠንቅቆ የሚያውቅና ቀደም ባሉት ጊዜያት የእርቅ አጨራረስን

---

*[31] እንደ ሀይሉ(ስክርብ፣16) ገለጻ ራጋ የሚለው የማረቆኛ ቃል አረጋዊ የሚለውን የአማርኛ ቃል ይወክላል። በዚህ ጥናት ራጋ የሚለው ቃል ሁለት ጽንሰ ሀሳቦችን ጎን ለጎን ይዞ የሚሄድ ነው። አንደኛው ራጋ የተቋሙ መጠሪያ ስም ሲሆን ሌላኛው ራጋ የማህበረሰባዊው የግጭት መፍቻ ተቋም የበላይ መሪ የሆነው የሀገር ሽማግሌ መጠሪያ ስም ነው።*

*[32] ሀይሉ፤ስክርብ፣16-18፤ሀጂ ጃተኖ፣40፤ አቢጋዝ ጃቢቦ፣55)።*

ከሚመራ ራጋ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበረውና እውቀቱን የቀሰመ መሆን ይኖርበታል። [33]ይህን ሀሳብ አበጋዝ ጃቢቦ፡-

> *ራጋው እስኪሞት ድረስ በቦታው ይሰራል፣ አይሻርም። ሁሉም የማረቆ ጎሳዎች በራጋው ላይ ጥያቄ አያነሱም፤ ሁሉም ያምኑበታል። በድሮ ጊዜ ብዙ ራጋዎች አልፈዋል፤ አንድ ሲሞት ሌላው እየተተካ ነው ሲሰራ የኖረው። ለምሳሌ አባቴ አበጋዝ ባፋ ራጋ ሆኖ ሰርቷል፣ ሌላም አዝማች ነበር። በኋላ ደግሞ አዝማ ካሳሞ ሆኑ። አዝማ ካሳሞ ሲሞት ደግሞ በልጆቹ አልተገኘም (ስክርብ፣55)።*

በማለት የስልጣን ሽግግር ስርዓቱን ጠቅለል አድርገው ይገልፁታል።

የአባቱን እውቀት በአግባቡ ያልቀሰመ ልጅ የራጋውን ስልጣን ሊወርስ አይችልም። እንደ ሽማግሌዎቹ ገልፃ ብዙ ጊዜ ልጅ ለአባቱ ቅርብ ስለሆነና ጧት ማታ የአባቱን እውቀት ለመቅሰም እድሉ ስላለው የራጋውን ስልጣን የመውረስ አጋጣሚ ይፈጠርለታል። ይህ ካልሆነ ግን ለራጋው ቅርበት ነበራቸው የተባሉ ወይም የራጋውን እውቀት ቀስመዋል ለሚባሉ የሀገር ሽማግሌዎች ስልጣኑ ይሰጣል። ተቋሙ ላይ ያለው የስልጣን ሽግሽግ ወገንተኛነት የማይታይበት በመሆኑ በተቋሙ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሁሉም የብሄረሰቡ አባላት ተቀባይነት እንዲገኙ አድርጓል።[34]

የማረቆ ብሄረሰብ የሚያጋጥሙትን የተናጠልም ሆነ የቡድን ግጭቶች እንደ ቅለታቸውና ክብደታቸው በቤተ-ዘመድ ጉባኤ፣ በማጋና ራጋ ይፈታቸዋል። እነዚህ የብሄረሰቡ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የሚመሩባቸውን ሀገረሰባዊ እውቀቶችና እሴቶች አስጠብቀውና አክብረው ይዘዋል። እንደ ብሄረሰቡ ተወላጆች ገለጻ ተቋማቱ ለመንግስት ለህዝብና ለሀገር አይበጅም ብሎ የህግ ጥብቅና የቆመላቸውን የህጻናትንና የሴቶችን የእኩልነት መብቶች[35] ከመጠበቅ አንጻር ሲታይ በተቋማቱ ላይ መሻሻሎች ታይተዋል።

በሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ላይ የታዩት ለውጦች የመጡት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ከረቀቀበትና የተለያዩ ፖሊሲዎች ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ማጋዎች ይናገራሉ። በተለይ ከህጻናትና ሴቶች መብቶች ጋር በተያያዘ ብዙ ለውጦች ተደርገዋል። እንደጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈርና ግርዛት ያሉ ድርጊቶች በመደበኛው የፍትህ ተቋም እንዲታዩ ሆነዋል። እነዚህ ለውጦች በተቋማቱ ላይም የአሰራር ለውጦች እንዲመጡ አድርገዋል። ይህን ሀሳብ

---

[33] *ሀይሉ(ስክርብ፣17፤ ሀጂ ጃተኖ፣40፤ አበጋዝ ጃቢቦ፣55)።*
[34] *ሀይሉ (ስክርብ፣17-18፤አበጋዝ ጀቢቦ፣55)።*
[35] *ሀይለ (ስክርብ፣18፤ ሀጂ ጃተኖ፣49፤ መላኩ፣64፤ ታደስ፣68፤ ሳጀን ግርማ፣90)።*

ሀይሉ፡-

> *ምን መሰለህ በተለይ በመሰረታዊ ነገሮች ላይ ማለትም ከማጋ እስከ ራጋ ባለው የእርቅ ሂደት ውስጥ ባሉት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ጥንትም አሁንም አንድ ነው። ምንም የተለወጠ፣ የተበረዘ ነገር የለም። የአጨራረሱ ሁኔታ፣ የማጋዎች አካሄድ ከጥንት ጀምሮ የመጣ ነው አሁንም ይኸው ነው ያለው። ይሁን እንጅ የተሻሻሉ ነገሮች ይኖራሉ። ከጊዜው ፖሊሲ ጋር፣በ ከአሁኑ ህገ መንግስት ጋር በማይጋጭ መልኩ ነው። ከህግ ጋር በማይጣረስ መልኩ ነው ማጋዎች የሚጨርሱት ጉዳዩን (ስክርብ፣18)።*

በማለት ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ከመደበኛው የፍትህ ተቋም ጋር ያለውን ግንኙነት ያስረዳሉ።

ይህ ለውጥ ተቋማቱንና በተቋማቱ በሚገለገለው ብሄረሰብ ላይ ያሳረፈው ተጽዕና የለም። ለዚህም ነው የብሄረሰቡ አባላትና የተቋሙ መሪዎች ከመደበኛ የፍትህ ተቋም ጋር ተባብረው የሚሰሩት። በማረቆ ወረዳ መደበኛው የፍትህ ተቋማትም ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም የሚመራባቸውን ሀገረሰባዊ እሴቶችና ልማዶች እንዲሻሻሉም ሆነ እንዲበረዙ ተጽዕኖ አላሳረፉም። በመሆኑም ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ከእርቅ አጀማመር እስከ አጨራረስ ድረስ የሚመራባቸው ሀገረሰባዊ ህገ-ደንቦች አልተለወጡም። ተቋማቱም በአሁኑ ሰዓት ከመደበኛው የፍትህ ተቋም ጋር እየተቀናጁ የተጓደለ ፍትህን በማስመለስ ብሄረሰቡን ያገለግላሉ።

## 4.3 የግጭት አይነቶችና መንስኤዎቻቸው በማረቆ ብሄረሰብ

በማረቆ ብሄረሰብ የሚከሰቱ ግጭቶች በርከት ያሉ ቢሆንም በተደጋጋሚ የሚከሰቱት ግጭቶችና መነሻ ምክንያቶቻቸው በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ተብራርተው ቀርበዋል።

### 4.3.1 ቤተሰባዊ ግጭቶች

በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ የስጋ ዝምድና ያላቸው ቤተሰቦች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ግጭት ያመራሉ። በብሄረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩት ቤተሰባዊ ግጭቶች ብዙ ጊዜ ከጋብቻና ከውርስ ይገባኛል ጋር የተያያዙ ናቸው።

በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ የባልና ሚስት ግጭቶች በተደጋጋሚ የሚታዩ ሲሆን ግጭቶቹም በሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም መፍትሄ ይፈለግላቸዋል። እንደ ሀይሉ (ስክርብ፣10) ገለጻ የባልና ሚስት ግጭቶች ብዙ ጊዜ የሚከሰቱት ባል በሚስቱ ላይ በሚያደርሰው የተለያየ ጫና ነው። በተለይ በብሄረሰቡ ባልና ሚስትን ለግጭት የሚያበቃቸው ሌላኛው ጉዳይ የልጅ

እጦት[36] ነው። በማረቆ ብሄረሰብ ልጅ መውለድ ዘርን ማብዛት ብቻ ሳይሆን መታደልም መመረቅም ነው። ይህን እድል ማግኘትና ማየት ያልቻሉ ጥንዶች ጥል ውስጥ ይገባሉ።

እንደ አበጋዝ መርኪ (ስክርብ፣84) ገለጻ በማረቆ ብሄረሰብ ባልና ሚስትን ለግጭት ከሚዳርጉ ነገሮች ውስጥ ጣውንት[37] አንዱ ነው። በማረቆ ብሄረሰብ ወንዶች በየቦታው ለሚያስቀምጧቸው ጣውንቶች የራሳቸው መተዳደሪያ ሀብትና መሬት ሊኖራቸው ግድ ነው። ይህን ቅድመ ሁኔታ ለማሟላት ባል የመጀመሪያ ሚስቱን ሀብትና መሬት ከፍሎ ለሌላኛዋ ጣውንት የሚሰጥ ከሆነ ግጭቱ ይፈጠራል።

በቤተሰብ መካከል ለሚፈጠር ግጭት ሌላው ምክንያት የውርስ ይገባኛል ጥያቄ ነው። በዚህም የአባትን፣ የእናትን፣ የወንድምን ወይም የእህትን ሀብት ለመውረስ ሲባል ግጭት ይከሰታል። በብሄረሰቡ የውርስ ይገባኛል ጥያቄ ከሚቀርብባቸው ነገሮች ውስጥ ሀብትና የወንድም ሚስት በዋናነት ይጠቀሳሉ። በብዙ ብሄረሰቦች ባህል ወንድሙ ቢሞት ሚስቱን የሚወርሰው ታናሽ ወንድሙ ነው። እንደ ሀይሉ (ስክርብ፣19) ገለጻ በማረቆ ብሄረሰብ ይህ ባህል ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው። ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ኢትዮጵያን ማስተዳደር ከጀመረ በኋላ ግን ድርጅቱ የሴቶችን መብት ለማስከበር ባወጣቸው በርካታ አዋጆችና መመሪያዎች ሳቢያ ይህ አይነቱ ጥያቄ ቀርቷል። አሁን ላይ እንደ መብት ታይቶ እወርሳለሁ የሚል ሰው የለም።

### 4.3.2 ከጥሬ ሀብት ውሱንነት ጋር የተያያዙ ግጭቶች

የማረቆ ብሄረሰብ በግብርና ሙያ የሚተዳደር በመሆኑ ለግብርና በግብአትነት የሚጠቀምባቸው የውሀና የመሬት እጥረት አለበት። ብሄረሰቡ እነዚህን ውስን ጥሬ ሀብቶች ለማሟላት ሲል ከአቅራቢያ ብሄረሰብ፣ ጎሳ፣ ወይም ቀበሌ ነዋሪ ጋር በተናጠልና አልፎ አልፎም በቡድን ግጭት ውስጥ ይገባል።

በተለይ የብሄረሰቡ አባላት ባለባቸው የመሬት ጥበት ምክንያት በተለያየ ጊዜ በድንበር ገፋኸኝ ግጭት ውስጥ ሲገቡ ማየት የተለመደ ነው። ይህ አይነቱ ግጭት እስከ ግድያ

---

*[36]በዚህ አገባብ የልጅ እጦት ስል በተለያየ ምክንያት የባልን ወይም የሚስትን መውለድ አለመቻል ለማመልከት ነው። የማረቆ ብሄረሰብ ዘሩ እንዲበዛለት የሚፈልግ ህዝብ ነው። በዚህም ብሄረሰቡ ሁለትና ከዚያ በላይ ሚስቶችን የማግባት ልማድ አለበት። ይህን ሀሳብ አበጋዝ ሙርኪ(ስክርብ፣84) በስፊው አብራርተውታል። ከፍቼ ጋር በተያያዘ ሀይሉ(ስክርብ፣15) ልጅ ማግኘት ያልቻለች የማረቆ ብሄረሰብ ሴት በባልዋ ቤተሰቦችና ጎሳ መልካም እንዲገጥማት ተመርቃ ፍቺ ይከናወናል።*

*[37]እንደ አበጋዝ ሙርኪ አባባል ጣውንት ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴቶችን ማግባት ማለት ነው። የማረቆ ብሄረሰብ ወንዶች ጣውንት የሚያበዙበት ምክንያት ዘርን ለማብዛት በሚል ነው።*

ሊደርስ ይችላል፡፡ በተለይም የእርሻና የግጦሽ መሬት ጥበት የብሄረሰቡን አባላት እርስ በርስና ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር እንዲጋጩ እያደረገ ነው፡፡

ሌላው ከጥሬ ሀብት ዉሱንነት ለተያያዙ ግጭቶች ምክንያት የከብቶች የመጠጥ ውሃ ነው፡፡ ብሄረሰቡ ከብት በማርባት ኑሮውን የሚደግፍ በመሆኑ የከብቶችን ጤና ለመጠበቅ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቅማል፡፡ ከነዚህ ዘዴዎች ውስጥ ሆራ አንዱ ነው፡፡ ሆራ ከብቶች ክረምት ላይ እንዲጠጡት የሚደረግ ውሀ ነው፡፡ ይህ ውሀ ለከብቶች ሆድ ጥሩ ነው ተብሎ ስለሚታመንና እንደመድሀኒትም ስለሚቆጠር ማንኛውም የብሄረሰቡ አባል ከብቶቹን ከዚህ ውሃ ያጠጣል፡፡ በማረቆ ብሄረሰብ ሆራ ለማጠጣት ሲሉ በሚጋጥማቸው ወረፋ ተማረው ወደ ግጭት ይገባሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግጭቱ ከግለሰብ አልፎ የቀበሌ፣ የጎሳ ወይም የብሄረሰብ ግጭት የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡[38]

4.3.3 ወንጀል

በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ ወንጀሎች ለተለያዩ የግጭት አይነቶች መነሻዎች ናቸው፡፡ በብሄረሰቡ ውስጥ ቀላል ከሚባሉት እንደ ዛቻ፣ ስድብና ጉሽሚያ እስከ ከፍተኛው ግድያ ድረስ ወንጀል በሚል ጥቅል መጠሪያ የሚታቀፉ ናቸው፡፡ ስርቆትና ውንብድና በብሄረሰቡ በብዛት የሚከሰቱ ሲሆን የነዚህ ግጭቶች ውጤት ደግሞ እስከ ግድያ የደርሱ ከባባድ ግጭቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናሉ፡፡

በብሄረሰቡ ዘረፋ ሰላማዊ ህይወትን ከሚያደፈርሱ ወንጀሎች ውስጥ ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ እንደ ሳጅን ግርማ (ስክርብ፣88) ገለጻ በብሄረሰቡ ውስጥ ስር ሰዶ የቆየ ሲሆን አሁን አሁን በመንግስትና በብሄረሰቡ የጋራ ጥረት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ለፍተው ያፈሩትን ሀብት ጨለማን ተገን በማድረግና ጭምብል በማጥለቅ የሚፈፀም ወንጀል ነው፡፡ በዚህ ወንጀል ጥቃት የደረሰበት አካል ወንጀሉን ለመከላከል ወንጀለኛው ደግሞ ለማምለጥ ሲል በሚያደርጉት የእርስ በርስ ግጭት ከአካል ጉዳት እስከ ግድያ የሚደርስ ጥፋት ይከሰታል፡፡

በብሄረሰቡ ስርቆት በተደጋጋሚ የሚከሰትና ለግጭት የሚዳርግ ወንጀል ነው፡፡ ከነዚህም የስርቆት ወንጀሎች ውስጥ በርበሬን ከማሳ ላይ ሰርቆ መውሰድ አንዱ ነው፡፡ አንድ

[38] *ሀይሉ(ስክርብ፣19 እና 22)፡፡*

የብሄረሰቡ አባል በርበሬው ሲሰረቅ ካጋጠመው እንዳያመልጠኝ በሚል ከሌባው ጋር ግጭት ውስጥ የሚገባበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡[39]

ከዚህ በተጨማሪ በብሄረሰቡ የከብት ስርቆት አንዱ የግጭት መነሻ ነው፡፡ ከብቶችን ስርቆ ከማረቆ ውጭ ባሉ ብሄረሰቦች ደብቆ ማስቀመጥ ተለምዷል፡፡ የማረቆ ብሄረሰብ አጎራባች በሆኑት ኦሮሚያ፣ስልጤ ወይም ሀድያ ውስጥ ከብቶችን ሰርቆ በመደበቅ ወንጀሉን ለማራቅ ሙከራ ይደረጋል፡፡ በብሄረሰቡ ውስጥ ከብቶቹ የተሰረቁበት የብሄረሰቡ አባል በነዚህ አጎራባች ብሄረሰቦችም ጭምር ከብቶቹን ይፈልጋል፡፡ በዚህ የፍለጋ ሂደት ከብቶችን ካገኛቸውና ሽማግሌ ፈጥኖ ጣልቃ ካልገባ የከረረ ግጭት ይፈጠራል፡፡ በዚህ የስርቆት ወንጀል የሚፈጠሩ ግጭቶች ከግለሰብ አልፈው የቡድን፣ የጎሳና፣የብሄረሰብ ግጭቶች የሚሆኑበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡[40]

ቃጠሎ በብሄረሰቡ ውስጥ ለግጭት ከሚያበቁ ወንጀሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በማረቆ ብሄረሰብ ከሚከሰቱ የቃጠሎ ወንጀሎች ውስጥ የቤትና የአዝመራ ቃጠሎዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ቃጠሎውም የተለያዩ ንብረቶች ማለትም እንደ እህል፣ ከብቶችና የቤት እቃዎች አብረው ሊወድሙ ይችላሉ፡፡ ለነዚህ ወንጀሎች ጥፋተኛው ከታወቀና ወንጀል ፈፃሚው በወንጀሉ የማይፀፀት ከሆነ በተበዳይ በኩል እንደ ንቀት ስለሚቆጠር ሁለቱ አካላት የከረረ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡[41]

በሌላ በኩል የአካል ማጉደልና ግድያ በብሄረሰቡ ለከፋ ግጭት የሚዳርጉ ወንጀሎች ናቸው፡፡ ብሄረሰቡ የአካል ማጉደል ወንጀልን የሚተካና የማይተካ ብሎው የሚከፍሉት ሲሆን ራጋ ማጋ ለነዚህ ወንጀሎች ተመጣጣኝ የካሳ ቅጣት ይሰጣል፡፡ የካሳ ክፍያውን አምኖ የማይቀበል የብሄረሰቡ ተወላጅ በተበዳይ ቤተሰብና ጎሳ የብቀላ እርምጃ ይጠብቀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዳይ ተጎጂውን በሽማግሌ አስለምኖና ካሳ አቅርቦ የመታረቅ ባህላዊ ግዴታ ስላለበት በእንቢተኝነት ካሳውን አልሰጥም አይልም፡፡[42]

በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ የግድያ ወንጀሎች ለከፋ ግጭት ከሚዳርጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በብሄረሰቡ የሚከሰቱ የግድያ ግጭቶች ሁለት መልክ አላቸው፡፡ የመጀመሪያው

---

[39] *ወልዩ(ስክርብ፣50)፡፡*
[40] *ሀይሉ(ስክርብ፣27)፡፡*
[41] *ሀይሉ (ስክርብ፣19)፡፡*
[42] *ሀይሉ(ስክርብ፣10-14)፡፡*

ገዳይ አቅዶና በዝግጅት ወንጀሉን የሚፈጽመው ሲሆን ሁለተኛው በአንድ አጋጣሚ ገዳይ ሳያስበው በሚፈጠር ስህተት ነፍስ ሲጠፋ ነው፡፡

በማረቆ ብሄረሰብም የግድያ ወንጀል እርስ በርስና ከሌሎች አጎራባች ብሄረሰቦች ጋር የሚፈጠርበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በብሄረሰቡ ለአካል ማጉደልና ግድያ የሚያበቁት ነገሮች ቀላል በሆኑት ገፋኝ ገፌተረኝ፣ በመጠጥ ሀይል በመገፋፋት እንዲሁም ድንበርን ተሻግሮ መስፈርና ከብቶችን ማስማራት ናቸው፡፡[43]

### 4.3.4 የጎሳና የብሄረሰብ ግጭቶች

እንደ ብሄረሰቡ የሀገር ሽማግሌዎች (ሀይሉ፤ስክርብ፣27፤ኢማም፣77፤አበጋዝ ሙርኪ፣85) ገለጻ በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ የጎሳና የብሄረሰብ ግጭቶች አልፎ አልፎ ይከሰታሉ፡፡ በብሄረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ጎሳዊ የሆኑ የቡድን ግጭቶች የሚከሰቱት አንድ የብሄረሰቡ አባል ቀደም ሲል በእርቅና በጉዳ (ቃል ኪዳ) የተጨረሰን እርቅ በመናቅ ብቀላ ሲፈፀም ነው፡፡ በብቀላ የተጎዳው አካል ቤተሰብና ጎሳ በበዳይና በብሄረሰቡ ዘንድ የተናቀና የተዋረደ ያህል ስለሚቆጠር ወደ ባሰ እልቂት የሚያመራ ግጭት ውስጥ ይገባል። ይህ ግጭት ከሌሎቹ የግጭት አይነቶች ሁሉ ተለይቶ የሚታይ ሲሆን የእርቅ ሂደቱም ለየት ያለ ነው፡፡[44]

በሌላ መልኩ በብሄረሰቡ ከሚከሰቱ ጎሳዊ የቡድን ግጭቶች ውስጥ የእጮኛን መቀማት መነሻ የሚያደርጉት ተጠቃሾች ናቸው። በማረቆ ብሄረሰብ የአንዱ ጎሳ አባል ያጫትን ልጃገረድ ሌላኛው ጎሳ በሀይልም ይሁን በብር አታሎ ከወሰደ ግጭት ይፈጠራል። በአሁኑ ወቅት ብሄረሰቡ ልጃገረዶችን ለጋብቻ እስኪደርሱ ያስተምራል። ይህም ሲሆን ያጫት ጎሳ ለልጅቱ የማስተማሪያ ወጭ እየከፈለ ነው። ይሁን እንጅ ሴቷ በቤተሰቦቿ ወይም በራሷ ፈቃድ በትምህርት ቤት ከተዋወቀችው ወንድ ጋር ጋብቻ እፈጽማለሁ ብትል እድሜዋ እስኪደርስ አስተምሬያለሁ በሚል ግለሰቦቹ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በግጭቱ ላይ የሁለቱም ግለሰቦች ቤተ ዘመድ አባላትና ጎሳዎዎች የሚሳተፉበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡[45]

---

[43] *ሀጂ ጃተኖ(ስክርብ፣54) እና ኢማም( ስክርብ፣77)፡፡*

[44] *ከእርቅና ከጉዳ መተሳሰር በኋላ አንድ የማረቆ ብሄረሰብ አባል እርቁን ንቆ በብቀላ ጥፋት ሲፈጽም በምን አይነት የእርቅ ሂደት ግጭቱ እንደሚበርድ የግጭት አፈታት ሂደት በማረቆ ብሄረሰብ በሚለው ርዕስ በሰፊው አየዋለሁ፡፡*

[45] *ሙርኪ(ስክርብ፣85)፡፡*

ይህ ጎሳዊና የቡድን ግጭት ሲፈጠር የብሄረሰቡ ማጋዎች ግጭቱን ለማብረድ ‹ ያደርጋሉ፡፡ የልጅቷ ቤተሰቦች የተቀበሉትን ጥሎሽ በማስመለስ ሁለቱ አካላት በሽማግለ የሚስማሙበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ ሀጅ ጃተኖ፡-

> *ቤት እንዳይቃጠል፣ ሰው እንዳይጋደል አንዱን በዚህ ይዘን አንዱን በዚህ ይዘን አ፡ ብለን ታረቁ ልጃገረድ ምልቷል ብለን እናስማማለን፡፡ እንዲይጣላ እንዳይ.ጋደል ከልከ ከእግዜር ጋር ምን ያደርጋል መጋደል፣በሞት ምን ትርፍ ይመጣል እያልን አ ትወለዳለህ እሷም ትወለዳለች የተወለዱት ልጆች ለሀገር ይረባሉ፣ይማራሉ እያልን የምናስማማው፡፡ ለሚወለዱት ለሀገሪቷ ይረዳሉ፣ይጠቅማሉ እንላለን (ስክርብ፣45)፡፡*

በማለት ግጭቱን በማብረድ ባልና ሚስቱን ለማስማማት የብሄረሰቡ ማጋዎች እንደማ ይገልፃሉ፡፡ ማጋዎች ግጭት ውስጥ ለገቡት አካላት እነዚህን ሀገራዊና የትውልድ ጥያቄ በማቅረብ ስነልቦናዊ የሆኑ ጫናዎችን እያሳረፉ የከረረውን ግጭት ያበርዱታል፡፡

ግጭቱ የጎሳ አባላትን የሚያነካካና ቂም ውስጥ የሚከት በመሆኑም ለማብረድ ብዙ ጎ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ይህን ግጭት ለማርገብ ሀላፊነት የሚጣልባቸው በብሄረሰቡ ‹ የተለየ ከበሬታን ያተረፉ ማጋዎች[46]ናቸው፡፡

## 4.4 የግጭት አፈታት ሂደት በማረቆ ብሄረሰብ

የማረቆ ብሄረሰብ የራሱን ሀገረሰባዊ እውቀት፣ ጥበብ፣ ሀገረሰባዊ እምነትና ልማድ ስር አደራጅቶ የሚኖር ሲሆን ይገዙኛል ብሎ በመሰረታቸው ሀገረሰባዊ የግጭት መ ተቋማትና ተቋማቱን ይመሩልኛል በሚላቸው ሽማግሌዎች[47] ችግሩን ይፈታል፡፡ ብሄረ ዕርስ በርስና ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር በሚኖረው ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንኙነት መነሻነት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን የሚፈታበት የራሱ ሂደቶች አሉት፡፡

የማረቆ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የግጭት አፈታት ሂደታቸው ሳይሆን የሚፈቷቸው የግጭት አይነቶችም የተወሰኑ ናቸው፡፡ በአንዱ የግጭት መ ተቋም መፍትሔ የሚፈልግለት ግጭት በሌላኛው ተቋም አይታይም፡፡[48] በመሆ በብሄረሰቡ ውስጥ የሚነሱ ግጭቶች ካላቸው ክብደትና ቅለት ማለትም ከሚያስከትሉ ጥፋት አንፃር በሶስቱ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ይፈታሉ፡፡ በዚህ ርዕስ

---

[46] *ይህን ግጭት ብዙ ጊዜ የሚፈቱት እንደ አበጋዝ ሙርኪ፣አበጋዝ ጃቢሶ፣ሀጂ ጃተኖ፣ኢማም ቱኬ፣ሀ ጎጉሮ እና ዲንቁላ ቧጎ ያሉት በሳል ማጋዎች ናቸው፡፡*

[47] *ይህ አካሄድ በመደበኛው የፍትህ ተቋም ከመጀመሪያ ፍርድ ቤት እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረስ ከሚታ ስልጣን መዋቅር ጋር በእጅጉ ተቀራራቢ ነው፡፡*

ትኩረት ሰጥቼ የማየው በቤተ-ዘመድ ጉባኤ፣ በማጋና በራጋ መፍትሔ የሚፈለግላቸውን ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸውን ነው።

### 4.4.1 በቤተ-ዘመድ ጉባኤ የሚታዩ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው

በማረቆ ብሄረሰብ የቤተ-ዘመድ ጉባኤ የሚያያቸው ቤተሰባዊ የሆኑ ግጭቶችን ብቻ ነው። በብሄረሰቡ በስጋ ዝምድና የተሳሰሩ ማለትም ባልና ሚስት፣እህትና ወንድም፣አክስትና አጎት፣ ልጅና አባት ወይም እናት እንዲሁም የአንድ ጎሳ አባላት እንደ አንድ ቤተሰብ የሚታዩ ናቸው። በነዚህ ቤተሰቦች መካከል የተለያዩ ግጭቶች ቢከሰቱ በቀዳሚነት የሚታየው በቤተ-ዘመድ ጉባኤ ነው።

በማረቆ ብሄረሰብ ጎልተው ከሚታዩት ቤተሰባዊ ግጭቶች ውስጥ የባልና ሚስት ግጭት አንዱ ነው። የባልና ሚስት ግጭቶች ሁለት የተለያዩ ቤተሰባዊ የእርቅ አይነቶችን ይይዛል። የመጀመሪያው የእርቅ አይነት ጎጆ ተጋርተው የሚኖሩ ባልና ሚስት በትዳር ህይወታቸው በሚኖራቸው ተቃራናዊ የሆኑ ሀሳቦችና ፍላጎቶች ምክንያት የሚፈጠረውን ግጭት ይመለከታል። እርቁ ይህን የባልና ሚስት ግጭት በማርገብ ወደ ቀደመ ሰላማዊ የትዳር ህይወታቸው መመለስ ላይ ትኩረት ያደርጋል።[49]

ግጭት ውስጥ የገቡ ጥንዶችን ወደ ቀደመ ሰላማዊ የትዳር ህይወት ለመመለስ የሚደረገው እርቅ የራሱ ሂደቶች አሉት። በማረቆ ብሄረሰብ በባሏ በደል ተፈጽሞብኛል የምትል ሴት መጀመሪያ ችግሩን የምታሳውቀው ለዋርሶቿ፣ ለባሏ ጎሳና ለባሏ ሚዜዎች ነው። እነዚህ የቤተሰብ አባላት ሴቷ ያቀረበችውን ቅሬታና በደል በመያዝ ሁለቱንም ባለጉዳዮች አቀራረበው በችግሩ ላይ ውይይት ያደርጋሉ። በዚህ ቤተሰባዊ ውይይት ባልና ሚስት የየራሳቸውን ሀሳብና ፍላጎት እንዲያንጸባርቁ ይደረጋል። ይህ ውይይት ችግሮቹን በቀላሉ ለመፍታት ብቻ ሳይሆን የባልና ሚስቱን የትዳር ህይወት ለማፍረስ የሚያበቁ ልዩነቶችን ለማጥፋት ትኩረት ያደረገ ነው።[50]

---

[49] *ሀይሉ(ስክርብ፣9-11 እና ከ14-15)።*
[50] *ሀይሉ(ስክርብ፣9-14)።*

የብሄረሰቡን የግጭት አፈታት ስርዓት በመስክ ቆይታዬ የተመለከትኩትን አብነት በማቅረብ ባሳዮው ይሻላል፡-

*አብነት አንድ*

> *ዳቆሮ ኤሌሞና ራሂማ ሹራላ ቢዳራ ፋቃ በተባለው ቀበሌ ሶስት ልጆችን ወልደው የሚኖሩ ባልና ሚስት ናቸው። ይሁን እንጂ ባልና ሚስቱን የሚያጋጭ ጉዳይ አጋጥሟቸው ራሂማ የፍቺ ጥያቄ አቀረበች። ባልና ሚስቱን ለግጭት የዳረጋቸው ጉዳይ ዳቆሮ አዲስ ሚስት በማግባቱ ከራሂማ ጋር ያፈሩትን አዲስ ላገባት ሚስት ከፍሎ በመስጠቱ ነው። ዳቆሮ አሌሞ በራሱ ፈቃድ አንዲት ላምና ወይፈን እንዲሁም አዝመራ በመስጠቱ ራሂማ ሹራላ ለማጋዎች ቅሬታዋን በማቅረብ ንብረቷ እንዲመለስና እንዲያፋቷት ጠይቃለች። የባልና ሚስቱን ግጭት ኢማሞ ቱኬ፣ መስቀሉ ደማሞና ዲንቆላ ቧጉ የፈቱት ሲሆን ዳቆሮ ያለ ራሂማ ፈቃድ ለሁለተኛ ሚስቱ የሰጣቸውን ከብቶችና እህል እንዲመልስ ተወስኖበታል። በመጨረሻም ራሂማ ሹራላ በራሷ ፈቃድ ለሁለተኛዋ ሚስት ወይፈኑን የሰጠቻት ሲሆን ከዳቆሮ ኤሌሞ ጋርም ተስማምተው ወደ ቀድሞ ትዳራቸው ተመልሰዋል።*

በብሄረሰቡ በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ግጭቶች በፍቺ ከመደምደማቸው በፊት በማጋዎች ታይቶ በእርቅ ይቋጫል። ይህ ደግሞ የቤተ-ዘመድ ጉባኤ በፍቺ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቦናዊ ችግሮች የሚታደግ ሀገረሰባዊ ተቋም መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በብሄረሰቡ በባል ቤተሰቦች የተጀመረው እርቅ የማይሳካበት አጋጣሚም አለ። በዚህ ጊዜ የሴቷ ቤተሰቦችና ጎሳ በአንድ ላይ ሆኖ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል። ይህ የሚሆነው ሴቷ ባሏ የሚያደርስባት በደል የጠነከረና ቤተሰቦቹ መስማት ይናርባቸዋል በምትልበት ጊዜ ነው።

በዚህ የእርቅ ሂደት የሴቷ ቤተሰቦች ጣልቃ መግባታቸው ባል ወደፊት በሚስቱ ላይ የሚያደርሰውን በደል እንዲያቆም፣ ትዳሩን ፈርቶና አክብሮ እንዲይዝ ከማገዙም በላይ ቀጣይ በሚኖራቸው የትዳር ህይወት ሁለቱ ግጭት ውስጥ ቢገቡ የፍቺ ጥያቄ ለማቅረብ ስለሚያመች ነው።

ሁለተኛው ቤተሰባዊ የእርቅ አይነት ባልና ሚስቱን ወደ ቀደመ የትዳር ህይወታቸው መመለስ የማይቻልበት አጋጣሚና ሁኔታ ሲኖር በቤተ-ዘመድ ጉባኤ የሚከናወነውን ሰላማዊና ቤተሰባዊ የፍቺ ሂደት ይመለከታል።[51]

---

[51] *ሀይሉ(ስክርብ፣15)።*

በማረቆ ብሄረሰብ ፍቺ ያለ አሳማኝ ምክንያት፣ያለጎሳውና ቤተሰብ የጋራ ስምምነት ሲከናወን አይችልም። በብሄረሰቡ እይታ ፍቺ በስምምነት በመመራረቅ ከተፈጸመ የወንዱም ሆነ የሴቷ የወደፊት ህይወት የሰመረና የተቃና[52]ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ብሄረሰቡ ባልና ሚስት ቀላልና ሊስተካከሉ በሚችሉ ችግሮች ምክንያት እንዲለያዩ አይፈቀድም። ባልና ሚስት እንዲፋቱ የሚደረገው ባል ሚስቱን ማስተዳደርና መንከባከብ ካልቻለ ነው። ይህን ሀሳብ ሀይሉ፡-

> *በተለይ ያልበደለች፣ በብዙ ነገር የተጎሳቆለች ከሆነች ጎሳውና ቤተሰብ በሙሉ ተስማምቶ፣ በባሏ ላይ ተፅዕኖ አድርጎ ነው የሚፈታት። ለምን ቢባል መጀመሪያም ያጫት የነበረው ወላጅ ነው፣ጎሳው ነው። አሁንም እሱ እሷን ተንከባክቦ ካልያዘ፣ ማስተዳደር ካልቻለ ወይም ያልወለደች ከሆነች፣ የእሷ ሁኔታ በብዙ ነገር የሚያሳዝንና የሚመስጥ ሲሆን ቤተሰብ እና ያስብነው ነገር አልተሳካም። ይወልዳሉ፣ ይከብዳሉ ብለን ነበር፣ አብረው ለረጅም አመታት በፍቅር ይኖራሉ ብለን ነበር። ይሁን እንጅ ችግሩ ያለው ከልጃችን በኩል ነው ስለዚህ ለምንድን ነው ነጻ የማናደርጋት ብሎ ቤተሰብ፣ ጎሳው፣የቅርብ ቤተ ዘመድ በእሷ ቤተሰብ ጠያቂነት ፍቺ ይከናወናል(ስክርብ፣15) በማለት ይገልፁታል።*

ይህ የብሄረሰቡ እይታ በመደበኛው የፍትህ ተቋምም ተቀባይነት አለው። በመደበኛው የፍትህ ተቋም የባልና ሚስት የፍቺ ጥያቄ በቀላሉ ተቀባይነት አያገኝም። ባልና ሚስቱ ከመፋታታቸው በፊት እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የማሰላሰያ ጊዜ (pariod of cooling time) ተሰጥቶ በሽማግሌ የሚስማሙበት እድል ይፈጠራል። ሁለቱም የፍትህ ተቋማት ፍቺ ላይ ያላቸው አመለካከት ተመሳሳይ ነው።[53]

በብሄረሰቡ ሴት ልጅ ትከበራለች። ይሁን እንጅ አንድ የብሄረሰቡ ወንድ ሚስቱን የሚደበድብና እየሰከረ የሚረብሽ ከሆነ እንዳልተንከባከባት ስለሚታይ የፍቺ ሂደቱን ያፋጥነዋል። በማረቆዎች ፍቺ ሲከናወን በሰላማዊ መንገድ ስለሆነ እንደ እርቅ ነው የሚታየው። በብሄረሰቡ ፍቺ የራሱ ስርአት አለው። እነዚህ ስርአቶች ለዘመናት ሲሰራባቸው የኖሩና አሁንም ድረስ የሚተገበሩ ናቸው።[54]

የባልና ሚስቱ ፍቺ ከመፈጸሙ በፊት የሁለቱ የጋራ ንብረቶች ተቆጥረው ክፍፍል ይፈፀማል። ልጆች የወለዱና የግዴታ መፋታት ካለባቸው ልጆቻቸውንም ተካፍለው ያሳድጋሉ። ይህን ሁኔታ ሀጅ ጃተኖ አብነት በማቅረብ፡-

---

[52] *ሀይሉ(ስክርብ፣10 እና 14)።*
[53] *ሀይሉ(ስክርብ፣9-11 እና ከ14-15፤ ወልዩ፣50፤ መላኩ፣58-59፣61)*
[54] *ሀይሉ(ስክርብ፣15)።*

## አብነት ሁለት

*አበራ የሚባል አንካሳው አኪም አለ። አንዲት ሴት አለች ኣላድርም አለች። አምስት ልጆች አሉ። ሁለቱን ልጆች ትንንሾቹን ለሷ ሰጥተን አታርሺ አትነግጂ ብለን ሶስቱን ደግሞ ለአባት ሰጥተን ንብረቱን ሁሉ አንድ ሳይቀር ሰባት ቦታ አድርገን። አባትዬው አራት ከሶስት ልጆቹ ጋር እናትዬዋ ሶስት ከሁለት ልጆቿ ጋር አድርገን አካፍለን። ኡሴን የሚባል ነበር ፍርድ ቤት ለእሱ ጥፈን ሰጠን በቃ እንደዚህ ተካፍለው እሷም አንድ ቤት ወሰደች፣ እሱም ትልቅ ቤትና ቦታ ወሰደ። አሁን እሱ አለ እሷም በወደደች አለች በአንድ ከተማ ውስጥ። አሉ ተስማምተው? አሉ ተስማምተው ልጆቻቸውም አድገዋል እነሱም ሰላም ናቸው (ስክርብ፣44)።*

በማለት የብሄረሰቡን የግጭት አፈታት ፍትሃዊነት ይገልፁታል።

ባልና ሚስቱ በንብረት ክፍፍሉ መስማማታቸውን ከገለጹ በኋላ ባልየው ለሚስቱ የተለያዩ አልባሳትና ጌጣጌጦችን እንዲሰጣት ይደረጋል። ባል ይህን የሚያደርገው አብረው በነበሩበት ጊዜ ስበደላት በደል ማካካሻና ወደፊትም የራሷን ትዳር እስክትመሰርት ለምትጠቀምበት ነው። ስጦታው ከተከናወነ በኋላ የባል ጉሳና ቤተሰብ በአንድ ላይ ምርቃት ይሰጣሉ። ይህን ስርዓት በተመለከተ ሀይሉ(ስክርብ፣10) "...ሲለያዩም ጎሳው ይመርቃታል። ስትሸኚ በባልዮው ቅቤ ትቀባለች፣አስፈላጊ የሚባሉ አልባሳትን ጌጣጌጦችን ሁሉ ሰጥቶ፣ አልብሷት ነው የምትሸኘው። ትመረቃለች፣ስትሄድም በቃ እህል ውሀ የምትበይበት፣የምትጠጭበት ቦታ አግኚ ተብላ ትመረቃለች" በማለት ይገልጹታል።

በማረቆ ብሄረሰብ ፍቺ ሲከናወን በሚደረገው የምርቃት ስርአት ሴቷ ቅቤ መቀባቷ የራሱ ባህላዊ ተመሳሌት አለው። ይህን ባህላዊ ተምሳሌት ሀያሉ፦

*...ፍቺ ሲካሄድ ለሴቷ የምትቀባው ይቅናሽ፣ገዳም ሁኚ፣ ሄደሽ እርጠቢ፣ጥሩ ነገር ያጋጥምሽ፣ ለምለም ሁኚ ተብሎ ድህነትን የማስወገጃ፣ የሚያለዝብ፣ የሚያረጥብ፣ ቀጣይ እድሏ ጥሩ እንዲሆን የሚያደርግ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። ምርቃቱ እንዲሰረግላት፣ ቀጣይ እድሏም ረጠብ ያለ እንዲሆን ወተት፣ ከብት፣ ልጅ ከእሷ እንዳይጠፋም ጭምር ልባዊ ምርቃት የማድረጋቸው ምልክት ነው። መሄዷ ላይም ምንም ተቃውሞ እንደሌለ፣ ጎሳው እንደፈታት፣ቀጣይ ብታገባም ምንም አይነት ተቃውሞ እንደሌለባቸው ማሳወቂያ ነው መርቀው፣ቅቤ ቀብተው፣መልካም ምኞታቸውን ገልፀው ለመላካቸው ማሳያና ማረጋገጫ ነው (ስክርብ፣14) በማለት ይገልፁታል።*

በብሄረሰቡ ምርቃት ስርዓት ሳይከናወን ፍቺ ሊካሄድ አይችልም። ተመርቃና ቅቤ ተቀብታ ያልተሸኘች ሴት ወደፊት ጥሩ የትዳር ህይወት አይኖራትም ተብሎ ይታመናል። በዚህም የተነሳ የሴቷ ቤተሰቦች ምርቃቱን ትኩረት ሰጥተው ያስፈጽማሉ።

በብሄረሰቡ ለሴቷ ምርቃት ከተካሄደ በኋላ ለወንድም እንደ ሴቷ ሁሉ የመልካም ያጋጥምህ ምኞት ከሴቷ (ከቀድሞ ሚስቱ) ይቀርብለታል። ሴቷ በቀድሞ ባሏ ላይ ምራቋት "ቱፍ

ቱፍ" እንድትልበት ይደረጋል። ይህን የምታደርገው አንድም አብረው በነበሩበት ወቅት ለበደላትና ላስቀየማት ሁሉ ይቅርታ ማድረጓን አንድም ከዚህ በኋላ እህትና ወንድም መሆናቸውን ለመግለፅና ወደፊት በሚኖራቸው የየግል ማህበራዊ ህይወት የተቃና እንዲሆን ለሱም ጥሩ ነገር እንዲያጋጥመው መመኘቷ ነው።

በማረቆ ብሄረሰብ እነዚህ ሂደቶች በሙሉ ተፈጽመው የተከናወነ ፍቺ እርቅ እንጂ መለያየት፣ግጭት አይደለም። የሁለቱም ቤተሰቦች ወደፊት የሚኖራቸው ማህበራዊ ግንኙነት የጠበቀ ነው። በተለያዩት ባልና ሚስት መካከልም የሚኖረው ግንኙነት የእህትና የወንድም እንዲሁም የቤተሰብ አይነት ሆኖ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይም ይገኛሉ።

### 4.4.2 በማጋዎች የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው

የማረቆ ብሄረሰብ እርስ በርሱና ከሌሎች አጎራባች ብሄረሰቦች ጋር ግጭቶች በሚያጋጥሙት ወቅት ግጭቶቹን ከሚያበርድባቸው ተቋማት መካከል ማጋ አንዱ ነው። በዚህ ተቋም ከቤተ-ዘመድ ጉባኤ አቅም በላይ የሆኑ ግጭቶችን ጨምሮ ድብድብ፣ ስርቆት፣ ስድብ፣ የአካል ማጉደልና መሰል ግጭቶች መፍትሄ ይሰጣቸዋል። ይህ ማህበረሰባዊ ተቋም ሙሉ በሙሉ መፍትሔ የሚያበጅላቸው ግጭቶች የመኖራቸውን ያህል በራጋ በኩል ፍጻሜ የሚያገኙትንም ግጭቶች በማብረድ ረገድ ሚናው የጎላ ነው። ማጋዎች የሚፈቷቸውንና የሚያበርዷቸውን ግጭቶች ከሚያደርሱት ጉዳት አንፃር ቀላልና ከባድ ግጭቶች ብሎ መክፈል ይቻላል። በዚህ ጽሁፍ እነዚህን ግጭቶች ለመፍታትና ለማብረድ የሚታለፉ ሂደቶችን ለማሳየት እሞክራለሁ።

#### 4.4.2.1 የቀላል ግጭቶች አፈታት ሂደት

በማረቆ ብሄረሰብ ቀለል ያለ ግጭት ቢከሰት ጉዳት ያደረሰው አካል ለጊዜው በመሰወር ማጋዎችን ወደ ተጎጂው ቤተሰቦች ይልካል። በብሄረሰቡ ጉዳት ያደረሰው አካል ቀድሞ ይቅርታ ከጠየቀ ለተጎጂ ቤተሰቦች አክብሮት አለው ተብሎ ስለሚታመን ጎጂው ታስሮም ቢሆን መፀፀቱን የሚገልጸው ማጋዎችን በመላክ ነው። ይህን ሀሳብ ሀይሉ (ስክርብ፣10) "እኔ በድያለሁ ወይም ሰይጣን አሳስቶኝ ነው ወይም በመጠጥ ሀይል ነው ይህን የፈፀምኩት ወይም በሆነ መንፈስ ውስጥ ሆኜ ስህተት ሰርቻለሁ፣ ወንድሜን ጎድቻለሁ ብሎ ያነሳል" በማለት በዳይ ስህተቱን አምኖ በማጋዎች አማካኝነት ለእርቅ ያለውን መልካም ፈቃድ እንደሚያቀርብ ገልጸውታል።

የብሄረሰቡ ማጋዎችም የበዳይን የአስታርቁኝ ተማፅኖ በመያዝ ወደ ተጎጂው ቤት ይሄዳሉ። ተጎጂውም የእናስታርቃችሁ ጥያቄ ይዘው የመጡትን ማጋዎች አልታረቅም ብሎ ሊመልሳቸው ይችላል። ማጋዎችም ቢሆኑ ተበዳይ አልታረቅም ስላላቸው ዝም ብለው አይመለሱም። በእለቱ ተበዳይ ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው በመጠየቅ ይመለሳሉ።

መጀመሪያ ላይ ተበዳዩ ሽማግሌዎችን የሚመልሳቸው ከቤተሰቦቹና ከጎሳው ጋር ለመመካከርና ከደረሰበት ጉዳት እስኪያገግም ቆዩ ለማለት ነው። ተጎጂ በሁለተኛው የቀጠሮ ቀን ከቤተሰቦቹና ከጎሳው ጋር በተመካከረው መሠረት ጥላ[55] ስጥቻለሁ ይላል።

አንድ ጉዳት የደረሰበት የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጅ በማጋዎች ጥያቄ ለእርቅ ፈቃደኛ ሆኖ ከተገኘ በበዳዩ አካል የተለያዩ ድጋፎች ይደርጉለታል። በዳዩ ለተጎጂው የሚያደርገውን እገዛ ሀይሉ፡-

> *ከዚያ በኋላ በመጀመሪያ ደረጃ ማገገሚያ እንዲሰጠው ይደረጋል። ይህ ማገገሚያ ማለት ለዚህ ለተጉዳው ደም ፈሶት ሊሆን ይችላል፤ አካል ላይ ጉዳት ደርሶ ሊሆን ይችላል ለነዚህ ነገሮች ለወጌሻ መታሻ፣ ደም የሚተካበት አንድ ጠቦት፣ግማሽ ጎን ቆጮ የሚባል ነገር አለ፣ አንድ ጥዋ ንፕር ቅቤ የሚባል ነገር አለ እና በርበሬና የተለያዩ ማጣፈጫዎች በአንድ ላይ እንዲሰጠው ያደርጋሉ ሽማግሌዎቹ። ይህ ሁሉ እንግዲህ በሽማግሌዎች የሚደረገው ተጎጂው እንዲያገግም ተብሎ ነው። ይህ ሁኔታ የድርድሩ ቅድመ ሁኔታ ስለሆነ የማይታለፍ የሽማግሌዎች ቅድሚያ ስራ ነው(ስክርብ፣11) በማለት ሂደቱን ገልጸውታል።*

በብሄረሰቡ ለማገገሚያ በሽማግሌ የቀረበውን ተበዳይ ከተቀበለ ከልቡ ለመታረቅ ማሰቡ ይረጋገጣል። ማጋዎች እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በበዳይ በኩል እንዲሟሉ ከማድረግም አልፈው በየጊዜው እየተመላለሱ ተበዳዩን ይጠይቃሉ። በዚህ ጊዜ ተበዳዩ የማይሻለው ከሆነና ተጨማሪ ማገገሚያ እንደሚያስፈልገው ካረጋገጡ እንዲሟላለት ያደርጋሉ። በተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት በወጌሻ መታሸት አለበት ብለው ካመኑ ወይም መታከም ይኖርበታል የሚሉ ከሆነ በዳይ ሙሉ ወጭውን እንዲሸፍን ይደረጋል። ይህን ሀሳብ በመስክ ቆይታዮ ሁለት ግለሰቦች ያደረጉትን እርቅ እንደ አብነት በማቅረብ ላሳይ፡-

---

[55] *ሜጤ ሃፋ(የአማርኛ አቻው ጥላ ይባላል) በማረቆ ብሄረሰብ ዘንድ ጥላ ማለት ግጭት ውስጥ የገቡ የብሄረሰቡ አባላት ለእርቅ የሚደረደሩበት ቦታ ነው። ማጋዎች ለእርቅ የሚቀመጡበት ቦታ ነው። ይህም ሲባል የዛፍ ጥላ ያለበትን ቦታ የሚመለከት አሳቤ ነው። ጥላው የዋርካ፣ የዕድ ወይም የግራር ሊሆን ይችላል።*

### አብነት ሶስት

*አምዲ ሹለላና አኩል ለሚሶ በቆሼ ዙሪያ ቀበሌ የሚኖሩ ገበሬዎች ናቸው። አኩል ለሚሶ ቤቱ መንገድ ዳር ሲሆን አምዲ ሹለላ ቆሼ ከተማ ሲጠጣ እያመሸ ወደ ቤቱ ይገባል። አምዲ ስለሚጠጣ አንዳንዴ በጩኸት አንዳንዴ ደግሞ መንገድ ዳር ያሉ ቤቶችን በድንጋይ እየደበደበ ያልፋል። ታህሳስ አስር ቀን በቆሼ ከተማ ሲጠጣ ያመሸው አምዲ ማታ ወደቤቱ ሲመለስ ወደ አኩል ለሚሶ ቤት ድንጋይ በማጣል ይደበድባል። አኩል እና አምዲም ግጭት ውስጥ ይገባሉ። በግጭቱም አምዲ ተደብድቦ ጉዳት ይደርስበታል። በሁለቱ ግለሶች መካከል የተፈጠረውን ግጭት አበጋዝ ሙርኪ ደመቀ፣ ሀይሉ ጓጉሮና ሰላሞን ወረቂቶ የተባሉ ማጋዎች ያበረዱት ሲሆን አምዲ ሹለላ የሰው ቤት በምሽት በመደብደቡና ስፈር በመበጥበጡ ጥፋተኛ ተብሏል። በመሆኑም ያፈሰሰውን ደም በራሱ ሽፍኖ እንዲያገግም ሲወሰንበት እኩል ለሚሶ ደግሞ አምዲ ለህክምናና ለወጌሻ ያወጣውን ብር እንዲከፍል በማድረግ ታርቀዋል።*

በማረቆዎች ተበዳይ በማጋዎች አማካኝነት ከበዳዩ አካል የተለያዩ የማገገሚያ ድጋፎችን አግኝቶ ሲሻለው ዋናው የእርቅ ሂደት ይጀምራል። በዚህ ጊዜ ተጎጂው ቀደም ብሎ ለህክምናም ሆነ ለማገገሚያ ያወጣው ወጭ እንዲሁም ለክስ የተመላለሰበት ታስቦ እንዲከፍል ይደረጋል። ይህን ሀሳብ ሀጂ ጃተኖ በአብነት ሲያስረዱ፡-

### አብነት አራት

*የመሃመዲ ሙስጠፋ ልጅ አለ ሀሰን የሚባል። እና ከጎረቤቱ ጀማል ከድር ጋር በዳንግ የተነሳ ተጣልተው ነበር። ሁለቱም የአንድ ጎሳ ናቸው ከአሻጌ ጎሳ። ተጣሉ እኛ ተነስተን አንተም ተው አንተም ተው ብለን ቃል አጋብተን አስታረቅን። እኔ አለሁ ሼ…ዲላ እያሱም ነበር ሌሎችም ሰዎች አሉ አስታረቅን በማረቆ ሴራ። ስናስታርቅ ጀማል ከድር ሀሰንን ደብድቦ ስለነበር የሀኪም እንዲከፍል አድርገነዋል። የደም መተኪያ እንዲሆነውም አንድ አነስ ያለ ፍየል ጀማል ሰጥቶታል። ከዚያ በኋላ ተጣልተው አያውቁም ተስማምተው ይኖራሉ አሁን።*

የእርቅ ሂደቱ በዋነኛነት የሚጀመረው ግጭት ውስጥ የገቡትን ሁለት አካላት በማወያየት ነው። በዚህ የውይይት ሂደት ሁለቱም አካላት ግጭት ውስጥ ስላስገባቸው ጉዳይ በግልፅ ለማጋዎች እንዲናገሩ እድል ይሰጣቸዋል። በተለይ በግጭቱ ድብደባ ተከናውኖ ከሆነ ደግሞ በዳይ እንዴትና በምን እንደደበደበው እንዲናገር ይደረጋል። ተበዳይም በበኩሉ በምን እንደተደበደበና እንዴት እንደተደበደበ ለማጋዎች ግልፅ አድርጎ ያስረዳል።

ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ጉዳያቸውን ለማጋዎች የሚያስረዱበት የብሄረሰቡ ባህልና ወግ የደነገገው ስርአት አለ። በብሄረሰቡ በዳይ በሽማግሌዎች ፊት ሲቆም በጥፋቱ ተፀፅቶና አዝኖ መቅረብ አለበት። ጉዳዩን ሲያስረዳም ለስለስ ያሉ የልመና አይነት ቃላትን እየተጠቀመ ነው። የበዳይን አቀራረብ በማየትም ተበዳዩ በቀላሉ ለመስማማት ፈቃደኛ

ይሆናል። በዳይ በማጋዎች ፊት ፀፀት የማይታይበት ከሆነ ለተበዳይ እንደ ንቀት ስለሚታይ ተበዳይ አልታረቅም ሊል ይችላል።[56]

በማረቆ ብሄረሰብ ጉዳት አድርሶ ለእርቅ በማጋዎች ፊት የቀረበ ሰው ጉዳዩን ቆሞ ወይም ተቀምጦ ሊያስረዳ ይችላል። በብሄረሰቡ የበዳዩን ቆሞ ወይም ተቀምጦ የማስረዳት ሁኔታ የሚወስነው በማጋዎች ነው። በእርቅ ሂደቱ ላይ ብዛት ያላቸው ማጋዎች የሚሳተፉ ከሆነ በዳዩ አካል ጉዳዩን ሲያስረዳም ሆነ ሲሰማ ቆሞ ነው። በዚህ የእርቅ ሂደት ተበዳዩ አካል ሀሳቡን ለማጋዎች ሲያስረዳም ሆነ ሲሰማ ተቀምጦ ነው። በብሄረሰቡ ተበዳይ አካል ከበደሉ በላይ ቆሞ እንዲያስረዳም ሆነ እንዲሰማ አይፈቀድም "እሱማ ተበድሏል" ይባላል።

እንደ ሀይሉ (ስክርብ፣24) ገለፃ ለእርቅ ጉዳያቸውን ለማጋዎች አሳልፈው የሰጡ የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጆች ጉዳያቸውን በሚስብና በሚመስጥ ሁኔታ ማስረዳት አለባቸው። እነዚህ ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን ፊት ለፊት እየተያዩ ወይም በየተራ ከማጋዎች በመራቅ ሊያስረዱ ይችላሉ። በማጋዎች ትእዛዝ አንዱ ጉዳዩን ካስረዳ በኋላ ሌላኛው ተጠርቶ ሊያስረዳ ይችላል። በተለይ ግጭቱ ባለጉዳዮችን ለጭቅጭቅ የሚጋብዝ አይነት ግጭት ከሆነ ጉዳያቸውን በተናጥል እንዲስረዱ ይደረጋሉ።

እነዚህ አካላት ሀሳባቸውን ለማጋዎች ካስረዱ በኋላ የተፈጠሩ የሀሳብ ልዩነቶች ይታያሉ። በተለይ በዳይ ጥፋቱን አላምንም ብሎ ከከዳ ማጋዎች እንዲያምንና እንዲታረቅ ይመክሩታል። በዳይ ምክር ተሰጥቶት ወንጀሉን የማያምን ከሆነ ተበዳይ ምስክር እንዲያቀርብ በማድረግ ምስክሮቹ ቃላቸውን ይሰጣሉ። ተበዳይ ምስክር ማቅረብ የማይችልና በድብቅ[57] ጉዳት የደረሰበት ከሆነ ግን ጉዳዩ በመሀላ ይጣራል። በምስክሮቹ ድምጽ በዳይ ጥፋተኛነቱ ከተረጋገጠ ከበደል በላይ በደል ተደርጎ ይቆጠራል። በበዳይ ላይ የሚጣልበት ቅጣትም ቢሆን በፊት ሊጣልበት ከሚችለው ቅጣት እጥፍ ይሆናል።

በእርቁ ሂደት ባለጉዳዮች በቀላሉ ከተማመኑ በተለይ በዳይ ጥፋቱን አምኖ ከቀረበ ወዲያውኑ ወደ እርቅ ይኬዳል። ማጋዎች የእርቅ ውሳኔውን ለማሳለፍ ሁለቱን ባለጉዳዮች ራቅ ብለው እንዲቆዩ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። ይህ የሚሆነው ማጋዎች በዳዩ አካል ለተበዳዩ መክፈል

---

*[56] ሀይሉ(ስክርብ፣25)።*
*[57] በማረቆ ብሄረሰብ የሀገር ሽማግሌዎችን (ማጋዎችንና ራጋን) ማክበር፣ ቃላቸውን መጠበቅ፣ የጠየቁትን መፈፀም እንደ አንድ የብሄረሰብ አባልነት መለኪያ፣ የአንድ ሰው ሙሉነትና አዋቂነት መመዘኛ፣ የባህልና የልማድ አክባሪነት መገለጫ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህን ማድረግ ያልቻለ የብሄረሰቡ አባል ሙሉ ሰው አይደለም። ጤነኛ ተብሎ አይጠራም፣አባት፣ እናት ቤተሰብ በሙሉ ያገለዋል።*

ያለበትን የካሳ ሁኔታ ተወያይተው ለመወሰን ነው፡፡ በዚህ የውሳኔ ሂደት ለእርቅ የተቀመጡት ሁሉም ማጋዎች እኩል የሆነ ስልጣን አላቸው፡፡[58]

ማጋዎቹ ተወያይተው ውሳኔ መስጠት ካልቻሉ ቀጠሮ ተሰጥቶ ይለያያሉ፡፡ ማጋዎች ውሳኔውን በቀላሉ ማስተላለፍ ከቻሉ ደግሞ እርቁ በዚያው እለት ያልቃል፡፡ ለተበዳይ የሚሰጠው ካሳ የተለያየ ሲሆን ይችላል፡፡ እንደ ማጋዎቹ ውሳኔ ገንዘብ፣ ከብት ወይም ፍየል ሊሆን ይችላል፡፡ ማጋዎች ይህንን ውሳኔ ለባለጉዳዮቹ በቃል ወይም በሰነድ ተፈራርመው ሊያሰሙ ይችላሉ፡፡ በተለይ ጉዳዩ ከህግ ጋር ሊያገናኝን ይችላል፣ በህግ ሊያስጠይቀን ይችላል ካሉ ሁለቱን ባለጉዳዮች በማስፈረም ለህግ አካል ያስረክባሉ፡፡

ይህን ለማድረግ እንዲመች ባለጉዳዮቹ መጀመሪያ ላይ ማጋዎቹን አስታርቁን ብለው ሲጠይቁ ያስፈርሟቸዋል፡፡ ማጋዎች ሁለቱን ባለጉዳዮች አፈራርሞ ወደ እርቅ የሚገቡትም ሆነ ፈፃሚውን በሰነድ መያዝ የሚፈልጉት አንዳንድ ሰዎች(ብዙ ጊዜ ሴቶች) የሌሎች ሰዎችን ምክር በመስማት ከእርቅ በኋላ ወደ ፍርድ ቤት ሄደው ስለሚከሱ እንደሆነ በመስክ ቆይታዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

በዚህ የእርቅ ሂደት በማጋዎች የተወሰነውን የካሳ ክፍያ በዳይ በእለቱ መክፈል የማይችል ከሆነ 'የሽማግሌ ቀጠሮ' ይሰጠኝ የማለት መብት አለው፡፡ በማረቆ ብሄረሰብ ‹‹የሽማግሌ ቀጠሮ›› የአስራ አምስት ቀን[59] ርዝማኔ ያለው ሲሆን በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ በዳይ ካሳውን ፈልጎ ለማጋዎች ያስረክባል፡፡ ማጋዎች ደግሞ ለተበዳይ አካል ወስደው ይሰጣሉ፡፡ የካሳ ክፍያው በማጋዎች በኩል ለተበዳይ የሚሰጥበት ዋናው ምክንያት ሽማግሌዎች በሌሉበት አጋጣሚ በዳይ ገንዘቡን ወይም ከብቱን ሲሰጥ ጥሩ የሆነ ፊት ካላሳየው ጥል ሊፈጠር ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

---

*[58] ሀይሉ(ስክርብ፣25)፡፡*

*[59] የሽማግሌ ቀጠሮ እየተባለ የሚጠራው የአስራ አምስት ቀን የጊዜ ርዝማኔ በዳይ አካል ቀጠሮው ከሽማግሌ ጋር ብቻ በመሆኑ ሲሆን ለስሙም መነሻ የሆነው ይኸው ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ የሽማግሌ ቀጠሮ በኢትዮጵያ እየተተገበረ ካለው የመደበኛው የፍትህ ተቋም አሰራር በተለይ ለይግባኝ ከሚሰጠው የ 15 ቀን ርዝማኔ ጋር ይመሳሰላል፡፡*

በብሄረሰቡ ተወላጆች መካከል የተፈጠረው ግጭት በድብደባ የተቋጨ ከሆነና በተበዳይ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ወደ ራጋ የማያደርስ ሲሆን በዳዩ አካል መጠነኛ ድግስ[60] አዘጋጅቶ ማጋዎች በተገኙበት ይመራረቃሉ፡፡ በማረቆ ብሄረሰብ ግጭቶች በሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም መፍትሔ ከተሰጣቸው በኋላ ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት እንዲመራረቁ ማድረግ የተቋሙ የተለመደ መርህ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ሀይሉ(ስክርብ፣11)"ሁለተኛ እጅህ አይተላለፍ እየተባለ ይመረቃል፡፡ ተጎጂው ሰው የጉዳት አድራሹን እጅ ይዞ 'ቱፍ ቱፍ' ብሎ ራሱን ቅቤ ይቀባዋል" በማለት እርቁ በምርቃት እንደሚደመደም ይገልጻሉ፡፡

በዚህ የእርቅ አጨራረስ ተበዳዩ አካል የበዳዩን እጅ ይዞ "ቱፍ ቱፍ"[61] ማለቱ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ቂሜን አውጥቻለሁ፣ ከልቤ ይቅር ብየሀለሁ የሚል ባህላዊ ተምሳሌት ተሸክሟል፡፡ ቅቤው ደግሞ በዳዩ አካል ወደፊት ሌሎች ሰዎች ላይ ይህን መሰል ጉዳት እንዳያደርስ ለማሳሰብ ነው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ በሰዎች ላይ ጉዳት ማድረስ የእርኩስ መንፈስ ተዋርሶ ነው ተብሎ ስለሚታመን የዚህን መንፈስ ማስወገጃና ማርከሻ ጎጂውን አካል ቅቤ በመቀባት ማንጻት ነው፡፡[62]

መንጻት ሰዎች በበሽታ በተለከፉ ጊዜና በእምነታቸው የተከለከሉ ድርጊቶችን በፈጸሙ ጊዜ ከበሽታቸው ለመዳንና ከአምላካቸው ምህረት ለማግኘት ሲሉ የሚፈጽሙት ጉድፍን፣ ሀጢያትን የማስወገጃ ዘዴ ነው፡፡ መንፃትን በተመለከተ Bell (1997፡118) "Purification is a major theme with in rites of affliction, although it can be understood in a variety of ways. It can involve freeing a person from demonic possession, disease, sin, or the karmic consequences of past lives" በማለት ይገልፁታል፡፡ ማረቆዎችም ወንጀል የፈፀመ የብሄረሰቡ አባል እርኩስ መንፈስ ተዋርሶታል ስለሚባል በሽማግሌዎች ፊት ተበዳይ ቅቤ እየቀባዉ ይመረቃል፡፡ በብሄረሰቡ ግጭት ውስጥ የገቡ

[60] በዚህ የግጭት አፈታት ሂደት መጠነኛ የሆነ ድግስ ይደገሳል ሲባል በድግሱ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች ቁጥር ጥቂት መሆኑን፣ለድግሱ ማስፈፀሚያ የሚሆን እርድ የማይከናወን ሲሆን ግብዣውም በቀን እንደሚሆን ለመጠቆም ነው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ድግስ ላይ የግድያ እርቅ ከሚፈፀምበት ስርዓት ጋር የማይመሳሰሉ ነገሮች ይበዙበታል፡፡

[61] በመመራረቁ ሂደት ምራቅን ‹ቱፍ ቱፍ› ማለት በቤተ ዘመድ ጉባኤ አማካኝነት በሚከናወነው ሰላማዊ የፍቺ ሂደት ላይም እንደሚከናወን ልብ ይሏል፡፡ ይህ የምርቃት ሂደት የያዘው ፅንሰ ሀሳብ በሁሉም ሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋማት የእርቅ ሂደት ላይ ተመሳሳይ ነው፡፡

[62] ሀይሉ(ስክርብ፣11)፡፡

አካላት እነዚህን ነገሮች በአግባቡ ፈፅመው እንዲታረቁ ሀገረሰባዊ እውቀቱና ጥበቡ የደነገጋቸው እምነቶች፣መርሆችና ልማዶች[63] ያስገድዷቸዋል።

በማረቅ ብሄረሰብ እርቅ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁለቱ አካላት ንፁህ የሆነ የጓደኝነትና የቤተሰብ ግንኙነት ይመሰርታሉ። ይህን ሀሳብ ሀጂ ጃተኖ (ስክርብ፣40) ‹‹ሁለቱ ከታረቁ በኋላ የእናትና የአባት ልጅ ይሆናሉ። ይህ ለልጅም ያልፋል እንደዚህ ነው የእርቁ ሁኔታ›› በማለት ከእርቅ በኋላ በሁለቱ አካላት መካከል የሚኖረውን ግንኙነትና የእርቁን ዘላቂነት ከቀጣይ ትውልድ ጋር አገናኝተው ይገልጹታል። ግንኙታቸውንም በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ማለት በደቦ፣ በሀዘንና በደስታ በመረዳዳት እንዲሁም ሀይማኖታዊ ስርዓቶች ላይ በአንድነት በመሳተፍ ያጠናክሩታል።

### 4.4.2.2 የአካል ማጉደልና የግድያ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ለእርቅ ማዘጋጀት

የማረቅ ብሄረሰብ ማጋዎች ውስጥ የሚፈጠሩ ቀለል ያሉ ግጭቶችን[64] ከመፍታት አልፈው ከባድ የአካል ማጉድልና የግድያ ግጭቶችን ለማብረድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። እነዚህን ግጭቶች ለማብረድ የእርቅ ሂደቱ የሚጀመረው በብሄረሰቡ ማጋዎች ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ወደ ባሰ ውስብስብ ግጭት እንዳያመሩ ለመጠበቅ ነው። ግጭቶቹ የእርቅ ፍፃሜ የሚያገኙት በራጋ ቢሆንም ግጭቶቹ አድማሳቸውን አስፍተው ጎሳን እንዳያካክሉ በመቆጣጠርና ባለጉዳዮችን ለእርቅ በማመቻቸት የመጨረሻውን የእርቅ አፈፃፀም ለራጋ ማሳለፍ የማጋዎች ሀላፊነት ነው።

በብሄረሰቡ ከባድ የሆነ የአካል ማጉደል ወይም የግድያ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ በበዳይ ቤተሰቦች ላይ ሊደርስ የሚችልን የበቀል ጥቃት ለመከላከል ማጋዎች የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ። የተከሰተው ግጭት የሰው ነፍስ የጠፋበት ከሆነ ማጋዎች በሟች ቤተሰቦች ላይ የደረሰውን መሪር ሀዘን የራሳቸው ጉዳይ አድርገው ያዝናሉ፣ሀዘንተኛን ያፅናናሉ፣ ያረጋጋሉ።

ገዳይና ቤተሰቦቹ ደግሞ የሰውን ነፍስ ከማጥፋት ያደረሰ እርኩስ መንፈስ በቤታቸው ስለገባ ባህሉ የሚጥልባቸውን ግዴታ በሙሉ ለመፈፀም ራሳቸውን ያዘጋጃሉ። እንደ Bell

---

[63] ይህን ሀሳብ "ሀገረሰባዊ እምነቶች" በሚል ርዕስ በሰፊው ስለማየው በዚህ ክፍል በጥልቀት አላየውም።
[64] ቀለል ያሉ ግጭቶች ሲባል ማጋዎች በቀላሉ መፍታት የሚችሉና በቤተሰብ፣ በጎሳና በብሄረሰቡ ሰላም ላይ ከባድ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ለማለት ነው። እነዚህ ግጭቶች ግጭት ውስጥ ከገቡት አካላት ውጭ ያሉትን ቤተሰቦችና ጎሳ ወደ ግጭቱ የመጋበዝ ሀይላቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ለእርቅ ውጣ ውረድ አይበዛባቸውም።

(2009:36) አገላለፅ አንድ ሰው ወይም ማህበረሰብ በህይወቱ ውስጥ አደጋ ሲያጋጥመው ወይም አደጋ ሲያደርስ(Life Crises) አደጋውን ለማስወገድ ወይም ከአደጋው ለመንፃት ሶስት የተለያዩ ደረጃዎችን ያልፋል፡፡ እነዚህም ደረጃዎች ከማህበረሰቡ መነጠል ወይም ከቦታው መራቅ(Separation period)፣ ጥፋትን አምኖ መቀበል(Akin to gestation period) እና በባህሉ ውስጥ ያሉ ሂደቶችን በማለፍ አዲስ ሰውነትን መላበስ(In effect, birth of the self) ናቸው፡፡ እነዚህን ተላጣጣቂነትና ተያያዥነት ያላቸው ደረጃዎች ማለፍ የአዲስነትንና የነፃነትን ስሜት ከመፍጠሩም በላይ አጥፊው ብሩህ ተስፋ እንዲኖረው ይረዱታል፡፡ በማረቆ ብሄረሰብም የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው ቤቱን ጥሎ ከአካባቢው በመሰወር፣ ጥፋትን አምኖ በመቀበል የአስታርቂኝ ተማፅኖ ለማጋዎች መላክና የሟች ቤተሰብ በወጪ ማገዝ እንዲሁም የራጋ ማጋን የእርቅ ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ ሟችን በመወከል ለሟች ቤተሰቦች እንደ ልጅ ለመሆንና ወደ ቀደመ ህይወቱ ለመመለስ እነዚህን ደረጃዎች ያልፋል፡፡

በማረቆ ብሄረሰብ አንድ ሰው የሰው ነፍስ ቢያጠፋ ወዲያውኑ ለቤተሰቦቹ ወይም የቅርብ ዘመዶቹ በመሄድ የፈፀመውን ወንጀል ተናግሮ ከአካባቢው ይሰወራል፡፡ ግጭቱ የሚያስከትለው መዘዝ ከባድ በመሆኑ የገዳይ ቤተሰብ ሀዘንና ድንጋጤ ውስጥ ይገባል፡፡ በገዳይ ቤተሰብ ላይ የሚፈጠረው ሀዘንና ድንጋጤ አንድም ከሟች ቤተሰብ ሊደርስ የሚችለውን የበቀል እርምጃ በመፍራት አንድም የብሄረሰቡ ባህል ገዳይ ቤተሰቡንና የቅርብ ዘመዶቹን በመያዝ ቤቱን ዘግቶ እንዲሰደድ ስለሚያዝ የት ልደበቅ የሚለው ጥያቄ ስለሚያስጨንቃቸው ነው፡፡

ገዳይ ቤተሰቦቹንና የቅርብ ዘመዶቹን ይዞ ሲሰደድ ከብቶቹንና ለጊዜው የሚጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች ብቻ ይይዛል፡፡ ገዳይና ቤተሰቦቹ ብዙ እቃ የማያሸሹት ለሟች ቤተሰብ ክብር ለመስጠት እና ማዘናቸውን ለመግለፅ ነው፡፡

የገዳይ አባት ወይም የቅርብ ዘመድ በዕለቱ ቤተሰቡን በሙሉ ከአካባቢው እንዲሰውሩ ካደረገ በኋላ ግጭቱን ያበርዱልኛል ወደሚላቸው ማጋዎች ይሄዳል፡፡ የገዳይ ወገኖች ከማጋዎች እንደደረሱም ባህላችንን ሰብረናል፣ትልቅ ስህተትም ሰርተናል በማለት የተፈፀመውን አደጋ በሀዘን ድባብ ያስረዳሉ፡፡ የተፈጸመውን ወንጀልም ባህላቸውንና ሴራቸውን በመጠበቅ የሟችን ቤተሰብ እንደሚክሱ በመግለፅ የአስታርቁን ተማፅኖ ያቀርባሉ፡፡ የገዳይ ቤተሰብ ጉዳዩን ሲያስረዱ ጀርባቸውን ለማጋዎች በመስጠት ነው፡፡ ይህን የሚያደርጉት አንድም

የተፈፀመው ወንጀል ከባድ መሆኑን ለመግለፅ እንድም የገዳይ ቤተሰብ በሙሉ ሀዘን ውስጥ መሆኑን ለማሳወቅና የበቀል እርምጃ እንዳይኖር አደራውን ለማጋዎች ለመስጠት እንድም የገዳይ ቤተሰቦች ለማጋዎች፣ ለባህላቸውና ለሴራቸው ያላቸውን ክብር ለመግለፅ ነው።[65]

ማጋዎች ከገዳይ ቤተሰብ የመጣላቸውን የአስታርቁኝ ተማጽኖ ወዲያውኑ በመቀበል የገዳይ ቤተሰቦች የሟችን ቤተሰቦች በአጋጣሚ ቢያገኙ እንዲሸሹ መክረው ይሸኟቸዋል። በእለቱ ማጋዎች ወደ ገዳይ ቤተሰቦች ቤት በመሄድ የቤቱን በር በእሾህ ይዘጋሉ። ይህን ሀሳብ ዲንቁላ፡-

> *ገዳይ እንደገደለ እንግዲህ ሽማግሌ የገዳይን ቤተሰብ ቶሎ ብሎ ከአካባቢው እንዲሰውሩ አድርጎ ቤቱን በእሾህ ይዘጋል። የሟች ቤተሰብ ለብቀላ እንዳይነሳሱና ቤቱን እንዳያቃጥሉትም ጭምር ቤቱን ሽማግሌ በሾህ ይዘጋል። ይህ ካልሆነ ብቀላ ሊኖር ይችላል። ሰላም ፈላጊ ሽማግሌ የሟች ቤተሰብን ለማረጋጋት ይኸው ቤት ዘግተናል በሌላ መታየት የለበትም ብሎ ያረጋጋል። የሟች ቤተሰብም ከሀገር እንወጣም ባህል አንሰጥም ብለው የብቀላ ነገር ይተዋሉ (ስክርብ፣37)።*

በማለት ማጋዎች በብሄረሰቡ የሚያከናውኑትን የቁጣ ማብረጃ ስልት ይገልፃሉ።

በማረቆ ብሄረሰብ የገዳይ ቤት በር በእሾህ መዘጋቱ ሁለት ባህላዊ ተመሳሌቶች አሉት። አንደኛው በሟች ቤት የደረሰው ሀዘን በገዳይም ቤት ደርሷል፣ ቤተሰቡም አዝኗል ለማለት ሲሆን ሌላኛው የገዳይ ቤተሰቦች የደረሰውን ችግር በብሄረሰቡ ሴራ መሰረት ለመጨረስ የመፈለጋቸው ምልክት ነው። እሾህ ለገዳይ ቤት ዘብ የቆመ ለሟች ቤተሰብ ደግሞ ባህሉ የጣለው፣ የደነገገው ማህበረሰባዊ ማዕቀብ ነው ማለት ይቻላል።

የብሄረሰቡ ማጋዎች የእርቅ ሂደቱን አንድ ብለው የሚጀምሩት በሟች የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ በመገኘትና ሀዘናቸውን በመግለፅ ነው። ማጋዎቹ በቀብር ስነ-ስርዓቱ ላይ ገዳይን በመወከል የሚያከናውኑትን ተግባር ሀይሉ፡-

> *ማጋዎች በእለቱ ይላኩና ከስር ቅበሩኝ ብሏል፤እኔን ከአስከሬኑ ስር ቅበሩኝ ብሏል እከሌ ብለው የገደለውን ሰው ስም ጠርተው ቀብሩ ሲፈፀም ይጠይቃሉ። እኔን ቅበሩኝ ብሎ ልኳል ተሳስቼ ወንድሜን አጥፍቻለሁ፤የእሱን ሞት እኔ ልሙት ከስሩ ቅበሩኝ ብሏል ይባላል። ይህ ጥያቄ ሲቀርብ የደም ፍላታቸው ይቀዘቅዛል። ሆኖም ግን አሁን ሀዘን ላይ ነን ይላሉ። ምላሽ ለመስጠትም ይቸገራሉ፤ግን የማጥፋት፣የማቃጠል፣የማሳደድ ርምጃውን ያረግበዋል (ስክርብ፣32)።*

በማለት የተፈጠረው ወንጀል ሌሎች ጥፋቶችን እንዳያስከትል የብሄረሰቡ ማጋዎች በሟች ቤተሰቦች ቤት እየተገኙ የደረሰውን የሀዘን ድባብ ይጋራሉ፣ያፅናናሉ። ይህ የማጋዎች

---

[65] *ሀይሉ(ስክርብ፣35)።*

ልመና በብሄረሰቡ ዘንድ የተለመደ ሲሆን ገዳይም ለሟች ቤተሰቦች ያለውን አክብሮት የሚገልፅበት አጋጣሚ ነው፡፡

በብሄረሰቡ ባህል ገዳይ በተለያየ አጋጣሚ ለተጎጂ ቤተሰቦች አክብሮት ያለው መሆኑን ካልገለፀ የተንቀናል ስሜትን ስለሚፈጥር ጠንካራ የብቀላ እርምጃ ይወስዳል፡፡ በዚህም የተነሳ የሰው ነፍስ ያጠፋ የብሄረሰቡ ተወላጅ ከሟች ቤተሰቦች በላይ ሀዘን እንደተሰማው ለመግለፅ በማጋዎች በኩል የተለያ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡

በማረቆ ብሄረሰብ ሟች አርባ ቀን እስኪሞላው ድረስ ቤተሰቡ ሀዘን ላይ ይቀመጣል፡፡ በዚህ የአርባ ቀን ጊዜ ውስጥ ማጋዎች ቤተሰቡን ሲያጽናኑና ሀዘንተኛው የሚስተናገድበትን ቡና፣ ስኳር፣መጠጥና ምግብ በገዳይ በኩል እንዲሟላ ያደርጋሉ፡፡ የሟች ቤተሰብን በተለያዩ ድጋፎች ለማገዝ እንዲረዳም ማጋዎች የገዳይንና የሟችን ቤተሰቦች የሚወክሉና የቅርብ ዝምድና ያላቸውን ሁለት ሰዎች ይመርጣሉ፡፡ በብሄረሰቡ እነዚህ ተወካዮች የጉዳ ዳኞች እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ እንደሀይሉ (ስክርብ፣81) ገለፃ በማረቆዎች የጉዳ ዳኛ ማለት የነገር አባት ማለት ነው፡፡ የጉዳ ዳኞች ዋና ተግባራቸው ከገዳይ ቤተሰብ የሚለኩ የተለያዩ ድጋፎችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተለዋውጦ ማድረስ፣የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች ድንገት መንገድ ላይ ቢገናኙ ብቀላ እንዳይኖ ማርገብና ከማጋዎች ጋር በመሆን የእርቅ ሂደቱን ማፍጠን ነው፡፡ የጉዳ ዳኞች ሁለቱን የደም ሰዎች ከማቀራረብና ለእርቅ እንዲበቁ ከማግባባትም በላይ ሁለቱ አካላት ከታረቁ በኋላ ቢኳረፉ የማስማማት ስራ ይሰራሉ፡፡[66]

በማረቆ ብሄረሰብ 'አይን ደም ይጠራል' ተብሎ ስለሚታመን የገዳይና የሟች ቤተሰቦች እንዲተያዩ አይፈቀድም፡፡ ምንም እንኳ እነዚህ የደም ሰዎች እንዲተያዩ ባይፈቀድም በአጋጣሚ መንገድ ላይ ተገናኝተው ወደ ግጭት እንዳያመሩ የክር ጉዳ ይታሰራል፡፡ የክር ጉዳ የሚታሰረው በሟችና በገዳይ የጉዳ ዳኞች መካከል ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ሀይሉ፡-

> *የክር ጉዳ የሚባል ነገር አለ፡፡ ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ጉዳ ሲሆን በገዳይ ተወካይና በሟች ተወካይ (የጉዳ ዳኞች) መካከል ይታሰራል፡፡ ሁለቱም የጉዳ ዳኞች ከለበሷቸው ጋቢዎች ክሮች ይመዘዙና በእግሮቻቸው ላይ ያስራሉ፡፡ ይህ ከአሁን በኋላ ለመቀራረባቸው ምልክት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ዘመድም መንገድ ላይ ቢተያዩ ለብቀላ አይፈላለጉም እንደ እምነት ነው፡፡ የወጭ ልውውጥም ሲካሄድ ለጉዳ ዳኛው ነው የሚሰጠው (ስክርብ፣35) ፡፡*

በማለት የጉዳ ዳኞቹ የሚፈፅሙትን ቃል ኪዳናዊ ስርዓት ይገልፁታል፡፡

---

[66] *ሀይሉ(ስክርብ፣33)፡፡*

በማረቆ ብሄረሰብ በክር መታሰር ከመገነዝ (ግንዘት) ጋር ያገናኙታል። በክርስትና ሀይማኖት የሚፈጸመው የምንኩስና ስርዓት ሀይማኖታዊ እሳቤ አለም በቃኝ የማለትና ሰዎች ምድራዊና ስጋዊ ፍላጎትን በመተው ሙሉ ትኩረታቸውን ወደ ሰማያዊ ህይወት የሚያዞሩበትና አዲስ የሆነ ህይወት፣ አዲስ መንፈሳዊ ግንኙነት የሚመሰረበት ጊዜ ነው። በማረቆ ብሄረሰብ አባላት ዘንድ የክር ጉዳ ታሰረ ማለት ቂም በቀል ሙሉ በሙሉ ይፋቃል፣ በምትኩ ጥብቅ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነት ይመሰረታል።

ሁለቱ የጉዳ ዳኞች የክር ጉዳ መተሳሰራቸው ራሱን የቻለ ባህላዊ ተምሳሌት አለው። እንደ ሀይሉ (ስክርብ፣36) ገለፃ የክር ጉዳው በተለያየ አጋጣሚ ቤተሰብ ቢገናኝ ብቀላ እንዳይኖር በጉዳ ዳኞች አማካኝነት ቃል ኪዳን መግባታቸውን የሚያሳይ ነው። በብሄረሰቡ ይህን ቃል ኪዳን አፍርሶ የበቀል እርምጃ መውሰድ በልጅ፣ በሀብትና በቀጣይ የዘር ሀረግ ላይ ጥፋት ያመጣል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ሁለቱ የደም ሰዎች በአጋጣሚ ቢገናኙ ችግሮች አይፈጠሩም።[67]

በሁለቱ የጉዳ ዳኞች መካከል ስምምነት የክር ጉዳ ከታሰረና የሟች ቤተሰቦች ለእርቅ ፍቃደኛ ከሆኑ በኋላ በስደት የሚኖሩት የገዳይ ቤተሰቦችና የቅርብ ዘመዶች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ይደረጋል። ይሁን እንጂ ሁለቱ የደም ሰዎች እንዲገናኙ አይፈቀድም። እነዚህ ደም የተቃቡ ቤተሰቦች በጋራ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች በማጋዎችና በጉዳ ዳኞች ውይይት ተለይተው ይሰጧቸዋል። በተለይ አንድን ወንዝ በጋራ የሚጠቀሙና መንገድ የሚያገናኛቸው ከሆነ ሁለቱም ሳይገናኙ የሚጠቀሙበት ዘዴ ይመቻቻል።

የሟችን ቤተሰብ ሲያፅናኑና ሲያረጋጉ የሰነበቱት ማጋዎች የሟችን አርባ መሙላት ካረጋገጡ በኋላ የእርቅ ሂደቱ እንዲጀመር ለቤተሰቡ ጥያቄ ያቀርባሉ። የእርቅ ጥያቄው ከአርባ ቀን በኋላ የሚቀርበው በብሄረሰብ እስከ አርባ ቀን ቤተሰብ ስለሚያዝንና የሩቅ ዘመዶችም እስከ አርባ ቀን ድረስ ለቅሶ ለመድረስ ስለሚመጡ ነው።

በማጋዎች የታረቁልን ጥያቄ የቀረበላቸው የሟች ቤተሰቦችም እርስ በርስ ከተወያዩና ከመከሩ በኋላ የማጋዎችን ሀሳብ በመቀበል ቀጠሮ ይሰጣሉ። የሟች ቤተሰቦች የቀጠሮ ቀን የሚሰጡት አንድም በሀዘናቸው ጊዜ ከጎናቸው ሳይለዩ ሲያረጋጓቸው የነበሩትን ማጋዎች

---

[67] *ሀይሉ(ስክርብ፣33)።*

ለማክበር አንድም ሲደረግላቸው የሰነበተው ድጋፍ ገዳይ ማዘኑንና መጸጸቱን ስለሚያሳይ ነው፡፡[68]

በመጨረሻም በሟች ቤተሰቦች በኩል ያለ አግባብ የወጡ ወጭዎችን በተለይ የህክምናና ሌሎች ተያያዥ ወጭዎችን በሙሉ ገዳይ እንዲከፍል ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች በአግባቡ ከተፈፀሙ በኋላ አጨራረሱን ራጋ ይንገር ተብሎ ጉዳዩ ወደ ራጋ ይመራል፡፡ ይህን አጠቃላይ ሂደት ሀይሉ (ስክርብ፣12) "የመጀመሪያ ሂደት ወጪን የማስመለስ፣ የማገገሚያ፣ የማስከፈል፣ ተበዳይን በእርቅ የማሳመንና ዝግጁ የማድረግ ሂደት የሚከናወነው በማጋዎች ነው፡፡ ማጋዎች ሁሉን ነገር ጨርሰው ካጠናቀቁ በኋላ ራጋ ይንገር፣ ራጋ ይወስን ተብሎ ራጋ ጋር ይኬዳል" በማለት ገልጸውታል፡፡ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመስማት ወደ ራጋው የሚሄዱት ማጋዎች፣ የጉዳ ዳኞች፣ገዳይና የሟች ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የሟች ቤተሰብና ገዳይ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚተያዩት በዚሁ በራጋው ፊት ነው፡፡

ማጋዎች እነዚህን የደም ሰዎች በራጋው ፊት ካቆሙ በኋላ ጉዳዩን በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡ ራጋ ማጋዎች ሁለቱን አባላት እዚህ ደረጃ ለማድረስ ያከናወኗቸውን ተግባራት በጽሞና ካዳመጠ በኋላ የራሱን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

### 4.4.3 የራጋ የእርቅ አፈፃፀም ሂደት

በማረቆ ብሄረሰብ ራጋ የመጨረሻው ሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋም ነው፡፡ በዚህ ተቋም የእርቅ ፍፃሜ የሚያገኙት ከባድ የሆኑ የአካል ማጉደል ወንጀሎችና ግድያ ናቸው፡፡ ማጋዎች በነዚህ ግጭቶች ምክንያት ለበቀል የተዘጋጁ የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጆችን ለእርቅ በማሳመንና በማዘጋጀት የመጨረሻውን የእርቅ አፈፃፀም ለራጋ እንደሚያቀርቡ በ 4.4.2.2 ላይ በሰፊው ለማሳየት ሞክሬያለሁ፡፡

በዚህ ዕሁፍ ራጋ ከማጋዎች የደረሰውን ግጭት እንዴት እንደሚጨርሰው በዝርዝር ይቀርባል፡፡ በዋናነት በብሄረሱ ራጋ የሚከናወነውን ምርመራና ውሳኔ፣ ለእርቅ ማስፈፀሚያነት ስለሚፈፀመው ድግስ፣ የእርድ ዝግጅት፣ እርድና የእርቅ ፍፃሜ የሚሉ ዋና ዋና ጉዳዮች በሰፊው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

---

[68] *ይህ ሀገረሰባዊ ተቋም በመደበኛው ፍርድ ቤት ከሚጣለው የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ስልት ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት አለው ማለት ይቻላል፡፡*

#### 4.4.3.1 በራጋ የሚከናወን ምርመራና ውሳኔ

የማረቆ ብሄረሰብ ራጋ እርቅ የሚጨርሰው የራሱን ምርመራ ከአከናወነ በኋላ ነው። ለማጋዎችና ለጉዳ ዳኞች እንዲሁም በሁለቱ የደም ሰዎች ላይ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ የመመርመር ስልጣን አለው። የእርቁን አጨራረስ ለማስወሰን የጉዳ ዳኖችን፣ ገዳይንና የሟች ቤተሰቦችን ወደ ራጋው የሚወስዱት ማጋዎች ናቸው። ማጋዎች ወደ ራጋው እንደደረሱም ስለግጭቱ አጠቃላይ ሁኔታና ያከናወኑትን ለእርቅ የማሳመንና የማመቻቸት ተግባር በዝርዝር ያስረዳሉ። ይህን ሀሳብ ሀይሉ፡-

> *ራጋው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከሁለቱም ባለጉዳዮች ጋር አብረው የሄዱት ማጋዎች በምን በምን መልኩ እንደጨረሱ ያስረዳሉ። እዚያው ላይ በማጋዎች ያላለቀ ነገር አለ ብሎ ካመነበት ራጋው እንደገና ይመልሳቸዋል። ይህን ይህን ነገር ማጋዎች ጨርሳችሁ መልሳችሁ አምጡ፣ የቀራችሁ ነገር አለ ብሎ ሊመልሳቸው ሁሉ ይችላል። የማጋዎችን ውሳኔና አካሄድ በሙሉ ካመነበት ግን ባለጉዳዮቹ የሚጨርሱበትን ነገር በሙሉ ነግሮ፣ በዚህ በዚህ መልክ እርቁ ይቋጫል ብሎ አፈፃፀሙን ይናገራል(ስክርብ፣18)።*

*በማለት የራጋውን የእርቅ አፈጻጸም ሁኔታ በዝርዝር ይገልጹታል።*

ማጋዎች ያከናወኑት የእርቅ ዝግጅት የአፈጻጸም ችግር ከሌለበት በራጋ ተቀባይነት ያገኛል። ራጋ የማጋዎችን ለእርቅ የማመቻቸት ተግባር ውድቅ የሚያደርገው የአገዳደሉን ሁኔታ ከግምት ያላስገባ ሲሆን ነው። ገዳይ ሟችን ሰባዊነት በጎደለው ጭካኔ የገደለው ከሆነና ማጋዎች እንደማንኛውም ግድያ አይተውት ከሆነ ራጋው ውድቅ ያደረግባቸዋል። ይህ የሚሆነው ራጋው የቅጣት ውሳኔውም[69] ሆነ የእርቅ ሂደት ከባድ መሆን አለበት ብሎ ስለሚያምን ነው።

ራጋው በማጋዎች የተከናወነውን ለእርቅ የማሳመንና የማመቻቸት ተግባር ተገቢ ነው ብሎ ካመነበት ገዳይንና የሟች ቤተሰብን ፊት ለፊት እንዲቀርቡ በማድረግ የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። በራጋው የሚቀርበው ጥያቄ እንደ ምርመራ የሚቆጠር ነው። ይህን ሀሳብ ሀይሉ (ስክርብ፣33) "ራጋው ሁለቱንም ከአሁን በፊት ምን አጥፍተሃል፣ አባትህ ምን አጥፍቷል፣ አያትህስ ብሎ አጣርቶ ጠይቆ አናውቅም ካሉ አጣርተው እንዲመጡ፣ ዘመድን ሁሉ ጠይቀው እንዲያጣሩ ያደርጋል"በማለት ይገልፁታል።

---

[69]*በሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋም የሚሰጠው ቅጣት መጠን መወሰኛ በመደበኛው ፍርድ ቤት ከሚጣለው የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያት ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት አለው።*

በብሄረሰቡ አንድ ደም ያለምክንያት አይመጣም ተብሎ ይታመናል። ይህንንም ሀይሉ(ስክርብ፣33) "በቃ ደም ሌላን ይጨምራል" በማለት ሀሳቡን አጠንክረው ይገልፁታል። ማረቆዎች ደም ሌላን ደም እንዲጠራ የሚያደርገው በርቼ ነው ብለው ያምናሉ። በብሄረሰቡ በርቼ ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ አንዱ ነው። አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሞ መደበቅና በራጋ ማጋ እርቅ አለመጨረስ በቀጣይ የዘር ሀረግ ላይ ትልቅ እዳ እንደማውረስ ይቆጠራል። በአጠቃላይ በዘር ሀረግ ላይ እልቂት የሚያመጣ እርኩስ መንፈስን አይቶና ደብቆ ማለፍ ነው። ግለሰቡም በብሄረሰቡ ይናቃል፣ይጠላል፣ የዘር ሀረጉንም ጭምር ያሰድባል። በዚህም የተነሳ በማረቆዎች በድብቅ የተፈጸመ ወንጀል አይደበቅም።

ከአሁን በፊት በገዳይና በሟች ቤተሰብ መካከል ወይም ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በድብቅ የተፈፀመና በራጋ ማጋ መፍትሄ ያልተሰጠው ወንጀል ከሌለ የሰው ነፍስ አይጠፋም፤ ከባድ የአካል ጉዳት ሊደርስ አይችልም ተብሎ ይታመናል። በዚህም የተነሳ በብሄረሰቡ ራጋ ሁለቱም ወገኖች ላይ ምርመራ ተደርጎና የቆየውን ወንጀል አውጥተው የእርቁ መቋጫ ይነገራቸዋል።[70]

ለገዳይና ለሟች ቤተሰብ በተሰጣቸው የአስራ አምስት ቀን ገደብ ሁሉንም አጣርተው ወደ ራጋው ይመለሳሉ። ሁለቱም ባለጉዳዮች ከቤተሰባቸውና ከዘር ሀረጋቸው ያጣሩትን መረጃ ለራጋው በማስረዳት የመጨረሻውን እርቅ አፈፃፀም ያዳምጣሉ። በዚህ ጊዜ ማጋዎችና የጉዳ ዳኞችም የእርቅ አጨራረሱ አስተባባሪዎች በመሆናቸው ከራጋው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ያደምጣሉ።

#### 4.4.3.2 በገዳይ የሚዘጋጅ የእርቅ ማስፈፀሚያ ድግስ

እንደ Bell (2009:120) እና McCrmick and Kim Kennedy (2011:483) ድግስ (Feast) አንዱ የከበራ አይነት (Rites of feasting) እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህ ስርዓትም በህብረት የሚከወን ሲሆን አጿማትን፣ ስርግን፣ ለቅሶን፣ ደቦን ወዘተ የመሳሰሉ የማህበራዊ ህይወት መስተጋብሮች ምክንያት በማድረግ የሚፈፀም ነው። በዚህም የቡድኖችን ማህበራዊ ግንኙነትና ከአምላክ ጋር የሚኖራቸውን ቁርኝነት በማጠንከር ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ይኖረዋል።

---

[70] *አበጋዝ ጃቢሶ(ስክርብ፣56)።*

ከበራ(Ritual) በባህሪው የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊ መርሆች፣ ልማዶችና የእምነት ስርዓቶች የመቆጣጠርና የመወሰን ሀይል አለው። እንዲሁም የእነዚህን ስርኣቶች ህልውና የማዝለቅና የማህበረሰቡን የጋራ ፍልስፍና፣ አተያይና አስተሳሰብ እና የዕርስ በርስ ተራክቦ ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል (Bell,2009:29)። በማረቆ ብሄረሰብም የድግስ ከበራ ከአካል ማጉደል እስከ ግድያ ለሚደርሱ ግጭቶች እንደ ዋና የእርቅ ማስፈፀሚ በመሆን ያገለግላል። የዚህ የድግስ ከበራ ዋና አላማ ግጭት ውስጥ የገቡትን ቤተሰቦች ዝምድና ለመፍጠርና ወደፊት የሚኖራቸውን የዕርስ በርስ ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው። በከበራው ላይም የብሄረሰቡን እምነት፣ ፍልስፍና፣ አተያይና አስተሳሰብ የሚያመለክቱ ስርኣተ ክዋኔዎች የሚቀርቡ ሲሆን እያንዳንዱ የክዋኔ ሂደትም የተለያዩ ተምሳሌታዊ ፍቺዎች አሉት።

ለእርቅ ማስፈጸሚያነት የሚዘጋጀው ድግስ ሙሉ ወጭ የሚሸፍነው በገዳይ ጎሳና ቤተሰብ ነው። ገዳይ ድግሱን ከጎሳው ወይም ከብሄረሰቡ ለምኖ እንዲያዘጋጅ በራጋ ይታዘዛል። ድግሱ ተለምኖ የሚዘጋጀው እርቁ እንዲፀና ነው።[71] ይህን ሀሳብ ሀጂ ጃተኖ (ስክርብ፣53) 'ከጎሳ ከተለመነ ይባርካል ጥሩ ነው። ቢችልም የአንድ ሰው ገንዘብ ፈርኦ[72] አይጨርስም ይባላል።...የሁሉንም ከጨመረ የአያንቶም[73] ይጨመራል፣ የልጃገረድም ይጨመራል፣ የዘመድ ሁሉ ከመጣ መዳኒት ይሆናል፤ ለእርቅ መዳኒት ነው' በማለት የብሄረሰቡን እምነታዊ የህይወት ፍልስፍና ይገልፁታል። በድግሱ ላይ ማንና ምን ያህል ሰዎች መሳተፍ እንዳለባቸው ራጋው ይወስናል። በድግሱ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች ብዛት የሚወሰነው በተፈፀመው ወንጀል ክብደትና ቅለት መነሻነት ሲሆን ከአስር እስከ አርባ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

የድግስ ከበራው በምሽት ተጀምሮ ንጋት ላይ የሚጠናቀቅ በመሆኑ ብሄረሰቡ "የአዳር ድግስ" በማለት ይጠሩታል። ከበራው በምሽት(በጨለማ) የሆነበት ምክንያት የደም ሰዎች ቀን ቢተያዩ ግጭቶች ሊቀሰቀሱ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው። ብሄረሰቡ ይህን እምነቱን "አይን ደም ይጠራል" በሚለው አባባሉ ያጠነክረዋል።[74] በዚህም የተነሳ የሟች ቤተሰቦች ወደ ገዳይ ቤት የሚሄዱት በምሽት ነው። እነዚህ እንግዶች አስቀድሞ በገዳይ ሰፈር

---

[71] *ሀይሉ(ስክርብ፣36)።*
[72] *ፈርኦ ማለት ቂም ማለት ነው።*
[73] *አያንቶ ማለት ትልቅ የሀገር ሽማግሌ ማለት ነው።*
[74] *ሀይሉ(ስክርብ፣15፣36፣57)።*

መድረሳቸው ሲታወቅ የጉዳ ዳኞች ይቀበሏቸዋል፡፡ የጉዳ ዳኞቹም እንግዶቹን በመያዝ ወደ ገዳይ ቤት ይወስዷቸዋል፡፡ የሟች ቤተሰቦችም ፊታቸውንና ራሳቸውን በመከናነብ ወደ በሩ ይጠጋሉ፡፡

የሟች ቤተሰቦች ወደ ገዳይ ቤት ከመግባታቸው በፊት ከሁለቱም የደም ሰዎች የተወከሉ የማር ጠጅ የያዙ ሁለት ልጃገረዶች ከቤቱ ግራና ቀኝ በኩል በመቆም እንግዶችን ይቀበላሉ፡፡ በብሄረሰቡ ሁለት ልጃገረዶች በእርቅ ስርአቱ ላይ የሚሳተፉበት የራሱ ባህላዊ ተምሳሌት አለው፡፡ ይህም ሀሳብ ዲንቁላ (ስክርብ፣35) "በእርቁ ላይ ሁለት ልጃገረዶች የሆኑበት ምክንያት ሴት ልጅ በኛ ማህበረሰብ በጣም ክብር ነች፡፡ ደግሞም ልጃገረድ ነች፣ ንፁህ ነች እና ይህ በጣም ይታመናል" በማለት የልጃገረዶቹን ተሳትፎ ከንፅህናና ከርህራሄ ጋር አገናኝተው ገልፀውታል፡፡ ብሄረሰቡ የልጃገረዶቹ በራጋ ማጋ የእርቅ ሂደት ላይ የሚኖራቸውን ሚና ከድንግልናቸው ጋር ይገናኛል፡፡

ድንግልና በተለያዩ ባህሎች ዘንድ የተለያዩ ውክልናዎችን የሚሸከም ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድንግልና ለልጃገረዷ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰብ ሰፋ ሲልም ለቤተ-ዘመድ የክብር መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከድንግልና ጋር በተያያዘ ጥናት የሰሩ ምሁራንም ይህንኑ አመክንዮ አቅርበዋል፡፡ በተለይ *Chen (2010:75)"When female virginity becomes a matter of life and death, a warranty of family honor and fortune, and a cornerstone of public morality and welfare"* በማለት አብራርተውታል፡፡

የድንግልናን ፅንሰ ሀሳብ ከጅማሮው ከስጋዊ ተራክቦ በመቆጠብ አካላዊ ንፅህናን ይዞ ከመቆየት ጋር ይገናኛል፡፡ ይህን ሀሳብ Chen (2010:78)" The concept of virginity is first and foremost associated with sexual innocence and bodily purity" በማለት ይገልፁታል፡፡ በማረቆ ብሄረሰብም ልጃገረዶች ንፁህና የጭካኔ መንፈስ የሌላቸው ፍጡሮች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን በራጋ ማጋ የእርቅ ሂደት ላይ ይሳተፋሉ፡፡

በማረቆ ብሄረሰብ የራጋ ማጋ እርቅ አጀማመር ላይ የሚሳተፉት ሁለት ልጃገረዶች ከገዳይ ቤት በር ግራና ቀኝ[75] መቆማቸውም የራሱ ፍቺ አለው፡፡ በብሄረሰቡ ገዳይ የሰው ነፍስ እንዲያጠፋ የሚያደርገው እርኩስ መንፈስ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በብሄረሰቡ እርኩስ መንፈስ በግራ ይመሰላል፡፡ ይህን ውክልና ለማመላከት ሲባል የገዳይን ቤተሰብ የወከለችው

---

[75] *ዲንቁላ(ስክርብ፣34)፡፡*

ልጃገረድ ከገዳይ ቤት በር በስተግራ በኩል እንድትቆም ይደረጋል፡፡ የሟችን ንፅህና ለማመላከትም ከሟች ቤተሰብ የተወከለችው ልጃገረድ ደግሞ ከበሩ በቀኝ በኩል ትቆማለች፡፡

የሟች ቤተሰቦች ከገዳይ ቤት በር ላይ እንደደረሱ ልጃገረዶቹ በአፋቸው የያዙትን የማር ጠጅ «ቱፍ ቱፍ» እያሉ ይረጩባቸዋል፡፡ ይህን ሀሳብ ኢማም (ስክርብ፣81) "ማታ ሰዎቹ ወደ ቤት ሲገቡ በሩ ላይ ሁለቱ ልጃገረዶች የማር ጠጅ በአፋቸው ይዘው ይብረድ፣ይቀዝቅዝ እያሉ "ቱፍ ቱፍ" ይላሉ ተከናንበው ከሚገቡት ሰዎች ላይ አዎ እንደዚህ ነው" በማለት ይገልፁታል፡፡

በድግሱ ላይ የሚሳተፉት የሟች ቤተሰቦች ወደ ቤት ሲገቡ መብራት እንዲጠፋ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ተጋባዥ የደም ሰዎች በጭለማ በማጋዎችና በጉዳ ዳኞች እየተመሩ በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ሁለቱ የደም ሰዎች ተረጋግተው ከተቀመጡ በኋላ የብሄረሰቡ ራጋ ንግግር ያደርጋል፡፡ እንደ ዲንቁላ (ስክርብ፣34) ገለጻ ራጋው የእርቅ ሂደቱ መጀመሩንና ነገር ለማብረድ መሰባሰባቸውን በመግለፅ ቂምና ቁርሾ እንዲያቆሙ ምክር ይለግሳል፡፡ በዚህም የተነሳ በድግሱ ላይ ጭፈራም ሆነ ሽለላ አይከናወንም፤ አይታሰብምም፡፡ የዚህን ምክንያት ሀይሉ (ስክርብ፣15) "...በድግሱም ላይ እንደነዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው ሰዎች አይደሉም የሚጋበዙት፡፡...ባለፈው ጉዳት በማድረሱ ተፀፅቶ ነው ጉዳት አድራሹ ድግሱን የሚደግሰው" በማለት ይገልፁታል፡፡ ይህ ሲባል ግን በድግሱ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች የሀዘን ስሜት እንዲታይባቸው አይፈለግም፡፡ በዚህ ድግስ ላይ የሚኖረው አጠቃላይ ድባብ ሟችን እንዲያስታውስ አይፈቀድም፡፡

የራጋው ምክርና ማሳሰቢያ ከተጠናቀቀ በኋላ ራጋው ሁለቱንም የደም ሰዎች የማር ጠጅ[76] ያቃምሳቸዋል፡፡ ይህን የማር ጠጅ የማቃመስ ስርአት በተመለከተ የብሄረሰቡ የሀገር ሽማግሌዎች ተወካይ ኢማም (ስክርብ፣81) "ቤት ውስጥ መብራት እንደጠፋ የማር ጠጅ በትልቅ ገበታ ተይዞ በጨለማ አንገት ለአንገት ተያይዘው ዋና ዋናዎቹ ሰዎች በአንድ ላይ ከዚያ ጠጅ ይቀምሳሉ" በማለት ይገልጹታል፡፡

---

[76] ማር በማረቆ ብሄረሰብ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ብሄረሰቦች የእርቅ ሂደትም ጉልህ የሆነ አስተዋፅዎ አለው፡፡ እንደ ብርሀን(2002፣86) እንዳብራራው በወግዲና ቦረና ወረዳዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች ያጋጠማቸውን የግድያ ወንጀል ለመፍታት ማርን ይጠቀማሉ፡፡ በማህበረሰቡ ገዳይና የገዳይ ቤተሰብ ሲታረቁ ማር የተቀባን ዳቦ ይጎራረሳሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በራጋ ማጋ የግድያ ግጭት አፈታት ሂደት የሌሊት ድግስ ላይ ሁለቱ የደም ሰዎች አይን ለአይን ከመተያየታቸው በፊት በማር የተበጠበጠ ጠጅ በራጋው አማካኝነት እንዲቀምሱ ይደረጋል፡፡

በብሄረሰቡ እነዚህ የደም ሰዎች በአንድ ገበታ ማር የሚቀምሱበት የራሱ ባህላዊ ተምሳሌት አለው፡፡ የማር ጠጅ መቅመሳቸው አንድም በብሄረሰቡ ማር የነገር ማብረጃ ነው ተብሎ ስለሚታመን ግጭቱን ቶሎ ለማብረድ፣ አንድም የሁለቱን የደም ሰዎች ውህደት፣ ጥምረት የሚያመላክት ቃል ኪዳን ነው፡፡ ይህን የራጋ እርቅ አፈፃፀም ሀጅ ጃተኖ የሚከተለውን አብነት በማቅረብ ያጠናክሩታል፡-

### አብነት አምስት

*አንድ ሰው በኡልቾ የአዝማ ገናሞ ልጅ ሁለቱን ሰዎች በሬ ለመፈለግ ይሄዱና ያደሩ ሰዎችን ደረበና ገደለ በጥይት፡፡ የአዝማ ገናሞ ልጅ መኮንን ገናሞ ደረበ አቢጋዝ ሸነምና አንድ ማን ኡስማን ነው ማን የሚባል ሰውዬ ደረበና ገደለ፤አስታረቅና እኔ ነኝ እኮ የሄድኩት አዝማ ካሳሞም አሉ፡፡ ሄድኩና አስታረኩ በምን በአምስተኛ አመት ለምኜ እምቢ ብሎ ድርቅ ብሎ ሰውዬው ለምኜ አስታረኩ፡፡ እስከዚህ ጊዜ ጠፍተው አካባቢውን ለቀው ቆዩ? አዎ ያኔ ወይኒ ቤቱን ሰብሮ ወጣ ወይኒ ቤቱ እንደዚህ በድንጋይ አልተሰራም እንደ አሁኑ፡፡ ሰብሮ ሲወጣ ሁሉም ሸፈተ ወጣ፡፡ ሸፈተና ለመነ እኛ በአምስተኛ ዓመት አስታረቅን፡፡ ስናስታርቅ 20ሺ ብር ነገሩን ወጭውን ዝም ብለን 6ሺ ከሁለት መቶ ሰጠን፡፡ በቃ ማር በጥብጦ ደግሶ ስንጋ አርዶ ለክርስቲያን በተለይ ለሙስሊም በተለይ አርዶ ማር የሁለቱም ደም ሰው የሁለቱን ወገን ስምንት ወገኖቹን የአንዱ አራት የአንዱ አራት ገቡ አስታረቅን ጥቁር አረድን ማታ እንዳልኩህ እኔ በእጄ በእኔ እጅ ይህንንም ይህንንም ለሁሉም አቃምሼ ሁሉንም ቱፍ ቱፍ አባብዬ በቃ ኩራዝ በርቶ ሲበሉ ሲጠጡ አደሩና ሲነጋ ውጭ ወጥቶ ጥቁር የገዳይ ቤተሰብ አርዶ አስታረቅን በቃ በነጣ አሁን ቤተሰብ ሆነዋል፤ የቅርብ ሰዎች፡፡ እየተባበሩ ይኖራሉ?ለቅሶም ይነገራል ይመጣል ይገናኛሉ(ስክርብ፣43)፡፡*

ሀጅ ጃተኖ ካቀረቡት አብነት በተጨማሪ ሀሳቡን ዲንቁላ ቧጉ ይጋሩታል፡፡ ይህንንም ሀሳብ አብነት ጠቅሰው ሲያስረዱ፡-

### አብነት ስድስት

*ሰው ተገዳድሎ ነበር፡፡ ብዙአየሁ ሙርኪን የሆነ መኪና ገጭቶ ገድሎ በሀገር ባህል የጨረስንበት ሁኔታ አለ፡፡ መጀመሪያ እርቅ ይዘን ከተመላለስን እና እርቅ ከሰጡን በኋላ የሀገር ሽማግሌዎች ወጭውን አስከፍለን፡፡ ወጭ መጀመሪያ ይከፈላል፡፡ እንዲያውም በማረቆ ሴራ የተወሰነው ወጭ ከበድ ያለ ነው፤ አስራ አምስት ሺህ ብር ነው፡፡ እሱን ከፍሏል ከእርቁ በፊት፡፡ ወጪ ተከፍሎ ነው የሚታረቁት፡፡ ይህን ካስከፈልን በኋላ እርቅ ጀምርን፡፡ ስንጀምር ውር ከፊን የሚባል ነገር አለ፡፡ ለእናትየዋ የምትታጠቅበት መቀነት ይገዛል፣ በድሮው ብልኮ ነበር አሁን ብርድ ልብስ ነው እሱንም ገዛ፡፡ ኧ…ለኮርማ የደረሰች ጊደርም ገዝቶ አመጣ፡፡ ሁሉን ነገር ሰቶ ታረቁ፡፡ ገዳዩ ኦሮሞ ነው የታረቀው ግን በማረቆ ሴራ ነው፡፡ አሁን በሰላም ወተው ይገባሉ፡፡*

ሁለቱ የደም ሰዎች በራጋው አማካኝነት ማር በአንድ ገበታ ከቀመሱ በኋላ መብራት ይበራል፡፡ ዋናው የምግብና መጠጥ መስተንግዶ የሚጀመረው የማር ማቃመሱ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ነው፡፡ በዚህ የአዳር ዝግጅት ራጋ፣ ማጋዎች፣ የጉዳ ዳኞች እንዲሁም የገዳይና የሟች ቤተሰቦች በአንድ ላይ በመሆን እየበሉና እየጠጡ ያድራሉ፡፡ በዝግጅቱ ላይ

የሚታደሙት ሁሉም ሰዎች ሟችን በተመለከተ ምንም አይነት ሀሳብ እንዲሰነዝሩ አይፈቀድም። የሟችም ሆነ የገዳይ ቤተሰቦች ወደፊት በሚኖራቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው ይጨዋወታሉ። በአዳር ዝግጅቱ ላይ ሟች የማይነሳው በሟች ቤተሰቦች ላይ የሀዘን ስሜት እንዳይፈጠርባቸው ነው። በዚሁ የአዳር ድግስ ስርዓት ገዳይ በጉዳ ዳኞች፣ በማጋዎችና በራጋ ፊት የሟች ምትክ ተደርጎ ስለተሰጠ ሁሉም የድግሱ ተካፋዮች በሚኖራቸው ግንኙነትና ዝምድና ብቻ እያነሱ በመጫዎት የአዳር ዝግጅቱን ያጠናቅቃሉ።

### 4.4.3.3 የእርድ ዝግጅት እርድና የእርቅ ፍፃሜ

> *Just as social groups and social life constitute the complex in which individuals acquire and use folklore, the life history of an individual and the structure and evaluation of an individual's repertoire represent important contextual frameworks for understanding the place of folklore in human life (Bauman,1983:365).*

እንደ Bauman ገለፃ ፎክሎር በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ ሰፊ ድርሻ አለው። ይህ የፎክሎር ሚና የማህበራዊ ቡድኖችንና ግለሰቦችን ማህበራዊ ህይወት ለማወቅም ያስችላል። ይህም የጥናት ዘርፉ በአውድ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ሲጠናና ሲተረጎም በሰው ልጆች የህይወት ምዕራፍ ላይ ያለውን አስተዋፅዖ ለመገንዘብ ይረዳል።

በፎክሎር የጥናት መስክ ክዋኔ ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ ዋናው ነው። አንድን ፎክሎራዊ አሀድ በአውዱና በክዋኔው ላይ ተመስርቶ ማጥናት በእንቅስቃሴና እውነተኛ ስሜትን ለማየት ስለሚያግዝ ጠቀሜታው ጉልህ ነው።

በማረቆዎች የራጋ ማጋ ስርዓት ላይ ክዋኔ ቦታ አለው። በተለይ በብሄረሰቡ የግድያና የአካል ማጉደል ግጭቶች እርቅ የራሱ ክዋኔ አለው። በብሄረሰቡ እነዚህ ግጭቶች ፍፃሜ የሚያገኙት የእርድ ክዋኔን በመፈፀም ነው። ብሄረሰቡ ጥቁር ፍየል [77]በማረድ ለግጭት

---

[77]በብዙዎቹ የሀገራችን ብሄረሰቦች ባህል ጥቁር የሰይጣንና የእርኩስ መንፈስ አምሳያ ተደርጎ ይቆጠራል። ሰዎችን ለጥል የሚያበቃውም ይህ እርኩስ መንፈስ ነው ብለው ስለሚያምኑ በእርቅ ሂደታቸው ላይ ጥቁር እንስሳ በማርከሻነት ይታረዳል። እንደ ብርሀን (2002፣86) በወግዲና በቦረና የደም ሰዎች የሚታረቁት መውሰድ ያቆመች ጥቁር በግ በማረድ ነው። ከጥቁሯ በግ የሚገኘው ስጋም ሆነ ቆዳ እርኩስ መንንፈስ አርፎበታል ስለሚባል አገልግሎት አይሰጥም። ለእርድ የቀረበችው በግ ከመሆኗ ውጭ ከማረቆ ብሄረሰብ ባህል ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት አለው።

የሚያበቃውን እርኩስ መንፈስ መቅበርና ዘለቄታዊ መፍትሄ መስጠት ሲቻል ነው ብሎ ያምናል።

የእርዱን ስርዓተ ክዋኔ ለመፈፀምም በገዳይ ቤት ሲበላና ሲጠጣ ያደረው የሟች ቤተሰብ፣ ገዳይና ቤተሰቦቹ፣ ማጋዎች፣ የጉዳ ዳኞችና ራጋ በጧት የእርድ ስርዓቱን ለማከናወን ከገዳይ ቤት ይወጣሉ። እነዚህ ሰዎች ጧት ከገዳይ ቤት ሲወጡ ምግብም ሆነ መጠጥ አይቀምሱም። ይህ የሆነበት ምክንያት ገዳይ በእርቁ ላይ ለሚቀርብለት ጥያቄ ሳይደብቅ እንዲናገር ነው። በብሄረሰቡ ምግብ ከተበላ በኋላ ምርመራ ማከናወን ለጥልና ለቂም በቀል የሚያበቃው እርኩስ መንፈስ እንዲደበቅ ያደርገዋል ተብሎ ያታመናል።

እንደ Bauman (1983፡363) ገለፃ የአንድን ፎክሎር አሀድ ባህላዊ ትርጉም ለማወቅ በራሱ በባህሉ ውስጥ ባሉ የአተረጓጎም እይታዎች ላይ መመርኮዝ ያስፈልጋል። የባህሉ ባለቤቶች ያላቸው የሕይወት ፍልስፍና በፎክሎሩ ውስጥ በምን መልኩ እንደተወከለና እንዴት እንደተላለፈ ማየት ተገቢ ነው። በማረቆ ብሄረሰብ የእርቅ ሂደት ላይ የሚፈፀሙ ባህላዊ እሳቤዎችም ትርጓሜያቸው ካላቸው የህይወት ፍልስፍናና አተያይ አንፃር የሚታዩ ናቸው።

በእርቅ ስርዓቱ ላይ ለመሳተፍ በገዳይ ቤት ያደሩት ሰዎች ከቤት ሲወጡ ወደ ቀኝ አቅጣጫ ነው። ከቤት የሚወጣው ተጋባዥ እንግዳ የሟች ቤተሰብ፣ ማጋዎች፣ ራጋና የጉዳ ዳኞች በሙሉ መልካም ቀን እዲሆን ይመኛሉ።[78] ይህን ሀሳብ ኢማም (ስክርብ፣76) "መጀመሪያ ወደ ቀኝ ሲወጣ ዛሬ ቀኝ ይሁን፣ ቀኑ ቀኝ ያድርግልን፣ ቀኑ ይበጅልን እያለ እየለመነ ይወጣል አዎ እንደ ሙዚቃ ነው እየተባለ የሚወጣው" በማለት ስርዓቱን ይገልፁታል።

በማረቆ ብሄረሰብ ቀኝ የመልካም አጋጣሚ ተምሳሌት ሲሆን ግራ ደግሞ እርኩስ መንፈስን ይወክላል። ለዚህም ነው ብሄረሰቡ እርቅን ከገዳይ ቤት በቀኝ በኩል የሚጀምረው። ማረቆዎች ስለ ቀኝ ያላቸውን ግንዛቤና እምነት በተመለከተ ኢማም፦

> *ከቤት ያደረው ሰው ሁሉ ወደ ቀኝ በኩል ከቤቱ የሚወጣውና የሚቀመጠው ነገሩ ሁሉ ቀኝ፣ ጥሩና የተቃና ነገር እንዲያጋጥም፣ ሁሉም ነገር እንዲበጅ ነው። ወደ ግራ በኩል ከወጡ ነገሩ ሁሉ አይበጅም፣ይበላሻል፣ግራ ግራ ነው ቀኝ ግን ጥሩ ነው ቀኝ ነው። ስለዚህ ወደ ቀኝ በኩል ነው ሰው የሚወጣውም የሚቀመጠውም። ቀኝ ማለት ጥሩ ነገር ነው፣ በቀኝ የሆነ ነገር ሁሉ ውጤት ያመጣል ስለሚባል ነው። ሽማግሌ በቀኝ በኩል ተቀምጦ ነገርን ጨርሶ፣ ክፉ ነገር በቀኝ በኩል ሲሆን ይወጣል። ነገር በግራ በኩል ከተያዘ አይወጣም፣ ይደበቃል ተብሎ ይታመናል (ስክርብ፣76) በማለት ገልፀውታል።*

---

[78] *ኢማም(ስክርብ፣76) እና አበጋዝ ጃቢሶ(ስክርብ፣76)።*

ይህ ሀገረሰባዊ እምነት በሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ የቀኝና የግራ ጽንሰ ሀሳብ በእርድ ጊዜም የብሄረሰቡን የመልካም አጋጣሚና የእርኩስ መንፈስ ውክልና ይይዛሉ፡፡

የሰው ልጆች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችና አደጋዎች የሚጋራ አንዳንዴም ከገቡበት ጭንቅ የሚያወጣ አንዳች ሀይል ይፈልጋሉ፡፡ ይህን ጭንቀት ያስወግዳል ለሚባለው ሀይልም የተለያዩ መስዕዋቶች ይቀርባሉ፡፡ ለመስዋትነት የሚቀርቡት ደግሞ እንስሳት ናቸው፡፡ እንደ Bell (2009፡35) ገለፃ የሰው ልጆችና እንስሳት በአምላክ (god) ከፍተኛ ቦታ የተሰጣቸውና የተፈጠሩ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ እንስሳትን ለመስዋትነት ማቅረብ አምላክ (god) ለሰው ልጅ ላደረገው ውለታ መታሰቢነት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

በማረቆ ብሄረሰብም ለእርቅ መቋጫነት የሚታረደው ጥቁር ፍየል ለእርኩስ መንፈስ ማስወገጃነት ታስቦ በመስዋትነት የሚቀርብ ነው፡፡ መንፈሱ መስዋት ካልቀረበለት በገዳይ ላይ የሰፈረው የግድያና የደም መንፈስ አይለቀውም እንደማለትም ነው፡፡

ለእርቅ ማስፈፀሚያነት የሚከናወነው እርድ የራሱ ስርዓታዊ አፈፃፀምና ቅድመ ዝግጅት አለው፡፡ የጉዳ ዳኞች፣ ገዳይ፣ የገዳይ ቤተሰብ፣ ማጋዎችና ራጋ እርድ በሚከናወንበት ቦታ ከተገኙ በኋላ ገዳይ ጥቁር ፍየል እንዲያቀርብ ይጠየቃል፡፡ ቀደም ብሎ ያዘጋጀውን ጥቁር ፍየልም ለጉዳ ዳኞች ያቀርባል፡፡

የጉዳ ዳኞችም ስርዓቱን በመጠበቅ ፍየሉን ያርዱታል፡፡ ጥቁሩ ፍየል ከተባረከ በኋላ 'ሆዱ ይቀድና' አንጀቱ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ይህን እርድ የሚፈፅሙት የጉዳ ዳኞች ሲሆኑ ገዳይና የገዳይ ቤተሰቦች እንዲሁም የሟች ቤተሰቦች በሙሉ ቆመው የእርድ ስርዓቱን ይከታተላሉ፡፡ የብሄረሰቡ ማጋዎች እርድ እንዲከናወን ከማስተባበር ያለፈ ሚና የላቸውም፡፡ ራጋው ግን የሚከናወነውን ስርዓት የመምራት ሀላፊነት አለበት፡፡

የደም መቋጫ እርድ በሌሎች አጋጣሚዎች ከሚታረደው የእርድ ሂደት ጋር አይመሳሰልም፡፡ እርዱ የእርኩስ መንፈስ ማስወገጃ ነው ተብሎ ስለሚታመን አይከበርም፤ ምንም አይነት የፀሎት ስርዓት አይከናወንም፡፡ ስጋውም ሆነ ቆዳው እርኩስ ስለሆነ አይፈለግም፡፡ ይህንንም ሀሳብ የብሄረሰቡ ማጋ የሆኑት አበጋዝ ሙርኪ ( ስክርብ፣79) 'የቁም ነገር ስልቻ ለየብቻ' በማለት ብሄረሰቡ ለእርዱ ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት በሀገርኛ አባባል ገልፀውታል፡፡

በብሄረሰቡ ለእርቅ መቋጫነት የሚመረጠው ጥቁር ፍየል ሲሆን የራሱ ተምሳሌታዊ ፍቺ አለው፡፡ ማረቆዎች ጥቁር ፍየል የሰይጣን፣ የጨለማና የጥፋት ተምሳሌት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ሀይሉ (ስክርብ፣53) "ያ ጥቁሩ የጥፋት ነው፤ የጨለማ ነው፤ ቂም ቁርሾ ከዚህ ጥቁር ነገር ጋር ይቀበር ነው" በማለት ጥቁር ፍየል በብሄረሰቡ የተሰጠውን ባህላዊ ውክልና ይገልፁታል፡፡[79]

ማንኛውም ፎክሎራዊ ጉዳዊ የራሱ የሁነት ቅደም ተከተል ያለው ሲሆን ማህበረሰቡም ድርጊቶቹን የሚያቀናጅበት ስምምነታዊ የሆነ ህግ አላቸው፡፡ ይህን ሀሳብ Bauman (1983:365) ፦

> *The structure of folkloric events is a product of the interplay of numerous situational factors, including physical setting, participates' identities and roles, cultural ground rules for performance, norms of interaction and interpretation, and the sequence of actions, making up the conventional scenario of the event it self as a cultural scene.*

በማረቆ ብሄረሰብ ግጭት ውስጥ የገቡ ግለሰቦችን የሚያቀራርቡ የጉዳ ዳኞች የሁለቱም የደም ሰዎች ተወካይ በመሆናቸው የእርድ ስርዓቱን የሚፈፅሙት በእርቁ ተሳታፊዎች ፊት ነው፡፡ ይህን ስርዓት አበጋዝ ሙርኪ፦

> *አንድ ዳኛ በዚህ አንዱ ዳኛ በዚያ ይሆናል፤ አንዱ ያርዳል፡፡ ሲያርድ ክፉ የሰራ እንዲህ ይታረድ ይላል፡፡ አንዱ ደግሞ ሆዱን ይሰነጥቃል፤ ይህን ጉዳ የጣሰ፣ ይህን ጉዳ ያፈረሰ ሆዱ እንዲህ ይሰንጠቅ ይልና ሆዱን ይሰነጥቃል፡፡ ሌላኛው የጉዳ ዳኛ ደግሞ አንጀቱን ስቦ እያወጣ ጉዳን የጣሰ አንጀቱ እንዲህ ይበጠስ ሲል አንጀቱን ስቦና በጥሶ ያወጣል፡፡ ከዚያ በኋላ አንጀቱን መሬት ላይ ያስቀምጣል (ስክርብ፣79) በማለት ገልፀውታል፡፡*

ይህ የእርድ ስርዓተ ክዋኔ በሚፈፀምበት ጊዜ የሁለቱም ቤተሰብ አባላት የሚከናወነውን የእርቅ አፈፃፀም ትኩረት ሰጥቶ ይከታተላል፡፡ ሌላኛው የጉዳ ዳኛ ደግሞ መሬት ላይ የተቀመጠውን አንጀት በማንሳት ከሴት ውጭ ያሉትን የደም ሰዎች የእግራቸውን አውራ ጣት ያስራል፡፡ በመጀመሪያ የሚታሰረው የገዳይ ወገን ሲሆን ራጋውም እነዚህ የደም ሰዎች የሚታሰሩበትን ምክንያት ለጉዳ ዳኞች በጥያቄ መልክ ያቀርባል፡፡ የጉዳ ዳኞች በራጋ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ ቤተሰቡን በመወከል ይመልሳሉ፡፡ ይህንን በአንጀት የማሰር ስርዓት አበጋዝ ሙርኪ(ስክርብ፣79) "ጉዳውን ያፈረሰ ዘሩ በሙሉ እንዲህ ይታሰር፤ እንዲህ

[79] ሀይሉ(ስክርብ፣34)፡፡

ይታሰር እያለ አጎትም፣ ዘሩም ጨምሮ እዚያ ቦታ የተገኙ በሙሉ ይታሰራል" በማለት ይገልፁታል፡፡

ሁሉም የደም ሰዎች በረድፍ ከታሰሩ በኋላ የሚከናወነው ስርዓት አንጀቱን መቁረጥ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የታሰሩበትን አንጀት መቁረጥ የሚችለው ሌላኛው የጉዳ ዳኛ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አውራ ጣታቸውን ያሰረው የጉዳ ዳኛ ተመልካች ይሆናል፡፡ ራጋው የጉዳ ዳኞች ለሚያከናውኑት ተግባር በሙሉ ጥያቄ ያቀርብላቸዋል፡፡ ይህን ስርዓት የሚፈፅሙት የጉዳ ዳኞች የሚጠየቁትን ጥያቄ እየመለሱ ነው፡፡

በአንጀት መቁረጥ ስርዓቱ ላይ ያለውን ሂደት በተመለከተ አበጋዝ ሙርኪ (ስክርብ፣79) "ሌላኛው የጉዳ ዳኛ ደግሞ የታሰሩበትን አንጀት ይቆርጣል፤ ይህን ጉዳ ያፈረሰ፣ ይህን ጉዳ የጣሰ ዘሩም ቢሆን፣ራሱም ቢሆን እንዲህ ይቆረጥ ብሎ ይቆረጣል" በማለት የሚከናወነው እያንዳንዱ የጉዳ ዳኞች ተግባር ከእርግማን ጋር የተገናኘ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በእርዱ ላይ የጉዳ ዳኞች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በሙሉ እርግማናዊ ይዘት የተላበሱ ይሁኑ እንጅ የቃል ኪዳን ስርአቶች ናቸው፡፡ በእርቁ ላይ የሚሳተፉት ቤተሰቦችም እርግማኑ ይመጣብናል በሚል እምነት[ፍራቻ ሊባል ይችላል] ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ እርቁ የጸናና ለትውልድም የሚተላለፍ ቃል ኪዳን ይሆናል፡፡

ሰዎቹ የታሰሩበት አንጀት ከአውራ ጣታቸው ላይ ከተቆረጠ በኋላ ሌላኛው የጉዳ ዳኛ አንጀቱንና አንጀቱ የተቆረጠበትን ቢለዋ ወይም ምላጭ በአንድ ላይ በመሰብሰብ ለመቅበር ወደ ዛፍ ስር ይሄዳል፡፡ በእርድ ጊዜ ከአንጀቱ ጋር የተነካኩ ሌሎች እቃዎችም ጭምር የሚቀበሩት ዛፍ ስር ነው፡፡ ይህ የእርቅ መቋጫ አንጀት ዛፍ ስር ከተቀበረ በኋላ ዛፉን መንካት፣ ከዛፉ ስር ማስታረቅ፣ ዛፉን ለቤት መስሪያም ሆነ ለማገዶ መጠቀም አይቻልም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በብሄረሰቡ ዛፉ ሰይጣን የተቀበረበት፣ እርኩስ መንፈስ የተጠጋበት ስለሆነ ዛፉን ስንጠቀም የግጭት መንፈሱ ወደ ቤታችን ይመጣል ተብሎ ስለሚፈራ ነው፡፡[80]

የፍየሉ አንጀትና በእርዱ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች ሲቀበሩ የጉዳ ዳኞቹ ሚና የጎላ ነው፡፡ ለመቅበሪያ የሚያገለግለውን ጉድጓድ የሚቆፍሩትም፣ አንጀቱንና ቁሳቁሶቹን የሚቀብሩት የጉዳ ዳኞቹ ናቸው፡፡ ይህን የአቀባበር ስርአት አበጋዝ ሙርኪ ጠቅለል አድርገው ሲገልፁ፡-

---

[80] *አቢጋዝ ጃቢቦ (ስክርብ፣77)፡፡*

*አንዱ ሽማግሌ ይቆፍራል በዚህ ጊዜ አንዱ ለምንድን ነው ይህን የምትቆፍረው ይላል ይህን ጉዳ የጣሰ ራሱም ዘሩም የሚቀበርበት መቃብር ነው የምምሰው እያለ ይምሳል። ሌላኛው ሽማግሌ አፈር ያወጣል። ሌላኛው ደግሞ አንጀቱንና ቢላዋውን ወይም ምላጩን ይቀብራል ይህን ጉዳ ያፈረሰ ራሱም ዘሩም እንዲሀ ይቀበር ይልና በሙሉ ስብስቦ ይቀብራል። ህዝቡ ይህን ሁሉ ቆሞ ያያል፣ ያዳምጣል (ስክርብ፣79)።*

በማረቆ ብሄረሰብ የእርቅ ሂደት መጨረሻ ጉማ (የደም ካሳ የሚለው አገላለፅ ይተከዋል) ማስከፈል ነው። ጉማ የሚጠየቀው በራጋው ሲሆን እንደ ዘመኑና እንደ ግጭቱ አይነት መጠኑ ይለያያል። እንደ ኢማም(ስክርብ፣77) ገለፃ የብሄረሰብ ግጭቶች ተከስተው የሰው ህይወት ከጠፋ "ወተታም ወተታም" የሆኑ ላሞች ለሚች ቤተሰብ ያለጥሎሽ ልጃገረድ ይሰጣል። ልጃገረዷን የሚያገባው የሚች ወንድም ሲሆን እርቁም የፀና ይሆናል ተብሎ ይታመናል። በብሄረሰቡ በነፍስ መጥፋት ምክንያት ለሌላ ብሄረሰብ አባላት የተሰጠች ልጃገረድ የምትወልዳቸው ልጆች አስታራቂዎች [ራጋ ወይም ማጋ] ይሆናሉ ተብሎ ስለሚታመን የገዳይ ቤተሰብ ወይም ጎሳ ልጃገረዷን ለጋብቻው ይሰጣል።

የግድያ ግጭት የተፈጠረው እርስ በርስ [ማረቆ ከማረቆ ጋር ማለቱ ነው] ከሆነ ጉማው ስድስት ሺ.ህ ብር ብቻ ነው። በብሄረሰቡ ባህል የጉማ ገንዘብ አይበላም። ይህም የሆነበት ምክንያት የጉማ ገንዘብ መብላት በርቼ[81] ያመጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ይህን ሀሳብ ኢማም (ስክርብ፣77) "ከእርቁ በኋላ ራጋው ቆሞ አትብሉ፣ ጉማውን ያቀረብነው ባህላችን እንዳይጠፋ ደም ማበጃ እንጂ እንዳትበሉ በርቼ ይመጣል" በማለት ለካሳ የቀረበው ስድስት ሺ.ህ ብር ለገዳይ እንደሚመለስለት ይገልጻሉ።

በመጨረሻም በዚ.ህ የእርቅ ስርአት ላይ የተገኙት የገዳይና የሚች ቤተሰቦች በሙሉ ወደ ወንዝ ወርደው ይታጠባሉ፤በመታጠባቸውም ለግጭት የሚያበቃውን እርኩስ መንፈስ እንዳስወገዱ ይቆጠራል። በብሄረሰቡ እነዚ.ህ የደም ሰዎች ወደ ወንዝ ወርደው መታጠባቸው ከእርኩስ መንፈስ ለመንጻት ነው።

በመጨረሻም ሁሉም ቤተሰብ በገዳይ ቤት በመሰብሰብ የመስነባበቻና የመመራረቂያ ዝግጅት ላይ ይሳተፋል። በዚ.ህ ዝግጅት ላይ የብሄረሰቡ ራጋና ማጋዎች ሁለቱንም ባለጉዳዮች

---

[81] *በማረቆዎች ዘንድ በርቼ ማለት ክፉ ነገር፣ ክፉ መንፈስ ማለት ነው። ኢማም ቱኬ (ስክርብ፣77) ብሄረሰቡ በበርቼ ላይ ያለውን እምነት በምሳሌ ሲያስረዱ 'አሁን ለምሳሌ ዛሬ ይህንን ገንዘብ እኔ ከበላሁ ነገ የኔ ልጅ ሄዶ ሰው ይገድላል ያም ነገ ከኔ ገንዘብ ይበላል ማለት ነው። ስለዚህ የጉማ ገንዘብ አይበላም' በማለት ማህበረሰቡ በርቼው በኔ ላይ ይደርሳል በሚል እምነት የጉማ ገንዘብ እንደማይበላ ያስረዳሉ። ይህ ሀገረሰባዊ እምነት በብሄረሰቡ ውስጥ በቂም በቀል ቀጣይነት ያላቸው ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ያደርጋል።*

ይመርቃሉ። በማረቆ ብሄረሰብ ባህል እርቅ በዚህ መልኩ ከተጨረሰ በኋላ ሁለቱ የደም ሰዎች "የጉዳ ሰዎች ናቸው" ይባላል። የጉዳ ሰዎች ከስጋ ዘመዳሞች በተሻለ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ እርስ በርስ ይረዳዳሉ። ይህ እርቅ የቃልኪዳን ዝርቅ ነው ተብሎ ስለሚታመን የጉዳ ሰዎቹ ዳግም ግጭት ውስጥ ላለመግባት ይጠነቀቃሉ። በአጋጣሚ በመካከላቸው አለመግባባቶች ቢፈጠሩ እንኳ ችግሩን የሚያበርዱት የጉዳ ዳኞቹ ናቸው።

ከሁለቱ የጉዳ ሰዎች አንዱ ጥፋት ቢያጠፋ በራሱና በቤተሰቡ ላይ የጤና ችግር፣ በሀብቱ ላይም ጥፋት ይመጣበታል ተብሎ ይታመናል። ጥፋቱ ሀጢያት በመሆኑ በቀጣይ የዘር ሀረግ ላይ እየተሸጋገረ ጥፋቱ ይቀጥላል ስለሚባል የሁለቱ መልካም ግንኙነት ዘለቄታነት ይኖረዋል።[82]

በማረቆ ብሄረሰብ በአንጀት መታሰር ለወንድ ልጅ ብቻ የተሰጠ ባህል ሲሆን የራሱ ተምሳሌታዊ ፍቺም አለው። ፍቺዎቹ ከሁለት መዓዘን የሚታዩ ናቸው። አንድም በአንጀት የመተሳሰር ባህላዊ ተምሳሌት ወንዶች ለበቀል እንዳይነሳሱ የሚገድብ የቃል ኪዳን ሰነድ፣ አንድም የሁለቱን ቤተሰቦች የወደ ፊት ግንኙነት፣ አንድነትና ዝምድና ለማሳሰብ ነው። የእግራቸውን አውራ ጣት መታሰራቸውም ግንዘት ነው፤ መሀላ ነው፤ ራሳቸውን ለተገባው ቃል ኪዳን እንዲያስገዙ ማሳሰቢያና ማስረገጫ ነው።

Ben-Amos (1975:188-189) የአፍሪካ የፎክሎር ክዋኔ ሴቶች የሚሳተፉባቸውና የማይሳተፉባቸው በማለት መክፈል እንደሚቻል ይገልፃሉ። በተለይ በቃላዊ ጥበባት ክዋኔ ላይ በዋናነት ከዋኝ፣ አጀቢና ተቀባይ ወንዶች ናቸው። የሴቶቹ ተግባር "whereas a woman is expected to sit and listen, clap to show her respect and appreciation, or join in the chorus of the songs" Ben-Amos (1975:189) ይሆናል። ምንም እንኳ በማረቆ ብሄረሰብ የእርቅ ስርዓተ ክዋኔ በሚፈፀምበት ቦታ ላይ ሴቶች ቢገኙም የእርቅ አፈፃፀም ክዋኔውን የሚመሩትና ሥርዓቱን የሚፈፅሙት ወንዶች ብቻ ናቸው። በተለይ ራጋውና የጉዳ ዳኞች በሚያስፈፅሙት መሀላ፣ ቃል ኪዳን መግባትና በአንጀት መታሰር ወንዶችን ብቻ የሚመለከት ስርዓት ነው። ሴት ልጅ መሀላና ቃል ኪዳን የማትገባበት እና በአንጀት የማትታሰርበት ምክንያት ለበቀል አትነሳሳም፤ደም አትመልስም፤

---

[82] ኢ.ማም(ስክርብ፣81)።

"ነገር አትጨርስም" ተብሎ ስለሚታመን ነው። ነገር ግን ይህ የእርቅ ስርዓተ ክዋኔ በሚፈፀምበት ቦታ በመገኘት ስርዓቱን ትመለከታለች፣ታደምጣለች። እንደ ሀይሉ(ስክርብ፣ 34) ገለፃ የሴቶች በክዋኔው ቦታ የመገኘታቸው ምክንያት ለያዙት ህፃን እና ወደፊት ለሚወልዷቸው ልጆች ስለእርቅ አፈፃፀሙ(ስለትዳው) እንዲናገሩ ነው። በዚህም አሁን ያሉትም ሆኑ ወደ ፊት የሚወለዱት ልጆችና ሙሉው የዘር ሀረግ ግጭት ውስጥ አይገቡም ተብሎ ይታመናል።

### 4.5 ሴቶችና ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም በማረቆ ብሄረሰብ

የማረቆ ብሄረሰብ እርስ በርሱና ከአጎራባቹ ብሄረሰቦች ጋር በሚኖረው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተራክቦ በሚፈጠሩ የሀሳብና የፍላጎት አለመጣጣሞች ግጭቶች ይፈጠራሉ። እነዚህን ግጭቶች በዘላቂነት ለማርገብ በሚከናወኑ የእርቅ ስርዓቶች ላይ ሴቶች ተሳትፏቸው የጎላ ነው።

በብሄረሰቡ ግጭቶች በእርቅ ከተደመደሙ በኋላ የእርቅ ስርአቱን ሲመሩ የዋሉት ማጋዎች ግብዣ ይደረግላቸዋል። ይህን የመስተንግዶ ዝግጅት በሀላፊነት የሚወጡት ሴቶች ናቸው። ምንም እንኳ እንደ ባለጉዳዮቹ የኢኮኖሚ አቅም ቢወስንም ሴቶቹ ለማጋዎች ጠጅ ጥለው፣ ቡና አፍልተው ሊያስተናግዱ ይችላሉ። የግድያ እርቅ ከሆነ ደግሞ ከገዳይና ሟች ቤተሰቦች ማለትም በአራት መአዘን የተውጣጡ ሰዎች በአዳር ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ። የሚጋበዙት የገዳይ እናትና አባትና ቤተሰቦች፣ የሚስቱ እናት አባት ቤተሰቦች ናቸው። በዚህ የአዳር ዝግጅት ወቅት ለተሳታፊዎች የሚበቃውን ምግብና መጠጥ ጊዜ ወስደው የሚያዘጋጁት ሴቶች ናቸው።[83]

እንደ መረጃ አቀባዮቹ አበጋዝ ጃቢቦ (ስክርብ፣52 እና አበጋዝ ሙርኪ.(ስክርብ፣80) ገለፃ ከሆነ በማረቆ ብሄረሰብ ያለሴቶች ተሳትፎ እርቅ ሊፈጽም አይችልም። በተለይ በብሄረሰቡ የተከሰተው ግጭት የአካል ማጉደልና የሰው ነፍስ የጠፋበት ከሆነ የእርቅ ስርዓቱ የሚጀመረው ከበዳይና ከተበዳይ ወገን በተወከሉ ሁለት ልጃገረዶች አማካኝነት ነው። እነዚህ ልጃገረዶች ከገዳይ ቤት በር ላይ የማር ጠጅ በአፋቸው ይዘው በግራና ቀኝ በመቆም የሟች ቤተሰቦች ወደ ቤት ሲገቡ ጠጁን "ቱፍ ቱፍ" በማለት ዘላቂና ሰላማዊ እርቅ እንዲከናወን

[83] *ሀይሉ(ስክርብ፣16፣49) እንዲሁም ሀጂ ጃተኖ (ስክርብ፣49)።*

ምኞታቸውን ይገልፃሉ። በብሄረሰቡ እነዚህ ግጭቶች መፍትሄ ያገኙ ዘንድ የግዴታ ልጃገረዶች መሳተፍ ይኖርባቸዋል።

በሌላ መልኩ የብሄረሰቡ ተወላጅ ከአጎራባች ብሄረሰቦች አባላት ጋር ግጭት ፈጥሮ የሰው ነፍስ ቢያጠፋ በሁለቱ ብሄረሰቦች መካከል ዘለቄታዊነት ያለውን እርቅ ለመፈጸም ሴት ልጅ ጉልህ ሚና ትጫወታለች።[84] በዚህ እርቅ የሟች ቤተሰቦች ከገዳይ ቤተሰቦች ጋር በጋብቻ እንዲተሳሰሩ ይደረጋል። በአጋጣሚ ገዳይ ሴት ልጅ የሌለው ከሆነ ከገዳይ ጎሳ የሆነች ልጃገረድ በማዘጋጀት እርቁ ይፈፀማል። ይህ አካሄድ ሴቶች በብሄረሰቡ ውስጥ ዘላቂ ሰላምን በማምጣት በኩል ያላቸውን ሚና የሚያሳይ ነው።

በአንዳንድ ብሄረሰቦች ግጭት ውስጥ ከገቡት ግለሰቦች ውጭ በእርቁ ላይ ሌሎች ሰዎችን መሳተፍ አይፈቀድላቸውም። አንዳንድ ብሄረሰቦች ደግሞ ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች ቤተሰቦች ሰፋ ሲልም ጎሳው ወይም የቀበሌው ነዋሪ እንዲሳተፍ ያደርጋሉ።[85] በማረቆ ብሄረሰብ ከፍተኛ የአካል መጉደልና የግድያ ግጭት ሲፈታ ግጭት ውስጥ የገቡት ግለሰቦች፣ የስጋ ዘመዶች (በራጋው ትዕዛዝ እንዲሳተፍ የተፈቀደላቸው ማለት ነው) ሴቶችንና ህጻናት ጨምሮ በእርቁ ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል። ምንም እንኳ ሴቶች በእርቁ ላይ ሀሳብ እንዲሰጡ ባይፈቀድላቸው ቁጭ ብለው እንዲሰሙ ይደረጋል። ሴቶቹ በእርቁ ላይ እንዲሳተፉ የሚደረገው ለምታጠባው ህፃን ልጅ ወይም ወደፊት ለምትወልደው ልጅ ስለተከናወነው እርቅ እንድትናገር ነው። ሴት ልጅ ዘርን ትቀጥላለች ብለው የሚያምኑት ማረቆዎች ለቀጣይ ትውልድ መረጃን በማቀበል ወደፊት ህጻናት እርቁን አክብረው እንዲኖሩ የማሳሰብ ሙሉ ሃላፊነት ይጣልባታል።

በብሄረሰቡ ሴቶች የትኛውንም አይነት ግጭት እንዲያስታርቁ ባህሉ አይፈቅድላቸውም። በማህበረሰቡ ሰዎችን ያለ አድሎ አስታርቆ ወደቀደመ ሰላማዊ ግንኙነታቸው መመለስ

[84] ብዙ ጊዜ ከፎክሎር (ከባህል) ጥናት የራቀ ምሁራን ይህን አይነት ጋብቻ እንደ ኋላ ቀርነት መገለጫ በመቁጥር ጎጂ ባህል ነው ሲሉ ይደመጣል። ይህ አስተሳሰብ በፎክሎር የጥናት ዘርፍ ተቀባነት የለውም። ምክንያቱም አንድ ባህል መዳኘት ያለበት በባህሉ ባለቤት በመሆኑ ነው።

[85] አበበ ሀይሉ "ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኚዋ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ በ1999 ዓ.ም የሰራው ጥናት እንደሚያሳየው በባህላዊ የእርቅ ስርዓት ላይ የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሳተፍ ከሚፈቅዱ ብሄረሰቦች መካከል አኚዋ ተጠቃሽ ነው። ማረቆዎች የማስታረቅ ፀጋ ከፈጣሪ ለወንዶች ብቻ የተሰጠ ነው ቢሉም በተለያዩ የሀይማኖት መፅሀፍት ላይ ሴቶች አለማዊያንን ከመለኮታዊ ሀይል ጋር እንደሚያስታርቁ የሚገልፁ ታሪኮች አሉ።

ለወንዶች የተሰጠ ፀጋ[86] ነው ብለው ያምናሉ። ይህ የማስታረቅ ፀጋም ከፈጣሪ የተሰጠው ነው ብለው ማመናቸውም ሴቶች ከተመላካችነት ባለፈ ሚና እንዳይኖራቸው አድርጓል።[87]

በማረቆ ብሄረሰብ እርቅ ሲከናወን የሴቶችና የህፃናት መብቶች እንዳይሸረሸሩ ጥንቃቄ ይደረጋል። ባሏ የተገደለባት ሴት በገዳይ አካል የገንዘብና የጉልበት እገዛና ልጆቿን እንደ ልጆች አድርጎ እንዲያስተምርና እንዲንከባከብ ባህሉ ያዘዋል።

እርቅ ከተፈፀመ በኋላ ገዳይ የሟች ምትክ ነው ተብሎ ስለሚታመን የሟችን እናት እንደ እናቱ ልጆቹንም እንደ ልጆቹ ቆጥሮ ያሳድጋል። የሟች እህትም የደረሰባትን ሀዘን እንድትረሳ ገዳዩ የእንባ ማድረቂያ የሚሆን ቁርበት ይሰጣታል። በዚህም ጊዜ ገዳይን ለሟች ወንድሟ ምትክ አድርጋ ትቀበላለች።

## 4.6 በራጋ ማጋ ላይ የሚታዩ ሀገረሰባዊ እምነቶችና ተግባሮቻቸው

> *Societal beliefs are defined as society members' shared cognitions on topics and issues that are of special concern for society and contribute to their sense of uniqueness. These beliefs construct society members' view of the conflict and motivate them to act. They thus provide the informational and motivational basis for societal action (Bar-Tal, 2000:353). {ሀገረሰባዊ እምነቶች የማህበረሰብ አባላት የሚጋሯቸው አዕምሮታዊ እሳቦቶችን የሚያጠቃልሉ፣ለአንድነቱ አስተዋፆ የሚያደርጉ አርስቶችና ጉዳዮችን ነው። እነዚህ እምነቶች የማህበረሰቡ አባላት ስለ ግጭትና ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና የሚቀርፁ ናቸው። እምነቶቹ የማህበረሰቡ አባላት በግጭት ላይ ለሚያከናውኗቸው ክንውኖች መረጃና ቀስቃሽ ግብዓቶችን ይሰጣሉ (Bar-Tal, 2000:353)}።*

የማረቆ ብሄረሰብ ከሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ጋር በቀጥታ የሚገናኙ የተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነቶች አሉት። ከነዚም ውስጥ በርቄ፣ በቀደምት አባቶች ሙት መስፈስ ማመን፣ እርግማንና ጡር ይደርስብኛል ብሎ መፍራት(ሀንታሞ ፌስቲማ ይሉታል) እነዚህም ልጅ አያድግልኝም፣ሀብት አይረባልኝም፣በቤተሰቤና በቀጣይ የዘር ሀረጌ ላይ ኍይ የቁምጥና በሽታ ይመጣብኛል ብሎ ማመን ተጠቃሾች ናቸው።

በብሄረሰቡ ግጭቶችን ለመፍታት የሚከናወኑት ሂደቶች ከሀገረሰባዊ እምነቶች ጋር ጥብቅ ቁርኛት አላቸው። ብሄረሰቡ እርስ በርስና ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም መፍትሔ እንዲያገኙ አምነቶቹ ጥቅም ላይ

---

[86] *አበጋዝ ሙርኪ(ስክርብ፣79)።*
[87] *ሀጂ ጃተኖ(ስክርብ፣49፤አበጋዝ ሙርኪ፣80)።*

ይውላሉ። እነዚህ እምነቶች በብሄረሰቡ ሀገረሰባዊ እውቀቶችና ጥበቦች የተቀረፁ የጋራ መርሆች በመሆናቸው አይሻሩም፣አይናቁም።

ሀገረሰባዊ እምነቶቹ ለእርቅ ለመለመን፣ ድብቅ ወንጀሎችን ለመመርመር፣ ውሳኔዎች እንዲፀኑ፣ እንዲጠነክሩና ዘላቂነታቸው እንዲረጋገጥ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። በብሄረሰቡ ግጭቶች በራጋ ማጋ መፍትሔ እስኪያገኙ የበቀል እርምጃዎች የማይፈፀሙት ብሄረሰቡ የሚመራባቸውን ሀገረሰባዊ እምነቶች ስለሚያከብር ነው።[88]

በብሄረሰቡ እነዚህን ሀገረሰባዊ እምነቶች መናቅና መድፈር በቤተሰብ፣ በሀብትና በጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል። ጉዳቱ በቀጣይ የዘር ሀረግ ላይም ይከሰታል ስለሚባል የብሄረሰቡ አባላት ተቋሙን በሚመሩት የቤት-ዘመድ ጉባኤ፣ ማጋዎችና ራጋ የታዘዙትን እየፈፀሙ ይታረቃሉ። ይህን ሀሳብ ሀይሉ፡-

> *በዳዩ ይህን ሁሉ ሂደት አልፎ የሚታረቀውና ሽማግሌዎች ያሉትን ሁሉ በፀጋ እየተቀበለ የሚፈፅመው ይህን አድርጌ ካልታረኩ ነገ ከነገ በኋላ ሌላ ችግር፣ የእጅ መተላለፍ ሊሆን ይችላል፤ ወይ በእሱ፣ ወይ በልጅ ልጆቹ ይደርስብኛል ሀብት፣ ጤና አጣለሁ ብሎ ስለሚያምን ነው። ይህን የማህበረሰቡን ልማድ ለመሻር የሚደፍር አካል የለም አድርግ የተባለውን አድርጎ ይታረቃል እንጅ (ስክርብ፣12)።*

በማለት የብሄረሰቡ አባላት በእምነቶቹ ላይ ያላቸውን አተያይ ገልፀውታል። ይህን ማህበረሰባዊ እምነት በአግባቡ የሚተግብሩና አለመግባባታቸውን በእርቅ የቋጩ የብሄረሰቡ አባላት በቀጣይ የሚኖራቸው ሁለንተናዊ ግንኙነት ጥሩ ይሆናል።

በማረቆዎች በዳይ ራሱን ጥፋተኛ አድርጎ በማቅረብ ነው ለእርቅ የሚቀርበው። ከእርቅ በኋላም ቢሆን በዳይ አካል ለተበዳዩ የተለያዩ እገዛዎችን እንዲያደርግ ባህሉ ያዛል። እገዛው የሚከናወነው በሽማግሌዎች ትዕዛዝ ሳይሆን በባህሉ እንደ አንድ መርህ ስለሚቆጠር ሳይታዘዝ በጉልበቱ፣ በብርና ልጅ በማስተማር ያግዛል። በዳይ ይህን የሚያደርገው ቀጣይ

---

[88] *በማረቆ ብሄረሰብ የራጋ ማጋ እርቅ በየደረጃው ከተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነቶችና መርሆች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። በዚህ ርዕስ ስር የማነሳቸው ሀገረሰባዊ እምነቶችና መርሆች በእርቅ ሂደቱ ላይ ጎልተው የታዩትን ነጥሎ በማውጣት ለማሳየት ብቻ ነው። ሀገረሰባዊ እምነቶቹ በሶስቱም ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት በእርቅ ሂደቱ ላይ የተለያዩ ሀገረሰባዊ ስርአቶች እንዲከናወኑ ምክንያት ሆኗል። የሚንፀባረቁ መሆናቸውን ልብ ይሏል። የብሄረሰቡ የግጭት መፍቻ ተቋማት ከእምነቶቹ ጋር የተቆራኙ መሆን*

ሊመጣ ከሚችል በርቼ ለመዳን ሲል ነው። ባህሉ የሚያዘውን የሚፈፅም ከሆነ ቤተሰቡንና የዘር ሀረጉን ከሀንታሞ ፌስቲማ[89] ያድናል ተብሎ ይታመናል ይቻላል።[90]

### 4.6.1 ሀገረሰባዊ እምነቶች በእርቅ መለመኛ ስልትነት

በማረቆ ብሄረሰብ ግጭት ውስጥ የገቡ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ጎሳዎች በማጋዎች አማካኝነት ለእርቅ ሲጠየቁ አሻፈረኝ የማለት ልማድ የላቸውም። ግጭት ውስጥ የገቡ የብሄረሰቡ ተወላጆች የእርቅ ጥያቄ ሲቀርብላቸው የሀገር ሽማግሌዎችን (ማጋዎችን) በማክበርና በመፍራት ወዲያውኑ ፈቃደኝነታቸውን ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ የተፈፀመው በደል የከፋና አሳዛኝ ከሆነ ተበዳይ አልታረቅም ሊል ይችላል። በብሄረሰቡ ባህል ተበዳዩ አልታረቅም ካለ በበዳዩ ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ አስቧል ስለሚባል ማጋዎች የታረቅልን ተማፅኗቸውን ይቀጥላሉ።

በማረቆ ብሄረሰብ አልታረቅም ያለን አካል ለማሳመን ማጋዎች የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ። እነዚህ የእርቅ መለመኛ ስልቶች ብሄረሰቡን አንድ አድርገው የኖሩና የሚፈሩ ሀገረሰባዊ እምነቶች ናቸው። እምነቶቹ የብሄረሰቡ አባላት ወደ በቀል እንዳያመሩና በማጋዎች የሚቀርበውን የእርቅ ጥያቄ እንዲቀበሉ የሚገፋፉ ናቸው።

ማረቆዎች ለማርና ለቅቤ የተለየ ክብር ስለሚሰጡ ለእርቅ አሻፈረኝ ያለ ግለሰብ በማር አማካኝነት ይለመናል። ማርና ቅቤ የብሄረሰቡ ሆዳ[91] ሲሆኑ በማርና በቅቤ ስም ለእርቅ ተለምኖ እምቢ ቢል ችግር ያጋጥመዋል ተብሎ ይታመናል። እንደ ሀጂ ጃተኖ(ስክርብ፣41) የማረቆ ብሄረሰብ ስለ ማር ያለውን ግንዛቤ "ይህንን ማር እምቢ ያለ ሰው ይጠፋል። አይድንም፣ድራሹ ይጠፋል" በማለት ይገልፁታል።

በብሄረሰቡ ማር እርቅን ያፀናል ተብሎ ይታመናል። ይህን ሀሳብ ዲንቁላ (ስክርብ፣38) "ማር በዚህ በአገራችን በጣም ይታመናል። ልጃገረድም ብትጠለፍ እንስራ ማር ካልሄደ

[89]እንደ ሀይሉ(ስክርብ፣13) "ሀንታሞ ማለት ግፍን የማስቀረት ነገር ማለት ነው። የእጅ መተላለፍ ነገርን አውቆም ሳያውቅም እጅ በስህተት በሰነዘረ ቁጥር ለአደጋ የሚያጋልጡ ነገሮች ርኩስ መንፈሶች ይቀራሉ፣ ይሸሻሉ ተብሎ ይታመናል" በማለት ይገልፁታል። በማረቆ ብሄረሰብ ሰዎችን ለአደጋ ያጋልጣል የሚባለው እርኩስ መንፈስ በርቼ ነው። እንደ ብርሀን(2002፣86) ገለፃ ይህ መንፈስ ሙርቲ ተብሎ ይታወቃል።
[90]ሀይሉ(ስክርብ፣12፣13፣14)።
[91]ለማረቆ ብሄረሰብ ሆዳ ማለት ቁጣ ማብረጃ ማለት ነው። በብሄረሰቡ ባህል የቁጣ ማብረጃ ተብለው የሚታወቁት ማርና ነጭ ጋቢ ናቸው። በማረቆዎች የቁጣ ማብረጃ ለተበዳይ የሚዘጋጀው የማጋዎችን ልመና አልቀበልም፣ተበድያለሁ ብሎ አሻፈረኝ ሲል ነው። አንዳንድ ጊዜ ተበዳይ ማጋዎች ወደ ቤቱ የእንስራ ማር ይዘው እንዳይመጡ ይከለክላል፣ግቢውን ሊጠብቅ ይችላል።

እርቅ አይሆንም። እርቁ የፀና አይሆንም" በማለት ብሄረሰቡ በማር ላይ ያለውን እምነት ይገልፃሉ።

በሌላ መልኩ ማረቆዎች ለቀደሙት አባቶቻቸውና አያቶቻቸው ክብር የሚሰጡ ህዝቦች ናቸው። ብሄረሰቡ በሞት የተለዩን አባቶቻችን መንፈስ ይጠብቀናል ብሎ ያምናል። በዚህም የተነሳ ከባድ ግጭት ውስጥ የገቡ የብሄረሰቡ ተወላጆች ለእርቅ አሻፈረኝ ካሉ የሚለመኑት በቀድሞ አባቶቻቸው መንፈስ ነው። በሞት ከተለዩ አባቶች መቃብር ላይ ነጭ ጋቢ ተነጥፎ የእርቅ ጥያቄ ይቀርባል። ነጭ ጋቢ በመቃብር ላይ ተነጥፎ የሚለመንበት የራሱ ምክንያት አለው።

በብሄረሰቡ ባህል ጋቢ የተለየ ክብር የሚሰጠው ልብስ ነው። በሀዘንና በደስታ ወቅት የብሄረሰቡ ትልልቅ አባቶች በክብር የሚለብሱትና በሆዳነት የሚያገለግለው ልብስ ነጭ ጋቢ ነው።[92] ይህን በነጭ ጋቢ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ለእርቅ የመለመንና የማሳመን

ሁኔታ ዲንቁሳ፡-

> *በትልቅ በታዋቂ ሽማግሌ መቃብር ላይ ያን ጋቢ ካለበሱት ያን ያየ ሰው በእከሌ መቃብር ላይ በሀጅ ወይም ደግሞ በግራዝማች፣ በአዝማች መቃብር ላይ ጋቢ አይተናል ከተባለ ተሄዶ ይታይና ያ ቤተሰቡ የዚያኛው ሰውዬ ዘር ይነሳሉ። አሁን ይሄ ያ ሰውዬ ተፈርቶ ነው ይህ የሚደረገው ወደ ሰፈሩ ሰው እንዳይቀርብ ተከላክሏል ስለዚህ ተፈርቶ ነው በመቃብር ላይ ጋቢ የሚለበሰው። ይህ ከሆነ ዕርስ በርስ ተጠራርተው ነገሩን ያበርዳሉ። ይህ ተደርጎ እምቢ ካለ ለዘሩም አይበጅም ተብሎ ይታመናል(ስክርብ፣42)።*

በማለት የሚከናወነውን የታረቁልን ልመና ከእምነቱ ጋር አገናኝተው ይገልፁታል።

በብሄረሰቡ ነጭ ጋቢ በበረት በር ላይ ታስሮ የእርቅ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። ተበዳይ ወደ አካባቢው ማንም እንዳይደርስ ግቢውን የሚጠብቅ ከሆነ በሌሊት ጋቢውን ከበረቱ መዝጊያ ቢቲማ[93] ላይ ይታሰራል። ጋቢው ከቢቲማው ላይ የሚታሰረው ነፋስ እንዳይወስደው ተብሎ ነው።

ማረቆዎች እነዚህን ሀገረሰባዊ እምነቶች ለማክበር ሲሉ በማጋዎች የሚቀርበውን የእርቅ ጥያቄ ይቀበላሉ። ሀገረሰባዊ እምነቶቹ በሚያሳድሩት ስነ-ልቦናዊ ጫና ለእርቅ አሻፈረኝ ብሎ

---

[92] *ሀጂ ጃተሮ፣ ሀይሉ፣ ዲንቁሳ(ስክርብ፣41)።*
[93] *ቢቲማ ከበረት የተሰራ የከብቶች በረት መዝጊያ ነው።*

የሚቀር የብሄረሰቡ ተወላጅ የለም። የደረሰበት በደል አበሳጭቶት የታረቁልን ጥያቄውን ውድቅ የሚያደርግ የብሄረሰቡ ተወላጅ ሆዳ ከቀረበለት ወዲያውኑ ለእርቅ ፈቃደኛ ይሆናል።

## 4.6.2 ሀገረሰባዊ እምነቶች በወንጀል መመርመሪያ ስልትነት

> *በጨለማ የነፍስ ግድያ ሊሆን ይችላል፤ ቤት ቃጠሎ ሊሆን ይችላል፤ በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ ሊሆን ይችላል፤ የከብት ስርቆት ከበረት አውጥቶ መውሰድ ሊሆን ይችላል የመሳሰሉ ነገሮች በጨለማ የሆኑ የተፈፀሙ ወንጀሎች በሚሆኑ ጊዜ እነዚህን ድርጊቶች ለሽማግሌና ለምርመራ ሂደት ትንሽ ሊወሳሰቡና አስቸጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን ሽማግሌ የራሱ አካሄድ አለው (ሀይሉ፤ስክርብ፤19)።*

በማረቆ ብሄረሰብ በድብቅ የተፈፀሙ ወንጀሎች ተደብቀው አይቀሩም። ብሄረሰቡ ድብቅ ወንጀሎችን ለማውጣጣት ሀገረሰባዊ የሆኑ የወንጀል ምርመራ ስልቶች ይጠቀማል። እነዚህ ሀገረሰባዊ የወንጀል ምርመራ ስልቶች ከብሄረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ሲሆን ምርመራው ራሱን የቻለ ሂደት አለው።

በማረቆ ብሄረሰብ የተደበቁ ወንጀሎች ይፋ የሚወጡት በመሃላ ነው። በብሄረሰቡ መሀላ የድብቅ ወንጀሎች መመርመሪያ ስልት ሲሆን ሂደቱም ሁለት አይነት ነው። የመጀመሪያው የመሀላ ሂደት የሚከናወነው የተፈፀመው ወንጀል ሙሉ በሙሉ ሲደበቅና ተጎጂው አካልም የሚጠረጥረው ሰው ሳይኖር ነው። ሁለተኛው የመሀላ አፈፃፀም ተጎጂው አካል ወንጀኛውን ካወቀውና ለሽማግሌዎች ከጠቆመ ነው። ይህ መሀላ የሚከናወነው ተጠርጣሪው ድርጊቱን አልፈፀምኩም ካለ ነው። የእነዚህን ድብቅ ወንጀሎች መመርመሪያ ስልቶች በምሳሌ ከተደገፈ ማብራሪያ ጋር በተናጠል ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ ስለታዩኝ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡-

በማረቆ ብሄረሰብ ማንነቱ ባልታወቀ ግለሰብ ወንጀል ከተፈፀመና ተበዳይ ጠላቱን ካላወቀው ወንጀሉ በመሀላ ይጣራል። ለምሳሌ የቤት ቃጠሎ በሌሊት ቢፈፀም የአካባቢው ማህበረሰብ በእሪታ(በጩኸት ለማለት ነው) ተሰባስቦ እሳቱን በማጥፋት ተጎጂዎችን ሲያረጋጋና እቃዎችን ሲሸክፍ ያድራል። ማረቆዎች ይህን ወንጀል መመርመር የሚጀምሩት በማግስቱ ነው። ይህን ሀገረሰባዊ የወንጀል ምርመራ ስርዓት ሀይሉ፡-

> *ይህንን ጥፋት ማንነቱ አድራጊው ካልታወቀ ያካባቢው ህብረተሰብ በሙሉ ሴት ወንድ ሳይለይ በዚያ አካባቢ ዙሪ ያለው ማግስቱን ይሰበሰቡና ማን ነበር በዚያ መንገድ የሄደ ማን ነበር በምሽት መንገድ ሲሸሽ የሰማችሁት ኧ...ወይስ አንተ የምትጠረጥረው አለ ወይ ይህን ያደርስብኛል ብለህ ለምትጠረጥረው ባላጋራ አለህ ወይ ተብሎ ይጠየቃል (ስክርብ፤20)።*

በማለት የምርመራ ሂደቱ እንደሚጀመር ይገልፃሉ።

ወንጀል በተፈፀመበት ቦታ ለምርመራ የተሰበሰበው የአካባቢው ማህበረሰብም በደረሰው ጥፋት እያዘነ እርስ በርስ ይወያያል። በዚህ ሰው ላይ ይህ ጥቃት ለምን ይፈፀማል የፈፀመውስ ማን ነው እየተባለ ውይይቱ ይቀጥላል። ይህን ውይይት የሚመሩት የአካባቢው ማጋዎች ሲሆኑ ለተሰበሰበው ህዝብ የመወያያ ጥያቄዎችን ይሰነዝራሉ። በማጋዎች የሚቀርቡ የመወያያ ጥያቄዎችን ሀይሉ (ስክርብ፣20) "በዚህ መድረክ ላይ ጥቃት በዚህ ሰው ላይ ተፈፅሟል አይንህ ያየ፣ ጆሮህ የሰማ፣ ልብህ ያስተዋለ ይህን ነገር ንገር፣ አጋልጥ በልጆችህ ላይ ያድራል ነገ በኔ ብለህ በሚስጥርም ቢሆን ለሽማግሌ ንገር፣ ጠቁም ተብሎ ይነገራል" በማለት አጠቃላይ ሂደቱን ይገልፁታል።

በእለቱ ውይይት ወንጀለኛው ካልታወቀ የተሰበሰበው ህዝብ ቀጠሮ ይዞ ይለያያል። በማረቆ ብሄረሰብ ይህን ድብቅ ወንጀል ለመመርመር ሶስት ጊዜ ቀጠሮ ይሰጣል። በብሄረሰቡ ለምርመራ ቀጠሮ የሚሰጥባቸው ቀናት ረቡዕና አርብ ሲሆኑ እነዚህ ቀናት ደረቅ ቀናት፣ የማህላ ቀናት[94] ተብለው ይታወቃሉ። ቀጠሮ የሚሰጥበት ምክንያት የአካባቢው ማህበረሰብ ለሳምንት ያህል መረጃ እንዲሰበስብና ወንጀለኛውን ለማውጣት እንዲያመች ነው።

በሁለተኛው የቀጠሮ ቀን መረጃ ሲሰበስብ የሰነበተው የአካባቢው ማህበረሰብ ቃጠሎው በተፈፀመበት ቦታ ይሰባሰባል። በዚህ የቀጠሮ ቀን ምን መረጃ እንደተገኘ ማጋዎች ለተሰበሰበው ሰው ጥያቄ ያቀርባሉ። ለመርመራ የተሰባሰቡት የአካባቢው ሰዎች ያገኙትን መረጃ ለሽማግሌዎች በሚስጥር እንዲጠቁሙ ይደረጋል። በእለቱ ምንም አይነት ፍንጭ ካልተገኘ ለሶስተኛ ጊዜ ቀጠሮ ይሰጣል። በብሄረሰቡ ይህ ቀጠሮ የእርማን ቀጠሮ እየተባለ ይጠራል።

በሶስተኛው የእርግማን ቀጠሮ የተሰበሰቡት ሰዎች በሙሉ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው ሊታወቅ ባለመቻሉ ለመርገም መዘጋጀታቸውን በመግለፅ ራሱን እንዲያጋልጥ ይጠይቃሉ። ብዙ ጊዜ በብሄረሰቡ ወንጀለኛ በዚህ ቀን ራሱን ያጋልጣል ወይም ለቤተሰቦቹ ድርጊቱን እንደፈፀመ ያምናል። ቤተሰቦቹም በሚስጥር ወይም በይፋ ልጃቸው ተሳስቶ ወንጀሉን እንደፈፀመ ያሳውቃሉ። ወንጀለኛው በሶስተኛው የቀጠሮ ቀን ሊገኝ ካልቻለ ግን ይረገማል። ይህን እርግማን ሀይሉ፡-

---

[94]*የማረቆ ብሄረሰብ ረቡዕ እና አርብን ለመሀላና እርግማን የተመረጡበትን ዋና ምክንያት "የእርቅ ቦታና ቀን መረጣ በማረቆ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ በሰፊው ይዳሰሳል።*

> *ምድሪቷ ትያዝሀ፣ በአፍህ ለፍልፍ፣ ራስህ ለፍልፈህ የሰራኸውን አጋልጥ አንተንም ያጋልጥህ፣ በአንተም ላይ እንዲህ አይነት ችግር፣ ጥፋት፣ ውድመት ይድረስብህ፤ እኔ ቀን አሳስቶኝ ነው ብለህ ጩህ፣ ያስጩህህ ተብሎ የተሰበሰበው በሙሉ ሴት ወንድ ሳይል ሁሉም መሬት በእጁ እየያዘ እኛ መሬትን በእጃችን እንደያዝን እሷ ደግሞ አንተን አሳዳ ትያዝህ ተብሎ ነው (ሀይሉ፤ስክርብ፣26)::*

በማለት በስርዓቱ ላይ የመታደምና የመርገም ማህበረሰባዊ ግዴታ ያለበት የብሄረሰቡ ተወላጅ በሙሉ እንደሚረግመው ይገልፃሉ።

እርግማኑ ለቤተሰብና ለዘር ሀረግ ይተርፋል ስለሚባል የብሄረሰቡ አባላት የሰሩትን ድብቅ ወንጀል በመጀመሪያው የቀጠሮ ቀን ለአካባቢው ማጋዎች ያሳውቃሉ። ወንጀለኛው በራሱና በቀጣይ የዘር ሀረግ ላይ ይህ አይነቱ ጥፋት እንዲያጋጥማቸው መረገሙ የሚያሳድረው ፍርሀት ከባድ በመሆኑ ድብቅ ወንጀሎች የሚያውጣጡት በእርግማን ነው።[95]

እንደ Ben Amos (1975:531-532) ገለፃ አንድን የፎክሎር ጥናት በአውድ ማዕቀፍ ውስጥ ሲጠና የሚፈፀሙ ስርዓተ ክዋኔዎችና ከበራዎች የተደራጁ መሆን እንዳለባቸው ይገልፃሉ። ፎክሎራዊ አህዱን በአውድ ውስጥ ማስገባትና አንዳች ቅጥ ማስያዝም በባህሉ ስይ ያለውን ሚናና ዕንሰ ሀሳባዊ ውክልና ተገቢነት ያለው ፍቺ ለመስጠት ያስችላል። በማረቅ ብሄረሰብ የተፈፀመውን ድብቅ ወንጀል ለማጣራት የሚከናወነው የመሀላ ስርዓተ ክዋኔ ራሳቸውን በቻሉ ተለጣጣቂ ስርዓቶች የተዋቀረ ሲሆን ስርዓቶቹ የብሄረሰቡን የህይወት ፍልስፍና የሚያሳዩ ባህላዊ ውክልናዎችን ይዘዋል።

ለምሳሌ ቤቱ የተቃጠለበት አንድ የብሄረሰቡ ተወላጅ በእርግጠኝነት ጥቃቱን ፈፅምብኛል የሚለውን አካል ከጠቆመና ተጠርጣሪው ከካደ ወንጀሉ በማጋዎች አማካኝነት በመሀላ ይጣራል። ይህ የወንጀል ምርመራ የሚከናወነው ተበዳይ ወንጀሉ በተጠርጣሪው ለመፈፀሙ እርግጠኛ ሆኖ ከተናገረ ብቻ ነው። መሀላው ሲፈፀም በብሄረሰቡ የሚከበሩ ትልልቅ ማጋዎች ይገኛሉ:: የመሀላውን ስርዓተ-ሂደት ሀይሉ፡-

> *እሳት ይዘጋጃል፣ ጉድጓድ ይቆፈራል፣ ጦር ይዘጋጃል፣ ጠመንጃ ይቀመጣል እነዚህ በአንድ ላይ ተዘጋጅተው ይህን ስራ ሰርቼ ከሆነ በዚህ ጉድጓድ ልቀበርበት፣ ከዚህ ጥይት አሳምልጥ፣ ከዚህ ጦር አሳምልጥ፣ይህ እሳት ያቃጥለኝ ይህ እሳት በሰማይ ቤትም በምድር ቤትም ያቃጥለኝ፣ ልቃጠልበት የዘራሁት አይብቀልልኝ፣ የወለድኩት አይባረክልኝ፣ በተማሰው ጉድጓድ ውስጥ እኔ ልግባበት ብሎ ይምላላ ከፊቱ የቀረበለትን እሳት፣ ጉድጓድ፣ ጠመንጃ፣ ጦር በእጁ እየጠቆመ እየሳየ ማለት ነው። እንደዚህ ብለህ ማል ይባላል (ስክርብ፣21)።*

[95] *ሀይሉ(ስክርብ፣21)::*

በማለት ተጠርጣሪው በማጋዎችና በተሰበሰበው ሰው ፊት የታዘዘውን አንድ በአንድ እየፈፀመ እንደሚምል ይገልፃሉ።

አንድ ተጠርጣሪ በማጋዎች ፊት ከማለ ከወንጀሉ ነፃ ይሆናል። በብሄረሰቡ ባህል መሀላ መፈፀም ከጥርጣሬ የመዳኛ ከወንጀለኛነት የማምለጫና የንፅህና ማረጋገጫ ምልክት ተደርጎ ይቆጠራል።

በማረቆ ብሄረሰብ መሀላ ጡት በማጥባትም ይፈፀማል። በብሄረሰቡ ተደጋጋሚነት ያላቸው ወንጀሎች ሲፈፀሙ መሀላው ጡት በመጣባት ይከናወናል። አንድ የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጅ ብዙ ጊዜ በአንድ ሰው ወንጀል እየተፈፀመበት ከተቸገረ ለብሄረሰቡ ማጋዎች ከእከሌ ጋር "ጡት አጣቡኝ" ይላል። ይህ የጡት ማጣባት ስርዓት የሚከናወነው በከብትና በአዝመራ ስርቆት፣ በመክዳዳት፣ በስም ማጥፋት ከሚከሰት የወንጀል ክስ ለመዳን፣ እርቅን በመናቅ ሊወሰድ ከሚችል የበቀል እርምጃ እንዲሁም ላለመበቀል ቃል ኪዳን ለመግባት ነው።[96]

ጡት የማጣባት ስርዓቱን የብሄረሰብ ጎንቱ ጎንቱ(ታላላቅ ለማለት ነው) ማጋዎች የሚያስፈፅሙት ሲሆን ግጭቱ ወደ ጎሳና ቀበሌ እንዳይስፋፋ ሂደቱ ይፋጠናል። በብሄረሰቡ ጡት መጣባት ማለት ወደ ፊት ላለመበቃቀል ቃል ኪዳን የመግባት፣ የትማማችንነትና የአንድነት ተምሳሌት ነው።

በማረቆ ብሄረሰብ የጡት መጣባት ሂደቱን ለማከናወን ወተትና ደም ጥቅም ላይ ይውላሉ። ሁለቱ ባለጉዳዮች ጡት የሚጣቡት በአፋቸው ደምና ወተት ቀላቅለው በመያዝ ሲሆን ደሙ የሚገኘው ነጭ ፍየል ታርዶ ነው። ይህን የጡት መጣባት ስርዓት ሀጂ ጃተኖ፡-

> *አንድ ነጭ ፍየል አርደን ደምና ወተት በአንድ ላይ አግብተን በአፍ አንዱም ይይዛል አንዱም ይይዛል ጡት ይጣባል። በዚህ ጡት ንገር፣የናት ልጅ ነው ንገር አትደብቅ የእናት ልጅ ነው፣እንደ እናት ልጅ ነው የጠባው ንገር ይባላል። እሱን ማለፍ አይችልም። ያገር ባህል የዋዛ አይደለም የደበቀውን ምስክር የሌለውን ያወጣል በጡት በጡት እናስታርቃለን፣ እናሳምናለን (ስክርብ፣46-47) በማለት ይገልፁታል።*

ሁለቱም ባለጉዳዮቹ ወተቱንና ደሙን በአፋቸው የያዙት እንጂ አይጠጡትም። ይህን ስርዓት ለመፈፀም የሚታረደው ነጭ ፍየል፣ ደምና ወተት በብሄረሰቡ ባህል የራሱ ተምሳሌት አለው። በብሄረሰቡ ነጭ ፍየል መታረዱ ወደፊት ብርሃን ይምጣልን፣ የተደበቀ ነገር ሁሉ ይውጣልን፣ሁሉም ነገር ብርሃን ይሁን ለማለት ሲሆን የወተቱና የደሙ

[96] *ሀይሉ(ስክርብ፣27፤ሀጂ ጃተኖ፣46፤ዲንቁላ፣47)።*

ውህደት የሁለቱን ሰዎች አንድነት፣ የወደፊት ትብብርና አብሮነት የሚወክል ነው። በብሄረሰቡ ነጭ ቀለም የቀን ተምሳሌት፣የብርሃን አቻ ተደርጎ ይወከላል።

ደምና ወተት ቀለማዊ ተቃርኖ የሚታይባቸው ነገሮች ናቸው። በብሄረሰቡ እነዚህን ተቃርኗዊ ነገሮች ቀላቅሎ ለእርቅ መጠቀም ደግሞ ግጭት ውስጥ በገቡት አካላት መካከል ጎልቶ የሚታየውን ተቃርኖ ለማጥፋት ነው። እንደ ደሙና ወተቱ ሁሉ በመካከላቸው ያለውን ተቃርኗዊ ስሜት፣ ፍላጎትና አመላካከት አጥፍቶ ውህደት ለመፍጠር ነው። ሁለቱ አካላት መዛመዳቸውም የሚታወቀውና የሚረጋገጠው በዚሁ የደምና ወተት ውህደት ነው።

በማረቆ ብሄረሰብ አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሞ ወይም የሰው ከብት ሰርቆ በመደበቅ የተበዳይን ጡት ቢጠባ የራሱ ሀብት ይጠፋበታል፣ በሽተኛ ይሆናል፣ ቤተሰቡን በሞት ይነጠቃል ተብሎ ይታመናል። ይህ ሀሳብ ሀጂ ጃተና በአብነት ሲያስረዱ፡-

**አብነት ሰባት**

> *ኮሞ ጎሼ የሚባል ሰውዬ ከብቶቹን ሰረቁት ሦስት ሆነው። ሦስት ሰዎች የስልጤዎችን ሰረቁ ከሰረቁ በኋላ ይህንን በጡት እንተማመን ተባለና ኮሞ ተጠርጣሪ ነበር የጡት ፕሮግራም ተያዘ ከዚህ ኮሞ ጎሼ ከተባለው ጋር ጡት ተጣቡ። ከዚያ በኋላ እሱ በጡት ላይ በዚያው በተዘጋጀው ፕሮግራም በቃል ኪዳኑ ላይ አላደረኩም ብሎ ማለ የነዚህ የስልጤዎችን ከብቶች አልወሰድኩም ብሎ ማለ። አመቱ ሳይደርስ ግን የሱ የበረት ከብት በሙሉ አለቀበት፣የልጆቹ እናት ዋና ሚስቱም ሞተችበት። ከዚያ በኋላ ሽማግሌ ፈልጎ እንደገና አመነ ያ ነገር ነው የጉዳኝ ብሎ ከፈለ። ከዚያ በኋላ እነዚያ ሰዎች መጥተው እግዚአብሄርን ለኛ ብለህ ተለመነን ይቅር በለው ብለው ቱፍ ቱፍ አሉለትና ተስተካከለ። አሁን ህይወቱ አለ ከብቱ አልመጣለትም እንጂ ይህ ነገር የደረሰንበት ነው(ስክርብ፣47)።*

በማለት የብሄረሰቡን እምነት ይገልፁታል።

ይህን ሀገረሰባዊ እምነት የሚፈሩት ማረቆዎች ከጡት መጣባት በፊት ጉዳያቸውን አምነው መታረቅን ይመርጣሉ። ጡት ተጣብተው ንፅህናቸውን ያረጋገጡ ባለጉዳዮች ወደ ፊት የሚኖራቸው መረዳዳትና ዝምድና ለትውልድ የሚተላለፍ ነው። በብሄረሰቡ እኛ "የጡት ሰዎች ነን" እየተባለ ለሚወለዱ ልጆች እየተነገረ ዝምድናው ይቀጥላል።

### 4.6.3 ሀገረሰባዊ እምነቶች የእርቅ ቦታና ቀንን ለመምረጥ

እንደ Ben Amos (1975:189) ሁሉም ቦታ የሚከወኑ የፎክሎር አሀዶችን ለመከወን ምቹ አይደለም። ብዙዎቹ ተከዋኝ አሀዶች የራሳቸው የመከወኛ ቦታና ጊዜ አላቸው። በማረቆ ብሄረሰብም እርቅ በማንኛውም ቦታና ቀን አይከናወንም። በብሄረሰቡ ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት በቀጣይ ለሚኖራቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት የሚበጅ

የሚሉት የማስታረቂያ ቦታና ቀን አላቸው። እነዚህ የእርቅ መፈፀሚያም ሆነ መጀመሪያ ቦታዎች ከሀገረሰባዊ እምነቶች ጋር ቁርኝት አላቸው።

በብሄረሰቡ እርቅ የሚከናወነው በተበዳይ ሰፈር ሲሆን ማጋዎች የሚመቻቸውን የዛፍ ጥላ ይመርጣሉ። በብሄረሰቡ ባህል ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን በቤት ውስጥ ማስታረቅ አይቻልም። የእርቅ ስርዓት ቤት ውስጥ የማይፈፀምበትን ምክንያት ሀይሉ፡-

> *እርቅ በማህበረሰባችን በቤት ውስጥ አይደረግም። ቤት ውስጥ እርቅ ቢደረግ ክፉ ነገር አብሮ ይገባል ተብሎ ስለሚታሰብ አይሞክርምም ማንም ይሁን አያስበውም። ምንም አስቸጋሪ ነገር ቢኖር ቤት ውስጥ አይከናወንም እርቅ ጥላ ስር ከተከናወነ ክፉ ነገር እዚያው ይቀራል፣ የግጭት መንፈሱ እዚያው ዛፍ ስር ይቀራል ተብሎ ይታሰባል። ከታረቁ ነው ወደ ቤት የሚገባው። ወደ ማን ወደ በዳዩ ቤት ነው የሚገባው። ጥላው ዋርካ ሊሆን ይችላል፣ ግራር ሊሆን ይችላል፣ ምሳና ሊሆን ይችላል ብቻ የትኛውም ለኛ ምቾት ይሰጠናል ተብሎ ነው እንጅ የሚመረጠው ሌላ ነገር የለም(ስክርብ፣26) በማለት ይገልፁታል።*

እርቁ በተበዳይ ሰፈር የሚሆንበት ምክንያት ሁለት ተምሳሌቶች ያሉት ሲሆን አንደኛው የበዳዩን አካል ፀፀት፣ ልመና፣ ጥፋተኝነት ለመግለፅና ተበዳይን አሳምኖ ይቅርታ ለማግኘት ነው። ሁለተኛው ማጋዎች በተበዳይ ሰፈር ሲቀመጡ የእርቅ ሂደቱ ይፈጥናል ተበዳይም ማጋዎችን በማክበር ተሎ ይታረቃል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ይህ አካሄድ የተበዳዩ ቤተሰብ ወይም ጎሳ በበዳዩ ቤተሰብ ወይም ጎሳ አልተናቅንም የሚል ስነ-ልቦናዊ የበላይነት እንዲላበሱ ስለሚያደርግ የሚከናወነውን የእርቅ ሂደትና እርቅ እንዲቀበሉ ይገፋፋል።

እርቅ ከረቡዕ እና አርብ ውጭ ባሉት ቀናት አይከናወንም። ብሄረሰቡ ረቡዕና አርብን የእርቅ ቀናት ናቸው ብሎ ስለሚያምን ማንኛውም አይነት ግጭት የሚፈታው በነዚህ ቀናት ብቻ ነው። እነዚህ ቀናት የተመረጡበትን ምክንያት ሀጅ ጃተኖ(ስክርብ፣42) "ቀኖቹ ጎበዝ ጎበዝ ቀኖች ናቸው። ሰው ሲመጣ አመጣጡ በማክሰኞ ይላል፣ ሰኞም ይላል፣ ሀሙስም ይላል እሁድም ይላል፣ ቅዳሜም ይላል፣ አርብና እሮብ ግን የደም ነገር ነው የሚነገረው ተብሎ አድሯል ድሮ የመጣ ክርስቲንም ቢሆን እስላም በነዚህ ቀናት ይስመናል" በማለት የብሄረሰቡን አመክንዮ ይገልፃሉ።

ለብሄረሰቡ ረቡዕና አርብ ከክፉ መንፈስ ጋር ግንኙነት ያላቸው የእርግማን ቀናት ናቸው። በማረቅዎች ከረቡዕና አርብ ውጭ ያሉት ቀናት ለሰርግ፣ ለልደትና ልጃገረድ ለማጨት የሚያገለግሉ ደጋግ ቀናት ተብለው ይጠራሉ። ዕረቡና አርብ ደግሞ በተሰጣቸው ባህላዊ

ተምሳሌት መነሻነት ደም ለማድረቅና በተለያዩ ነገሮች የተከዳዱ የብሄረሰቡ ተወላጆች የሚማማሉባቸው ደረቅ ቀናት ናቸው::[97]

በአጠቃላይ ብሄረሰቡ ግጭትን የጥቃት መመለሻና ጥቅም ማስከበሪያ ያየዋል። በደል የተፈጸመበት የብሄረሰቡ ተወላጅ መጀመሪያ ላይ የተፈፀመበትን በደል ይበቀላል ተብሎ የብሄረሰቡ ማጋዎችና ራጋ ተበዳይን በመሳመን ግጭቱን በእርቅ ይቋጩታል። በብሄረሰቡ በርካታ ግጭቶች ቢኖሩም በተደጋጋሚነት የሚከሰቱት የቤተሰብ ግጭቶች፣ ከጥሬ ሀብት ውስንነት ጋር የተያያዙ ግጭቶች፣ ወንጀሎች እንዲሁም የጎሳና የብሄረሰብ ግጭቶች ናቸው። ግጭቶቹን ለመፍታትም የቤተ- ዘመድ ጉባኤ፣ ማጋና ራጋ የሚባሉ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን እንደሚጠቀሙ ለማየት ተችሏል። ተቋማቱ የየራሳቸው የግጭት አፈታት ሂደት ያላቸው መሆኑን በሰፊው ለማየት ተችሏል። በዚሁ ምዕራፍ ሴቶች በግጭት አፈታት ሂደቱ ላይ ጉልህ ተሳትፎ እንዳላቸው ጥናቱ አሳይቷል።

[97] *ሀጂ ጃተሞ እና ሀይሉ (ስክርብ፣42፣ ዲንቀላ፣43)::*

# ምዕራፍ አምስት

## የራጋ ማጋና መደበኛው የፍትህ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር በማረቆ ብሄረሰብ

*ባህላዊ እርቅ እንደ መደበኛው የፍትህ ተቋም ሁሉ እንደ አንድ የፍትህ መስጫ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል። እንዴት ነው በአብዛኛቸው በማረቆ ብሄረሰብ ውስጥ በባህላዊ መንገድ ብዙ ችግሮች ይፈታሉ። አሁን ከባድ ወንጀል የምንላቸው ከነፍስ ግድያ ተያይዞ ያለው ነገር ራሱ በባህል ተይዞ የሚያልቅበት አግባብ አለ። ማለት ሰውዬው በወንጀሉ በፍርድ ቤት ቢቀጣም ወደ ቤተሰቡ ከተመለሰ በኋላ በአካባቢው ከህብረተሰቡ እንዲቀላቀል፣ ቤተሰቡ ሌላ ጉዳት እንዳይደርስበት በሰላም እንዲኖር ሽማግሌ ባህል አለ፣ የማረቆ ባህል ጥቁር ፍየል አርደው በዚያ መልኩ አስታርቀው የሞተው ቀርቶ ያለው እንደ ልጅ ሆኖ ቤተሰብ እንደ ምትክ አድርጎ ቆጥሮ የሚተሳሰቡበት ባህል ነው ያለው። ጥሩ ነገር ነው ከዚያ በኋላ እንደገና ጥሩ ተግባብተው የሚኖሩበት አግባብ ነው ያለው። በዚያ መልክ አግባብተው ሰው በሰላም እንዲኖር ያደርጋሉ። እንግዲህ ከዚህ በላይ ትልቅ ወንጀል የለም(ሳጅን ግርማ፣ስክርብ፣86)።*

የወረዳው ፖሊስ አዛዥ ሳጅን ግርማ እንደገለፁት በራጋ ማጋ የሚፈፀመው እርቅ በመደበኛው የፍትህ ተቋም ተቀባይነት ያለው ሲሆን ተቋሙም እንደ አንድ የፍትህ ተቋም ይታያል። ብሄረሰቡም የራጋ ማጋ ስርዓትን ከጥንት አባቶቻቸው የወረሱት በመሆኑ ወደፊትም ተጠብቆ እንዲኖር ይፈልጋሉ።[98]

በዘመናዊው እውቀት ህግ ተረቆላቸውና መመሪያ ወጥቶላቸው የሚንቀሳቀሱ የማረቆ ወረዳ የፍትህ ተቋማት በተለይም ፍርድ ቤት፣ አቃቢ ህግና ፖሊስ እንዲሁም የሴቶችንና የህጻናት ጉዳይ ቢሮ ከማረቆ ብሄረሰብ የራጋ ማጋ እርቅ ጋር በአንድነት የሚሰሯቸው ስራዎች ብዙ ናቸው።

ፍትህን ለማስፈን የሚንቀሳቀሱት የመደበኛው የፍትህ ተቋማት የተነሱበት መሰረታዊ አላማ ለብሄረሰቡ የተሟላ የፍትህ አገልግሎት መስጠት ቢሆንም አሰራራቸውና የስራ ድርሻቸው የተለያየ ነው። ይሁን እንጅ አንዱ የፍትህ ተቋም ለሌላኛው የፍትህ ተቋም የመረጃ ግብዓትን በማሟላት የትብብር ስራዉ የተቃና እንዲሆን ይጥራሉ።

ፖሊስ ተፈፀመ በተባለ ወንጀል ላይ መረጃ በማጠናቀር፣ አቃቢ ህግ በመክሰስ እንዲሁም ፍርድ ቤት ለቀረበለት ክስ ውሳኔ መስጠት ተለጣጣቂነት ያለው የቅንጅት ስራ ይሰራሉ። የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ደግሞ ከፖሊስና ከአቃቢ ህግ ጋር በመቀናጀት የሴቶችንና የህፃናትን መብቶች ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል።

---

[98] ሀይሉ(ስክርብ፣18፣አበጋዝ ሙር፣84)።

የእነዚህ ተቋማት የመጨረሻ ግብ ተመሳሳይ ቢሆንም በዚህ ርዕስ ስር ተቋማቱ ከሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ጋር ያላቸውን የቅንጅት ስራ በተናጠል በቀጣይ ይዳሰሳሉ፡-

## 5.1. ራጋ ማጋ ከፍርድ ቤትና ከአቃቢ ከህግ ጋር ያለው ግንኙነት

በማረቆ ብሄረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶች በሀገረሰባዊውና በመደበኛው የፍትህ ተቋማት የጋራ ትብብር መፍትሄ ይሰጣቸዋል። እነዚህ ተቋማት በብሄረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን ግጭቶች እንደ ግጭቶቹ አይነት በተናጠልና በቅንጅት እንደሚፈቷቸው የብሄረሰቡ የሀገር ሽማግሌዎችና የመደበኛው ፍትህ ተቋም ባለሙያዎች ይገልፃሉ።[99]

የሁለቱን የፍትህ ተቋማት የጋራ ትብብር በተመለከተ የወረዳው ፍርድ ቤት ዳኛ የሆኑት መላኩ[100](ስክርብ፣58) በሰፊው እንደሚገልጹት ግጭቶችን በሽማግሌዎች በመፍታት ሰዎች ሰላማዊ ህይወት እንዲመሩ ማስቻል የሁለቱ የፍትህ ተቋማት የጋራ ስራ ነው። ሁለቱን የፍትህ ተቋማት አቀናጅቶ በመስራቱም ተበታትኖ የሚኖረው ህዝብ ጊዜውን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን ቆጥቦ ልማቱን እንዲያለማ እያደረገው ነው።

ራጋ ማጋን የሚመሩት የሀገር ሽማግሌዎች የመደበኛው ፍትህ ተቋም አጋዥና የስራ ጫናን የሚያቃልሉ ናቸው። የብሄረሰቡ ማጋዎች እርስ በርስና ከቤተሰብ ጋር የተገናኙ ግጭቶችን በተለይም የባልና ሚስት ግጭቶች በተመለከተ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጋር ተቀናጅተው ይሰራሉ። ፍርድ ቤትም በሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋማት የተሰጡ ውሳኔዎች በይሁንታ ተቀብሎ ያፀድቃል። ይሁን እንጅ በፍርድ ቤት ብቻ የሚታዩና ለሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋማት የማይፈቀዱ ግጭቶች አሉ። ይህን ሀሳብ የብሄረሰቡ የሀገር ሽማግሌ ሀይሉ፡-

> *ሽማግሌ የጨረሰበትን ነገር በሰነድ ይዞ ለፍርድ ቤት ይሰጣል። በዚህ አይነት እኔም ሰብሳቢ ሆኜ በዳኛ ተሰይሜ ሰርቻለሁ ከአሁን በፊት ማለት ነው። በሽማግሌ ውሳኔ መሰረት ውሳኔውን አጽንቻለሁ ብሎ ፍርድ ቤቱ ክሱን ወደ መዝገብ ቤት ያለበት ጊዜ ብዙ ነው። ስለዚህ ጎን ለጎን ነው የሚሄደው። ፍርድ ቤቱም ይህ የሽምግልና ስርዓቱ ሽማግሌ የመብቱን ደረጃ አውቆ ከሰራ ችግር የለውም። ደረጃዎች አሉ፤ ሽምግልናው የሚያያቸው መለስተኛ ችግሮችን ነው (ስክርብ፣51)።*

[99] *ሀጂ ጃተኖና ዲንቁላ (ስክርብ፣45፤ ሀይሉ፣51፤መላኩ፣58-65፤ታደለ፣66-72፤ ወርቅነህ፣69-73)፤ አበጋዝ ሙርኪ፣82)፤ አበጋዝ ጃቢሶ፣83) ሳጀን ግርማ፣86-91)።*

[100] *ረቡዕ የካቲት 7-2004 ዓ.ም፣መላኩ ፈቃዱ አባላለሁ። የማረቆ ወረዳ ፍርድ ቤት የፍርድ ኦፊሰር ነኝ። የፍርድ ኦፊሰር ማለት የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራል፣ተከሳካይ ጠበቃና ረዳት ዳኛ የሚለውን አጠቃሎ የያዘ ነው። እድሜዬ 29 ነው። የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጅ ነኝ።*

በመደበኛው ፍርድ ቤት የማስላሰያ ጊዜ[101] የተሰጣቸውን የባልና ሚስት ግጭት በቀጥታ የሚያዩት በፍርድ ቤቱ አጋዥነትና በባለጉዳዮቹ የጋራ አቅራቢነት የተመረጡት ሽማግሌዎች ናቸው። የብሄረሰቡ ማጋዎች ከወረዳው ፍርድ ቤት በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ሁለቱን ያስማማሉ። ይህን ሀሳብ መላኩ (ስክርብ፣59) "ሽማግሌ አስታርቆ ካመጣልን የታረቁበትን በመመዝገብና በማጽደቅ የሽማግሌውን ውጤት ተቀብለን ነው እንግዲህ የምንሸኘውና የእነሱን እ…በባህላዊ ያደረጉትን እርቅ ወደ ዘመናዊ ለውጠን የምናጸድቀው" በማለት ሁለቱ የፍትህ ተቋማት ያላቸውን የቅንጅት ስራ ይገልፁታል። ይህን ሀሳብ መላኩ አብነት ጠቅሰው ሲያብራሩ፡-

*አብነት ስምንት*

> *…እም ለምሳሌ በባልና ሚስት ፍቺ ዙሪያ የምነግርህ ነገር ቢኖር ለምሳሌ ከሳሽ መርክብ ሰይፉና ተከሳሽ አቶ ደረጀ ደመቀ የሚባሉ እዚህ ቆሼ ከተማ ውስጥ ማረቆ ወረዳ የምስጋና ሆቴል ባለቤት ከሚስቱ ጋር የተወሰነ ግጭት ኖሯቸው ሚስትዬዋ እዚህ ፍቺ ልትጠይቅ መጥታ ነበር። ነገር ግን ፍርድ ቤቱ በሰጠው የማስላሰያ ጊዜና ሽማግሌ ባቀረበልን ሪፖርት መሰረት ታርቀው የዛሬ ዓመት አካባቢ ነው በአሁኑ ሰዓት በሰላማዊ ሁኔታ ሽማግሌ ባቀረበውና ባስታረቋቸው መሰረት ፍርድ ቤቱ የሽማግሌዎችን ሪፖርት ተቀብሎ አፅድቆ በአሁኑ ሰዓት በሰላማዊ ሁኔታ ልጆቻቸውን እያሳደጉ ነው፤ኑሮአቸውን እየመሩ ያሉበት ሁኔታ አለ (ስክርብ፣61)።*

በማለት የፍርድ ቤቱንና የራጋ ማጋን ግንኙነት ይገልጹታል።

ይህ የሚያሳየው ሁለቱ የፍትህ ተቋማት ያላቸውን የርስ በርስ ግንኙነት ነው። ሁለቱ ተቀናጅተው መስራታቸው የመፍረስ አደጋ የተጋረጠበትን የትዳር ህይወት በመመለስ ለተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቦናዊ ችግሮች ሊጋለጥ የቀረበን ቤተሰብ እየመለሱ መሆኑን በተግባር የሚያረጋግጥ ነው።

ሁለቱ የፍትህ ተቋማት በጋራ የሚሰሯቸው ፍትህን የመስጠት ስራዎች ከተራና ቀላል ከሆኑ ግጭቶች እስከ ከባድ ወንጀሎች ድረስ ነው። እንደ መላኩ ገለፃ እንደ ስድብ፣ ማዋረድና ዛቻ ያሉ ቀላል ወንጀሎች ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ በሽማግሌዎች እንዲያልቁና ብሄረሰቡም ስራ እንዳይፈታ ጥረት ይደረጋል። ይህን የራጋ ማጋ እርቅ ጠቀሜታና አማራጭነት መላኩ፡-

> *አንድ ቀበሌ ሰሜን ቆሼ እዚህ ቅርብ ቢሆንም እንደ እርጎ ሩቅ አለ፤ እንደ ሸሪንቶ ሶስት እንደነዚህ ባሉ አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች እዚያው የተነሳውን ግጭት በቀላሉ ሊያበርዱ የሚችሉ ግጭቶችን እንደ ማዋረድ ዛቻና ስድብ የመሳሰሉትን እዚያው ጨርሰው*

[101]በብሄረሰቡ ራጋ ማጋ እንዲያልቁ የሚፈለጉ ግጭቶችን በዚሁ ምዕራፍ 5.4 ላይ በስፋት ተዳሶ ቀርቧል።

*አርሶ አደሩ እዚያው ልማቱን ቢያከናውን እንዴና ዋናው አማራጭ ነው (ስክርብ፣61) በማለት ይገልጹታል፡፡*

የማረቆ ወረዳ ፍርድ ቤትና የብሄረሰቡ ማጋዎች ከውርስ ጋር የተገናኙ ግጭቶችንም በጋራ ይፈታሉ፡፡ በብሄረሰቡ ከውርስ ይገባኛል ጋር የተያያዙ ክሶች ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪ ማጋዎችን በማቋቋም ንብረቱ እንዲጣራ ይደረጋል፡፡ እንደ ወልዩ (ስክርብ፣50፣መላኩ፣59) ገለጻ የውርስ ይገባኛል ጥያቄ የቀረበበት ንብረት ከተጣራ በኋላ ባለጉዳዮች በማጋዎች እንዲስማሙ ፍርድ ቤት ፈቃድ ይሰጣል፡፡ ባለጉዳዮችም በማጋዎች ከተስማሙ የማጋዎች ውሳኔ በፍርድ ቤት ፀድቆ የቀረበው ክስም ተዘግቷል ተብሎ ወደ መዝገብ ቤት ይላካል፡፡ ከዚህ በኋላ በዚህ የውርስ ይገባኛል ጥያቄ ቢነሳ ፍርድ ቤት አያስተናግድም፡፡

የማርቆ ወረዳ ፍርድ ቤት የግድያ ወንጀሎችን ከባህላዊ የፍትህ ተቋም ጋር በመሆን በጋራ ይፈታል፡፡ የሰው ህይወት ያጠፋ የብሄረሰቡ ተወላጅም ሆነ ከብሄረሰቡ ተወላጅ ውጭ የሆነ ሰው ለሟች ቤተሰብ ጉማ ከከፈለ በመደበኛው ፍርድ ቤት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ይታይለታል፡፡[102] ይህ የቅጣት ውሳኔ አንድ ወንጀለኛ በአንድ ወንጀል ሁለት ጊዜ ሊቀጣ እንደማይችል ከሚገልፀው የኢትዮጵያ የህግ ድንጋጌ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይህን ጉዳይ መላኩ አብነት ጠቅሰው ሲያስረዱ፡-

አብነት ዘጠኝ

*ለምሳሌ አንድ የማረቆ ተወላጅ ከዚህ አካባቢ በመኪና ቢገጭና ቢሞት የተገጨው ልጅ ለምሳሌ ባለፈው ወር[103] አካባቢ አንድ ፈረንጅ እዚሁ አካባቢ በመኪና ገጭቶ ሰው ገድሎ ነበር፡፡ የሰባት አመት ልጅ ነች፤ ልጅቷ ሞታለች፡፡ ያ ፈረንጅ ግን ቀጥታ በባህላዊ መንገድ በማረቆ ብሄረሰብ ሴራ ደሟን አውጥቶ፣ ለደም የወጣውን በጠቅላላ ከፍሎ ከጨረሰ በኋላ እንግዲህ ሊገጭ አይደለም የወጣው ይህን ነገር ተቀብሎ ፍርድ ቤቱም በራሱ አነሳሽነት አስተያየት ያደረገበትና ሰውዬውን (ፈረንጁን) በገደብ ቅጣት የለቀቀበት ሁኔታ አለ (መላኩ፣ ስክርብ፣61) በማለት ይገልጹታል፡፡*

እንደባለሙያው ገለፃ በመኪና አደጋ የግድያ ወንጀል የፈፀመው ፈረንጅ በህገረሰባዊው እና በመደበኛው ፍርድ ቤት ቅጣት ተጥሎበታል፡፡ ይሁን እንጅ በባህሉ የተጣለበትን ቅጣት በመወጣቱ በመደበኛው ፍርድ ቤት የሚጣልበትን ቅጣት ቀንሶለታል፡፡ አንድ ወንጀለኛ ባጠፋው ጥፋት ሁለት ጊዜ መቀጣት እንደሌለበት ብሄረሰቡ ያምናል፡፡ ይሁን እንጅ ባህሉን

---

[102] *ሀይሉ(ስክርብ፣18)፤መላኩ(ስክርብ፣59)፡፡*

[103] *ይህን መረጃ የሰበሰብኩት የካቲት ላይ ነው፡፡ መረጃ አቀባዩ ባለፈው ወር ሲል ጥር ላይ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡*

ለማክበርና ከሟች ቤተሰብ ጋር ዝምድና ለመፍጠር ሲባል እርቁ ይከናወናል። ይህንንም ሀይሉ (ስክርብ፣18) "እንዲሁ ባህሉን ጠብቆ ጉዳዩ በማጋና በራጋ ታይቶ ከሟች ቤተሰብ ጋር እርቀ-ሰላም ለማውረድ፣ ጉዳ ለማሰር ያህል፤ዝምድና ለመፍጠር ያህል መገናኘት፣ መታረቅ ስላለባቸው ነው። ይህ ራሱ ከህግ ጋር አይጋጭም፤ በአንድ ጥፋት ሁለት ጊዜ አይጠየቅም" በማለት ገዳይ ከሟች ቤተሰቦች ጋር ዘላቂታዊ የሆነ ሰላምና ዝምድና ለመፍጠር የህግ ቅጣቱን ጨርሶ ሲወጣ የራጋ ማጋን ስርአት ጠብቆ እንደሚታረቅ ይገልፃሉ።

የማረቆ ወረዳ ምርመራና ክስም ከብሄረሰቡ ማጋዎች ጋር ተባብሮ ይሰራል። ማጋዎች ፍርድ ቤት መድረስ የለበትም የሚሉትን ግጭት በየስፈሩ ይፈታሉ። ይሁን እንጅ በመደበኛው የፍትህ ተቋም ማለቅ አለበት የሚሉትን ግጭት ወደ ፍርድ ቤት ይወስዱታል። ይህን ሀሳብ የመደበኛው ፍርድ ቤት አቃቢ ህግ የሆኑት ታደሰ (ስክርብ፣66) "ከሁለቱ አንዱ ካልተስማማ ምን አልባት ተበዳይና በዳይ በባህሉ መሰረት አንስማማም ካሉ ወደ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ምርመራና ክስ ይዘውት ይመጣሉ" በማለት የብሄረሰቡን ማጋዎች የስራ ሃላፊነትና አስተዋፆ ይገልጹታል።

ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም የህዝብንና የመንግስትን ጥቅም የማይጋፋ ተራ ግጭቶችን እንዲፈቱ ህግ ከለላ ሰጥቷቸዋል። በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ያልተከሰተባቸውን ውሳኔዎች በየጊዜው ተቀብሎ በማፅደቅ ያጸናቸዋል። የብሄረሰቡ ማጋዎችም በመደበኛው የፍትህ ተቋም የተሰጣቸውን ሀላፊነት በአግባቡ ይወጣሉ።[104] በራጋ ማጋ የሚከናወን የቀላልም ይሁን የከባድ ግጭት እርቅ ከመደበኛው የፍትህ ተቋም አላማና ግብ ጋር አይቃረንም። ይህን የህግ ጥሰት የሌለበትን ውሳኔ የሚያሳልፉት ከመደበኛው የፍትህ ተቋም የሚነገራቸውን ትእዛዝና መመሪያ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ማጋዎቹ ይናገራሉ።[105] ይህን ሀሳብ አበጋዝ ጃቢቦ (ስክርብ፣83) "...እዎ እነሱም ይነግሩናል ከህግ በታች ሆናችሁ እናንተን የሚመለከትን ነገር ትሰራላችሁ ይላሉ። እኛም ህግን ደግፈን ነው የምንሰራው፤ህግ የሚለውን አናፈርስም። አሁን የጠለፋን ጉዳይ ህግ እንደሚጠላ እኛም እንጠላለን" በማለት ከመደበኛው የፍትህ ተቋም ጋር ያላቸውን የጠበቀ ግንኙነት ይገልፁታል።

---

[104] መላኩ(ስክርብ፣63፤ታደሰ፣67)።

[105] ሀይሉ(ስክርብ፣24፤ሀጂ ጃተኖና ዲንቂላ፣45፤አበጋዝ ሙርኪ፣82፤ አበጋዝ ጃቢቦ፣83)።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## 5.2. ራጋ ማጋ ከፖሊስ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር

> *ሽማግሌዎቹና እኛ እንተጋገዛለን። ወንጀልን በጋራ ነው የምንከላከለው። ህብረተሰቡና ፖሊስ በጋራ ሆነን ነው ወንጀልን የምንከላከለው። ብቻችን እንስራ ብንል ወንጀልን ማጥፋት አንችልም። ወንጀልን ማጥፋት የምንችለው ከህብረተሰቡ ጋር ነው። እኛ በአብዛኛዎቹ ጊዜ ወንጀሎች ሲፈፀሙ ሽማግሌዎችን አሰባስበን ነው የማወጣጣት ስራ የምንሰራው። ሽማግሌዎች ደግሞ ሰፈር ውስጥ ገብተው የመረጃ ስራ ሰርተው የማውጣጣት ስራ አለ። እናም ውጤታማ የሚያደርግበት አገባብ አለ። ከባድ ወንጀል ሳይቀር ተፈፅሞ አባት ያላገኘ ወንጀል[106] እንዲገኝ የማድረግ፣የማውጣጣትና አውጥተውም ለፍትህ አካል የመስጠት ሁኔታ አለ፣እስከ ግድያ የደረሱ ወንጀሎችን አውጥተው ለፖሊስ ሰጥተው ማረሚያ የገባበት ሁኔታ አለ(ሳጅን ግርማ[107] ፣ስክርብ፣88)።*

የማረቆ ብሄረሰብ ማጋዎች ከወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ጋር በመተባበርም የብሄረሰቡን ሰላም ይጠብቃሉ። የማረቆ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ከፖሊስ ጋር በመተባበር በየሰፈሩ የሚፈፀሙ የዘረፋ ወንጀሎችን አጋልጦ በመስጠት ተበዳ አካላት ተገቢ ፍትህ እንዲያገኙ ያደርጋሉ። ይህ የሚከናወነው ፖሊስ የብሄረሰቡን አባላት በማሰባሰብና የአውጫጭኝ ስራ በመስራት ነው። ይህ አሰራር በብሄረሰቡ ይከሰቱ የነበሩትን ወንጀሎች ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ከማስቻሉም በላይ ወንጀለኞችን ለማደንና ለመከላከል ይወጡ የነበሩ ጥሬ ሀብቶችን በተለይ የሰው ሀይል፣ ገንዘብና ጊዜ ለመቆጠብ አስችሏል። ይህ ደግሞ ጥሬ ሀብቶቹ በሌሎች ልማታዊ ስራዎች ላይ እንዲውሉ የሚያግዝ በመሆኑ የተቋሙን ሚና አጉልቶ ያሳያል።

ማጋዎች በወንጀል ተጠርጥሮ በቁጥጥር ስር የዋለን ሰው ከፖሊስ ጋር በመነጋገር እርቅ እንዲወርድ ያደርጋሉ። በተለይ በብሄረሰቡ ባል ከሚስቱ ጋር ተጣልቶ ሲታሰር ማጋዎች ለፖሊስ የእናስታርቅ ጥያቄ በማቅረብ ያስማማሉ። ማጋዎች የባልና ሚስቱን የበፊት አኗኗር ለፖሊስ በማስረዳትና በማሳመን በእስር ላይ ያለው ባል እንዲለቀቅና ከሚስቱ ጋር ታርቆ ቤተሰቡን በሰላም እንዲያስተዳድር የትብብር ስራ ይሰራሉ።

በሌላ መልኩ ባልሰራው ወንጀል የተከሰሰን የብሄረሰቡን አባል በማጋዎች ጥያቄ ከከሳሽ ጋር እንዲታረቅ ይደረጋል። ይህም ሲሆን የብሄረሰቡ ማጋዎች የተከሳሹን የቀደመ ታሪክና የክሱን መነሻ ምክንያት ለፖሊስ ግልጽ በማድረግ የሁለቱ አካላት መታረቅ ለወደፊት የቤተሰባቸው ግንኙነት አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ ግጭቱ በእርቅ እንዲያልቅ ይደረጋል።

---

[106] አባት ያላገኘ ወንጀል ማለት ድብቅ ወንጀል ማለት ነው።
[107] ማክሰኞ የካቲት 13-2004 ዓ.ም፣ ሳጅን ግርማ ንጉሴ እባላለሁ። የማረቆ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ነኝ። እድሜዬ 38 ዓመት ሆኖኛል። የማረቆ ብሄረሰብ ተወላጅ ነኝ። ለብዙ አመታት በዚሁ ሀላፊነት ከዚህ ወረዳ ሰርቻለሁ።

### 5.3. ራጋ ማጋ ከሴቶች ጉዳይ ቢሮ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትና በተለያዩ አዋጆች የጸደቁትን የሴቶችንና የህጻናትን መብቶች ለማስጠበቅ በመንግስት የተዋቀረው የማረቆ ወረዳ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ከሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ጋር በመቀናጀት ከሴቶችና ከህጻናት መብቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግጭቶች ለመፍታት ይጥራል።

ሀገረሰባዊውን የፍትህ ተቋም የሚመሩት ራጋና ማጋዎች ከዚህ የመንግስት ተቋም ጋር በመሆን በመንግስትና በብሄረሰቡ "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች"[108] ተብለው የተፈረጁት ለማስቆም ይሰራሉ። ይህንንም ወርቅነህ፡-

> *በሽማግሌዎች ዙሪያ ጉጂ ልማዶች ላይ በጣም እንሰራበታለን። ይህም በምሳሌ በግርዛት ዙሪያ እዚህ አካባቢ ላይ በህገ መንግስቱ እና በህገ ደንቡ ላየ የተቀመጠው እንዳለ ሆኖ እኛ በራሳችን ሽማግሌዎችን ተርተን በሰጠናቸው ስልጠና መሰረት...አምስት አምስት ሽማግሌዎች ቢያንስ በየቀበሌ ደረጃ ጠርተን በሰጠናቸው ስልጠና መሰረት የራሳቸውን ህገ ደንብ አላቸው (ስክርብ፣69-70) በማለት ይገልጹታል።*

ይህ የመንግስት ተቋም በብሄረሰቡ ተሰሚነት ያላቸውን ማጋዎች የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ኮሚቴ ብሎ በማቋቋም የሴቶችንና የህጻናትን መብቶች ያስጠብቃል። ይህን በተመለከተ የወረዳው የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ምክትል ሀላፊ የሆኑት ወርቅነህ (ስክርብ፣70) "በወረዳ ደረጃ 210 የሚሆኑ የጎጂ ልማድ ድርጊቶች አስወጋጅ ኮሚቴ አሰልጥነን እስከታች ቀበሌ ድረስ ወርዶ በየጎጡ፣ በየቀበሌው ሁለት ሁለት መቶ ሰዎችን እንዲያሰለጥኑ አድርገን አሁን በኛ ዞን ውስጥ ካሉት ወረዳዎች የተሻልን ነው" በማለት ማጋዎች በየቀበሌው ያለውን ህዝብ ስለ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲያስተምሩ ሀላፊነት የተጣለባቸው መሆኑን ይገልፃሉ። ይህ የሁለቱ የፍትህ አካላት ያላቸውን የጠበቀ ግንኙነት ከማሳየቱም በላይ የስራቸውንም ጥልቀት በግልፅ ያሳያል።

በየቀበሌው የሚገኙ የብሄረሰቡ ማጋዎች "ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን" ለማጥፋት የራሳቸውን የመተዳደሪያ ደንብ አውጥተው እንደሚንቀሳቀሱ የባለሙያው ገለፃ ያሳያል። እንደ ወርቅነህ ማብራሪ ከሆነ የብሄረሰቡ ማጋዎች በየቀበሌያቸው "ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች" የፈፀሙ

---

[108] *ሀሙስ የካቲት 8-2004 ዓ.ም፣ወርቅነህ ማሌሞ አባላለሁ። የማረቆ ወረዳ ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ተወካይ ነኝ። ብሄረሰቡ ተወላጅ አይደለሁም። ይሁን እንጂ ለ8 ዓመታት ያህል በዚህ ቢሮ ውስጥ ሰርቻለሁ። እድሜዬ ከሰላሳ ኣለት በላይ ነው።*

ኀሄረሰቡ ተወላጆችን ለህግ አሳልፈው በመስጠት፣በራሳቸው ህግ በመቅጣትና በማስተማር
ሰሩት ወንጀል" እንዲማሩ ያደርጋሉ።

ቤቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮም ከማጋዎች ጋር በመተባበር ወንጀሎችን ይመረምራሉ። ብብር ወንጀሎችን መመርመራቸውም በስም ማጥፋት ክስ የተመሰረተባቸውን የብሄረሰቡ ወላጆች ነፃ እንዲወጡም ያደርጋሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ወርቅነህ ያጋጠማቸውን አብነት ቅሰው ሲያስረዱ፡-

*አብነት አስር*

*አንዲት ሴት ልጅ እንደዚሁ ህፃን ተደፍሬያለሁ ምናምን ብላ በቀረበች ጊዜ ላይ የሆነ ነገሩ የማስተባበያ ነው፤ ከዚህ በፊት የህፃኗ እናት እዳ ስለወሰደች ልጁ ደግሞ ለዚያ እዳ ትኩረት ሰጥቶ ስለሚመጣ ብቻ ይህንን እንደ አስገድዶ መድፈር ወንጀል አድርጎ ቆጥሮ ህፃኗን ያለ አግባብ እንዲህ አድርጓል ብለው ነው እስከዚህ ደረጃ ድረስ ያመጡት በማለት መጥተው ሽማግሌዎች በመውሰድ እንደገና ሽማግሌዎቹ በራሳቸው አስታርቀው ያመጡበት ሂደት ነው ያለው (ወርቅነህ፤ስክርብ፣71)።*

ህን አይነት ወንጀል ለመከላከልና ወደ ክስ የሚመጡ ሰዎችን ወደ ቀደመ ግንኙነታቸው መመለስ ማጋዎች ሚናቸው የላቀ ነው። ማጋዎች ተቀባይነት ማግኘታቸው በሀሰት ንጀላ ወደ እስር ቤት የሚወረወሩ ሰዎችን ከመታደጋቸውም በላይ በወረዳው ፍትህ ነዳይጓደል ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። ማጋዎች በመደበኛው ፍትህ ተቋም በቀላሉ ቀባይነት የሚያገኙት ከህዝቡ ጋር አብረው የሚኖሩ በመሆናቸው እያንዳንዱን የብሄረሰቡን ንቅስቃሴ ያውቃሉ ተብሎ ስለሚገመትና በብሄረሰቡም ስለሚከበሩ ድብቅ ወንጀል ማጋዎች ስለማያመልጥ ነው።

## 4. በመደበኛው የፍትህ ተቋም መፍትሔ የሚሰጣቸው ጉዳዮች

ማረቆ ብሄረሰብ የራጋ ማጋ የእርቅ ስርአት በተለያየ ምክንያትና አጋጣሚ የሚከሰቱ ጭቶችን በመፍታት ለብሄረሰቡ አባላት የተሟላ የፍትህ ስርዓት እንዲኖር አስተዋጾው ቀ ነው። ይሁን እንጂ ተቋሙ እንዳይፈታቸው የታገዱ የግጭት አይነቶች አሉ። በተለይ መንግስትን ፖሊሲ እና የህዝብን ጥቅም ይጋፋሉ የሚባሉ ጉዳዮች እንደ ግርዛት፣ ጠለፋ፣ ቷያ፣ አስገድዶ መድፈር ያሉ ወንጀሎች በራጋ ማጋ የሽምግልና እርቅ አይታዩም። ይህን ነብ የማረቆ ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ የሆኑት መላኩ ሲያብራሩ፡-

*ፍርድ ቤት አንዳንድ መብቶችን የሚዘነጋ ውሳኔ ወይም ደግሞ የህጻናትን ጉዳይ በተመለከተ ወደ ሽማግሌ የሚላክበት ጉዳይ የለም።ሌላው መሰል ጥቃቶችን በተመለከተ ጉዳዩ በሽማግሌ እንዲታይ አንፈቅድም። ከባባድ ወንጀሎችና ፍትሐብር ኬዞች በኛ በኩል ነው የሚታዩት። ባህላዊው የፍትህ ተቋም እና እኛን የሚያስተሳስረን አንዳንድ ነጥቦች አነሳሁልህ እንጅ*

መንግስት በሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ላይማ የሚያስተሳስረንም የሚያገናኘንም የለም (ስክርብ፤64)።

ወረዳው ፍርድ ቤት ባለሙያዎች (መላኩ፤ስክርብ፣65፤ ታደሰ፣68፤ ወርቅነህ፣71) ህዝብንና የመንግስትን ጥቅም ይጋፋሉ የሚባሉት ጉዳዮች በመደበኛው የፍትህ ተቋም ብቻ ንዲታዩ የሚደረገው የራጋ ማጋ የሽምግልና እርቅ ለወንጀሎቹ አስተማሪ የሆነ ቅጣት ለማይሰጣቸው ወንጀሎቹ አይቆሙም ስለሚባል ነው። ይህን ሀሳብ ታደሰ (ስክርብ፣68) አንዳንዶቹ እከሌ መቼ ተቀጣና ብለው ይባስ ብዙ ወንጀሎችን ሊሰሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰል ጉዳዮችን አንዘላቸውም፤እንዲቀጡና እንዲታረሙ ይደረጋል" በማለት የፍርድ ቤቱን ቋም ይገልጻሉ።

ነዚህን ወንጀሎች የፈፀመ ግለሰብ ወይም ቡድን በመደበኛው የፍትህ ተቋም ተመጣጣኝና ስተማሪ የሆነ ቅጣት ይጣልበታል። በመደበኛው የፍትህ ተቋም የተወሰነበትን ቅጣት ተቀበለ በኋላ ደግሞ ባህሉ የሚያዘውን ይፈፅማል። በተለይ ወንጀሉ ግድያ ከሆነ ገዳይ ሟች ቤተሰብ ጋር መታረቅና ዝምድና መፍጠር ስላለበት የባህሉን ስርዓት መፈጸም ያኖርበታል። ይህን ሀሳብ ሀይሉ (ስክርብ፣18) "እስራቱን ጨርሶ ከተመለሰ በኋላ ማህበረሰቡ ጋር በሰላም ሊቀላቀል የሚችለው በሽማግሌ ከታረቀ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ግን እሱ እኮ የመንግስት እንጀራ በልቶ ነው የመጣው የእኛ ግን ሞቶ ቀርቷል በሚል ብቀላ አዝማሚያዎች በቤተሰብ ይጀመራል" በማለት በብሄረሰቡ የራጋ ማጋ እርቅ ያለው ተቀባይነት ይገልፃሉ።ይህ ሲባል ግን በራጋ ማጋ ሽምግልናው ገዳይ የተጋነነ ቅጣት ኣይጣልበትም።[109]

## 5.5. ለራጋ ማጋ መሪዎች የሚደረጉ እገዛዎች

የብሄረሰቡ ማጋዎች ግጭት ውስጥ የሚገቡ አካላትን የሚያስማሙት ባህል የጣለባቸውን አደራና ማህበራዊ ግዴታ ለመወጣት እንጅ እንደ ቋሚ ስራ ክፍያ በማግኘት ኑሯቸውን ለመደጎም አይደለም። ማጋዎቹ እገዛዎቹን የሚያገኙት ከብሄረሰቡ ተወላጆችና ከመደበኛው የፍትህ ተቋማት ነው።

አንደኛው ከብሄረሰቡ ተወላጆች የሚደረጉላቸውን ልዩ ልዩ ድጋፎች ያጠቃልላል። ማጋዎች ግጭት ውስጥ የነበሩ አካላትን ካስታረቁ በኋላ በዳይ አካል ቁርሳቸውንና ምሳቸውን

[109] ሳጂን ግርማ(ስክርብ፣87)።

ማብላትና የትራንስፖርት ወጭ በመሸፈን ምርቃት ተቀብሎ ይሸኛቸዋል። የብሄረሰቡ
ላት ለሽማግሌዎች የሚያደርጉትን እገዛ በተመለከተ ሀይሉ፡-

*ሽማግሌ ደግሞ ደረቆ በሄደበት ጥሩ አይደለም ይረግመናል ነገሩ አይሳካልንም ተብሎ ስለሚታመን ሽማግሌዎችም እንዲመርቁ የሆነ ነገር ማድረግ አለባቸው። ያ ግን እንደየማ ሰው ባለበት ሽማግሌ ተርቦ ተጠምቶ እንዳይመለስ ይደረጋል። አንዳንድ የማያስብ ሲያጋጥም ደግሞ ሽማግሌ ደክሞ የሚመለስበት ይኖራል። በፍቃደኝነት እንጂ ግዴታነት የለውም (ስክርብ፣49) በማለት ይገልፁታል።*

በሄረሰቡ አባላት ለሽማግሌዎች የሚያበሉትና የሚያጠጡት በመመረቃችን እርቁ ፀናልናል ብለው ስለሚያምኑ ነው። በአብዛኛው ብሄረሰቡ በግብርና የሚተዳደር በመሆኑ ማጋዎችንና የራጋውን እርሻ በማረስ፣ ሰብላቸውን በመሰብሰብና ቤታቸውን በመስራት በሄረሰቡ የጉልበት እገዛ አይለያቸውም።

ለተኛው ደግሞ መደበኛው የፍትህ ተቋም ለብሄረሰቡ ማጋዎች የሚያደርግላቸውን ልዩ ፉ እገዛ ይመለከታል። ተቋሙ በተለያዩ ጊዜዎች ስለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ስለሴቶችና ጻናት መብት የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ስልጠናዎችን ይሰጣል። ይህን ሀሳብ ወረዳው ፍርድ ቤት ጠበቃ የሆኑት ታደሰ (ስክርብ፣68) "ሽማግሌዎች...እስከ ክልል ድረስ ጠርተው የሚሄዱና ነገሮችን አረጋግተው በወረዳው ሰላም እንዲሰፍን የሚሰሩ ማግሌዎች ሲሆኑ በወረዳው ለተለያዩ ውይይቶች እየተጠሩ ይወያያሉ፣ስልጠናም ሰጣቸዋል" በማለት ይገልፁታል።

ብሄረሰቡ ማጋዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች በመደበኛው የፍትህ ተቋማት ስለዘለመናዊ ጎችና አሰራሮች እንደሚመከሩና የሚሰጣቸውንም ምክር ስራ ላይ እንደሚያዉሉት ናገራሉ። "ህግ የሚጠላውን እንጠላለን" የሚሉት ማጋዎች ከፍርድ ቤት፣ ከፖሊስ፣ አቃቢ ህግ እንዲሁም ከሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ መመሪያዎችና ህጎች ጋር የሚቃረኑ ራዎችን አይሰሩም።[110]

ማረቆ ወረዳ ፖሊስና አቃቢ ህግ ዕርስ በርስ በመቀናጀት በብሄረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ብቅ ወንጀሎችን ለመመርመርና ለመከላከል በየቀበሌውና በየጎሳው ማጋዎችን እየሰበሰቡ ኮሚኒቲ ፖሊሲግ ዙሪያ ስልጠናዎችንና ውይይቶች ይሰጣሉ። ምንም እንኳ የሚሰጡት

[110] *አቢጋዝ ጃቢቦ(ስክርብ፣83)፤ አቢጋዝ ሙርኪ(ስክርብ፣83)።*

ጠናዎችና የሚካሄዱት ውይይቶች በቂ ባይሆኑም ወንጀሎችን ከመከላከል አንጻር ተዋፅዖ አድርገዋል፡፡[111]

## 6. የራጋ ማጋ ጥንካሬና ድክመት በብሄረሰቡ አተያይ

*ሽማግሌዎች የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው፡፡ ባህሉን ደግሞ የሚያውቁት እነርሱ ናቸው፡፡ ወንጀለኞች ደግሞ የህብረተሰቡ አካሎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ወንጀል ከነዚህ ሽማግሌዎች ሊያመልጥ አይችልም፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ስውር ወንጀል ሰርቶ ቢደበቅ በባህሉ መሰረት ያስምላሉ፤ወንጀለኛውም ራሱን ለሽማግሌዎች አጋልጦ እንዲሰጥ ያደርጋሉ (ታደሰ፤ስክርብ፣68)፡፡*

ፃረቆ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ጠንካራ ጎኖች አሉት፡፡ እነዚህ ንካሬዎች ተቋሙን በመደበኛው የፍትህ ተቋም እውቅና እንዲያገኝ አግዘውታል፡፡ ራጋ ጋ የብሄረሰቡ አባላት ርስ በርስና ከአጎራባች ብሄረሰቦች ጋራ የሚያጋጥሟቸውን ግጭቶች ለቁታዊነት ስለሚፈታ ተመራጭ ሆኗል፡፡

በሄረሰቡ በድብቅ የተፈፀሙ ወንጀሎች ተደብቀው አይቀሩም፡፡ የብሄረሰቡን ሰላም ያሳጡ ውር ወንጀሎችን በማውጣጣት በኩል ከመደበኛው የፍትህ ተቋም ይልቅ የብሄረሰቡ ሴራ ›ጋ ማጋን መሰረት ያደረገ ባህል ለማለት ነው) የተሻለ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ(ሀጂ ጃተኖ፤ ክርብ፣48) የብሄረሰቡ የራጋ ማጋ የግጭት አፈታት ስርዓት በመደበኛው የፍትህ ተቋም ፍትሔ የማይገኝላቸው ድብቅ ወንጀሎች በቀላሉ እንደሚወጡና ባህላቸው ጠንካራ ሆኑን "የአገር ሰርዶ የአገር በሬ ያወጣል" በሚል በሀገረኛ አባባል ጠቅለል አድርገው ገልፁታል፡፡

ብሄረሰቡ አባላት ለባህላቸውና ለሀገር ሽማግሌዎች የተለየ ክብር ስላላቸው የሰሩትን ንጀል ለሽማግሌዎች ተናግረው ይታረቃሉ፡፡ በብሄረሰቡ ወንጀል መደበቅ ለሌላ ጥፋት ዳርጋል ተብሎ ስለሚታመንና የሽማግሌዎችም እርግማን ዘር ያጠፋል ተብሎ ስለሚታሰብ ንጀል ሊደበቅ አይችልም፡፡ በማረቆዎች ወንጀል የሚደበቀው ሽማግሌዎች እስኪሰሙና ክር ጉዳ እስኪታሰር ብቻ ነው፡፡

ግጭቶችን በሀገረሰባዊ እርቅ መጨረስ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ብሄረሰቡ በግብርና ሚተዳደርና ተበታትኖ የሚኖር በመሆኑ ለክስ ወደ ፍርድ ቤት በመመላለስ የሚወጣውን ንዘብ፣ጉልበትና ጊዜ ይቆጥባል፡፡ በመደበኛው የፍትህ ተቋም ተመላልሰው ችግራቸውን

---
[11] *መላኩ(ስክርብ፣63)፡፡*

ፍታት የገንዘብና የጉልበት አቅም ለሌላቸው የብሄረሰቡ ተወላጆች አፋጣኝ መፍትሄ
ጠት መቻሉ ጠቀሜታውን የላቀ ያደርገዋል፡፡[112]

ረሰባዊ የፍትህ ተቋም በመደበኛው የፍትህ ተቋም ላይ ያለውን የስራ ጫና ያቃልላል፡፡ ፖሊሴውና በየጎሳው በሽማግሌዎች የሚፈቱ ጥቃቅን ችግሮችን ወደ ፍርድ ቤት ሆምታት ለመፍታት ከፍተኛ የሰው ሀይል ያስፈልጋል፡፡ ይህ የሰው ሀይል እጥረት ደበኛው የፍትህ ተቋም ቢኖርም የማረቆ ብሄረሰብ የራጋ ማጋ እርቅ ለጥቃቅን ችግሮች ፍትሔ ስለሚሰጥ በተቋሙ ላይ ያለውን የስራ ጫና አቃሎታል፡፡ በመደበኛው የፍትህ ቋም የህግ ቅጣቱን የጨረሰ የብሄረሰቡ አባል በሰላም ወደ ቤተሰቦቹ እንዲቀላቀል ሚፈለግ የራጋ ማጋ እርቅ በመደበኛው የፍትህ ተቋም ይበረታታል፡፡[113]

ንም እንኳ የራጋ ማጋ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም አንዳንድ ድክመቶችም እንዳሉበት ነሄረሰቡ ተወላጆች ይናገራሉ፡፡ ተቋሙ በፍርድ ቤት ማለቅ ያለበባቸውን ከባድ ወንጀሎች ፎኖ በማስቀረትና ወንጀለኞችን በዘላቂነት የማያስተምሩ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ችግሩ ደ ፊት የሚበረክትበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡[114]

ጋ ማጋ በመንግስትና በህዝብ ላይ ጉዳት አላቸው ተብለው የተፈረጁ "ጎጂ ልማዳዊ ርጊቶች" እንዳይከሰሙ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጅ አሁን አሁን የተቋሙ የሀገር ማግሌዎችና የመደበኛው የፍትህ ተቋም ባለሙዎች እየተወያዩ ችግሮቹ እንዳይከሰቱ ረት ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች ከተከሰቱ ደግሞ በፍርድ ቤት በኩል ህጋዊ እርምጃ ንዲሰጥ የሁለቱም ተቋማት መሪዎች ተስማምተው ይሰራሉ፡፡

---

[12] መላኩ(ስክርብ፣61-64፤መሃመድ፣73፤ሽመልስ፣74፤ኤሊሉ፣74፤መሃመድ፣73)፡፡
✓ ሽመልስ ቅዳሜ የካቲት10-2004 ዓ.ም፣ ሽመልስ ዳርጋ እባላለሁ፡፡ እድሜዬ ሃያ ስምንት(28) ነው፡፡
የኑረመና ጎሳ ተወላጅ ነኝ፡፡ በግብርና ስራ እተዳደራለሁ፡፡
✓ መሃመድ ቅዳሜ የካቲት 10-2004 ዓ.ም፣ ስሜ መሃመድ ከድር ይባላል፡፡ የምኖረው ቆሼ ዘሬያ ቀበሌ ነው፡ የኢልማም ጎሳ ተወላጅ ነኝ፡፡ እድሜዬ ከሰላሳ በላይ ነው፡፡ የምተዳደረው በግብርና ነው ፡፡
✓ ኤሊሉ ቅዳሜ የካቲት 10-2004 ዓ.ም፣ኤሊሉ ጋሼ እባላለሁ፡፡ እድሜዬ ሃያ ስምንት ነው፡፡ የምወለደው ከጎሮስ ጎባ ነው፡፡ መካከለኛ ጀርተን በቃ ቀበሌ ነው የምኖረው፡፡ በግብርና በእርሻ እተዳደራለው፡፡
[113] ሳጅን ግርማ(ስክርብ፣90፣91)፡፡
[114] መላኩ(ስክርብ፣64፤ታደሰ፣67)፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ማጠቃለያና ይሁንታ

### *ማጠቃለያ*

ጥናት ይዞት የተነሳው ዋና አላማ የማረቆ ብሔረሰብን ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታታ
ንት መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ "ራጋ ማጋ- ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማረቆ
ረሰብ" በሚል ርዕስ የተካሄደ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ነው፡፡

'ረቆ ብሐረሰብ "ራጋ ማጋ" የሚለው ድርብ ቃል ሁለት ፍቺዎች አሉት፡፡ አንደኛው
፡ው የብሐረሰቡ ሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋም ጥቅል መጠሪያ ሲሆን ሁለተኛው ተቋሙን
!መሩት የሀገር ሽማግሌዎች መጠሪያም ነው፡፡ በብሄረሰቡ ራጋ ከፍተኛ የሆኑ ግጭቶችን
!ፈታ የመጨረሻው ሀገረሰባዊ ተቋም መጠሪያ ሲሆን ማጋ ደግሞ ከቤተ-ዘመድ ጉባኤ
ም በላይ የሆኑ መካከለኛ ግጭቶችን የሚፈታ ሀገረሰባዊ ተቋም መጠሪያ ነው፡፡

ነሄረሰቡ ግድያና ከባድ የአካል ማጉደል ወንጀል በራጋ አማካኝነት የመጨረሻ መፍትሄ
ሂሰጣቸው ሲሆን ከቤተ-ዘመድ ጉባኤ አቅም በላይ የሆኑ ግጭቶችን ደግሞ ማጋ
ፍትሔ ይሰጣቸዋል፡፡ የቤተ-ዘመድ ጉባኤ ቀላል የሆኑ ቤተሰባዊ ግጭቶችን እንደሚፈታ
ፑናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

ፑናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በማረቆ ብሄረሰብ ግጭቶች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች
ከፈላሉ፡፡ እነሱም ቤተሰባዊ ግጭቶች (የባልና ሚስት፣ የውርስ ይገባኛል፣ የአባትና ልጅ
ንዲሁም የእናትና ልጅ ግጭቶች)፣ ከጥሬ ሀብት ውሱንነት ጋር ተያያዥ የሆኑ ግጭቶች
'እርሻና የግጦሽ መሬት ጥበት፣የመጠጥ ውሃ ችግሮች)፣ ቀላልና ከባድ ወንጀሎች (እንደ
ርቆት፣ ዝርፊያ፣ ድብድብና ግድያ)፣ የጎሳና የብሄረሰብ ግጭቶች (ወሰን ተሻጋሪ የሆነ
ከብት ስርቆት፣ ድንበር ተሻግሮ ቤት መስራትና ከብቶችን ማሰማራት) በዋናነት የሚጠቀሱ
ቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች በብሄረሰቡ በተደጋጋሚነት የሚከሰቱ ሲሆን ሀገረሰባዊ የግጭት
ፍቻ በሶስቱ ተቋማትና በመደበኛው የፍትህ ተቋም የጋራ ትብብር መፍትሄ ይሰጣቸዋል፡፡

'ማረቆ ብሄረሰብ እርስ በርስና በአጎራባች ብሄረሰቦች ጋር ግጭት ውስጥ ሲገባ በሀገረሰባዊ
'ፍትህ ተቁም መፍትሄ መፈለግን ይመርጣል፡፡ ብሄረሰቡ በሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ላይ
ሙሉ እምነት ያለው ሲሆን ከተቋሙ አሰራርና ውሳኔ የሚያፈነግጥ የብሔረሰቡ ተወላጅ

ነቤተሰቡ፣ በዘር ሀረጉና በሀብቱ ላይ ጥፋት ያጋጥመዋል ተብሎ ይታመናል። የብሄረሰቡ ራጋ ማጋ በተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነቶችና መርሆች ላይ የተመሰረተ በመሆኑም ግጭት ውስጥ የገቡ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በራጋ ማጋ ላይ እምነት እንዲጥሉ አድርጓቸዋል።

የማረቆ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋም በየጊዜው የሚመጡለትን ግጭቶች ለመፍታት የተለያዩና ተለጣጣኒት ያላቸውን የእርቅ ሂደቶች ይከተላል። የእርቅ ሂደቶቹ ግጭቶቹ ከተከሰተበት እለት የእርቅ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ የሚከናወን ሲሆን በየደረጃው የተዋቀሩት የቤተ-ዘመድ ጉባኤ፣ ማጋና ራጋ ሂደቶቹን ያከናውኗቸዋል። እነዚህ ተቋማት አንዱ በአንዱ ላይ ጣልቃ የማይገቡ ባህሉ በሰራላቸውና በፈቀደላቸው የስልጣን ልክ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ያበርዳሉ፣ በዘለቄታዊነትም ይፈታሉ።

በማረቆ ብሄረሰቡ እርቅ የሚቋጨው በድግስና በካሳ (ጉማ) ነው። በብሄረሰቡ እርድ የእርቅ ማፅኛ፣ የቃል ኪዳን (በማርቅኛ ጉዳ ይባላል) ማሰሪያና የእርኩስ መንፈስ ማስወገጃ ነው። በብሔረሰቡ ሁለት አይነት እርድ ይፈፀማል። አንደኛው ግጭት ውስጥ የገቡ የብሃረሰቡ ተወላጆች እርስ በርስ የደበቁትን ለማውጣት የሚከናወን የነጭ ፍየል እርድ ነው። በዚህ እርድ ሀገረሰባዊ የወንጀል ምርመራ የሚከናወን ሲሆን ሁለቱ ወገኖች ወተትና ደም ተቀላቅሎ በአፋቸው እንዲይዙ በማድረግ የጡት ማጣባት ስርዓት ይከናወናል። በብሄረሰቡ ግጭት የገቡ አካላት ወተቱንና ደሙን በአፋቸው እንዲይዙ የሚደረገው በእርቁ ውህደትና ዝምድና መፍጠራቸውን ለማመልከት ነው።

ሁለተኛው የእርድ አይነት የእርቅ እርድ ነው። ለዚህ ስርዓት የሚታረደው ጥቁር ፍየል ሲሆን ፍየሉ በሰይጣን ስለሚመሰል የተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነቶች ይከናወኑበታል። በተለይ የአንጀት ማሰርና የመቁረጥ፣ የአንጀት መቅበርና ወደ ወንዝ ወይም ምንጭ ሄዶ የመታጠብ ስርዓቱ ግጭት ውስጥ የገቡትን አካላት ከእርኩስ መንፈስ ለማስወጣት በስርዓቱ ላይ የተካፈለውን ቤተሰብ በሙሉ ከዚህ መንፈስ ለማንፃት ሲባል ነው።

ለእርቅ ማስፈፀሚያነት የሚያገለግለው የደም ካሳ (ማረቆዎች ጉማ ይሉታል) ከዘመን ዘመን እንደተከሰተው የግጭት አይነት ተሻሽሏል። በብሄረሰቡ ለደም ካሳ (ለጉማ) የሚቀርቡት ከብቶች፣ ብርና ልጃገረድ ናቸው። ይሁን እንጅ አሁን አሁን የከብት ጉማ ቀርቶ ብር እየሆነ ነው። በብሄረሰቡ ልጃገረድ በጉማነት የምትሰጠው ግጭቱ ከአጎራባች ብሄረሰብ ጋር ሲሆን ነው። በብሄረሰቡ እምነት በጉማነት ለሌላ ብሄረሰብ የተሰጠች ልጃገረድ ወደፊት

ምትወልዳቸው ልጆች ራጋ ማጋን ይመራሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ እምነትም የገዳይ
.ተሰብ ወይም ጎሳ ልጃገረዷን በጉማነት ሰጥቶ እንዲታቅ ይገፋፋል፡፡

ማረቆ ብሄረሰብ የጉማ ገንዘብ አይበላም፡፡ በተለይ ግጭቱ እርስ በርስ የተከሰተ ከሆነ
እርቁ መጨረሻ የብሄረሰቡ ራጋ የጉማውን ገንዘብ ተበዳይ እንዳይበላ በብሄረሰቡ ራጋ ምክር
ሰጣል፡፡ የጉማ ገንዘብ በእርቅ መጨረሻ ላይ በበዳይ አካል ተዘጋጅቶ የሚቀርበው ባህሉን
ማክበርና በዳይ ለተበዳይ ያለውን አክብሮት ለመግለፅ ብቻ ነው፡፡ በብሄረሰቡ የጉማ ገንዘብ
ተበላ በቀጣይ የቤተሰቡ የዘር ሀረግ ላይ ችግር ይከሰታል ተብሎ ይታመናል፡፡

ማረቆ ብሄረሰብ ድብቅ ወንጀሎችን የሚመረምርባቸው የራሱ ሀገረሰባዊ ስልቶች አሉት፡፡
ብሄረሰቡ ጨለማን ተገን በማድረግ የተፈፀሙ ወንጀሎች ተደብቀው አይቀሩም፡፡ እነዚህ
ወንጀል መመርመሪያ ስልቶች ከብሄረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው
ሆን መሃላና እርግማን በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሀላው እና በእርግማኑ ላይ
ሚከናወኑት የተላያዩ ስርዓተ ክወኔዎች የብሄረሰቡ የህይወት አተያይና ፍልስፍና
ሻራዎች ያረፉባቸው በመሆናቸው ይከበራሉ፤ይፈራሉም፡፡

ጋ ማጋ በወረዳው ከሚገኙት መደበኛ የፍትህ ተቋማት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው፡፡
ሁለቱ የፍትህ ተቋማት በብሄረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን በትብብር ለመፍታትና
ላቂ ሰላምን ለማስፈን የጋራ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ተቋማት የሚመሩባቸው ህጎች፣
ንቦችና መርሆች የተለያዩ ቢሆንም የብሔረሰቡ ሰላም የጋራ ጉዳያቸው ነው፡፡

ነዚህ ተቋማት በተናጠልና በትብብር የሚፈቷቸው በርካታ ግጭቶች ያሉ ሲሆን
ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም ውሳኔ የተጣለበት አካል በመደበኛው የፍትህ ተቋም እንደ
ንድ የቅጣት ማቅለያ ይታይለታል፡፡

ጋ ማጋ እንደ ተቋም የህፃናትን፣ የሴቶችንናና የአረጋዊያንን መብቶች አክብሮና አስከብሮ
ሚሰራ ሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋም በመሆኑ በመደበኛው የፍትህ ተቋም ከበሬታንና
ውቅናን አግኝቷል፡፡ በተለይ “የህዝብን የጋራ ጥቅም ይጋፋሉ በሚባሉ” እንደ አስገድዶ
 መድፈር፣ ጠለፋና ያለእድሜ ጋብቻ ያሉትን “ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች” በመደበኛው የፍትህ
ቋም ብቻ መታየታቸውና ሀገረሰባዊውም የፍትህ ተቋም ለነዚህ ድርጊቶች ሽፋን
ማይሰጥ መሆኑ በመደበኛው የፍትህ ተቋም ዘንድ አመኔታ እንዲጣልበት አድርጓል፡፡

## .2. ይሁንታ

.ጋ ማጋ ለብሄረሰቡ የሚሰጠው ሁለንተናዊ አስተዋፅዖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። ·ቋሙ የብሄረሰቡን ሰላም ከማስጠበቅ አልፎ ሰላምን ፍለጋ ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት .መጣ የነበረውን ባለጉዳይ ቀንሶታል። ይህ ደግሞ ያለ አግባብ የሚወጣውን ጉልበትና ንዘብ እንዲሁም የስራ ሰዓት በመቀነስ ብሄረሰቡ ያለ እንግልት ወደ ልማት እንዲሰማራ ደርገዋል። እነዚህን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች እየሰጠ ያለውን ፍትህ ተቋም ማረታታት፣ከማጋዎችና ራጋ ጎን መቆምም ተገቢ ነው። ከዚህ አንፃር ጥኚው ለተቋሙ ቢሟሉ ያላቸውን ነጥቦች እንዲህ አስቀምጧቸዋል።

- የብሄረሰቡ ማጋዎች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ የሚደርስባቸውን የዝናብና የፀሀይ መፈራረቅ የሚያሳልፉበት እንዲሁም የተለያዩ ውይይቶችን የሚያካሂዱበት መጠለያ ቢኖራቸው ለስራቸው እንደ ማበረታቻ ነው። ለዚህም አገልግሎት ማዕከላዊ የሆነ ቦታ ቢዘጋጅ፡-
- ራጋ ማጋን ለሚመሩት የሀገር ሽማግሌዎች (ማጋዎችና ራጋ) እንደ ሽልማት አይነት የሞራል ድጋፍ ቢያገኙ፡-
- ከመደበኛው የፍትህ ተቋም ጋር ያለውን ጠንካራ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ለተቋሙ መሪዎች ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ቢሰጣቸው፡-

## ዋቢ ጽሁፎች


አባተ:: "የሸኮች ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት" የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፤2002::

·ው በቀለ(አርታኢ):: *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ*: አዲስ አበባ፤ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፤ 2004::

ዓው የህዝብ ግንኙነት ቢሮ የተዘጋጀ ጥራዝ:: 2002

ን አሰፋ:: "ባህላዊ የግጭት አፈታት በወግዱ እና በብረና ወረዳዎች" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፤2002::

ነገን ምንዋጋው:: "ሀረገሰባዊ የግጭት መፍትሔ ስርዓት በደከ ጋሞ" የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፤1998::

ፑው ኬፅሚሶ እና ሳሙኤል ሀንዳሞ:: *የሀድያ ሕዝብ ታሪክና ባህል*: አዲስ አበባ፤ሰፊር አታሚ፤2002::

ሃም ታደሰ:: "ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሄረሰብ" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፤1999::

·ዮጵያ *ህገ መንግስት*:: አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ፤1948::

·ዮጵያ *ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ህገመንግስት*:: አዲስ አበባ፤ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤ 1987::

·ዮጵያ *ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ መንግስት*:: ነጋሪት ጋዜጣ፤ የተሸሻለው የቤተሰብ ህግ፤ አዲስ አበባ፤ 1992::

·ዮጵያ *ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ*:: አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤1997::

·ሪካ አንድነት ድርጅት፤የአፍሪካ የባህል ቻርተር:: አዲስ አበባ፤ በባህልና ስፖርት ሚኒስተር ተቀነባብሮ የቀረበ፤1970::

·ድወሰን አውላቸው:: "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታታ" የኤም.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤የኢትዮጲያ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፤1998፡

ማ ተፈራ:: "የሽምግልናና እርቅ ስርዓት በወላይታ" የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፤1998::

ተክለወልድ። *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

*ነገስት ንባብና ትርጓሜ*። አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1958።

ch, K. *Conflict resolution: Encyclopedia of Cultural anthropology.* New York: Henry Holt printing press, 1996.

Amos, Dan. "'*Context' in context*" *western folklore.* Vo.52.No.214.Theorizing folklore: Toward new perspectives on the politics of culture (Apr- oct. 1993): 209-226 pp. online. http:;/:www.jstor.org/stable/1500087.

-*Folklore in African Society.* Research in African Literatures, Vol. 6, No. 2(Autumn,1975); pp.165-198. Indiana University Press. Online : http://www.jstor.org/stable/3819059.

er M.L. and etal (eds.). *Languages in Ethiopia. London:* oxford University Press, 1976.

ian, Richard. *Handbook of American Folklore: The Field Study of Folklore in Context.* Ed, Richard M. Dorson with Inta Gale Carpenter, pp. 362-368. Bloomington: Indiana University Press, 1983.

Catherine. *Ritual: perspectives and dimensions*. New York: Oxford University press, 2009.

, Kuo-jung. *The Concept of Virginity and Its Representations in Eighteenth-Century English Literature*. National Chung Cheng University, Chiayi, Taiwan, 2010.

*igan, John. Religion and Emotion: Approaches and Interpretations.* Oxford university press, 2004

r, Lewis A. *The Functions for social conflict*. 1st ed. New York: free press, 1964.

kulu Zewde. *Fetha Negast: Nomocanon.* Addis Ababa University, Berhanna Selam Printing Press,1993.

on, Richard. *Folklore and Folk Life: an Introduction.* London: University of Chicago press,1972

er, R. *Sources of Conflict and Methods of Conflict Resolution.* International Peace and Conflict Resolution: School of International Service, the American University, Rev. 2000.

ighe, Thomas A. *The OAU (AU) and OAS in Regional Conflict Management: A comparative assessment.* Ibadan: spectrum book Limited, 2003.

g, Ho-won. *Peace and conflict studies an Introduction.* ASHGARE: Institute for conflict analysis and resolution, George Mason University, 2000.

rt. and Myers. *50 Activities for Conflict Resolution.* Human Resource Development Press, Inc. U.S and Canada, 1999.

, Wolf. *English- Amharic context dictionary.* Belgium: ottharra-Sowitz- Wiesbaden, 1973.

on, D and Melvin Ember. Eds. *Encyclopedia of Cultural Anthropology*. Vol. 2. New York: Henry Holt and Company Inc, 1996.

'onald, K. *Evolution, Psychology and Conflict Theory of Culture*. Department of Psychology California State University-Long Bench, CA, USA. www.epjournal.net- 2009.7(2) pp.208-233.

iinty,R. *No War No Peace*. The Rejuvenation of Stalled Peace Processes and Peace Accords, 2006.

ɪromick C. and Kennedy. *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art.* U.S.A: ABC-CLIO, LLC. 2011.

Martha C. and Stephens. *Living Folk lore፡ Introduction of the Study of People and their raditions.* Utah State University Press, 2005.

*irst Constitution of Ethiopian*. Addis Ababa□ Hamle 9, 1923.

:, J. *Trust and Conflict Transformation*. The Institute for Multi-Track Diplomacy. Occasional ?aper Number 5. April, 1995.

:hand, Nongthombam. *Folklore and Performance*. Educational Multimedia Research Centre, Manipur University, *Indian Folklore* Serial No.30 August 2008.

d Nations Peacekeeping Operations: Principles and Guidelines. Department of Peacekeeping Operations, New York, 2008.

l, Charles and Galtung, Eds. *Handbook of Peace and conflict studies.* London: Rutledge, 2007.

:, Stefan and Yakinthou C. *Conflict Resolution: Theories and Practice*: London and New York: Routledge, 2011.

lhouse, Tom and Ramsbothan. Eds. Peace Keeping and Conflict Resolution. New York: Frank class and co: Ltd, 2000. Organization of Africa Union Charter, Addis Ababa, OAU, 1963.

ıan, William and Francis (Ed). *Conflict Resolution in Africa*. Washington, D.C: the Brooking Institution, 1991.

# የመረጃ አቀባዮች ዳራ

| የመረጃ ሰጭዎች ስም | ፆታ | የሚኖሩበት አካባቢ | የሚወለዱበት ጎሳ | ስራ | ሀይማኖት | እድሜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሃጂ ጃተኖ መኬ | ወ | ዋሼ ቬራ | ጫቦ | ግብርና | እስልምና | 85 |
| ኢማም ቱኬ | ወ | ኡዳሳ ረጼ | አገኘ | ግብርና | እስልምና | 67 |
| ዲንቀላ ቧጎ | ወ | ቆሼ ዙሪያ | በቼ | ግብርናና ንግድ | እስልምና | 52 |
| ሀይሉ ጋጉሮ | ወ | ቆሼ ዙሪያና እንሴኖ | እንሴኖ | የመንግስት ሰራተኛ | ክርስትና | 52 |
| አበጋዝ ጃቢቦ ባፋ | ወ | ዋሽ ቬራ | ሳሾ | ግብርና | እስልምና | 70 |
| አበጋዝ ሙርኪ ደመቀ | ወ | በቼ ጉልቻ | ዋረመና | ግብርና | ክርስትና | 65 |
| ሳጅን ግርማ ንጉሴ | ወ | ቆሼ | ጎሮስ | የፖሊስ አዛዥ | ክርስቲያን | 38 |
| ወርቅነህ ማሌሞ | ወ | ከሌላ ብሄረሰብ የመጡ | --- | የመንግስት ሰራተኛ | ክርስትና | ከ 32 በላይ |
| መሳኩ ፊቃዱ | ወ | ቆሼ | ኢልማም | ዳኛ | ክርስትና | 29 |
| ሰለሞን ወርቂቶ | ወ | እንሴኖ | | ግብርና ንግድ | ክርስትና | 50 |
| ወልዩ ዲተሞ | ወ | ቆሼ | አገኘ | መንግስት ሰራተኛና የባህል ቡድን መሪ | እስልምና | 27 |
| ታደሰ አበራ | ወ | | ሳሾ | አቃቢ ህግ | ክርስትና | 28 |
| ኤሊሉ ጋሼ | ወ | መካከለኛ ጀርተን በቃ | ጎሮስ | ግብርና | እስልምና | 25 |
| መሃመድ ከድር | ወ | ቆሼ ዙሪያ | ኢልማም | ግብርና | እስልምና | ከ 30 በላይ |
| ሽመልስ ዳርጋ | ወ | | ኑሪመና | ግብርና | ክርስትና | 28 |
| ዘይኔ አጤሮ | ወ | ቆሼ ዙሪያ | | ግብርና | ክርስትና | 25 |
| መሀመድ ለሙሼ | ወ | እንሴኖ | ኑሪመና | የባህል ቢሮ ሀላፊ | እስልምና | 42 |
| ቡሽራ ዱኬ | ወ | እንሴኖ | ሳሾ | የመንግስት ሰራተኛ | እስልምና | 39 |

# የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፎቶ መግለጫ




ሃጂ ጃተኖ መኪ
በአሁኑ ጊዜ የብሄረሰቡ ራጋ



አቶ ኢማም ቱኬ
የማጋዎች ተወካይ



ዲንቁላ ቧጎ
የብሄረሰቡ ማጋ



አበጋዝ ሙርኪ ደመቀ
የብሄረሰቡ ማጋ



ሀይሉ ጓጉሮ
የብሄረሰቡ ማጋ



አበጋዝ ጃቢዮ ባፋ
የብሄረሰቡ ማጋ




ወርቅነህ ማሌሞ የማረቆ ወረዳ
ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ተወካይ




ሳጅን ግርማ ንጉሴ
የማረቆ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ




*ወልዩ ዲተሞ የማረቆ ወረዳ ፍርድ ቤት ረ/ኦፊሰርና የባህል ቡድን መሪ*



*መላኩ ፈቃዱ*
*የማረቆ ወረዳ ፍርድ ቤት የፍርድ ኦፊሰር*




ታደሰ አበራ
የወረዳው ፍርድ ቤት አቃቢ ህግ



ኤሊሉ ጋሼ
ገበሬና የብሄረሰቡ ተወላጅ



መሃመድ ከድር
ገበሬና የብሄረሰቡ ተወላጅ



ሽመልስ ዳርጋ
ገበሬና የብሄረሰቡ ተወላጅ

## የቡድን ፎቶዎች



